https://ethiolex.com

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

# የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ

**(ረቂቅ)**

| አንቀጽ ቁጥር | የአንቀጽ ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | አጭር ርዕስ | 1 |
| ፪ | የተሻሩ ሕጎች እናተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች | 1 |
| ፫ | የመሸጋገሪያ ድንጋጌ | 2 |
| ፬. | ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ | 2 |
| | | |
| **አንቀጽ ቁጥር** | የአንቀጽ ርዕስ | **ገጽ** |
| የወንጀል ህግ ስነ-ስርዓት እና የማስረጃ ህግ<br>አንደኛ መጽሐፍ<br>ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ መርሆዎች፣ የተቋማት ሃላፊነት እና የዳኝነት ሥልጣን<br>ምዕራፍ አንድ<br>ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና መርሆች<br>ክፍል አንድ<br>ጠቅላላ ድንጋጌዎች | | 3 |
| አንቀጽ ፩ | የተፈፃሚነት ወሰን | 3 |
| አንቀጽ ፪ | ትርጓሜ | 3 |
| አንቀጽ ፫ | ዓላማ | 6 |
| ክፍል ሁለት<br>መሠረታዊ መርሆዎች | | 6 |
| አንቀጽ ፬ | ጠቅላላ | 6 |
| አንቀጽ ፭ | ነፃ ሆኖ የመገመት መብት | 7 |
| አንቀጽ ፮ | በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ እና ቅጣት ስለመከልከሉ | 7 |
| አንቀጽ ፯ | በሕግ ፊት እኩል መሆን | 7 |
| አንቀጽ ፰ | ስለመያዝና ማሰር | 7 |
| አንቀጽ ፱ | ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ | 8 |
| አንቀጽ ፲ | በጠበቃ መወከል | 8 |
| አንቀጽ ፲፩ | ቀልጣፋ ውሳኔ ስለመስጠት | 9 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፲፪ | በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት | 9 |
| አንቀጽ ፲፫ | የተከራካሪዎች እኩልነት | 9 |
| አንቀጽ ፲፬ | የቋንቋ አጠቃቀም | 9 |
| አንቀጽ ፲፭ | እውነትን ስለማውጣት | 10 |
| አንቀጽ ፲፮ | ሕጋዊነት | 10 |
| አንቀጽ ፲፯ | የወንጀል ክስ የመንግሥት መሆኑ | 10 |
| | ምዕራፍ ሁለት<br>የፍትሕ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት | 11 |
| አንቀጽ ፲፰ | የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት | 11 |
| አንቀጽ ፲፱ | የፖሊስ ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት | 12 |
| አንቀጽ ፳ | የዐቃቤ ሕግ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት | 13 |
| አንቀጽ ፳፩ | የማረሚያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት | 14 |
| አንቀጽ ፳፪ | የጥብቅና ተቋም ተግባርና ኃላፊነት | 15 |
| አንቀጽ ፳፫ | የፍትሕ ተቋማት የወል ተግባርና ኃላፊነት | 15 |
| | ምዕራፍ ሶስት<br>የዳኝነትና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን<br>ክፍል አንድ<br>የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን | 17 |
| አንቀጽ ፳፬ | የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን | 17 |
| አንቀጽ ፳፭ | የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ድልድል | 18 |
| | ክፍል ሁለት<br>የፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን | 20 |
| አንቀጽ ፳፮ | የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን | 20 |
| አንቀጽ ፳፯ | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን | 20 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፳፰ | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን | 20 |
| አንቀጽ ፳፱ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን | 21 |
| አንቀጽ ፴ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን | 21 |
| አንቀጽ ፴፩ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር የዳኝነት ሥልጣን | 21 |
| አንቀጽ ፴፪ | የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን | 22 |
| አንቀጽ ፴፫ | የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን | 22 |
| አንቀጽ ፴፬ ፴፭ | የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን | 22 |
| አንቀጽ ፴፭ | የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን | 23 |
| አንቀጽ ፴፮ ፴፯ | የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን | 23 |
| አንቀጽ ፴፯ | ክሶችን ስለማጣመር | 23 |
| አንቀጽ ፴፰ | በግልጽ ስላልተደነገ የወንጀል የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን | 24 |
| አንቀጽ ፴፱ | የመሰየም ሥልጣን | 24 |
| ክፍል ሦስት<br>የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን | | 24 |
| አንቀጽ ፵ | መደበኛ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን | 25 |
| አንቀጽ ፵፩ | የወንጀሉ ድርጊትና ውጤት በተለያዩ የአስተዳደር ወሰን ሲሆን የሚኖር የዳኝነት ሥልጣን | 25 |
| አንቀጽ ፵፪ | ተያያዥነት ያላቸውን ወንጀሎች የመዳኘት ሥልጣን | 25 |
| አንቀጽ ፵፫ | ወንጀል የተሠራበት ቦታ ያልታወቀ ሲሆን ክሱ የሚታይበት ፍርድ ቤት | 25 |
| አንቀጽ ፵፬ | በጉዞ ላይ የተፈጸመ ወንጀል | 26 |
| አንቀጽ ፵፭ | ተደራራቢ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን | 26 |
| አንቀጽ ፵፮ | ክስን ማዛወር | 26 |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ አራት<br>የሌሎች ፍትሕ አካላት ሥልጣን እና ስለመነሳት<br>ክፍል አንድ<br>የሌሎች ፍትሕ አካላት ሥልጣን | | 27 |
| አንቀጽ ፸፪ | የፌዴራል የፍትሕ አካላት ሥልጣን | 28 |
| አንቀጽ ፸፫ | የክልል የፍትሕ አካላት ሥልጣን | 28 |
| አንቀጽ ፸፬ | ውክልና ስለመስጠት | 28 |
| ክፍል ሁለት<br>ከወንጀል ምርመራ እና ከፍርድ ሂደት ስለመነሳት | | 29 |
| አንቀጽ ፹ | ጠቅላላ | 29 |
| አንቀጽ ፹፩ | አስቀድሞ የታየ ጉዳይ | 30 |
| አንቀጽ ፹፪ | አቤቱታ ስለማቅረብ | 30 |
| አንቀጽ ፹፫ | አቤቱታዉ የሚቀርብበት ጊዜ | 30 |
| አንቀጽ ፹፬ | የአቤቱታ አቀራረብ | 30 |
| አንቀጽ ፹፭ | ዉሳኔ መስጠት | 31 |
| ሁለተኛ መጽሐፍ<br>የወንጀል ምርመራ<br>ምዕራፍ አንድ<br>የወንጀል አቤቱታ እና አቤቱታን ማጣራት | | 32 |
| አንቀጽ ፹፮ | ጠቅላላ | 32 |
| አንቀጽ ፹፯ | ስለወንጀል አቤቱታ | 32 |
| አንቀጽ ፹፰ | የግል አቤቱታ | 33 |
| አንቀጽ ፹፱ | የወንጀል አቤቱታን ወይም የግል አቤቱታን መቀበል | 33 |
| አንቀጽ ፺ | ስልጣን ለሌለዉ ተቋም የሚቀርብ አቤቱታ | 34 |
| አንቀጽ ፺፩ | አቤቱታን ስለማንሳትና ዉጤቱ | 34 |
| አንቀጽ ፺፪ | ማንነቱ ባልታወቀ ሰዉ የሚቀርብ የወንጀል አቤቱታ | 34 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፳፫ | መረጃ ስለመስጠት | 35 |
| አንቀጽ ፳፬ | የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት | 35 |
| አንቀጽ ፳፭ | የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ድርጊት | 35 |
| አንቀጽ ፳፮ | የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት ከተደረገ በኋላ ምርመራ መዛግብትን ስለመዝጋት | 36 |
| አንቀጽ ፳፯ | ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ | 36 |
| | ምዕራፍ ሁለት<br>የወንጀል ምርመራ ሥነ-ሥርዐት<br>ክፍል አንድ<br>የምርመራ አጀማመር እና የማስረጃ አሰባሰብ | 37 |
| አንቀጽ ፳፰ | ጠቅላላ | 37 |
| አንቀጽ ፳፱ | የወንጀል ምርመራ | 38 |
| አንቀጽ ፴ | በምርመራ ወቅት ተመጣጣኝ ኃይል ስለመጠቀም | 38 |
| | ክፍል ሁለት<br>የምስክር ቃል መቀበል እና መመርመር | 38 |
| አንቀጽ ፴፩ | የምስክርን ቃል ስለመቀበል እና ስለመመርመር | 38 |
| አንቀጽ ፴፪ | ለምስክር የሚሰጥ መጥሪያ | 39 |
| አንቀጽ ፴፫ | የምስክር ቃል መቀበል | 39 |
| አንቀጽ ፴፬ | የተከለከለ ተግባር | 40 |
| ክፍል ሶስት<br>ብርበራና ዕቃ መያዝ | | |
| አንቀጽ ፴፭ | በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብርበራ ማድረግ ወይም ማስረጃ መያዝ | 41 |
| አንቀጽ ፴፮ | ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ብርበራ ማድረግና ዕቃ መያዝ | 41 |
| አንቀጽ ፴፯ | የተያዘን ሰው ስለመበርበር | 42 |
| አንቀጽ ፴፰ | ስለብርበራና የመያዝ ሒደት አፈጻጸም | 42 |
| አንቀጽ ፴፱ | በመንግሥት ወይም ሕጋዊ ሰውነት ባለው ተቋም ላይ የሚደረግ ብርበራ | 43 |
| አንቀጽ ፵ | በተለያዩ ዕቃዎች ላይ የሚፈጸም ብርበራ | 43 |
| አንቀጽ ፵፩ | በብርበራ ትዕዛዙ ውስጥ ያልተጠቀሱ ዕቃዎች | 44 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፵፪ | የኤግዚቢት አያያዝና አቀማመጥ | 44 |
| አንቀጽ ፵፫ | በተያዘ ዕቃ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ | 44 |
| አንቀጽ ፵፬ | ተጠርጣሪ ባልሆነ ሰው እጅ የሚገኝ ማስረጃ | 45 |
| አንቀጽ ፵፭ | በመንግሥት ወይም በሌላ ተቋም የሚገኝ ማስረጃ | 46 |
| አንቀጽ ፵፮ | በፋይናንስ ተቋም የሚገኝ ማስረጃ | 46 |
| ክፍል አራት<br>ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ የሚደረግ ምርመራ እና ማስረጃ ማሰባሰብ | | |
| አንቀጽ ፵፯ | ዓላማ | 47 |
| አንቀጽ ፵፰ | ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ መገኘት | 47 |
| አንቀጽ ፵፱ | ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ ስለሚደረግ ምርመራ | 48 |
| አንቀጽ ፶ | አስከሬን መመርመር | 48 |
| አንቀጽ ፶፩ | የቤተ ሙከራ ምርመራ ቴክኒክን መጠቀም | 49 |
| አንቀጽ ፶፪ | በምርመራና በድጋሚ ምልከታ መሳተፍ | 50 |
| አንቀጽ ፶፫ | የባለሙያ ሪፖርትና ምስክርነት | 51 |
| ክፍል አምስት<br>ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴዎች | | |
| አንቀጽ ፶፬ | ዓላማ | 51 |
| አንቀጽ ፶፭ | የልዩ ምርመራ ዘዴዎች ተፈፃሚነት | 51 |
| አንቀጽ ፶፮ | የፍርድ ቤት ስልጣን | 52 |
| አንቀጽ ፶፯ | ልዩ ማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ | 52 |
| አንቀጽ ፶፰ | መሟላት ስላለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች | 52 |
| አንቀጽ ፶፱ | የጊዜ ገደብ | 53 |
| አንቀጽ ፷ | ለፍርድ ቤት ሪፖርት ስለማቅረብ | 53 |
| አንቀጽ ፷፩ | ማስረጃ ተቀባይነት የማያገኝበት ሁኔታ | 54 |
| ክፍል ስድስት<br>የተጠርጣሪ  አያያዝ፣ ቃል አቀባበል እና አቆያየት | | |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፪ | ተጠርጣሪን ስለመያዝ | 54 |
| አንቀጽ ፻፫ | ተጠርጣሪን ስለመጥራት | 55 |
| አንቀጽ ፻፬ | የፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ | 55 |
| አንቀጽ ፻፭ | አስቸኳይ ሁኔታ | 56 |
| አንቀጽ ፻፮ | በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ተጠርጣሪን መያዝ | 56 |
| አንቀጽ ፻፯ | የመተባበር ግዴታ | 57 |
| አንቀጽ ፻፰ | ተጠርጣሪ ሲያዝ ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት | 57 |
| አንቀጽ ፻፱ | የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍና ናሙና መውሰድ | 58 |
| አንቀጽ ፻፲ | የተጠርጣሪነት ቃል | 58 |
| አንቀጽ ፻፲፩ | በመርማሪ ፖሊስ የሚሰጥ ዋስትና | 59 |
| አንቀጽ ፻፲፪ | ተጠርጣሪን ፍርድ ቤት ማቅረብ | 60 |
| አንቀጽ ፻፲፫ | ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ | 61 |
| አንቀጽ ፻፲፬ | ያልተጠናቀቀ ምርመራ ስለሚኖረው ውጤት | 61 |
| አንቀጽ ፻፲፭ | በማቆያ ቤት ያለ ሰው ስላለው መብት | 62 |
| አንቀጽ ፻፲፮ | በፍርድ ቤት የሚሰጥ ተጠርጣሪነት ቃል | 62 |


ክፍል ሰባት

የንብረት እግድ


| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፲፯ | መርህ | 63 |
| አንቀጽ ፻፲፰ | የዕግድ ማመልከቻ ማቅረብ | 64 |
| አንቀጽ ፻፲፱ | የማመልከቻው ይዘት | 64 |
| አንቀጽ ፻፳ | የዕግድ ትእዛዝ መስጠት | 65 |
| አንቀጽ ፻፳፩ | የዕግድ ትእዛዝን ማንሳት ወይም ማሻሻል | 65 |
| አንቀጽ ፻፳፪ | የዕግድ ትእዛዝ ቀሪ መሆን | 66 |


ክፍል ስምንት

ቀዳሚ ምርመራ


| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፳፫ | ዓላማ | 66 |
| አንቀጽ ፻፳፬ | ቀዳሚ ምርመራ የሚደረግባቸው ወንጀሎች | 66 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፷፭ | ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት | 67 |
| አንቀጽ ፻፷፮ | ቀዳሚ ምርመራ እንዲደረግ ስለማመልከት | 67 |
| አንቀጽ ፻፷፯ | የማስረጃ አመዘጋገብ | 67 |
| አንቀጽ ፻፷፰ | ተጨማሪ ማስረጃ | 68 |
| አንቀጽ ፻፷፱ | ምስክሮች እንዲቀርቡ ስለማሳወቅ | 68 |
| አንቀጽ ፻፸ | የመዝገብ ዝርዝር | 68 |
| አንቀጽ ፻፸፩ | የተጠርጣሪ አቆያየት | 69 |

ሦስተኛ መጽሐፍ

ዋስትና

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፸፪ | መርህ | 70 |
| አንቀጽ ፻፸፫ | ዋስትና በፍርድ ቤት ስለሚከለከልበት ሁኔታ | 70 |

ምዕራፍ ሁለት

በዋስትና ላይ ስለሚሰጥ ዉሳኔ

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፸፬ | በዋስትና ለመለቀቅ የሚቀርብ ማመልከቻ | 71 |
| አንቀጽ ፻፸፭ | በማመልከቻ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ | 71 |
| አንቀጽ ፻፸፮ | ዋስትናን መፍቀድ | 72 |
| አንቀጽ ፻፸፯ | በመያዣ ትእዛዝ ላይ ዋስትናን ማመልከት | 73 |
| አንቀጽ ፻፸፰ | ዋስትና ለማቅረብ ያልቻለ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ | 73 |
| አንቀጽ ፻፸፱ | ስለመልቀቅ | 73 |
| አንቀጽ ፻፹ | በስህተት ወይም በማታለል የተሰጠ ዋስትና | 74 |
| አንቀጽ ፻፹፩ | አዲስ ፍሬ ነገር | 74 |
| አንቀጽ ፻፹፪ | የዋስትና ግዴታ ቀሪ መሆን | 75 |
| አንቀጽ ፻፹፫ | የዋስትና ግዴታ | 75 |
| አንቀጽ ፻፹፬ | የዋስትና ግዴታን አለመፈጸም | 75 |
| አንቀጽ ፻፹፭ | ዋስትናን ስለማዉረድ | 76 |
| አንቀጽ ፻፹፮ | ይግባኝ ማቅረብ | 77 |

አራተኛ መጽሐፍ
በምርመራ መዝገብ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ
ምዕራፍ አንድ
በምርመራ መዝገብ ላይ የዐቃቤ ሕግ የመወሰን ስልጣን


| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፵፯ | ጠቅላላ | 77 |
| አንቀጽ ፻፵፰ | የዐቃቤ ሕግ ሥራ ከተፅዕኖ ነጻ ስለመሆኑ | 79 |
| አንቀጽ ፻፵፱ | የምርመራ መዝገብን መዝጋት | 79 |
| አንቀጽ ፻፶ | ክስ የማይመሰረትባቸው ሁኔታዎች | 79 |
| አንቀጽ ፻፶፩ | ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ አለመመሥረት | 80 |
| አንቀጽ ፻፶፪ | በክስ አለመመሠረት ጊዜ የሚኖር ሥነ-ሥርዐት | 81 |
| አንቀጽ ፻፶፫ | የምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም ክስ አለመመስረት ውጤት | 81 |
| አንቀጽ ፻፶፬ | በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ | 81 |


ምዕራፍ ሁለት
የወንጀል ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጥባቸው አማራጭ መንገዶችና ተለዋጭ መፍትሔዎች
ክፍል አንድ
ጠቅላላ


| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፶፭ | ዓላማ | 82 |
| አንቀጽ ፻፶፮ | አማራጭ  መንገዶች | 82 |


ክፍል ሁለት
የአማራጭ  መንገዶች አፈጻጸም
ንዑስ ክፍል አንድ
ዕርቅ


| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፶፯ | ዓላማ | 83 |
| አንቀጽ ፻፶፰ | መርህ | 83 |
| አንቀጽ ፻፶፱ | ዕርቅ የሚደረግበት ሁኔታ | 83 |
| አንቀጽ ፻፷ | የዕርቅ ይዘት | 84 |
| አንቀጽ ፻፷፩ | የዕርቅ ውጤት | 84 |


ንዑስ ክፍል ሁለት
የጥፋተኝነት ድርድር

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፸፪ | ዓላማ | 85 |
| አንቀጽ ፻፸፫ | የጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓት | 85 |
| አንቀጽ ፻፸፬ | በጥፋተኝነት ድርድር የሚታዩ ጉዳዮች | 85 |
| አንቀጽ ፻፸፭ | የተከለከሉ ተግባራት | 85 |
| አንቀጽ ፻፸፮ | ቅድመ ሁኔታ | 85 |
| አንቀጽ ፻፸፯ | ሂደቱን ለተከሳሽ ማስረዳት | 86 |
| አንቀጽ ፻፸፰ | በድርድር ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሥነ ሥርዓት | 87 |
| | | |
| አንቀጽ ፻፸፱ | የጥፋተኝነት ድርድር ይዘት | 87 |
| አንቀጽ ፻፹ | የፍርድ ቤት ሥልጣን | 88 |
| አንቀጽ ፻፹፩ | የስምምነት አለመጽደቅ ውጤት | 88 |
| አንቀጽ ፻፹፪ | የተጎጂ ተሳትፎ | 88 |
| | ንዑስ ክፍል ሦስት<br>ባሕላዊ ስርዓቶች | |
| አንቀጽ ፻፹፫ | ዓላማ | 89 |
| አንቀጽ ፻፹፬ | መርህ | 89 |
| አንቀጽ ፻፹፭ | የተከለከሉ ተግባራት | 89 |
| አንቀጽ ፻፹፮ | ቅድመ ሁኔታ | 90 |
| አንቀጽ ፻፹፯ | በባሕላዊ ሥርዓት እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ አቀራረብ | 90 |
| አንቀጽ ፻፹፰ | በባሕላዊ ሥርዓትና በመደበኛው ሥርዓት የሚታዩ ተያያዥ ወንጀሎች | 91 |
| አንቀጽ፻፹፱ | የውሳኔ አሰጣጥ | 91 |
| | ክፍል ሶስት<br>ተለዋጭ መፍትሔዎች | |
| አንቀጽ ፻፺ | ዓላማ | 91 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፹፩ | ተለዋጭ መፍትሔዎች ተፈጻሚ የሚሆኑባቸው ሰዎች | 92 |
| አንቀጽ ፻፹፪ | ተለዋጭ መፍትሔዎች እና የመወሰን ስልጣን | 92 |
| አንቀጽ ፻፹፫ | የውሳኔው ይዘት | 93 |
| አንቀጽ ፻፹፬ | ተለዋጭ መፍትሔዎች ፈጻሚ አካላት | 93 |
| አንቀጽ ፻፹፭ | የተፈጸመ ተለዋጭ መፍትሔ የሚኖረው ውጤት | 94 |
| አንቀጽ ፻፹፮ | ያልተፈጸመ ወይም ውጤታማ ያልሆነ ተለዋጭ መፍትሔ ውጤት | 94 |
| አንቀጽ ፻፹፯ | ይግባኝ | 95 |

ምዕራፍ ሶስት

ክስ መመስረት

ክፍል አንድ

በዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ ክስ

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፹፰ | መርህ | 95 |
| አንቀጽ ፻፹፱ | የክስ ማመልከቻ ይዘት | 95 |
| አንቀጽ ፻፺ | ክስን ማጣመር | 96 |
| አንቀጽ ፻፺፩ | ክሶችን መነጣጠል | 96 |
| አንቀጽ ፻፺፪ | ተከሳሾችን አጣምሮ መክሰስ | 97 |
| አንቀጽ ፻፺፫ | አማራጭ ክስ | 97 |
| አንቀጽ ፻፺፬ | ቅጣትን የሚያከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ | 97 |
| አንቀጽ ፻፺፭ | በሙከራ፣ በአነሳሽነት፣ በአባሪነት ወይም በመዘጋጀት ጥፋተኛ መሆን | 98 |
| አንቀጽ ፻፺፮ | ክስ ስለሚመሠረትበት የጊዜ ገደብ | 98 |
| አንቀጽ ፻፺፯ | በጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አለመመሥረት | 98 |
| አንቀጽ ፻፺፰ | ክስ ማቋረጥ እና ማንሳት | 99 |

ክፍል ሁለት

የግል ክስ የሚቀርብበት ሥነ-ሥርዓት

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፺፱ | የግል ክስ አቀራረብ | 100 |
| አንቀጽ ፪፻ | የግል ክስ ለማቅረብ መብት ያለው ሰው | 101 |
| አንቀጽ ፪፻፩ | የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል ስለማዘዝ | 101 |
| አንቀጽ ፪፻፪ | ተከራካሪዎችን ስለመጥራት | 101 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፫ | ተከራካሪዎችን ስለማስታረቅ | 101 |
| አንቀጽ ፪፻፬ | ኪሣራ ላይ ስለሚደረግ መተማመኛ | 102 |
| አንቀጽ ፪፻፭ | ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ በታወቀ ጊዜ የሚፈጸም ሥነ-ሥርዓት | 102 |

ክፍል ሶስት

የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ የሚቀርብበት ሥርዐት

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፮ | በዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ | 103 |
| አንቀጽ ፪፻፯ | ተጎጂ ስለሚያቀርበው የፍትሐብሔር ክስ | 103 |
| አንቀጽ ፪፻፰ | የዳኝነትና ሌሎች ወጪዎች ክፍያ | 104 |
| አንቀጽ ፪፻፱ | ክስ አቅራቢው ስለሚኖረው መብት | 104 |
| አንቀጽ ፪፻፲ | የተከሳሽ ጥፋተኛ አለመሆን ወይም የመለቀቅ ውጤት | 104 |

አምስተኛ መጽሐፍ

መደበኛ የክርክር ሥነ- ሥርዓት፣ ማስረጃ እና ፍርድ

ምዕራፍ አንድ

መደበኛ የክርክር ሥነ- ሥርዓት

ክፍል አንድ

መጥራት

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፲፩ | ጠቅላላ | 105 |
| አንቀጽ ፪፻፲፪ | የመጥሪያ ይዘት | 105 |
| አንቀጽ ፪፻፲፫ | መጥሪያ የማዘጋጀትና የማድረስ ኃላፊነት | 105 |
| አንቀጽ ፪፻፲፬ | መጥሪያ የመቀበል ግዴታ | 106 |
| አንቀጽ ፪፻፲፭ | የመጥሪያ አለመድረስ | 106 |
| አንቀጽ ፪፻፲፮ | የተከሳሽ ወይም በፍርድ ቤት የተጠራ ሰው አለመቅረብ | 107 |
| አንቀጽ ፪፻፲፯ | ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ክስ | 107 |
| አንቀጽ ፪፻፲፰ | ተከሳሹ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ | 108 |
| አንቀጽ ፪፻፲፱ | የክሱ እንደገና መታየት | 108 |
| አንቀጽ ፪፻፳ | ማመልከቻ የሚቀርብበት ጊዜ | 108 |
| አንቀጽ ፪፻፳፩ | ተከሳሽ በሌለበት የማይታይ ክስ | 108 |

ክፍል ሁለት

የችሎት አመራር

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፹፪ | ግልፅ ችሎት | 109 |
| አንቀጽ ፪፻፹፫ | የችሎት ስርዐት ማስጠበቅ | 109 |
| አንቀጽ ፪፻፹፬ | የዉሳኔ አሰጣጥ | 109 |

ክፍል ሶስት

ቅድመ ክስ መስማት ተግባራት

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፹፭ | የክስ ማመልከቻ ማቅረብ | 110 |
| አንቀጽ ፪፻፹፮ | የክስ መዝገብ መክፈት | 110 |
| አንቀጽ ፪፻፹፯ | የክስ ሕጋዊ ብቃት ማረጋገጥ | 111 |
| አንቀጽ ፪፻፹፰ | ክሱ የሚሰማበትን ቀን ስለመወሰን | 112 |
| አንቀጽ ፪፻፹፱ | የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት | 112 |
| አንቀጽ ፪፻፺ | በቅድመ ክስ መስማት የሚከናወኑ ተግባራት | 113 |

ምዕራፍ ሁለት

ክስ መስማት

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፺፩ | የክስ መስማት አጀማመር | 114 |
| አንቀጽ ፪፻፺፪ | የመደበኛ ክርክር ሥነ-ሥርዓት ተፈጻሚነት | 114 |

ክፍል ሁለት

ቀጠሮና የቀጠሮ ውጤት

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፴፫ | የፍርድ ሂደት ተከታታይነት | 115 |
| አንቀጽ ፪፻፴፬ | የመደበኛ ክርክር ሥርዓት የጊዜ ገደብ | 115 |
| አንቀጽ ፪፻፴፭ | የቀጠሮ ምክንያት | 115 |
| አንቀጽ ፪፻፴፮ | የክስ መስማት ሂደትን በሕመም ምክንያት መከታተል አለመቻል | 117 |

ክፍል ሦስት

የክስ መቃዎሚያ እና የተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል

ንዑስ ክፍል አንድ

የክስ መቃወሚያ

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፴፯ | ክስን መቃወም | 118 |
| አንቀጽ ፪፻፴፰ | በመቃወሚያ ላይ መወሰን | 120 |
| አንቀጽ ፪፻፴፱ | ክስ ተነጣጥሎ የሚታይበት ሁኔታ | 120 |
| አንቀጽ ፪፻፵ | ክስን መለወጥ፣መጨመር ወይም ማሻሻል | 120 |

ንዑስ ክፍል ሁለት

የተከሳሽ እምነት ክህደት ቃል

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፵፩ | ተከሳሹን የእምነት ወይም ክህደት ቃል መቀበል | 121 |
| አንቀጽ ፪፻፵፪ | የተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃል | 122 |
| አንቀጽ ፪፻፵፫ | የተከሳሹን የእምነት ክህደት ቃል ስለማሻሻል | 122 |

ምዕራፍ ሶስት

ማስረጃና ብይን

ክፍል አንድ

የክስ መግለጫና የክርክር መክፈቻ ንግግር

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፵፬ | የክርክር መክፈቻ ንግግር | 123 |

ክፍል ሁለት

በማስረጃ መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸውና የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

ንዑስ ክፍል አንድ

በማስረጃ የሚረጋገጡ ፍሬ ነገሮች

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፵፭ | ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ፍሬ ነገር | 124 |
| አንቀጽ ፪፻፵፮ | አግባብነት ያለው ማስረጃ | 124 |

ንዑስ ክፍል ሁለት

በማስረጃ መረጋገጥ የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፷፯ | ጠቅላላ | 125 |
| አንቀጽ ፪፻፷፰ | የታመነ ፍሬ ነገር | 125 |
| አንቀጽ ፪፻፷፱ | ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ፍሬ ነገር | 126 |
| አንቀጽ ፪፻፸ | የሕግ ግምት | 126 |

ንዑስ ክፍል ሶስት

የማስረጃ ተቀባይነት

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፸፩ | ተቀባይነት ስላለው ማስረጃ | 127 |
| አንቀጽ ፪፻፸፪ | ተቀባይነት የሌለው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ | 127 |
| አንቀጽ ፪፻፸፫ | የተከሳሽን ወይም የተጎጂን ጠባይ የሚያስረዳ ማስረጃ | 128 |
| አንቀጽ ፪፻፸፬ | የቀድሞ ጥፋቶችና መሰል ተግባራት | 129 |

ክፍል ሶስት

የማስረጃ አይነቶች

ንዑስ ክፍል አንድ

የሰው ማስረጃ

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፪፻፸፭ | የመመስከር ብቃትና ግዴታ | 129 |
| አንቀጽ ፪፻፸፮ | ለመመስከር ያለመገደድ ልዩ መብት | 130 |
| አንቀጽ ፪፻፸፯ | በምስክርነት አለመቅረብ | 130 |
| አንቀጽ ፪፻፸፰ | የመንግሥት ምስጢርን ስለመጠበቅ | 130 |
| አንቀጽ ፪፻፸፱ | በሌላ ፍርድ ቤት የተሰጠ የምስክርነት ቃል ስለሚቀርብበት ሁኔታ | 131 |
| አንቀጽ ፪፻፹ | በምርመራ ላይ የተሰጠ ቃል በማስረጃነት መቅረብ | 131 |
| አንቀጽ ፪፻፹፩ | የምስክሮች ብዛትና አቀራረብ ቅደም ተከተል መወሰን | 131 |
| አንቀጽ ፪፻፹፪ | ቃለ-መኃላ መፈጸም ወይም ማረጋገጫ መስጠት | 132 |
| አንቀጽ ፪፻፹፫ | የምስክርነት ቃል መቀበል | 132 |
| አንቀጽ ፪፻፹፬ | ማስታወሻ፣ሰነድ ወይም መዛሪያን ስለመጠቀም | 133 |
| አንቀጽ ፪፻፹፭ | ለምስክር የሚቀርብ ጥያቄ አግባብነት | 133 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፩፻፳፮ | ለምስክር የሚቀርብ ዋና ጥያቄ | 134 |
| አንቀጽ ፩፻፳፯ | መስቀለኛ ጥያቄ | 135 |
| አንቀጽ ፩፻፳፰ | የማስተባበያ ጥያቄ የተከለከለ መሆን | 135 |
| አንቀጽ ፩፻፳፱ | ድጋሚ ጥያቄ | 135 |
| አንቀጽ ፩፻፴ | የፍርድ ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ | 136 |
| አንቀጽ ፩፻፴፩ | በፍርድ ቤቱ ስለሚጠራ ምስክር | 136 |
| አንቀጽ ፩፻፴፪ | በዳኛ ስለሚወሰድ ጥንቃቄ | 136 |
| አንቀጽ ፩፻፴፫ | ክንዋኔዎችን መመዝገብ | 137 |
| ንዑስ ክፍል ሁለት<br>የሰነድ ማስረጃ | | |
| አንቀጽ ፩፻፴፬ | ፍሬ ነገሮችን በሰነድ ስለማስረዳት | 138 |
| አንቀጽ ፩፻፴፭ | የአንድን ፍሬ ነገር መከሰት ስለማስረዳት | 138 |
| አንቀጽ ፩፻፴፮ | የሕዝብ መዛግብትን ይዘት ትክክለኛነትን ማረጋገጥ | 139 |
| አንቀጽ ፩፻፴፯ | የመንግስት ሰነድ ይዘት ትክክለኛነት ማረጋገጥ | 139 |
| አንቀጽ ፩፻፴፰ | የንግድ መዝገብ ይዘትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ | 139 |
| አንቀጽ ፩፻፴፱ | የፊርማን ወይም የጽሑፍ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ | 140 |
| አንቀጽ፩፻፵ | በማኅተም ወይም ፊርማ ላይ የሚወሰድ የሕግ ግምት | 140 |
| አንቀጽ ፩፻፵፩ | የሕግ ግምት የሚወሰድበት ሰነድ | 141 |
| አንቀጽ ፩፻፵፪ | በሦስተኛ ወገን ይዞታ ስለሚገኝ ሰነድ | 141 |
| ንዑስ ክፍል ሶስት<br>የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ | | |
| አንቀጽ ፩፻፵፫ | በኤሌክትሮኒክ ማስረጃ የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር | 141 |
| አንቀጽ ፩፻፵፬ | የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ትክክለኛነት | 142 |
| ንዑስ ክፍል አራት<br>ኤግዚቢት | | |
| አንቀጽ፩፻፵፭ | ኤግዚቢት | 143 |
| አንቀጽ ፩፻፵፮ | የኤግዚቢትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ | 143 |
| ክፍል አራት | | |

| | | |
|---|---|---|
| ብይን ስለመስጠት | | |
| አንቀጽ ፪፻፹፯ | በዐቃቤ ህግ ማስረጃ ላይ የሚሰጥ አስተያየት | 143 |
| አንቀጽ፪፻፹፰ | የዐቃቤ ሕግ የማስረዳት ኃላፊነትና የማስረዳት ደረጃ | 144 |
| አንቀጽ ፪፻፹፱ | ብይን | 144 |
| ክፍል አምስት<br>የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ | | |
| አንቀጽ ፪፻፺ | የተከሳሹ የክርክር መክፈቻ ንግግር | 145 |
| አንቀጽ ፪፻፺፩ | የተከሳሽን የመከላከያ ማስረጃ መስማት | 145 |
| አንቀጽ ፪፻፺፪ | በዐቃቤ ሕግ ወይም በፖሊስ እጅ የሚገኝ ማስረጃ | 146 |
| አንቀጽ ፪፻፺፫ | የተከሳሹ የማስረዳት ኃላፊነት | 146 |
| አንቀጽ ፪፻፺፬ | የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት | 146 |
| ክፍል ስድስት<br>የወል ድንጋጌዎች | | |
| አንቀጽ ፪፻፺፭ | ተጨማሪ ማስረጃ | 147 |
| አንቀጽ ፪፻፺፮ | አግባብነት ወይም ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ውጤት | 147 |
| አንቀጽ ፪፻፺፯ | በማስረጃ ላይ ስለሚቀርብ መቃወሚያ | 147 |
| አንቀጽ ፪፻፺፰ | የክርክር ማቆሚያ ንግግር | 148 |
| አንቀጽ ፪፻፺፱ | የሥርዓት ጉድለትን ማረም | 148 |
| ምዕራፍ አራት<br>ፍርድ እና ቅጣት<br>ክፍል አንድ<br>የፍርድ አሰጣጥ | | |
| አንቀጽ ፫፻ | ፍርድ | 149 |
| አንቀጽ ፫፻፩ | የፍርድ አፃፃፍ | 149 |
| አንቀጽ ፫፻፪ | የቅጣት አስተያየት | 150 |
| አንቀጽ ፫፻፫ | የቅጣት ውሳኔ | 151 |
| ክፍል ሁለት<br>የቅጣት አፈፃፀም<br>ንዑስ ክፍል አንድ<br>ጠቅላላ ድንጋጌዎች | | |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፻፺፬ | መርህ | 152 |
| አንቀጽ ፻፺፭ | የቅጣት አፈጻጸም ትእዛዝ | 152 |
| ንዑስ ክፍል ሁለት<br>የሞት ቅጣት አፈጻጸም | | |
| አንቀጽ ፻፺፮ | የሞት ቅጣት ውሳኔ የሚፈጸምበት ሁኔታ | 153 |
| አንቀጽ ፻፺፯ | የሞት ቅጣት አፈጻጸምን ስለማገድ | 153 |
| ንዑስ ክፍል ሶስት<br>የእስራት ቅጣት አፈጻጸም | | |
| አንቀጽ ፻፺፰ | ቅጣት እንዲፈፀም የሚሰጥ ትእዛዝ | 154 |
| አንቀጽ ፻፺፱ | የእስራት ቅጣት እንዲተላለፍ የሚቀርብ አቤቱታ | 154 |
| አንቀጽ፻፺፲ | የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ | 155 |
| አንቀጽ ፻፺፲፩ | የተላለፈን ቅጣት ማቋረጥ | 156 |
| ንዑስ ክፍል አራት<br>የገንዘብ ቅጣት | | |
| አንቀጽ፻፺፲፪ | የገንዘብ ቅጣት አፈጻጸም | 157 |
| አንቀጽ ፻፺፲፫ | የክፍያ ቅደም ተከተል | 158 |
| ንዑስ ክፍል አምስት<br>የተጨማሪ ቅጣት አፈጻጸም | | |
| አንቀጽ ፻፺፲፬ | ተጨማሪ ቅጣት | 158 |
| አንቀጽ ፻፺፲፭ | ተጨማሪ ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎችን ስለማሳወቅ | 158 |
| አንቀጽ ፻፺፲፮ | ንብረትን መውረስ | 158 |
| አንቀጽ ፻፺፲፯ | ይቅርታ | 159 |
| ክፍል ሶስት<br>ቅጣትን ስለመለወጥ፣አማራጭ ቅጣትና ስለመሰየም<br>ንዑስ ክፍል አንድ<br>ቅጣትን ስለመለወጥ | | |
| አንቀጽ ፻፺፲፰ | የቅጣት ትእዛዝን መለወጥ | 160 |
| አንቀጽ ፻፺፲፱ | የማመልከቻ አቀራረብና ውሳኔ | 160 |
| ንዑስ ክፍል ሁለት | | |

| | | |
|---|---|---|
| አማራጭ ቅጣት | | |
| አንቀጽ ፫፻፷ | መርህ | 161 |
| አንቀጽ ፫፻፷፩ | በውሳኔ የሚገለጹ ጉዳዮች | 161 |
| አንቀጽ ፫፻፷፪ | አማራጭ ቅጣትን ማቋረጥ | 162 |
| አንቀጽ ፫፻፷፫ | የአማራጭ ቅጣት አስፈፃሚ አካል | 163 |
| ንዑስ ክፍል ሶስት<br>ስለመሰየም | | |
| አንቀጽ ፫፻፷፬ | ዓላማ | 163 |
| አንቀጽ ፫፻፷፭ | የመሰየም ሥነ-ሥርዓት | 163 |
| ስድስተኛ መጽሐፍ<br>ፍርድን እንደገና ማየት፣ ይግባኝና ሰበር<br>ምዕራፍ አንድ<br>ተከሳሽ በሌለበት የተካሄደን የፍርድ ሂደትና ፍርድን እንደገና ስለማየት | | |
| አንቀጽ ፫፻፷፮ | ማመልከቻ ማቅረብ | 164 |
| አንቀጽ ፫፻፷፯ | በማመልከቻው ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ | 164 |
| ምዕራፍ ሁለት<br>ይግባኝ | | |
| አንቀጽ ፫፻፷፰ | ዓላማ | 165 |
| አንቀጽ ፫፻፷፱ | ይግባኝ ማቅረብ | 166 |
| አንቀጽ ፫፻፸ | ይግባኝ ስለሚያቀርቡ ሰዎች | 166 |
| አንቀጽ ፫፻፸፩ | ይግባኝ የሚባልባቸው ጉዳዮች | 166 |
| አንቀጽ ፫፻፸፪ | ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች | 167 |
| አንቀጽ ፫፻፸፫ | የቅጣት ውሳኔ ማገድ | 167 |
| አንቀጽ ፫፻፸፬ | የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሥልጣን | 168 |
| አንቀጽ ፫፻፸፭ | ሰነድ፣ ግልባጭ ወይም መረጃ ማግኘት | 168 |
| አንቀጽ ፫፻፸፮ | የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ | 169 |
| አንቀጽ ፫፻፸፯ | የይግባኝ ማመልከቻ ይዘት | 169 |
| አንቀጽ ፫፻፸፰ | ሬጅስትራር የሚያከናውነው ተግባር | 170 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፫፻፴፱ | የይግባኝ ማስፈቀጃ | 171 |
| አንቀጽ ፫፻፵ | የይግባኝ ቅሬታ መመርመር | 171 |
| አንቀጽ ፫፻፵፩ | መጥሪያ | 172 |
| አንቀጽ ፫፻፵፪ | ይግባኙን መስማት | 172 |
| አንቀጽ ፫፻፵፫ | የተዘጋ መዝገብ መክፈት | 173 |
| አንቀጽ ፫፻፵፬ | ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል | 173 |
| አንቀጽ ፫፻፵፭ | ውሳኔ መስጠት | 174 |
| | ምዕራፍ ሦስት<br>ሰበር | |
| አንቀጽ ፫፻፵፮ | ዓላማ | 175 |
| አንቀጽ ፫፻፵፯ | መርህ | 175 |
| አንቀጽ ፫፻፵፰ | የሰበር ማመልከቻ ማቅረብ | 175 |
| አንቀጽ ፫፻፵፱ | መሠረታዊ የሕግ ስሕተት | 176 |
| አንቀጽ ፫፻፶ | ለሰበር የማይቀርብ ጉዳይ | 176 |
| አንቀጽ ፫፻፶፩ | ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝን ማገድ | 176 |
| አንቀጽ ፫፻፶፪ | የሰበር ማመልከቻ ይዘት | 177 |
| አንቀጽ ፫፻፶፫ | የሰበር ማመልከቻን መመርመር | 177 |
| አንቀጽ ፫፻፶፬ | የሰበር ውሳኔ መስጠት | 177 |
| አንቀጽ ፫፻፶፭ | የሰበር ውሳኔ ውጤት | 178 |
| | ምዕራፍ አራት<br>የመጨረሻ ፍርድን እንደገና ማየት | |
| አንቀጽ ፫፻፶፮ | ዓላማ | 178 |
| አንቀጽ ፫፻፶፯ | የወንጀል ፍርድ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ | 178 |
| አንቀጽ ፫፻፶፰ | የማመልከቻው ይዘትና የሚቀርብበት ጊዜ | 179 |
| አንቀጽ ፫፻፶፱ | ማልከቻውን መስማት እና መወሰን | 179 |
| አንቀጽ ፫፻፷ | ካሣ | 180 |
| | ሰባተኛ መጽሐፍ<br>ልዩ ሥነ-ሥርዐት<br>ምዕራፍ አንድ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ተፈፃሚነት | |
| አንቀጽ ፫፻፷፩ | ተፈፃሚነት | 180 |
| | ምዕራፍ ሁለት<br>በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶችና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች<br>ክፍል አንድ<br>በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች የክስ ሥነ-ሥርዐት | |
| አንቀጽ ፫፻፷፪ | መርህ | 181 |
| አንቀጽ ፫፻፷፫ | ተፈጻሚነት | 181 |
| አንቀጽ ፫፻፷፬ | የምርመራ አጀማመርና የክስ አመሠራረት | 182 |
| አንቀጽ ፫፻፷፭ | ምርመራው የሚያካትታቸው ሁኔታዎች | 183 |
| አንቀጽ ፫፻፷፮ | ቤተሰብ ወይም አሳዳጊ መጥራት | 183 |
| አንቀጽ ፫፻፷፯ | በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ማቆየት | 184 |
| አንቀጽ ፫፻፷፰ | የተቋም ክትትል | 184 |
| አንቀጽ ፫፻፷፱ | ጊዜያዊ ትእዛዝ | 185 |
| አንቀጽ ፫፻፸ | ክስ መመሥረት | 185 |
| አንቀጽ ፫፻፸፩ | መጥራት | 186 |
| አንቀጽ ፫፻፸፪ | ክሱ የሚሰማበት ሁኔታ | 186 |
| አንቀጽ ፫፻፸፫ | ፍርድ | 187 |
| አንቀጽ ፫፻፸፬ | ሌሎች ሰዎች ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ | 188 |
| አንቀጽ ፫፻፸፭ | ትእዛዝ ወይም ውሳኔ መለወጥ ወይም ማሻሻል | 188 |
| | ክፍል ሁለት<br>ደንብ መተላለፍ ስለ ሚመራበት ሥነ ሥርዐት | |
| አንቀጽ ፫፻፸፮ | ተፈጻሚነት | 189 |
| አንቀጽ ፫፻፸፯ | ደንብ ተላላፊ እንዲጠራ የሚቀርብ ማመልከቻ | 189 |
| አንቀጽ ፫፻፸፰ | መጥሪያ መላክ | 189 |
| አንቀጽ ፫፻፸፱ | ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ክስን ማመን | 190 |
| አንቀጽ ፫፻፹ | ክሱ በታመነ ጊዜ የሚኖር ሥነ-ሥርዐት | 190 |
| አንቀጽ፫፻፹፩ | ክሱ በተካደ ጊዜ የሚኖር ሥነ-ሥርዐት | 191 |
| አንቀጽ ፫፻፹፪ | ደንብ ተላላፊ ባልቀረበ ጊዜ የሚኖር ሥነ-ሥርዐት | 191 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፫፻፹፫ | ልዩ ሁኔታ | 192 |
| ስምንተኛ መጽሐፍ<br>በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር<br>ምዕራፍ አንድ<br>በወንጀል የምርመራና ክስ ሂደት ጉዳዮች ትብብር<br>ክፍል አንድ<br>ጠቅላላ ድንጋጌዎች | | |
| አንቀጽ ፫፻፹፬ | ዓላማ | 193 |
| አንቀጽ፫፻፹፭ | መርህ | 194 |
| አንቀጽ ፫፻፹፮ | ትብብር ማድረግ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች | 194 |
| አንቀጽ ፫፻፹፯ | የትብብር ዓይነቶች | 195 |
| አንቀጽ፫፻፹፰ | የትብብር መስመርና የማስፈጸም ሥልጣን | 195 |
| አንቀጽ ፫፻፹፱ | የትብብር ወጪ | 196 |
| አንቀጽ ፫፻፺ | የትብብር ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ አካላት | 196 |
| ክፍል ሁለት<br>የትብብር ጥያቄ | | |
| አንቀጽ ፫፻፺፩ | የጥያቄው አቀራረብ | 197 |
| አንቀጽ ፫፻፺፪ | የትብብር ጥያቄ ይዘት | 197 |
| አንቀጽ ፫፻፺፫ | የጥያቄውን ተቀባይነት፣ አግባብነት ማረጋገጥ እና ውሳኔ መስጠት | 198 |
| አንቀጽ ፫፻፺፬ | ማረጋገጫ መስጠት | 199 |
| ክፍል ሶስት<br>የትብብር አፈጻጸም | | |
| አንቀጽ ፫፻፺፭ | ጠቅላላ | 200 |
| አንቀጽ ፫፻፺፮ | የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ትብብር | 200 |
| አንቀጽ ፫፻፺፯ | በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ሰው በጊዜያዊነት የማስተላለፍ ትብብር | 201 |
| አንቀጽ ፫፻፺፰ | በውጭ ሀገር ያለን ሰው ለትብብር መጠየቅ | 202 |
| አንቀጽ ፫፻፺፱ | በጠያቂ ሀገር ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት መቆየት ያለው ውጤት | 202 |
| አንቀጽ ፬፻ | መረጃና ማስረጃ ልውውጥ | 202 |
| አንቀጽ ፬፻፩ | መጥሪያና ሌሎች ሰነዶች የማድረስ ትብብር | 202 |

| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፩፻፪ | የፍርድ ሂደትን ማስተላለፍ | 203 |
| አንቀጽ ፩፻፫ | ፍርደኛን ማስተላለፍ | 203 |
| አንቀጽ ፩፻፬ | የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ፍርድ፣ ብይን ወይም ውሳኔ ዕውቅና መስጠትና ማስፈጸም | 204 |
| አንቀጽ ፩፻፭ | በኢትዮጵያ ግዛት እስረኛን ማስተላለፍ | 205 |
| ምዕራፍ ሁለት<br>በወንጀል ተፈላጊን ሰው አሳልፎ ስለመስጠት<br>ክፍል አንድ<br>አሳልፎ ለመስጠት በቀረበ ጥያቄ ላይ የሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት | | |
| አንቀጽ ፩፻፮ | ትርጉም | 206 |
| አንቀጽ ፩፻፯ | አሳልፎ የሚያሰጥ ወንጀል ወይም ቅጣት | 206 |
| አንቀጽ ፩፻፰ | ጣምራ የወንጀል ድርጊት | 207 |
| አንቀጽ ፩፻፱ | አሳልፎ መስጠት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች | 207 |
| ክፍል ሁለት<br>የአሳልፎ መስጠት ሥነሥርዐት | | |
| አንቀጽ ፩፻፲ | የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ይዘትና ስለሚቀርብ ሰነድ | 208 |
| አንቀጽ ፩፻፲፩ | ተደራራቢ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ | 209 |
| አንቀጽ ፩፻፲፪ | ጊዚያዊ እሥር | 209 |
| አንቀጽ ፩፻፲፫ | የአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄን ለፍርድ ቤት ማቅረብ | 210 |
| አንቀጽ ፩፻፲፬ | ተፈላጊውን ሰው መያዝ | 211 |
| አንቀጽ ፩፻፲፭ | ተፈላጊውን ሰው ፍርድ ቤት ማቅረብ | 211 |
| አንቀጽ ፩፻፲፮ | መስማትና ውሳኔ መስጠት | 212 |
| አንቀጽ ፩፻፲፯ | በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት | 213 |
| አንቀጽ ፩፻፲፰ | ይግባኝ ወይም እንደገና እንዲታይ መጠየቅ | 213 |
| አንቀጽ ፩፻፲፱ | ውሳኔን ስለማሳወቅ | 213 |
| አንቀጽ ፩፻፳ | ተፈላጊውን ማስረከብ | 213 |
| አንቀጽ ፩፻፳፩ | የውሳኔ ተፈጻሚነትን ማራዘም ወይም ማገድ | 214 |
| አንቀጽ ፩፻፳፪ | ውድቅ በተደረገ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ላይ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት | 214 |
| አንቀጽ ፩፻፳፫ | በጊዚያዊነት ተላልፎ የተሰጠ ሰው | 215 |

https://ethiolex.com


| | | |
|---|---|---|
| አንቀጽ ፬፻፷፬ | የተፈላጊው ሰዉ እና ማስረጃ ርክክብ | 215 |
| ምዕራፍ ሶስት<br>በኢትዮጵያ ማስተላለፍ የሚፈጸምበት ሥነ-ሥርዐት | | |
| አንቀጽ ፬፻፷፭ | ማስተላለፍን ስለመፍቀድ | 216 |
| አንቀጽ ፬፻፷፮ | በመተላለፍ ያለ ተፈላጊን ስለማሰር | 216 |
| አንቀጽ ፬፻፷፯ | ልዩ ሁኔታ | 216 |
| ዘጠነኛ መጽሐፍ<br>ልዩ ልዩ ጉዳዮች<br>ምዕራፍ አንድ<br>ኪሳራና ወጪ | | |
| አንቀጽ ፬፻፷፰ | የዐቃቤ ሕግ የክስ ወጪ | 217 |
| አንቀጽ ፬፻፷፱<br>፬፻፸፱ | በግል አቤቱታ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወጪ | 217 |
| አንቀጽ ፬፻፸ | የፍትሐብሔር ክርክር ወጪና ኪሳራ | 218 |
| አንቀጽ ፬፻፸፩ | የምስክር ወጪ | 218 |
| ምዕራፍ ሁለት<br>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን | | |
| አንቀጽ ፬፻፸፪ | ደንብ የማውጣት ሥልጣን | 219 |
| አንቀጽ ፬፻፸፫ | መመሪያ የማውጣት ሥልጣን | 219 |
| ምዕራፍ ሦስት<br>የሥነ-ሥርዐት ሕጉን ማሻሻል | | 220 |
| አንቀጽ ፬፻፸፬ | ሕጉን ስለማሻሻል | 220 |

https://ethiolex.com

**አዋጅ ቁጥር..../፳፻፲ ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ**

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣መርሆች እና እሴቶች ጋር ለማጣጣምና ለማስፈጸም የሚያስችል ዘመናዊ የወንጀል ፍትህ ሂደት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሥርዐት የወንጀል ፍርድ ሂደት የተጠርጣሪን እና የተከሳሽን እንዲሁም የወንጀል ተጎጅዎችን ሰብዓዊ መብቶችን ለማክበርና ለማስከበር፣ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚያስችል ወጥ እና የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፣

ሀገሪቱ በወንጀል ፍትሕ ሥርዐት በዓለም አቀፍ ሕግ ያሏትን መብቶች ለማስከበርና የተጣሉባትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤

የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ለጠቅላላው ጥቅም እንዲሰራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና የወንጀል ክርክር የሚመራበትን የሥነ-ሥርዐትና የማስረጃ ድንጋጌ ወጥና አካታች በሆነ መልኩ እንደገና ማደራጀት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና ፶፭ (፭) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ሕግ የ **"፳፻፲ዓ.ም የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ "** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

**፩.** የ፲፱፻፶፬ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፶፬ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ተሽሯል፡፡

**፪.** በሌሎች አዋጆች የተመለከቱ የወንጀል ምርመራ፣ የዳኝነት ስልጣን፣ የሥነ-ሥርዐት ፣ የማስረጃ እና ዓለምአቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

፫. ከዚህ ሕግ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ ፣ መመሪያ እና አሰራር በዚህ ሕግ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ስለ ወታደራዊ ወንጀሎች የተደነገጉ ልዩ የሥነ-ሥርዐት እና ማስረጃ ደንቦች የተጠበቁ ናቸው፡፡

፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

፩. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የተጀመረ ጉዳይ በተጀመረበት የሥነሥርዐት ሕግ መሠረት ይጠናቀቃል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም፣ ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የተፈጸመ የወንጀል ጉዳይ ተጠርጣሪውን የሚጠቅም ከሆነ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል፡፡

፫. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት ምርመራው ያልተጀመረ የወንጀል ጉዳይ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል፡፡

፬ . በዚህ ሕግ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም ዋስትናን በተመለከተ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻ጠ፪/፩ ተፈፃሚ የሚሆነው ይህ ሕግ ከፀደቀ ከአምስት ዓመት በኋላ ነው፡፡

**፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተደነገገው ቢኖርም የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እንደአግባብነቱ ተፈፃሚነቱን ለተጨማሪ አምስት ዓመት ሊያራዝመው ይችላል፡፡**

**፮. ለሽብር ወንጀል እና በሕግ ዋስትና የሚከለከሉ ወንጀሎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ለተደነገገው የጊዜ ገደብ ያህል ዋስትና አይፈቀድም፡፡**

**፯.የተለዋጭ ቅጣት አስፈፃሚ ቦርድ እስኪቋቋም ድረስ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች እና የተከላካይ ጠበቃ ተቋም እስኪቋቋም ድረስ ጠቅላይ ፍርድቤት ተግባራቱን እያከናወኑ ይቆያሉ፡፡**

፬. <u>ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ሕግ አዋጅ ቁጥር .../ <u>፳፻፲</u> ዓ.ም ሆኖ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከሙቶ ሰማንያ ቀናት በኋላ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ____________ ቀን <u>፳፻፲</u> ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# የወንጀል ሕግ ሥነሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ

## አንደኛ መጽሐፍ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ መርሆዎች፣ የተቋማት ኃላፊነት እና የዳኝነት ሥልጣን

## ምዕራፍ ፩

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና መርሆዎች

## ክፍል ፩

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፩ የተፈፃሚነት ወሰን

፩. ይህ ሕግ የ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪. የወንጀል ሕግ ማለት የ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ እና በሕጉ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚወጡ ልዩ የወንጀል ሕጎችን ያካትታል፡፡

### አንቀጽ ፪ ትርጓሜ

በዚህ ሕግ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡-

፩.**"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጠው ክልል ነው፡፡

፪. **"መርማሪ ፖሊስ"** ማለት በሕግ መሠረት የወንጀል ምርመራ ለማድረግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው፡፡

፫. **"ፖሊስ"** ማለት የፌዴራል ወይም የክልል ፖሊስ ተቋም ነው፡፡

፬. **"የፌዴራል ፖሊስ"** ማለት የፌዴራል ፖሊስ ተቋም ሲሆን፣ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ፖሊስን ይጨምራል፡፡

፭. **"የዐቃቤ ሕግ ተቋም"** ማለት የፌዴራል ወይም የክልል ዐቃቤ ሕግ ተቋም ነው፡፡

፮.**"ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ"** ማለት የፌዴራል ወይም የክልል ዐቃቤ ሕግ ተቋም ኃላፊ ነው፡፡

፯. **"ዐቃቤ ሕግ"** ማለት በሕግ የዐቃቤ ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን እና ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን ያጠቃልላል፡፡

፰. **"ፍርድ ቤት"** ማለት በወንጀል ጉዳይ ላይ የዳኝነት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው፡፡

፱. **"ሬጅስትራር"** ማለት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፰ሥር የተመለከቱት እና በሌላ ሕግ የተለዩ ተግባራትን የሚያከናውን የፍርድ ቤት ሹም ነው፡፡

፲. **"የጥብቅና ተቋም"** ማለት በወንጀል ጉዳይ ለተጠረጠረ፣ ለተከሰሰ ወይም ለተፈረደበት ግለሰብ በግል ወይም በተቋምየጥብቅና አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የተከላካይ ጠበቃ ተቋምንና የወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃን ያካትታል ፡፡

፲፩. **"ማቆያ ቤት"** ማለት በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የወንጀል ምርመራው እስከሚጠናቀቅ የሚቆይበት በፖሊስ ወይም በወታደራዊ ፖሊስ ተቋም የሚተዳደር ለሕዝብ በግልፅ የሚታወቅ ቦታ ነው፡፡

፲፪. **"ማረፊያ ቤት"** ማለት ለሕዝብ በግልፅ የሚታወቅ የወንጀል ምርመራ ተጠናቆ ክስ እስኪመሠረት ወይም ክስ ተመሥርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚቆይበት ቦታ ነው፡፡

፲፫. **"ማረሚያ ቤት"** ማለት ለሕዝብ በግልፅ የሚታወቅ ታራሚዎች የተወሰነባቸውን ፍርድ የሚፈፅሙበት፣ የሚታረሙበትና የሚታነፁበት ቦታ ነው፡፡

፲፬. በዚህ አንቀጽ ላይ ትርጉም የተሰጠው ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤት፣ማቆያ ቤት፣ ማረፊያ እና ማረሚያ ቤት የተሰጠው ትርጉም የወታደራዊ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤት፣ማቆያ ቤት፣ማረፊያና ማረሚያ ቤትንም ያካትታል፡፡

፲፭. **"ከባድ ወንጀል"** ማለት በወንጀል ሕግ መሠረት የቅጣት መነሻው አስርዓመት እና ከዛ በላይ የሚያስቀጣ የወንጀል አይነት ነው፡፡

፲፮. **"መካከለኛ ወንጀል"** ማለት በወንጀል ሕግ መሠረት እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ የወንጀል አይነት ነው፡፡

፲፯. **"ቀላል ወንጀል"** ማለት በወንጀል ሕግ መሠረት የቅጣት ጣሪያው አምስት ዓመትና ከዛ በታች የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡

፲፰. **"ምርመራ"** ማለት ተፈጸመ የተባለውን ወንጀል አስመልክቶ በዚህ ሕግ መሠረት መረጃና ማስረጃ የመሰብሰብ እና ተያያዥ ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡

፲፱.**"ምርመራ መምራት"** ማለት የምርመራ ሂደት ሕጋዊነትን ለማረጋገጥ በዐቃቤሕግ የሚከናወን የምርመራ ክትትል ፣ የሕግ ምክር፣ ምርመራ እንዲጀመር እና ሌሎች ትዕዛዞችን የመስጠት ተግባር ነው፡፡

፳. **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት "** ማለት አንድ ምክንያታዊ ሰው አስቀድሞ ሊገምተው እና ሊያስቀረው የማይችል ነገር ነው ፡፡

፳፩. **"ማስረጃ"** ማለት በጭብጥ የተያዘን አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የሚያስችል ማንኛውም ነገር ነው፡፡

፳፪. **"ኤግዚቢት"** ማለት አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል ለፍርድ ቤት እይታ የሚቀርብ ማንኛውም ወንጀሉ የተፈፀመበትን ወይም የወንጀሉ ፍሬ ነገር ሆኖ ድምፅን፣ ምስልን፣ ዳታን የያዘ ዕቃን ወይም የወንጀል ምልክት ሆኖ ፈሳሽን፣ አሻራን፣ ፈለግን እና ሌሎች መሰል ነገሮችን ይጨምራል፡፡

፳፫. **"አግባብነት ያለው ማስረጃ"** ማለት የአንድን ድርጊት ውጤት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመወሰን የሚያስችል፣ ሊረጋገጥ የተፈለገ ፍሬ ነገርን የሚያሳይ ወይም አጠራጣሪ የሚያደርግ ማንኛውም ማስረጃ ሲሆን፤ በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገርን የሚገልጽ ወይም የሚያረጋግጥ ወይም ፍሬ ነገሩ ያመለከተውን ሁኔታ የሚያፈርስ ወይም የሚደግፍ፣ ድርጊቱ የተፈፀመበትን ቦታ ወይም ጊዜ ወይም ድርጊቱን የፈፀሙ ወገኖች ግንኙነትን የሚያሳይ ወይም የሚያረጋግጥ ማስረጃን ይጨምራል፡፡

፳፬.**‹‹በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር››** ማለት ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ ያልተስማሙበት በፍርድ ሂደት እንዲረጋገጥ መደረጉ በጉዳዮ ላይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ፍሬ ነገር ነው፡፡

፳፭ **‹‹አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር ››** ማለት በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ፣ የዚህ ፍሬ ነገር መረጋገጥ በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መከሰቱን ወይም አለመከሰቱን የማሳየት አዝማሚያ ያለው ፍሬ ነገር ነው፡፡

.፳፮ **"ብይን"** ማለት በወንጀል ጉዳይ በዋስትና፣ በክስ መቃወሚያና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሹ መከላከል እንዳለበትና እንደሌለበት የሚሰጥ ውሳኔ ነው፡፡

፳፯. **"ውሳኔ"** ማለት ከብይን፣ ከትእዛዝና ከፍርድ የተለየ ሆኖ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ ሲሆን የቅጣት ውሳኔን ይጨምራል፡፡

፳፰. **"ፍርድ"** ማለት የቀረበን ክስ፣ ክርክር፣ማስረጃ እና ሕግን በመመርመር ተከሳሹ ነፃ ወይም ጥፋተኛ የሚባልበት ነው፡፡

፳፱. **"ትእዛዝ"** ማለት ከውሳኔ የተለየ ሆኖ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማናቸውም ዓይነት የክርክር ማስቀጠያ ወይም ውሳኔ ማስፈፀሚያ ትእዛዝ ነው፡፡

፴.**"ሰው"** ማለት ግለሰብ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

፴፩. በዚህ ሕግ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡

**አንቀጽ ፫ ዓላማ**

የዚህ ሕግ ዓላማ፡-

፩. በወንጀል ምርመራ፣ ክስ፣ ፍርድ ሂደትና የውሳኔ አፈጻጸም በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ የሰብዓዊ መብቶችን ማክበር እና ማስከበር፣

፪. የወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱ እውነትን ማውጣት የሚያስችል፣ ውጤታማ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ ማስቻል፤ እና

፫. በወንጀል ፍትሕ ሥርዐቱ ውስጥ የመንግስትን ኃይል የመጠቀም ብቸኛ ሥልጠን መገደብ፣ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፣

ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## መሠረታዊ መርሆዎች

**አንቀጽ ፬ ጠቅላላ**

፩. የዚህ ሕግ አፈጻጸም በዚህ ክፍል በተመለከቱት መርሆዎች ይመራል፡፡

፪. በዚህ ክፍል የተደነገጉት መሠረታዊ መርሆዎች ከሕገ መንግስቱ፣ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የሰብዓዊ መብት ሕግጋት፣ ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ፣ዓለምአቀፍ መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ይተረጎማሉ፡፡

**አንቀጽ ፭ ነፃ ሆኖ የመገመት መብት**

፩.ማንኛውም ሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት በተሰጠ ፍርድ ጥፋተኝነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ በተጠረጠረበት ወይም በተከሰሰበት ወንጀል ነፃ ሆኖ የመገመት መብት አለው፤ በራሱ ላይም እንዲመሰክር ወይም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም፡፡

፪.ዐቃቤ ሕግ የመሠረተውን ክስ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ ተከሳሽ ራሱን የመከላከል መብት አለው፡፡

**አንቀጽ ፮ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ እና ቅጣት ስለመከልከሉ**

ማንኛውም ሰው በዚህ ሕግ እና በወንጀል ሕግ መሠረት በተቀጣበት፣በነፃ በተለቀቀበት ወይም በአማራጭ መንገድ እና መፍትሄ እልባት ባገኘበት የወንጀል ጉዳይ እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም ፡፡

**አንቀጽ ፯ በሕግ ፊት እኩል መሆን**

የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤በመካከላቸውም ማንኛውም ዐይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ የወንጀል ሕግና ሥነ-ሥርዐቱ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በኃብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ በሕግ ባልተፈቀደ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፰ ስለመያዝና ማሰር**

ማንኛውም ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ ሳይኖር ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

**አንቀጽ ፱ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ**

በወንጀል የተጠረጠረ፣ የተከሰሰ፣የተፈረደበት ወይም በፍርድ ሂደቱ ተሳታፊ በሆነ ሰው ላይ የማሰቃየት ተግባር ፣ጭካኔ የተሞላበት፣ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብሩን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

**አንቀጽ ፲ በጠበቃ መወከል**

**፩.** የተያዘ ፣የተከሰሰ ወይም የተፈረደበት ሰው ከተያዘበት ወይም ከተከሰሰበት ጊዜ ጀምሮ በመረጠው የሕግ ጠበቃ ምክርና ድጋፍ የማግኘት ወይም የመወከል መብት አለው፡፡ በመረጠው የሕግ ጠበቃ ለመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም የገንዘብ አቅም የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ እና በዚህም ምክንያት ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግሥት ወጪ ጠበቃ ይመደብለታል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍርድ ቤቱ ፍትሕ ሊጓደል ይችላል ብሎ ሊወስን የሚችለው፡-

**(ሀ)** የጉዳዩን ውስብስብነት፣

**(ለ)** የወንጀሉን ክብደት፣

**(ሐ)** የተጠርጣሪውን ሁኔታና

**(መ)** ሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎችን

በመመዘን ነው፡፡

**፫.** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

**(ሀ)** በወንጀል ድርጊት ገብቶ የተገኘ ወጣት፣

**(ለ)** የጥፋተኝነት ድርድር፣

**(ሐ)**የቅጣት መነሻው አስር ዓመት እና ከዛ በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰው፣ ወይም

**(መ)** በሕግ ጠበቃ መወከል ግዴታ መሆኑ በግልጽ የተደነገገ፣

እንደሆነ ጉዳዩ ያለጠበቃ አይታይም፡፡

**አንቀጽ ፲፩ ቀልጣፋ ውሳኔ ስለመስጠት**

ማንኛውም የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሂደት በዚህ ሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ይከናወናል፡፡

**አንቀጽ ፲፪ በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት**

**፩.**ማንኛውም ክስ በግልጽ ችሎት ይታያል፤ይሰማል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ **፩** የተደነገገው ቢኖርም በተከሳሹና በተጎጂው የግል ሕይወት፣ በሕዝብ የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱ ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፫ የተከራካሪዎች እኩልነት</u>**

ማንኛውም የፍርድ ሂደት የዐቃቤ ሕግ ወይም የግል ከሳሽን እና የተከሳሽን እኩልነት በሚያረጋግጥ መልኩ ይካሄዳል፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፬ የቋንቋ አጠቃቀም</u>**

፩. የወንጀል ፍርድ ሂደቱ በፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ ይመራል፡፡

፪. በወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው የተጠረጠረበት ወይም የተከሰሰበት ክስና ምክንያቱ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚረዳው ቋንቋ ይነገረዋል፡፡

፫. የፍርድ ሂደቱ በማይረዳው ቋንቋ በሚካሔድበት ወቅት በሚረዳው ቋንቋ ወይም በምልክት ቋንቋ እንዲተረጎምለት በመንግሥት ወጪ አስተርጓሚ ይመደባል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው የክስና የሰነድ ማስረጃ ትርጉምን ያጠቃልላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፭ እውነትን ስለማውጣት</u>**

፩. ማንኛውም የምርመራና የፍርድ ሂደት እውነትን በማውጣት መርህ ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፡፡

፪. እውነትን የማውጣት ሂደት ወንጀል ፈጻሚ ከሕግ ተጠያቂነት እንዳያመልጥ፣ ወንጀል ያልፈጸመ ንጹህ ሰው አላግባብ እንዳይያዝ እና ተጠያቂ እንዳይሆን በሚያደርግ መርህ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

፫. እውነትን የማውጣት ሂደቱ የምስክሩን ወይም የተጠርጣሪውን ክብር የማይነካ፣ ቃሉን በተፅዕኖ ሥር ሆኖ እንዳይሰጥ፣ ተጠርጣሪውን ለተራዘመና ለተደጋገመ ጥያቄ የማይዳርግ መሆን ይኖርበታል፡፡

፬.ተጠርጣሪው ቃል የሚሰጥበት ጊዜ ፣ ቃል በመስጠት ሂደት የሚኖር የእረፍት ሰዓት፣ቃል የሚሰጥበት ቦታ ድባብ እና የመርማሪው ባህሪ እውነትን ለማውጣት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፮ ሕጋዊነት</u>**

፩.ማንኛውም በዚህ ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ተቋም በሕግ የበላይነት መርህ ይመራል፡፡

፪.በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ በሕገ መንግሥቱና በዚህ ሕግ ይመራል፡፡

፫.ማንኛውም የተከሰሰ ሰው ጉዳይ የሚታየው በሕግ በተቋቋመ እና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

፬.የወንጀል ምርመራ፣ የፍርድና የውሳኔ አፈጻጸም ሂደት የሚከናወነው በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፯ የወንጀል ክስ የመንግሥት መሆኑ</u>**

፩. በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ ተበዳዩ በራሱ ወጭ የግል ክስ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የፍትሕ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

### አንቀጽ ፲፰ የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ፍርድ ቤት ፦

፩.የጊዜ ቀጠሮ፣ የብርበራ፣ የመያዣ እና ሌሎች ቅድመ ክስ ተግባራትን በተመለከተ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፪. ፍርድ ቤት የቀረበ ተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ፣ ምስክር የፍርድ ቤቱን የሥራ ቋንቋ የማይረዳው ወይም በምልክት ቋንቋ መግለጽ አስፈላጊ እንደሆነ አስተርጓሚ ይመድባል፡፡

፫. የቀረበ የወንጀል ክስን ይመረምራል፣ ማስረጃ ይቀበላል፣ያከራክራል፣ እንደአግባብነቱ ትእዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ይሰጣል፣ የሰጠውን ውሳኔ ያስፈጽማል ወይም እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

፬. በያዘው ጉዳይ ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መኖሩን ሲረዳ ወይም አቤቱታ ሲቀርብለት ጉዳዩ እንዲጣራና ርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፭.የቀረበን የወንጀል ጉዳይ በነፃነት፣ በገለልተኝነት ፣ አድሎ በሌለበት ፣ በብቃት እና በግልፅ ችሎት ይዳኛል፡፡

፮.በሕመም ምክንያት ችሎት መቅረብ የማይችል ሰው ወይም ለጥቃት የተጋለጠ ምስክር ችሎት ሳይቀርብ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፯.በእርቅ፣ በጥፋተኝነት ድርድር፣ በባህላዊ ሥርዐት እልባት የተሰጠባቸውን ጉዳዮች ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ይመዘግባል፡፡ የተመዘገበው እንደ ፍርድቤት ውሳኔ ሆኖ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፰. በንብረት ላይ የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የታገደ ንብረትን የሚያስተዳድር አካል ይሾማል፣ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፱. በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን በዚህ ሕግ መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

፲. በዚህ ሕግ መሠረት በወንጀል ጉዳይ አለምአቀፍ ትብብር ጉዳዮች ላይ አስፈላውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፲፩. በወንጀል ጉዳዮች ዓይነት ችሎቶችን ያደራጃል፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር በየችሎቶቹ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፡፡

**አንቀጽ ፲፱ የፖሊስ ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት**

የፖሊስ ተቋም የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ ከዐቃቤ ሕግ የሚሰጠው ትእዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ መሠረት:-

፩. ተፈፀመ የተባለ የወንጀል ድርጊትን አስመልክቶ ምርመራ ያደርጋል፣

፪. የዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብን አስመልክቶ ከዐቃቤ ሕግ የሚሰጠውን ትእዛዝ ይፈፅማል፡፡

፫. የመያዣና የብርበራ ትእዛዝ በማውጣት ብርበራ ያካሂዳል፣የተገኘውንም ማስረጃ ይይዛል፤ ተጠርጣሪው ከተጠረጠረበት ወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃም ሲያገኝ ለተከሳሹ ይሰጣል፡፡

፬. መጥሪያ ለተከሳሽና ለምስክር ያደርሳል፣ ተጠርጣሪንና ተከሳሽን ይይዛል፡፡

፭. የወንጀል ክስ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ኤግዚቢትን ያስተዳድራል፡፡

፮. በሌለበት የተቀጣን ሰው ተከታትሎ በመያዝ ውሳኔ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

፯.ተጠርጣሪ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ከሕግ አማካሪው፣ ከሐኪሙ ፣ ከኃይማኖት አባቱ ወይም ከኃይማኖት መሪው የጥብቅና፣ የጤና ወይም መንፈሳዊ  አገልግሎት ለማግኘት እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ፣ከልጆቹ፣ከትዳር አጋሩ ጋር በግል የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፰.በምርመራ ወቅት በማቆያ ቤት የሚቆዩ ተጠርጣሪዎች አያያዝ ሰብዓዊ ክብራቸውን እና መብታቸውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ግዴታውን ለመወጣት በሚያስችለው መልኩ ያደራጃል፡፡

፱. ለወንጀል ምርመራ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የምርመራ ክፍሎችን ያደራጃል፡፡

፲. ሌሎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትእዛዞችን ይፈፅማል፡፡

**አንቀጽ ፳ የዐቃቤ ሕግ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት**

የዐቃቤ ሕግ ተቋም :-

፩. የወንጀል ምርመራን  ይመራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም በራሱ ምርመራ ያከናውናል፡፡

፪. የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር፣ በፖሊስ የተጀመረ የወንጀል ምርመራ ላይ የክትትል ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፣ የወንጀል ምርመራ በሕግ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፣ በምርመራ መዝገብ ላይ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫. በተጣራ የምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ በፍርድ ቤት ክርክር ያደርጋል፣ ክስ ያነሳል፣ ከክስ በፊት በኤግዚቢት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬.የተጠርጣሪ ወይም የተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ከመደበኛው የወንጀል የፍርድ ሂደት ውጭ ባለ አማራጭ መንገድ እንዲታይ የሚያስችል ሥርዐት ያደራጃል፡፡

፭.በተከሳሽ ላይ የሚቀርብ ማስረጃን በዚህ ሕግ መሠረት ለፍርድ ቤት እና ለተከሳሽ እንዲደርስ ያደርጋል፣ በማንኛውም ሁኔታ ያገኘውንና ለተከሳሽ በመከላከያ ማስረጃነት ሊጠቅም የሚችል ማስረጃን ለፍርድ ቤት ወይም ለተከሳሹ ይሰጣል፡፡

፮. በያዘው የምርመራ መዝገብ ውጤታማ ስራ ያላከናወነ መርማሪ ፖሊስ በሌላ መርማሪ ፖሊስ እንዲተካ ያደርጋል፡፡

፯.የፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚያስከትል የወንጀል ድርጊት ሲያጋጥም የወንጀልና የፍትሐብሔር ክሶችን አጣምሮ ያቀርባል፡፡

፰.ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸውን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈጸማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፣ሳይፈጸሙ ከቀሩ ወይም አፈጻጸማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የእርምት ርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

፱. ማቆያ፣ ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤትን ይጎበኛል፣ እንደአስፈላጊነቱም የእርምት ርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፲. ምስክሮች በሕግ መሠረት ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፲፩. የይቅርታ አሰጣጥ አፈጻጸምና ክትትል ሥርዐትን ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

፲፪. የግዴታ ሥራ ወይም የማኅበረሰብ አገልግሎት ቅጣት፣ በገደብ፣ በአመክሮ እና በይቅርታ የተለቀቁ ፍርደኞችን የመከታተያ ሥርዐት ይዘረጋል፤ አስፈላጊውን አደረጃጀት ይፈጥራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ አስፈላጊውን ርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## <u>አንቀጽ ፳፩ የማረሚያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

ማረሚያ ቤት ፡-

፩. በፍርድ ቤት ትእዛዝ በጥበቃ ሥር ያለ ተከሳሽ የወንጀል ምርመራ ወይም ክርክር እስከሚጠናቀቅ ድረስ በማረፊያ ቤት ያቆያል፣ ጥፋተኛ የተባለን ያርማል፣ ታራሚዎች ከሕብረተሰቡ ጋር መልሶ እንዲቀላቀሉ ያደርጋል፡፡

፪.ታራሚ ወይም ተከሳሽ ከሕግ አማካሪው፣ ከሐኪሙ ፣ ከኃይማኖት አባቱ ወይም ከኃይማኖት መሪው የጥብቅና፣ የጤና ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት ለማግኘት እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ፣ከልጆቹ፣ከትዳር አጋሩ ጋር በግል የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፫.በማረፊያ ቤት የሚገኝ ተከሳሽን እና በማረሚያ ቤት ያለ ታራሚን ለፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡

፬. በማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት የሚቆዩ ሰዎች በዕድሜ፣ በጾታ፣ ሕግ በሚፈቅደው አግባብ በወንጀል ዓይነት፣ በቅጣትና በጤና ሁኔታ ተለይተው እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

፭. በማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት የሚቆዩ ሰዎችን አያያዝ ሰብዓዊ መብታቸውንና ክብራቸውን የጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፮. የአመክሮ አሰጣጥ አፈጻጸምና ክትትል ሥርዐትን ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፪ የጥብቅና ተቋም ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የጥብቅና ተቋም ፡-

፩.ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወይም ታራሚው በተጠረጠረበት ፣በተከሰሰበት ወይም በተፈረደበት የወንጀል ጉዳይ የጥብቅና አገልግሎት ይሰጣል፤ የጉዳዩን ሂደትና ያለበትን ደረጃ ለደንበኛው ያሳውቃል፡፡

፪.ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወይም ታራሚው በማቆያ፣ በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት በሚገኝበት ጊዜ ከጥብቅና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ይቀበላል፤ ይሰጣል፡፡

፫. የጥብቅና ተቋሙ በሚመራበት የሥነምግባር ደንብ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፫ የፍትሕ ተቋማት የወል ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩.በሌላ ሕግ የተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የፍትሕ ተቋማት በየሥራ መስካቸው የሚከተሉት የወል ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

**(ሀ)** የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ሚዛናዊነት፣ ቀልጣፋነት፣ ተገማችነትና ግልጽነት በማረጋገጥ ውጤታማ እና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን ያደርጋሉ፣ የሕዝብ ተዓማኒነትና ፍትሐዊነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡

**(ለ)** በወንጀል ጉዳይ ጥናትና ምርምር ያደርጋሉ፤ ዘመናዊ አሠራርንም ይዘረጋሉ፡፡

**(ሐ)** የወንጀል መረጃንና ስታስቲክስን ይሰበስባሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይተነትናሉ፣ ያሰራጫሉ፡፡

**(መ)** ተጠርጣሪዎች የሚያቀርቡትን አቤቱታ በአፋጣኝ ለመመርመር የሚያስችል አፋጣኝ፣ አደሎአዊ ያልሆነ፣ ግልፅና ተደራሽ የተጠያቂነት ሥርዐት ይዘረጋሉ፡፡

**(ሠ)** የተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ፣ ተጎጂ፣ ምስክርና ታራሚ አያያዝ ሥርዐት የሕገ መንግሥቱንና የዚህን ሕግ ድንጋጌዎች የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

**(ረ)** የሥራ ክንውን መመዘኛ ያዘጋጃሉ፣ያስፈጽማሉ፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

**(ሰ)** ለሚጠሯቸው ምስክሮች የውሎ አበልና የወጪ ማካካሻ ይከፍላሉ፡፡

**(ሸ)** ተግባራቸው በሕግ መሠረት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ የኢንስፔክሽን ክፍል ያደራጃሉ፣ ጉድለቶችን በመለየት እንዲታረሙ ያደርጋሉ፡፡

**(ቀ)** ወጥ የሆነ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውጤታማነት መመዘኛ ያዘጋጃሉ፣ ይተገብራሉ፡፡

**(በ)** የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት አስተዳደር የጋራ ጉዳዮችን በመለየት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

**፪.**ለዚህ ምዕራፍ አፈጻጸም **‹‹የፍትሕ ተቋም››** ማለት የፌዴራል ወይም የክልል ፖሊስ፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ የተከላካይ ጠበቃ ተቋም እና ጠበቃን ያካትታል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የዳኝነትና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን

## ክፍል አንድ

## የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

### አንቀጽ ፳፬ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

**፩.**የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ ግዛት ክልል በሚፈጸም ወንጀል ላይ ቀዳሚ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡ በኢትዮጵያ መርከብ ወይም አይሮፕላን ላይ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ የተፈጸመ ወንጀል በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደ ተፈጸመ ይቆጠራል፡፡

**፪.**ወደ ጎረቤት አገሮች በሚደረግ የየብስ ጉዞ በመጓጓዣ ላይ በተፈጸመ ወንጀል፣ በኢትዮጵያ የግዛት ወሰን በተፈጸመና ውጭ አገር ውጤት ባገኘ ወንጀል ወይም ውጭ አገር በተፈጸመና ኢትዮጵያ ውስጥ ውጤት ባገኘ ወንጀል ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ቀዳሚ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፫. ከኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውጭ በወንጀል ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፴፰ እስከ ፪፻፵ እንዲሁም ከአንቀጽ ፫፻፵፫ እስከ ፫፻፸፩ የተደነገገውን በመጣስ በኢትዮጵያ መንግሥት በደህንነቱ ወይም በአንድነቱ ላይ፣ በሕጋዊ ተቋማቱ ወይም በዋና ዋና ጥቅሞቹ ወይም በገንዘቡ ላይ በሚፈጸም ወንጀል፣ በሀገር፣በሕዝብ ሞራልና ደህንነት ላይ በሚፈጸም የኮምፒዩተር ወንጀል ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ቀዳሚ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ ቢኖርም የማይደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ በውጭ ሀገር ሆኖ ስለሚያደርገው ወንጀል በሚከሰስበት ጉዳይ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፲፬)፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አባል ሆኖ በውጭ ሀገር በሚያደርገው ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፲፫) ላይ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፭. ዘር ማጥፋት፣ ፣ በሠው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት ርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን መሠወር፣የጦር ወንጀል፣ የባህር ላይ ዘረፋ እና ሌሎች ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለምአቀፍ ሕጎች በመጣስ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፮.የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፱ እስከ ፫፻፳፪ ድንጋጌን በመጣስ በተፈፀሙ ወንጀሎች ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፯.ማንም ሰው በኢትዮጵያዊ ዜጋ ላይ ወይም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከኢትዮጵያ ውጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፲፫ እስከ አንቀጽ ፲፯ የተደነገጉትን ወንጀሎች ፈጽሞ ሲገኝ ጉዳዩ ወንጀሉ በተፈጸመበት አገር ሕግ መሠረት ዳኝነት ካላገኘ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡ በውጭ ሀገር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የወንጀል ፍርዶችን የማስፈፀም ስልጣን አላቸው፡፡

<u>**አንቀጽ ፳፫ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ድልድል**</u>

**፩.**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**(ሀ)** አፈጻጸማቸው የፌዴራል መንግሥት ወይም በአንድ የክልል መስተዳድር በሚያስተዳድረው የአስተዳደር ክልል ወሰን ያልተገደቡ ወንጀሎች፤

**(ለ)** ዓለም አቀፍ ባሕርይ ያላቸው ወይም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፤

**(ሐ)** ከውጭ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወንጀሎች፤

**(መ)** ወታደራዊ ወንጀሎች፤

**(ሠ)** በፌዴራል መንግሥቱ ተቋማት፣ ንብረት፣ ሰነድ እና ገንዘብ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

**(ረ)** በፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናትና ሠራተኞች ከኃላፊነት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ወንጀል፤

**(ሰ)** በብሔርና ብሔረሰቦች መካከል ከተፈጠረ ግጭቶች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፤

**(ሸ)** ለፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ወይም ቦታዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

**(ቀ)**የጉምሩክና የፌዴራል መንግሥት ግብርና ገንዘብ ነክ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

**(በ)** በፌዴራል ሥርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤

የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**፪.**የክልል ፍርድ ቤቶች፤

**(ሀ)** በአፈጻጸማቸው የክልል መንግሥት ላይ የሆኑ ወይም ከአንድ የአስተዳደር ክልል በላይ ባልሆኑ ወንጀሎች፣

**(ለ)** ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ባልተሰጡ ጉዳዮች ላይ፣

የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**፫.** የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በክልሉ መንግስት ባለስልጣናትና ሠራተኞች ላይ ከኃላፊነታቸውና ከስራቸው ጋር በተገናኘ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ብቻ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**፬**. በልዩ ሕጎች ተለይተው ለፍርድቤት የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ የተመለከተው የዳኝነት ስልጣን የዚህ ሕግ አካል በሆነው ሰንጠረዥ ተደልድሏል፡፡

**፭.**በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ **፬** የተደነገገው ቢኖርም ክልሎች የክልላቸውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የዳኝነት ሥልጣንን በሚያወጡት ሠንጠረዥ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን</u>

### <u>አንቀጽ ፳፮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ- ነገር ሥልጣን</u>

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሠንጠረዡ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደለደሉ ወንጀሎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ - ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

### <u>አንቀጽ ፳፯የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ -ነገር የዳኝነት ሥልጣን</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፡-

**፩.**በሠንጠረዡለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት በተደለደሉ የወንጀል ጉዳዮች፣

፪.ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለምአቀፍ ስምምነቶች የመነጬ ወንጀሎች በመጣስ የተፈፀሙ ፣

፫.ከአንድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ የወንጀል ክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ፤

፬.በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጡ የወንጀል ፍርዶችን ማስፈፀም፣

ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ - ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፯ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን</u>**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፡-

**፩.** የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ እና

**፪.** የክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፣

ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

፩.አንድ ጉዳይ ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ፣ ወይም

፪.በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮችን በሚመለከት ከአንድ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ፣

ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**<u>አንቀጽ፴ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

፩.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፤

፪.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፤

፫.የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውክልና በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፤

፬.የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል የውክልና ዳኝነት ሥልጣን በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና የዳኝነት ሥልጣኑ ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፣

ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**<u>አንቀጽ ፴፩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር የዳኝነት ሥልጣን</u>**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው፡-

፩.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ዐይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸው፣

፪.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸው፤

፫.የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸው፤ እና

፬.የወታደራዊ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው፤

የወንጀል ጉዳዮች በሰበር የማየት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፴፪ የክልል ወረዳ ፍርድቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን**

የክልል ወረዳ ፍርድቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሡንጠረዡበተመለከተውና ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደለደለ የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፴፫ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ -ነገር የዳኝነት ሥልጣን**

የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፡-

፩.በሠንጠረዡበተደለደለ በክልል የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በተፈጸመ የወንጀል ጉዳይ ላይ፤

፪. በሠንጠረዡለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደለደሉ ወንጀሎች ላይ የውክልና፤

፫. ከአንድ የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደሌላ የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ የወንጀል ክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ላይ፤

የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፴፬ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን**

የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ ላይ የይግባኝ ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፴፭ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን**

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

፩. በሠንጠረዡ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደለደሉ ወንጀሎች ላይ የውክልና፣

፪. አንድ የወንጀል ጉዳይ ከአንድ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲዛወር በሚቀርብ አቤቱታ እና

፫. በውክልና ለክልል ፍርድ ቤት በተሰጠ የወንጀል ጉዳይ በሚመለከት ከአንድ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር በሚቀርብ የወንጀል ክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ላይ፣

የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ- ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፴፪ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን**

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

**፩.** የክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣኑ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፤

**፪.** የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ፤

ላይ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፴፫ክሶችን ስለማጣመር**

**፩.** በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት፡-

**(ሀ)** በተለያዩ ተመሳሳይ የሥረ- ነገር የዳኝነት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ክሶች እንዲጣመሩ ጥያቄ ሲቀርብ እና ተጣምረው መታየታቸው የተከሳሹን የመከላከል መብት የማያጠብ ወይም ፍትሀዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ሲረዳ ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የክሶቹን ክብደት በማየት ከሁለቱ በአንደኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተጣምሮ እንዲታይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

**(ለ)** የቀረቡት ክሶች በከፊል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ በከፊል በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ እንደሆነ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ክሶቹን በማጣማር ያያል፡፡

**(ሐ)** ከቀረቡት ክሶች በከፊል በፌዴራል ፍርድ ቤት እና በከፊል በተለያዩ የክልል ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ከሆነ የፌደራሉ ፍርድ ቤት ክሶቹን በማጣመር ያያል፡፡

**(መ)** የቀረቡት ክሶች በአንድ ክልል ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆነው ከባዱን የወንጀል ክስ ለመለየት ያልተቻለ እንደሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአንደኛው ፍርድ ቤት እንዲታይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**(ሠ)** የቀረቡት ክሶች በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የሚወድቁ እንደሆነ ከባዱን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ክሶቹን አጣምሮ ያያል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩(መ)** መሠረት ከባዱን የወንጀል ክስ ለመለየት ያልተቻለ እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከባዱን ጉዳይ ለይቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፴፷ በግልጽ ስላልተደነገገ ወንጀል የሥረ -ነገር የዳኝነት ሥልጣን**

የወንጀል የዳኝነት ስልጣን በግልፅ ባልተደነገገ ጊዜ የቀላል ወንጀልን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ፣ መካከለኛ እና ከባድ ወንጀል ሲሆን የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥረ- ነገር የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ ፴፱ የመሰየም ሥልጣን**

በወንጀል ጉዳይ ላይ ፍርድ የሰጠ ፍርድ ቤት በዚያው ጉዳይ ላይ በሚቀርብ የመሰየም ጥያቄ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን አለው፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን**

**አንቀጽ ፵ መደበኛ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን**

፩. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚገኙበት የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በተፈጸመ በሠንጠረዥበተጠቀሰ የወንጀል ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፪. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በተፈጸሙ የወንጀል ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፫. ከኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ውጭ በተፈጸመ ወይም ውጤት ባገኘ ወንጀል ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

፬. የክልል ፍርድ ቤቶች በክልሉ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በተፈጸመ በሠንጠረዡ በተጠቀሰ የወንጀል ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

**አንቀጽ ፵፩ የወንጀሉ ድርጊትና ውጤት በተለያየ የአስተዳደር ወሰን ሲሆን የሚኖር የዳኝነት ሥልጣን**

ወንጀሉ የተፈጸመው በአንድ የአስተዳደር ወሰን ሆኖ የወንጀሉ ውጤት የተገኘው በሌላ የአስተዳደር ወሰን እንደሆነ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወይም ወንጀሉ ውጤት ባገኘበት የአስተዳደር ወሰን የሚገኘው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፵፪ ተያያዥነት ያላቸውን ወንጀሎች የመዳኘት ሥልጣን**

ተያያዥነት ያላቸው ወንጀሎች በተለያየ የአስተዳደር ወሰን በተፈጸሙ ጊዜ ከሁለቱ አንዱን ለማየት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሁለቱንም ወንጀሎች የማየት የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፵፫ ወንጀል የተሠራበት ቦታ ያልታወቀ ሲሆን ክሱ የሚታይበት ፍርድ ቤት**

ወንጀሉ የተሠራበት ወይም ውጤቱ የተገኘበት የአስተዳደር ወሰን ያልታወቀ እንደሆነ ክሱ የሚታየው የሥረ- ነገር የዳኝነት ሥልጣን ባለው በአንድ የአስተዳደር ወሰን በሚገኝ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፵፬ በጉዞ ላይ የተፈጸመ ወንጀል**

ተጠርጣሪው በጉዞ ላይ ሳለ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተጎጂው ወይም ወንጀል የተፈጸመበት ነገር በጉዞው በሚያልፍበት ወይም በሚደርስበት ሥፍራ ያለ ፍርድ ቤት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**አንቀጽ ፵፭ ተደራራቢ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን**

**፩.** ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ እንደሆነ አስቀድሞ ክስ የተመሠረተበት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀዳሚነት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**፪.** ጉዳዩ በአንድ ክልል ባሉ ከአንድ በላይ በሆኑ የክልል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ እንደሆነ አስቀድሞ ክስ የተመሠረተበት የክልል ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀዳሚነት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**፫.** ጉዳዩ በክልል ወይም በፌዴራል ወይም በተለያዩ ክልሎች ባሉ ተመሳሳይ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን ባላቸው የአስተዳደር ወሰን ዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ እንደሆነ አስቀድሞ ክስ የተመሠረተበት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

**፬.** በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀዳሚነት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው የክልል ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት እያከራከረ ያለውን መዝገብ ይዘጋዋል፡፡

**አንቀጽ ፵፮ ክስን ማዛወር**

**፩.** በዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ጉዳዩ ከአንድ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ካለው ፍርድ ቤት የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ስልጣን ወደሌለው ፍርድ ቤት ማስረጃ ከመሠማቱ በፊት እንዲዛወርለት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** መሠረት ክስ የሚዛወረው :-

**(ሀ)** ክሱ በቀረበበት ፍርድ ቤት ፍትሐዊና ሚዛናዊ ፍርድ ለማግኘት አይቻልም ተብሎ ሲታመን፣

**(ለ)** ክሱ የሚሰማበት ቦታ ለሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ወይም ምስክሮች ምቹ አለመሆኑ ሲታምን፣

**(ሐ)** ጉዳዩ በአጭር ጊዜ ውሳኔ ሊያገኝ የማይችል መሆኑ ሲታመን፣ ወይም፣

**(መ)** በሌላ አሳማኝ ምክንያት በተለመደው ሁኔታ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚያስቸግር መሆኑ ሲታመን፣

ነው፡፡

፫. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሥር ከተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች አንዱ መኖሩን ሲረዳ፡-

**(ሀ)** የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ባይኖረውም የሥረ- ነገር ሥልጣን ባለው ማንኛውም ፍርድ ቤት፣ ወይም

**(ለ)** ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በራሱ እንዲታይ፣

ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

፬. አቤቱታ የቀረበለት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሆነ ጉዳዩን ወደራሱ አዛውሮ ማየት አይችልም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚሰጠው ትእዛዝ የመጨረሻና ይግባኝ የሌለው ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የሌሎች ፍትሕ አካላት ሥልጣን እና ስለመነሳት
## ክፍል አንድ
## የሌሎች ፍትሕ አካላት ሥልጣን

### አንቀጽ ፵፤ የፌዴራል ፍትሕ አካላት ሥልጣን

፩. የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቅ የወንጀል ጉዳይ እና አግባብ ባለው የአስተዳደር ወሰን በሚፈጸም ወንጀል ላይ ምርመራን የመምራትና የመክሰስ ሥልጣን አለው፡፡

፪. የፌዴራል ፖሊስ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ የወንጀል ጉዳይ እና አግባብ ባለው የአስተዳደር ወሰን የሚፈጸም ወንጀል የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡

፫. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ውሳኔን ያስፈፅማሉ፡፡

### አንቀጽ ፵፩ የክልል የፍትሕ አካላት ሥልጣን

፩. የክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተቋም በክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቅ የወንጀል ጉዳይ እና አግባብ ባለው የአስተዳደር ወሰን በሚፈጸም ወንጀል ላይ ምርመራን የመምራትና የመክሰስ ሥልጣን አለው፡፡

፪. የክልል ፖሊስ በክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቅ የወንጀል ጉዳይ እና አግባብ ባለው የአስተዳደር ወሰን የሚፈጸም ወንጀል የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡

፫. የክልል ማረሚያ ቤቶች በፌዴራል ፍርድቤቶች የሚሰጡ ትዕዛዞችን ማስፈፀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ውሳኔን ያስፈፅማሉ፡፡፡፡

**<u>አንቀጽ ፵፱ ውክልና ስለመስጠት</u>**

፩. የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ፣ የፖሊስና የማረሚያ ቤት በዚህ ሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን እንደአግባብነቱ ለክልል የፍትሕ አካላት በውክልና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

፪. በዚህ ክፍል መሠረት የክልል የፍትሕ አካላት ለሚያከናውኑት የፌደራል ተግባር የፌዴራል ፍትሕ አካላት አስፈላጊውን ወጪ ይሸፍናሉ፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ከወንጀል ምርመራ እና ከፍርድ ሂደት ስለመነሳት</u>**

**<u>አንቀጽ ፶ ጠቅላላ</u>**

፩. ማንኛውም ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወይም መርማሪ፡-

**(ሀ)** በተፈጸመው ወንጀል የግል ተበዳይ፣ ተከሳሽ ወይም የግል ተበዳይ ወይም የተከሳሽ የትዳር ጓደኛ እንደሆነ፣

**(ለ)** ከተበዳይ ወይም ከተከሳሽ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፤

**(ሐ)** ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የራሱ ወይም የዘመዱ የግል ጥቅም ካለ፣

**(መ)** በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲል፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በዳኝነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት ወይም በአማካሪነት ሲከራከርበት ወይም ተሳትፎ ሲያደርግበት የነበረ እንደሆነ፤

**(ሠ)** በጉዳዩ ላይ በልዩ አዋቂነት፣ በአስተርጓሚነት ወይም በምስክርነት ቀርቦ አስተያየቱን ወይም ምስክርነቱን የሰጠበት እንደሆነ፣

**(ረ)** ሥራውን እንዲያከናውን በሕግ መሠረት ያልተመደበ እንደሆነ፣

**(ሰ)** በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ **፩(ሀ)** እስከ **(ረ)** ከተዘረዘሩት ውጭ ፍትሐዊ ወይም ገለልተኛ ውሳኔ ከመስጠት የሚያግዱት ሌሎች ምክንያቶች ያሉ እንደሆነ፣

ከፍርድ ወንጀል ፍትህ ሒደቱ ተነስቶ በሌላ ዳኛ፣ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ይተካል፡፡

፪. ማንኛውም ጠበቃ፡-

**(ሀ)** ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በዳኝነት፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በመርማሪነት፣ ፣ በአስታራቂነት፣ በምስክርነት ወይም በልዩ አዋቂነት በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ ሲያደርግ የቆየ ከሆነ፣ ወይም

**(ለ)** በጠበቆች የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት የጥቅም ግጭት ሊያስነሳ የሚችል ከሆነ፣

ከፍርድ ሂደቱ ተነስቶ በሌላ ጠበቃ ይተካል፡፡

**<u>አንቀጽ ፶፩ አስቀድሞ የታየ ጉዳይ</u>**

**፩.** ማንኛውም ዳኛ ክርክር በተነሳበት የወንጀል ጉዳይ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን፣ ወይም ትእዛዝ አሰጣጥ ላይ የተካፈለ እንደሆነ ጉዳዩን በድጋሚ ተሰይሞ ማየት አይችልም፡፡

**፪.** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** ቢኖርም ጉዳዩን በጊዜ ቀጠሮ፣ በይግባኝ ማስፈቀጃ፣ እንደገና በማስከፈት አቤቱታ፣ በፍትሐብሔር ወይም በሥነ-ምግባር ወይም በሌሎች መሰል ጉዳዮች በሚሰጥ ዳኝነት መሳተፍ ጉዳዩን አስቀድሞ እንደማየት አይቆጠርም፡፡

**<u>አንቀጽ ፶፪ አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

**፩.** ማንኛውም ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ መርማሪ፣ ጠበቃ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፶** እና **፶፩** በተደነገገው መሠረት በፍርድ ሂደት መሳተፍን የሚከለክሉ ምክንያቶች መኖሩን እንዳወቀ በራሱ ተነሳሽነት ከሒደቱ መነሳት ይኖርበታል፡፡

**፪.** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሹ በዚሁ ጉዳይ የፅሑፍ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፣

**፫.** ከአቤቱታውም ጋር አግባብነት ያለውን ምክንያትና ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፶፫ አቤቱታው የሚቀርብበት ጊዜ</u>**

አቤቱታ የሚቀርበው አቤቱታውን ለማቅረብ ምክንያት መኖሩ እንደታወቀ ወዲያውኑ መሆን ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፶፬ የአቤቱታ አቀራረብ</u>**

ከፍርድ ወይም ከምርመራ ሂደት የመነሳት ጥያቄ የቀረበው፡-

**፩.** በዳኛ ላይ ከሆነ ጥያቄው ጉዳዩን ለሚመለከተው ችሎት ይቀርባል፤

**፪.** በዐቃቤ ሕግ ወይም በመርማሪው ላይ ከሆነ ጥያቄው ለቅርብ ኃላፊው ይቀርባል፤

**፫.** በጠበቃ ላይ ከሆነ ለችሎት ይቀርባል፡፡

**<u>አንቀጽ ፶፭ ውሳኔ መስጠት</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ **፶፬** መሠረት ከምርመራ ሂደት እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ሰው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታ የቀረበበት ሰው ስለጉዳዩ አስተያየቱን እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላል፡፡

**፪.** ከችሎት የመነሳት አቤቱታ የቀረበው በዳኛ ላይ ከሆነ፡-

**(ሀ)** አቤቱታው የቀረበበት ዳኛ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ አቤቱታው የቀረበው ከአንድ በላይ በሆነ ዳኛ በሚታይ ችሎት ከሆነ አቤቱታው ያልቀረበበት ዳኛ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**(ለ)** አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ ከችሎት አልነሳም ብሎ ከወሰነ ጉዳዩ በሌላ አቻ ዳኛ እንዲታይ ወደሌላ ችሎት ይመራዋል፡፡

**(ሐ)** አቤቱታው የቀረበላቸው ዳኞች በድምጽ የተለዩ እንደሆነ በሹመት ቀደምትነት ያለው ዳኛ ውሳኔ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**(መ)** አቤቱታው የቀረበው አንድ ዳኛ ብቻ ባለበት ችሎት በሚያስችል የወረዳ ዳኛ ላይ ከሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቤቱታ የቀረበበትን ዳኛ መነሳትና አለመነሳት፣ የሚነሳም ከሆነ ጉዳዩን በሥረ- ነገር የዳኝነት ስልጣን የሚያይ ዳኛ ይመድባል፡፡

፫. ከፍርድ ሂደት ይነሳልኝ አቤቱታ ወይም ከችሎት የመነሳት ጥያቄ እንደቀረበ የፍርድ ሂደቱ ከመቀጠሉ በፊት ውሳኔ ያገኛል፣ ለሂደቱ ማስረጃ መስማትና መዝገቡን አስቀርቦ ማየት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ከሦስት ቀን በማይበልጥ ጊዜ መወሰን ይኖርበታል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተደነገገው ቢኖርም በወንጀል ክሱ ላይ ውሳኔ የሰጠው ዳኛ አቤቱታ የቀረበበት ሆኖ አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ ቀድሞ አቤቱታ ያቀረበው ወገን ቅሬታውን በዋናው ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር በማጣመር ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

<u>**ሁለተኛ መጽሐፍ**</u>

<u>**የወንጀል ምርመራ**</u>

<u>**ምዕራፍ አንድ**</u>

<u>**የወንጀል አቤቱታ እና አቤቱታን ማጣራት**</u>

<u>**አንቀጽ ፶፺ ጠቅላላ**</u>

፩. የወንጀል ምርመራ ሥራ በመርማሪ ፖሊስ ይከናወናል፡፡ ምርመራውን የመምራትና የመከታተል ሃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

፪. ፖሊስ ወንጀል ስለመፈጸሙ:-

**(ሀ)** በቅኝት፣ በክትትል፣ በጥናት ወይም በመሳሰሉት መንገዶች ሲረዳ፣

**(ለ)** የወንጀል አቤቱታ ወይም የግል ተበዳይ አቤቱታ ሲቀርብለት፣

(ሐ) ጥቆማ ሲደርሰውና ወንጀል ስለመፈጸሙ በበቂ ሁኔታ ሲጠረጥር፣

(መ) የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈጸም፣ ወይም

(ሠ) የወንጀል ምርመራ እንዲጀምር ከዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ሲደርሰው፣

የወንጀል ምርመራ ይጀምራል፣ መጀመሩን ለዐቃቤ ሕግ ያሳውቃል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተዘረዘሩት መሠረት ለመርማሪ ፖሊስ የደረሰው አቤቱታ፣ መረጃ፣ ጥቆማ ወይም ትእዛዝ የሚያጠራጥር ነው ብሎ ቢያስብም መርማሪው ፖሊስ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተነገረው መሠረት ምርመራ ማከናወን ይኖርበታል፡፡

፬. መርማሪ ፖሊስ የየዕለቱን የምርመራ ተግባር ክንውን በዕለት ምርመራው መዝገብ ውስጥ ያሰፍራል፡፡ የምርመራ መዝገቡ ይዘትም ማንኛውንም የፍርድ ቤት ወይም የዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ይጨምራል፡፡

**አንቀጽ ፶፯ ስለወንጀል አቤቱታ**

፩. የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ያወቀ ወይም መረጃ ያገኘ ማንኛውም ሰው የወንጀል ምርመራ እንዲካሄድ በአቅራቢያው ለሚገኝ የፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም የወንጀል አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በፍሬ ሕጉ የተመለከተው ወንጀል ስለመፈጸሙ የማስታወቅ ግዴታ እንደተጠበቀ ነው፡፡

**አንቀጽ ፶፰ የግል አቤቱታ**

፩. በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል መፈጸሙን ያወቀ የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ አቤቱታዉን በማንኛውም አመቺ መንገድ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም ማቅረብ ይችላል፡፡ ከአንድ በላይ የሆኑ አቤቱታ አቅራቢዎች አቤቱታቸውን በግል ወይም በጋራ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፪. በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል የተፈጸመበት ሰው አቤቱታውን ሳያቀርብ የሞተ እንደሆነ አቤቱታው እንደ ቅደም ተከተሉ በትዳር ጓደኛ፣ በሟች ልጅ እና ወላጆች ሊቀርብ ይችላል፡፡

፫. አካለመጠን ያላደረሰ ወይም በሕግ የተከለከለ የግል ተበዳይ አቤቱታውን በሞግዚቱ ወይም በአሳዳሪው አማካኝነት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፬. አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን ባቀረበ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን በአካል ቀርቦ ካላስረዳ አቤቱታው ይሰረዛል፤በጉዳዩ ላይ ድጋሚ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፡፡

**አንቀጽ ፶፱ የወንጀል አቤቱታን ወይም የግል አቤቱታን መቀበል**

፩. የወንጀል ወይም የግል አቤቱታ ለፖሊስ ወይም ለዐቃቤ ሕግ ተቋም እንደቀረበ ይመዘገባል፡፡ ተቋሙም የቀረበለትን አቤቱታ አልቀበልም ማለት አይችልም፡፡

፪. የወንጀል ወይም የግል አቤቱታው ለፖሊስ ተቋም የቀረበ እንደሆነ መርማሪው ይመዘግባል፤ ይህንኑም ወዲያውኑ ለዐቃቤ ሕግ ያሳውቃል፤ ለዐቃቤ ሕግ ተቋም የቀረበ እንደሆነ ተቋሙ ወዲያውኑ ምርመራ እንዲጀምር ለፖሊስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫. አቤቱታውን የተቀበለ ወይም የተመራለት መርማሪ ፖሊስም ወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቀን፣ ቦታ፣ የተጠርጣሪው ሙሉ ስምና አድራሻ፣ የምስክሮችን ስምና አድራሻ እና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን ወዲያውኑ በመዝገቡ ላይ ማስፈር ይኖርበታል፡፡

፬. ፖሊስም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፬ መሠረት ወዲያውኑ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፷ ስልጣን ለሌለው ተቋም የሚቀርብ አቤቱታ

ስልጣን ለሌለው ተቋም አቤቱታ ከቀረበ አቤቱታውን ለፖሊስ ወይም ለዐቃቤ ሕግ ተቋም ወዲያውኑ ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ ፷፩አቤቱታን ስለማንሳትና ውጤቱ

፩. በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል የተፈጸመበት የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ ያቀረበውን አቤቱታ በማናቸውም ምክንያት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ማንሳት ይችላል፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ሕፃናትን እና ጾታዊ ጥቃት የሚመለከት እንደሆነ ፍርድቤቱ የዐቃቤሕግን አስተያየት ይቀበላል፡፡ በዚህ መልኩ በተነሳ አቤቱታ ላይ እንደገና አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ከነበረበት ለማስቀጠል አይቻልም፡፡

፪. የግል አቤቱታው በዚህ ሕግ መሠረት ከተነሳ መዝገቡ ይዘጋል፤ የተያዘ ዕቃ ወይም ኤግዚቢት ለተጠርጣሪው፣ ለተከሳሹ ወይም ለሕጋዊ ባለመብቱ ይመለሳል፡፡

፫. ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ላይ የቀረበ የግል አቤቱታ ለአንደኛው ወንጀል አድራጊ ቢነሳም በቀሪዎቹ ላይ ይቀጥላል፡፡

## አንቀጽ ፷፪ ማንነቱ ባልታወቀ ሰው የሚቀርብ የወንጀል አቤቱታ

፩. ማንኛውም ወንጀል ስለመፈጸሙ የሚያውቅ ሰው ማንነቱን መግለጽ ሳያስፈልገው በማንኛውም መንገድ ወንጀል ስለመፈፀሙ ለፖሊስ ወይም ለዐቃቤ ሕግ ተቋም ማሳወቅ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ካልታወቀ ጠቋሚ የቀረበ የወንጀል ጥቆማ ወንጀል ስለመሠራቱ በአካባቢው ሁኔታ የተደገፈና የሚታመን መስሎ የተገኘ እንደሆነ ስለምርመራ በተደነገገው መሠረት ፖሊስ የቀረበውን የወንጀል አቤቱታ ጥቆማ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ምርመራ ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፫ መረጃ ስለመስጠት</u>**

የሌሎች ሰዎችን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የወንጀሉን የምርመራ ሥራ የሚያደናቅፍ ካልሆነ በቀር ፖሊስ ጥያቄ ሲቀርብለት ምርመራው ስለደረሰበት ደረጃና ስለተወሰደው ርምጃ አቤቱታ ላቀረበው ሰው መረጃ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፬ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት</u>**

**፩.**መርማሪ ፖሊስ አቤቱታ በቀረበበት ወይም በዚህ ሕግ መሠረት ምርመራ በሚጀምርበት ጉዳይ ላይ በዐቃቤ ሕግ የሕግ ማብራሪያ በመደገፍ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ በማድረግ ድርጊቱ፡-

**(ሀ)** ወንጀል መሆን አለመሆኑን፣

**(ለ)** የእጅ ከፍንጅ የወንጀል ድርጊት፣ የደንብ መተላለፍ ፣ በዕርቅ፣ በባሕላዊ ሥርዐት ወይም በሌሎች መፍትሔ እልባት ሊያገኝ የሚችል መሆኑን፤

**(ሐ)** የወንጀል ምርመራ ማድረግ ሳያስፈልግ ከወዲሁ በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ የሚዘጋ ወይም ምርመራ ሊጣራበት የሚገባ የወንጀል ድርጊት መሆኑን፤

**(መ)** ባህሪው ተለይቶ የማይታወቅ ተጨማሪ ጥናትን የሚጠይቅ ድርጊት መሆኑን፤

ለይቶ ይወስናል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ያደረገው መርማሪ ፖሊስ ውሳኔውን ለዐቃቤ ሕግ ያሳውቃል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፭የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ድርጊት</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ <u>፳፬</u> መሠረት በተደረገ ማጣሪያ ተፈጽሞ የተገኘው የእጅ ከፍንጅ የወንጀል ድርጊት እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**(ሀ)** ማስረጃውን በአግባቡ ይሰበስባል ያደራጃል፡፡

**(ለ)** አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወንጀል ድርጊት በተፈጸመበት ቦታ በመገኘት ማስረጃ እንዳይባክን የጥንቃቄ ርምጃ ይወስዳል፤ ያሰባስባል፡፡

**(ሐ)** ኤግዚቢት ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ያደርጋል፣ በኤግዚቢትነት የማይፈለግ ዕቃ ወዲያውኑ ዕቃው ለተወሰደበት ባለይዞታ ወይም ባለቤት ይመልሳል፡፡

**(መ)** አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ የምርመራ እና የማጣራት ሥራ ያከናውናል፡፡

**(ሠ)** ምርመራው ከተጠናቀቀ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ወዲያውን ያስተላልፋል፡፡

**፪.** አንድ የወንጀል ድርጊት **"የእጅ ከፍንጅ ወንጀል"** ነው የሚባለው ተጠርጣሪው የወንጀል ድርጊቱን በመፈጸም ላይ እያለ፣ ለመፈጸም ሲሞክር ወይም እንደፈጸመ ወዲያው ሳይሸሽ ሲያዝ ወይም ድርጊቱን ፈጽሞ ሲሸሽ ሕዝቡ ወይም ምስክሮቹ የተከታተሉት እንደሆን ወይም ጩኸትና እሪታ የተሰማ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፯ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት ከተደረገ በኋላ ምርመራ መዛግብትን ስለመዝጋት</u>**

በዚህ ሕግ መሠረት በተደረገው ማጣራት ተፈፅሞ የተገኘው ድርጊት ወንጀል ካልሆነ፣ በይርጋ ከታገደ፣ በምህረት ወይም በይቅርታ ከታለፈ፣ ፖሊስ የምርመራ መዝገቡን ለውሳኔ ለዐቃቤ ሕግ ይልካል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፰ ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፬ መሠረት በተደረገው ማጣራት ተፈጽሞ የተገኘው ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ አመላካች ነገር ሲኖር ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ እንዲደረግ ይወስናል፡፡

**፪.** የጉዳዩ ምንነት የማይታወቅ በመሆኑ ተጨማሪ የማጣራት ሥራ ማድረግ ካስፈለገ ዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግ ይወስናል፣ በተገኘው ውጤት መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፫.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተገለፀው ቢኖርም ተፈጸመ የተባለው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ማጣራት ወንጀል ስለመፈፀሙ በበቂ ሁኔታ ሲታመን ፖሊስ የዐቃቤ ሕግን ውሳኔ መጠበቅ ሳያስፈልገው ምርመራ ይጀምራል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>የወንጀል ምርመራ ሥነ-ሥርዐት</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>የምርመራ አጀማመር እና የማስረጃ አሰባሰብ</u>**

**<u>አንቀጽ ፳፱ ጠቅላላ</u>**

**፩.** የወንጀል ምርመራ ሥራ በመርማሪ ፖሊስ ይከናወናል፡፡ ምርመራውን የመምራትና የመከታተል ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

**፪.** የወንጀል አቤቱታ ወይም የግል አቤቱታ የተቀበለ መርማሪ ፖሊስ ወንጀል መፈጸሙን ካመነ በዚህ ሕግ መሠረት ምርመራ ይጀምራል፤ ይህንኑ ወዲያውኑ ለዐቃቤ ሕግ አመች በሆነ ማንኛውም መንገድ ያሳውቃል፡፡

፫. ዐቃቤ ሕግ በማንኛውም የወንጀል ጉዳይ የወንጀል ምርመራ የመምራትና የመከታተል ኃላፊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ ለሚመለከተው መርማሪ ፖሊስ የሕግ ምክርና ድጋፍ የመስጠት፣ አግባብ ያለው ትእዛዝ የመስጠትና የምርመራ ሂደትን ሕጋዊነት የማረጋገጥ፣ እንደአስፈላጊነቱም በጋራ የመመርመር ስልጣን አለው፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም መርማሪ ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ በዐቃቤ ሕግ የሚሰጥ ትእዛዝን ይፈፅማል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፱ የወንጀል ምርመራ</u>**

፩. የወንጀል ምርመራ፡-

**(ሀ)** የምስክርን ቃል መቀበልና መመርመር፤

**(ለ)** ተጠርጣሪን ጨምሮ በሌላ ሰው ላይ ብርበራ በማድረግ፣ በንብረት እና ቦታ ላይ ብርበራ በማካሄድና ዕቃን በመያዝ፤

**(ሐ)** በምልከታና ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝቶ ማስረጃን በማሰባሰብ፣

**(መ)** ከሦስተኛ ወገን ማስረጃ በመጠየቅና በመቀበል፤

**(ሠ)** የልዩ አዋቂ ባለሙያ አስተያየት በመቀበል፤

**(ረ)** ናሙናዎችን በመውሰድ፤

**(ሰ)** በልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ማስረጃን በመሰብሰብ፤

**(ሸ)** ከተጠርጣሪ ቃል በመቀበል፤

ይከናወናል፡፡

፪.የወንጀል ምርመራ ማስረጃን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፴ በምርመራ ወቅት ተመጣጣኝ ኃይል ስለመጠቀም</u>**

፩. መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪን ለመያዝ ፣ለብርበራ እና በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ተመጣጣኝ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፡፡

፪. መርማሪ ፖሊስ የምርመራ ተግባሩን ለማከናዎን የሚጠቀመው ተመጣጣኝ ኃይል የግድ አስፈላጊ ሲሆንና ሌላ አማራጭ መንገድ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

፫. በኃይል አጠቃቀም ወቅት ጥንቃቄ የማድረግ፣የሕጋዊነት፣አድሎ ያለማድረግ መርሆችን ያከበረ እና በማናቸውም መልኩ ሞትን የሚያስከትል መሆን የለበትም፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**የምስክር ቃል መቀበል እና መመርመር**

**አንቀጽ ፸፩ የምስክርን ቃል ስለመቀበል እና ስለመመርመር**

**፩.** መርማሪ ፖሊስ ተፈጸመ ስለተባለው ወንጀል፣ስለተጠርጣሪው ወይም ስለድርጊቱ አፈጻጸም ወይም ተያያዥነት ስላላቸው ሌሎች ጉዳዮች ማንኛውንም መረጃ፣ ሙያዊ ትንተና ወይም ማስረጃ መስጠት የሚችልን ሰው መጥራትና መረጃውን ወይም ሙያዊ አስተያየቱን ሊቀበል ይችላል፡፡

**፪.** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፯የተደነገገው ለመመስከር ያለመገደድ ልዩ መብት እንደተጠበቀ ነው፡፡

**አንቀጽ ፸፪ ለምስክር የሚሰጥ መጥሪያ**

**፩.** መርማሪ ፖሊስ ምስክር ይሆናል ብሎ ያመነበትን ሰው የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ በመጥሪያ ይጠራዋል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ መጥሪያ፡-

**(ሀ)** የምስክሩን ሙሉ ስም፤

**(ለ)** የምስክርነት ቃል የሚሰጥበት ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት እንዲሁም ቦታ፤

**(ሐ)** የምስክርነት ቃል የሚሰጥበት የወንጀል ጉዳይ፤

**(መ)** ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን ፤

የሚይዝ ሆኖ እንደአመቺነቱ በአካል፣ በጽሑፍ፣ በስልክ ወይም በሌላ መንገድ ሊደርስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፸፫ የምስክር ቃል መቀበል**

**፩.** መርማሪ ፖሊስ በምርመራ ክፍል ወይም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የምስክሮችን ቃል ይቀበላል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በሕመም፣ በዕድሜ ወይም በሌላ አስገዳጅ ምክንያት የምስክሩን ቃል በምርመራ ክፍል መቀበል የማይቻል እንደሆነ ምስክሩ በሚገኝበት ወይም አመቺ በሆነ ቦታ የምስክርነት ቃሉን መቀበል ይችላል፡፡

**፫.** መርማሪው ምስክሩ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ፡-

**(ሀ)** የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በወንጀል የሚያስከስሰው ከሆነ ለመመስከር እንደማይገደድ፣ ቃሉን ለመስጠት ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ እንደሆነ እና የሚያውቀውን እንዲናገር፣ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት አስፈላጊውን ጥበቃ እንደሚደረግለት ለምስክሩ መንገር፤

**(ለ)** የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈፀመበት፣ ፆታዊ ጥቃት የተፈፀመበት ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ በተለይም በወንጀል ድርጊት ተጎጂ የሆነ ሰው የምስክርነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚቱ ወይም አሳዳሪው እና የማኅበራዊና የሥነልቦና ምክርና ድጋፍ የሚሰጥ ባለሙያ መገኘቱን ማረጋገጥና ለምስክሩ ማስተዋወቅ፤

ይኖርበታል፡፡

**፬**.የምስክርነት ቃል አቀባበል፡-

**(ሀ)** ከመርማሪ ለሚቀርብ ጥያቄ በቃል ፣ በምልክት ወይም እንደምስክሩ ሁኔታ አመቺ በሆነ መንገድ ምላሽ በመስጠት ይመዘገባል፡፡

**(ለ)** ጥያቄና መልሱን ጥያቄው በቀረበበትና ምስክሩም በመለሰበት አግባብ በመመዝገብ፣ እንደ አስፈላጊነቱም ሂደቱን በምስል ወይም በድምጽ በመቅረጽ ሊከናዎን ይችላል፡፡ የምስክርነት ቃል መስጠት ሲጀመርና ሲጠናቀቅ ስለሂደቱ የምስክሩ ማንነት፣ አድራሻና ቃሉን በፈቃደኝነት ስለመስጠቱ ይመዘግባል፡፡

**(ሐ)** የተመዘገበውን የምስክርነት ቃል ለምስክሩ ተነቦለት በየገጹ እንዲፈረም ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምስክሩ ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይኸው ይመዘገባል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳፬ የተከለከለ ተግባር</u>**

**፩**. መርማሪ ፖሊስ የምስክርነት ቃል በሚቀበልበት ጊዜ ዛቻ፣ ማታለያ፣የተስፋ ቃል ፣ ኃይል ፣ ማስገደድ እና ሌላ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሰል ተግባራትን መፈፀም የለበትም፡፡**፪**.ከአንድ በላይ የሆኑ ምስክሮችን በአንድ ላይ በማድረግ በጋራ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ብርበራና ዕቃ መያዝ

**<u>አንቀጽ ፳፫ በፍርድቤት ትእዛዝ ብርበራ ማድረግ ወይም ማስረጃ መያዝ</u>**

**፩**. ያለፍርድ ቤት የብርበራና የመያዣ ትእዛዝ በሰው አካል ወይም ቦታ ላይ ብርበራ ማድረግ ወይም በብርበራ የተገኘ ዕቃ መያዝ ክልክል ነው፡፡

**፪**. የብርበራ ማዘዣ በማንኛውም ፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የብርበራና የመያዣ ትእዛዝ የሚሰጠው ብርበራውና የዕቃው መያዝ ለምርመራው ሂደት የሚረዳ መሆኑን ሲረዳ ብቻ ነው፡፡

**፫**. ማናቸውም የብርበራ ማዘዣ የሚበረበረውን ቦታና የሚያዘውን ዕቃ ወይም ዳታ በግልጽ ለይቶ ማመልከት ይኖርበታል፡፡ በማዘዣው ውስጥ ከተመለከተው በቀር መርማሪው ሌላ ቦታ መበርበር ወይም ሌላውን ዕቃ መያዝ አይችልም፡፡

፬. በዚህ ሕግ ምርመራን ለሚመለከቱ ድንጋጌዎች አፈጻጸም “ቦታ” ማለት ቤት፣ ተሽከርካሪ፣ አውሮፕላን፣ መርከብ፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ቋት እና ሌላ ማንኛውንም ዕቃ ማስቀመጫ ነገርንና ሥፍራን ያካትታል፡፡

፭.በፍርድ ቤቱ የሚሰጥ የብርበራ ትእዛዝ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ይህንንም ሲወስን የሚያዘውን ንብረት ብዛት፣ የሚበረበረውን ቦታና በብርበራው የሚሳተፉትን ሰዎች ብዛት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

፮. ፍርድቤቱ የተሠጠው የብርበራ ትዕዛዝ በስህተት መሆኑን ሲረዳ ወይም በማንኛውም ወገን አቤቱታ ሲቀርብለት ሊሰርዘው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፷፩ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ብርበራ ማድረግና ዕቃ መያዝ**

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፷፩ የተደነገገው ቢኖርም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ቦታ መበርበር ወይም ዕቃን መያዝ የሚቻለው፦

፩.ተጠርጣሪውን እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ክትትል እየተደረገ አንድ ቦታ ውስጥ ሲገባ ወይም ወንጀል የሠራበትን ነገር ቤት ውስጥ ሲያስቀምጥ፣

፪. መነሻ ቅጣቱ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ የወንጀል አቤቱታ ቀርቦ ለዚሁ ወንጀል ማስረጃ የሚሆን ነገር በአንድ ቦታ የተደበቀ ወይም የተቀመጠ መሆኑ መርማሪው ፖሊስ ተገቢ ጥርጣሬ ሲያድርበት እና የብርበራ ማዘዣ ከፍርድ ቤት እስከሚያወጣ ድረስ የተባለው ዕቃ ካለበት ቦታ ሊጠፋ ይችላል ተብሎ በበቂ ምክንያት የታመነ ሲሆን፤

ነው፡፡

**አንቀጽ ፷፪ የተያዘን ሰው ስለመበርበር**

፩.የተያዘ ሰው የሚበረበረው ተመሳሳይ ፆታ ባለው ሰው ሲሆን፣ ብርበራውም አካላዊ ጤንነቱንና ደህንነቱን በማይጎዳ እና ሰብዓዊ ክብሩን በማይነካ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

፪.መርማሪ ፖሊስ ብርበራውን ለማካሄድ ተጠርጣሪው ፍቃደኛ ካልሆነ ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም ብርበራውን ማከናወን ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፷፫ ስለብርበራና የመያዝ ሂደት አፈጻጸም**

፩. ብርበራው በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚፈጸም እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ የብርበራውን ትእዛዝ ለባለይዞታው ማንበብና ሲጠየቅም ማሳየት ይኖርበታል፡፡

፪. መርማሪው ብርበራ የሚያደርግበት ቦታ ዝግ እንደሆነና ነዋሪው ወይም ባለሙብቱ በአካባቢው ከሌለ ወይም ለመክፈት ፈቃደኛ ካልሆነ እና ብርበራውን ለማድረግ ሌላ አማራጭ ዘዴ ከሌለ ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም ቦታውን በመክፈት መግባት ይችላል፡፡

፫. ብርበራ የሚደረገው ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤት በተለየ ሁኔታ ከዚህ ሰዓት ውጭ ብርበራ እንዲፈጸም ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. መርማሪው የተያዘውን ዕቃ ትክክለኛነት ከሁለት ባላነሱ ምስክሮች ፊርማ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡ የሚቻል እንደሆነም የብርበራው ሂደት በምስልና በድምፅ ተቀርፆ ይቀመጣል፡፡

፭. መርማሪ ፖሊስ የተያዘውን ዕቃ ዝርዝር ባለሙብቱ እንዲፈርምበት እና ደረሰኝ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ባለሙብቱ ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ወይም ከሌለ ይኸው ይመዘገባል፡፡

፮. መርማሪ ፖሊስ ከተያዙት ዕቃዎች ለማስረጃነት የሚያስፈልጉትን ይይዛል፤ ለማስረጃነት የማያስፈልጉትን ለተወሰደበት ሰው አስፈርሞ ይመልሳል፡፡

<u>**አንቀጽ ፸፱ በመንግሥት ወይም ሕጋዊ ሰውነት ባለው ተቋም ላይ የሚደረግ ብርበራ**</u>

መርማሪ ፖሊስ የመንግሥት ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ላይ በሚደረግ ብርበራ የተቋሙ ኃላፊ ወይም ተወካዩ እንዲገኝ ያደርጋል፡፡ ኃላፊው ወይም ተወካዩ ለመገኘት ፍቃደኛ ካልሆነ ወይም ለመገኘት ሳይችል ከቀረ ቢያንስ ሌሎች ሁለት ታዛቢዎች ባሉበት ብርበራውን ያከናውናል፡፡

<u>**አንቀጽ ፹ በተለያዩ ዕቃዎች ላይ የሚፈጸም ብርበራ**</u>

፩.ብርበራውን የሚያከናውነው መርማሪ ፖሊስ በብርበራ የሚፈለገው ዕቃ ወይም የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ በሌላ ዕቃ ወይም መሣሪያ ውስጥ በቀላሉ ሊገኝ በማይችል ሁኔታ የተቀመጠ መሆኑን ሲያረጋግጥ በተመጣጣኝ ኃይል ዕቃውን በመስበር ወይም ከነመያዣ ዕቃውን አሽጎ ሊወስድ ወይም ባለበት ሁኔታ ጥበቃ እንዲደረግለት ሊወስን ይችላል፡፡

፪. የዕቃው መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ወይም ብርበራውን ማጠናቀቅ የቤቱን ወይም የቦታውን ነዋሪ ወይም ባለቤት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚያውክ እንደሆነ በፍርድ ቤት ፍቃድ ዕቃውን ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ ብርበራውን ማከናወን ይችላል፡፡

፫. የሚያዘው ዕቃ ከሌላ ዕቃ ጋር የተጣበቀ ወይም የተቀላቀለ በመሆኑ መለያየቱ በንብረቱ ወይም በሰው ላይ አደጋ የሚያስከትል እንደሆነ በፍርድ ቤት ፍቃድ ዕቃው ባለበት ሁኔታ በጥበቃ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

፬.የኤሌክትሮኒክ ማስረጃን እንደ አመቺነቱ ወደ ሰነድ በመለወጥ፣ ከነመያዣው በመውሰድ ወይም በሌላ መሣሪያ እንዲዛወር በማድረግ መያዝ ይችላል፡፡

፷.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ቢኖርም መርማሪ ፖሊስ በብርበራ እንዲያዝ የተፈለገውን የኮምፒዩተር ዳታ የብርበራ ፈቃድ በወጣበት የኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ሊገኝ በሚችል ሌላ የኮምፒዩተር ሥርዓት ውስጥ የተከማቸ መሆኑን በበቂ ምክንያት ሲያምን ለፍርድ ቤት በማሳወቅ የብርበራ ሥራውን ማከናወን ይችላል።

**አንቀጽ ፹፩ በብርበራ ትዕዛዙ ውስጥ ያልተጠቀሱ ዕቃዎች**

መርማሪ ፖሊስ በዚህ ሕግ መሠረት በተደረገ ብርበራ እንዲያዝ ከተፈለገው ዕቃ ውጭ በግለሰብ እጅ እንዲገባ ያልተፈቀደ ዕቃ ያገኘ እንደሆነ እና በአምስት ዓመት ጽኑ እስራትና ከዚያ በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል መፈጸሙን ካመነ ወይም ዕቃው ለሕዝብ ጤንነት ወይም ደህንነት አደገኛ መሆኑን ከተረዳ መያዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፹፪ የኤግዚቢት አያያዝና አቀማመጥ**

፩. ኤግዚቢት ቁጥርና ምልክት ተደርጎበት ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀ ቦታ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

፪. የተያዘ ዕቃ በሕግ በግለሰብ እንዲያዝ ያልተፈቀደ ሲሆን ለማስረጃ የሚሆን ናሙና ወይም የምስል ማስረጃ በማስቀረት ተወርሶ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

፫. የተያዘ ዕቃ ልዩ ፍቃድ የሚያስፈልገው መሆኑ ሲረጋገጥና ባለቤቱ ልዩ ፍቃድ ሳይኖረው ይዞ የተገኘ እንደሆነ ይቀመጣል፡፡

**አንቀጽ ፹፫ በተያዘ ዕቃ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ**

፩. ዐቃቤ ሕግ በኤግዚቢትነት የተያዘው ዕቃ የሚበላሽ፣ አያያዙ አስቸጋሪ ወይም ከፍተኛ ወጪን የሚያስከትል ከሆነ ናሙና በመውሰድ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ተለዋጭ ማስረጃ እንዲኖር በማድረግ ዕቃውን መሸጥና ገንዘቡ በመንግሥት ሂሳብ ተቀማጭ እንዲደረግ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፪. በኤግዚቢትነት የተያዘው የቤት እንስሳ እንደሆነ ምስሉን በፎቶግራፍ ወይም በቪዲዮ በመቅረጽ እንደነገሩ ሁኔታ ለባለቤቱ ወዲያውኑ ይመለሳል ወይም በጨረታ ተሸጦ ገንዘቡ በመንግሥት ሂሳብ ይቀመጣል፡፡

፫. በኤግዚቢትነት የተያዘ ዕቃ ክሱን ለማስረዳት በማስረጃነት የማያገለግል ወይም የማያስፈልግ፣ በሕግ መሠረት ሊወረስ የማይችል ወይም በወንጀል ፍሬነት የተያዘ ሆኖ ለባለቤቱ ሊመለስ የሚችል መሆኑን ዐቃቤ ሕግ ሲረዳ ወዲያውኑ ዕቃው ለተወሰደበት ሰው እንዲመለስ ትእዛዝ ይሰጣል፣ እቃው የሚወረስ ወይም ልዩ ፍቃድ የሚያስፈልገው ከሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፪ መሠረት ይፈጸማል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የኤግዚቢቱን ባለቤት ወይም ባለይዞታ ማን እንደሆነ ማወቅ የማይቻል እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በፍትሐብሔር መፍትሔ እንዲያገኝ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ባለቤቱ ወይም ባለይዞታው ተለይቶ እንዲወሰን ክስ ያቀርባል::

፭. በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ወንጀል ለመፈጸም ያገለገለ ተሽከርካሪ ወይም ሌላ እቃ በፎቶግራፍና በምስል በመቅረጽ ንብረቱ በሕግ መሠረት ሊወረስ የማይችል እንደሆነ ለባለቤቱ በበቂ ዋስትና እንዲለቀቅ ዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፮. ክስ ከተመሰረተ በኋላ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፬ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ፍርድ ቤቱ በተመሳሳይ ሊወስን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፹፬ ተጠርጣሪ ባልሆነ ሰው እጅ የሚገኝ ማስረጃ</u>**

፩. መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪ ባልሆነ ሰው እጅ የሚገኝ ማስረጃን ባለይዞታው እንዲያስረክብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪. መርማሪ ፖሊስ ባለይዞታው ማስረጃውን ሲያስረክብ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡ ማስረጃውም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተይዞ እንዲቆይ ወይም በቅጂ፣ በቪዲዮ፣ በፎቶግራፍ ወይም መሰል ተለዋጭ ዘዴዎች በመጠቀም ተለዋጭ ማስረጃ እንዲቆይ በማድረግና ለዐቃቤ ሕግ በማሳወቅ ለባለይዞታው እንዲመለስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫. ባለይዞታው ማስረጃውን ለማስረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ መርማሪ ፖሊስ ማስረጃው እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

፬. ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት የተጠየቀን ዕቃ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለመርማሪ ፖሊስ እንዲያስረክብ ያዛል፤ በዕቃው አያያዝና አመላለስ ላይም ይወስናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፹፭ በመንግሥት ወይም በሌላ ተቋም የሚገኝ ማስረጃ</u>**

፩.ማስረጃ በማናቸውም የመንግሥትም ሆነ ሌላ ተቋም የሚገኝ ወይም የሚመነጭ መሆኑን መርማሪ ፖሊስ ሲያረጋግጥ ተቋሙ ማስረጃውን እንዲያስረክብ በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪. በሕግ ካልተከለከለ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተጠየቀ ተቋም ማስረጃውን ለመርማሪ ፖሊስ ይሰጣል፡፡

፫. ተቋሙ ማስረጃውን ለማስረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ መርማሪ ፖሊስ ማስረጃው እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፹፮ በፋይናንስ ተቋም የሚገኝ ማስረጃ</u>**

፩. በማስረጃነት የሚፈለግ የባንክ ሂሳብ ወይም የገንዘብ እንቅስቃሴን የሚመለከት መግለጫ ለመርማሪ ፖሊስ እንዲሰጥ በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** መሠረት የሚሰጥ ትእዛዝ፡-

**(ሀ)** የተጠርጣሪን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

**(ለ)** ተጠርጣሪው ፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት፣

**(ሐ)** ከፋይናንስ ተቋሙ የሚፈለግ ማስረጃ ፣

**(መ)** ትእዛዙን የሚፈጽመው ወይም የሚያስፈጽመው መርማሪ ስም፣

መያዝ ይኖርበታል፡፡

**ክፍል አራት**

**ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ የሚደረግ ምርመራ እና ማስረጃ ማሰባሰብ**

**አንቀጽ ፹፯ ዓላማ**

ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ የሚደረግ ማስረጃ የማሰባሰብ ሂደት ዓላማ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ በመገኘት የፎረንሲክ፣ ቴክኒካዊና አካላዊ ማስረጃ እንዳይባክን እና እንዳይበከል በማድረግ ማስረጃ ሳይጠፋና ሳይበላሽ ለማሰባሰብ ነው፡፡

**አንቀጽ ፹፰ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ መገኘት**

**፩.** መርማሪ ፖሊስ ምርመራ ለማካሄድ ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ መገኘትና ማስረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በስፍራው በአፋጣኝ መድረስ ይኖርበታል፡፡

**፪.** መርማሪው ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ እንደደረሰ፡-

**(ሀ)** በቦታው የወንጀል ተጎጂ ወይም የሞተ ሰው መኖሩን ያረጋግጣል፤ የወንጀል ተጎጂ ካለ እንደአስፈላጊነቱ ተገቢው የሕክምና ርዳታ እንዲያገኝ፣ የሞተ ሰው ካለ ምርመራ እንዲደረግ ወደ ሕክምና ተቋም እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

**(ለ)** ማስረጃ እንዳይጠፋ ሥፍራውን ይከልላል፣ ጥበቃ ያደርጋል፣

**(ሐ)** ማስረጃዎችን ይለያል፣ ይሰበስባል፣ ይመዘግባል፣ ይጠብቃል፣

**(መ)** ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያገኙ ማድረግ እና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፫.** ዐቃቤ ሕግ ወንጀል ወደ ተፈፀመበት ቦታ መሄድ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ወይም በመርማሪ ፖሊስ ሲጠየቅ ወንጀል ወደተፈፀመበት ቦታ ሊሄድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፹፱ ወንጀል በተፈፀመበት ቦታ ስለሚደረግ ምርመራ**

፩. የወንጀል ሥፍራ ምርመራ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወይም ማስረጃ በተገኘበት ቦታ የወንጀል ፈለግን በመከተል፣ የሞተ ሰው አስከሬን ማውጣትን፣ አስፈላጊ የሆነ መረጃ አለበት ተብሎ የሚገመት ቦታን፣ ዕቃን እና ሌላ ሰነድን በመፈተሽ ይከናወናል፡፡

፪. ወንጀል የተፈጸመበት ሥፍራ ምርመራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ተከልሎ እንዲቆይ ይደረጋል፤ ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ቦታውን ከልሎ ማቆየት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነ ከሰባት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ቦታው እንዲከለል ሊደረግ ይችላል፡፡

፫. ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የተሰበሰበ ማስረጃ በየዓይነቱ እንዲመዘገብ፣ ለየብቻ ተጠብቆ እንዲቆይ፣ ለእያንዳንዱ ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ እንዲዘጋጅለት እና ታሽጎ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ሂደቱ እንዳስፈላጊነቱ በቪዲዬ እንዲቀረፅ ሊደረግ ይችላል፡፡

፬. ወንጀል በተፈፀመበት ቦታ የሚገኝ ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክ ዳታ የያዘ ግለሰብ ወይም ተቋም ዳታው ለአንድ ወር ተጠብቆ እንዲቆይ መርማሪ ፖሊስ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፺ አስከሬን መመርመር**

፩. መርማሪ ፖሊስ በተፈጸመ ወንጀል የሞተ ሰው ሲኖር ወይም አስከሬኑ የተደበቀ፣ የተቀበረ ወይም በሌላ ሁኔታ የተበላሸ መሆኑን ሲረዳ አካሉ በተገቢው ባለሙያ በጥንቃቄ እንዲነሳ ወይም እንዲወጣ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፪. መርማሪም በአስከሬን ላይ የሚገኝ የአሻራ ምልክትን ወይም ለፎረንሲክና ቴክኒካዊ ምርመራ የሚረዱ ሌሎች ናሙናዎችን መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ፤ አስፈላጊው ሙያዊ ትንተናም ወዲያውኑ እንዲካሄድ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፫. የአስከሬኑ ማንነት ያልታወቀ እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ አግባብ ላለው አካል በማሳወቅ የቀብር ሥነ ሥርዐቱ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ ፺፩ የቤተ ሙከራ ምርመራ ቴክኒክን መጠቀም**

**፩.** በተሰበሰበ ማስረጃና በተካሄደ ትንተና ላይ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን መርማሪ ፖሊስ እና ሌላ በምርመራ ሂደት የተሳተፈ ባለሙያ ምርመራውን በቤተ ሙከራ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

**፪.** በቤተ ሙከራ የሚካሄድ ምርመራ፡-

**(ሀ)** የወንጀሉ አፈጻጸም እና ከባቢያዊ ሁኔታን ለመለየት፣

**(ለ)** ወንጀሉ የተፈጸመበት ዕቃ ወይም ማንኛውንም ሌላ ነገር በአግባቡ ለመለየት፣

**(ሐ)** በወንጀል ሥፍራ የተገኙ ማስረጃዎች ከወንጀሉ አፈጻጸም ጋር ያላቸውን ግንኙነት በአግባቡ ለመተንተን፣

**(መ)** በወንጀል ሥፍራው ከተሰበሰቡ የቃል ምስክርነቶች አንፃር የተፈጸመውን ወንጀል እንደገና በሚያመላክት ሁኔታ ለመሥራት ወይም ለማነፃፀር፣

**(ሠ)** ስለወንጀሉ አፈጻጸም በተለያዩ ምስክሮች የተሰጡ የምስክርነት ቃሎችን ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማነፃፀር፣

ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፺፪ በምርመራና በድጋሚ ምልከታ መሳተፍ</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፫ መሠረት ምስክርነቱን የሰጠ ሰው፡-

**(ሀ)** ለምርመራ ሥራው የግድ አስፈላጊ እንደሆነ በቤተ ሙከራ በሚካሄድ ምርመራ እንዲሳተፍና በድጋሚ ቃሉን እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላል፡፡

**(ለ)** ምርመራው የሚካሄደው በወንጀል ሥፍራው ከተሰበሰበ የቃል ምስክርነት አንፃር የተፈጸመውን ወንጀል አካሄድ በድጋሚ ምልከታ ለመሥራት ወይም ለማነፃፀር እንደሆነ የምስክሩ ቃል ከተረጋገጠው ማስረጃ አንፃር ታይቶ መረጋገጥ ይኖርበታል፤ ምስክሩም ያየውን ወይም የተሳተፈበትን ሁኔታ በዝርዝር ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

**፪.** በምርመራው ሂደት የማስረጃውን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በወንጀል ሥፍራ በመገኘት ሁኔታውን እንደገና ማስረዳት አስፈላጊ እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ ስለሚከናወነው እና በድጋሜ ምልከታ ስለሚፈጸመው ተግባር በዝርዝር ለምስክሮች ይገልፃል፤ እንደአስፈላጊነቱ ዐቃቤ ሕግ በአካል በመገኘት ሂደቱን እንዲከታተልና በቪዲዮ እንዲቀረጽ ሊደረግ ይችላል፡፡

፫. ምስክሩ ወይም በምርመራው የተሳተፈ ባለሙያ ሂደቱን በምርመራ  በተመለከተው መሠረት ማሳየት ወይም በቃል የገለጸውን ማረጋገጥ ወይም ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተደነገገው መሠረት ምስክሮች ወይም በምርመራ የተሳተፉ ባለሙያዎች ሂደቱን በጋራ ማሳየት የለባቸውም፡፡ እያንዳንዱ ሰው የየራሱን በተናጠል ያሳያል፣ አስፈላጊውን ማብራሪያ ያለሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ወይም ጠያቂነት መስጠት ይኖርበታል፡፡

፭. በምርመራ ሂደት የተሳተፈ ሌላ አካል ስለወንጀሉ አፈጻጸም ሂደት ምልከታው በድጋሚ እንዲካሄድ መጠየቅ፣ ማስረጃ በማሰባሰብ ሂደት ምን እንደሠራ እንዲገልጽ ወይም እንዲያሳይ እና መሰል ጥያቄዎችን ለምስክሩ ወይም በምርመራ ሂደት ለተሳተፈ ሰው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፶፫ የባለሙያ ሪፖርትና ምስክርነት**

፩. በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት ሳይንሳዊ፣ ቴክኒካዊ ወይም ልዩ የሙያ አስተያየት የሚሰጥ ልዩ አዋቂ ወይም የቤተ-ሙከራ ምርመራ ያከናወነ ባለሙያ የሙያ አስተያየቱን ወይም የምርመራውን ውጤት ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሚዘጋጀው ሪፖርትም ባለሙያው የሙያ አስተያየቱን ለመስጠት ወይም ለምርመራው የተጠቀሙበትን ግብዓት፣ የተከተለውን የምርመራ ዘዴ፣ ዘዴው ለምን እንደተመረጠ፣ የምርመራውን ውጤትና ሌላ አማራጭ ማጠቃለያ መኖርና አለመኖሩን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፫. በቴክኒክ ወይም በቤተ-ሙከራ ምርመራው የተሳተፈና የምርመራውን ውጤት ያዘጋጀው ባለሙያ የሙያ አስተያየቱን በተመለከተ በፍርድ ቤት ቀርቦ ይመሰክራል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴዎች

**አንቀጽ ፶፬ ዓላማ**

የልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴ ዓላማ በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰብ ባልተቻለባቸው የወንጀል ዓይነቶች ምርመራውን መርዳት ነው፡፡

**አንቀጽ ፶፭ የልዩ የምርመራ ዘዴዎች ተፈፃሚነት**

ልዩ የምርመራ ዘዴ ተፈፃሚ የሚሆነው የተደራጁ ወንጀሎች፣ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች ፣ የሽብር ወንጀል፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትና ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል፣የሙስና ወንጀል፣ሕገ-ወጥ የሰዎች

ዝውውር ወንጀል፣ የኮምፒውተር ወንጀሎች እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ላይ ነው፡፡

**አንቀጽ ፺፯ የፍርድ ቤት ሥልጣን**

በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃን ማሰባሰብ የሚቻለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ወይም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፬ ላይ የተገለፀውን ዓላማ ያሳካል ብሎ ሲያምን እና ሲፈቅድ ነው፡፡

**አንቀጽ ፺፸ ልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ**

ልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ በሚከተሉት መንገዶች ማሰባሰብ ይቻላል፡፡

**፩.** ተጠርጣሪው በግል ፖስታ የሚላላካቸውን ደብዳቤዎች፣ በስልክ እና ሌሎች በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች በመጥለፍ እና ክትትል በማድረግ፣

**፪.** ድምጽና ምስል ለመቅረጽ የሚያስችል መሣሪያ በአንድ በግል ይዞታ በሚገኝ ቦታ በማስቀመጥና ይህንኑ መልሶ በመውሰድ ወይም የግንኙነት ዱካን በመከተል፣

**፫.** ሠርጎ በመግባትና አብሮ በመሆን የተጠርጣሪውን እንቅስቃሴ መከታተል፣ በምስልና ድምፅ በመቅረጽ፤ ወይም

**፬.** ሰነዶችንና የተለያዩ የይምሰል ግንኙነቶችን መፍጠር ፣

**፭.** ሕገወጥ ዕቃን ወይም ተጠርጣሪን ወደ አንድ የተከለከለ ቦታ ወይም ድንበር መግባትን እና መውጣትን መከታተል፣በምስልና ድምፅ በመቅረጽ፣

ነው፡፡

**አንቀጽ ፺፹ መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

**፩.** መርማሪ ፖሊስ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሲፈቅድ በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበሰብ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት፤

**(ሀ)** የወንጀል ድርጊቱ በረቀቀ ሁኔታ በመፈጸሙ በመደበኛው የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ማስረጃ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን፤ እና

**(ለ)** ተጠርጣሪውን፣ ማስረጃውን እና የወንጀል ፍሬውን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን፣

በበቂ ምክንያት ያመነ እንደሆነ ማስረጃው በዚህ ሕግ በተደነገጉት ልዩ የምርመራ ዘዴዎች እንዲሰበሰብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ፤

**(ሀ)** የሚታወቅ ከሆነ የተጠርጣሪውን ስምና አድራሻ፣

**(ለ)** እንደነገሩ ሁኔታ ትእዛዙ የሚፈጸምበት ቦታ ወይም አድራሻ፣

**(ሐ)** ትእዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበት የጊዜ ገደብ፣

**(መ)** በልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴ የሚሰበሰበውን ማስረጃ፣ እና

**(ሠ)** ሌላ አግባብነት ያለውን ዝርዝር መረጃ መያዝ፤

ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፺፱ የጊዜ ገደብ</u>**

፩. በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበሰብ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ትእዛዝ ከሦስት ወር ሊበልጥ አይችልም፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መርማሪ ፖሊስ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥ ሲያመለክት ፍርድ ቤት አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ሲረዳ በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ማስረጃ የማሰባሰብ ጊዜ ሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለልዩ ማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የሚፈቀድ የጊዜ ገደብ ከአስራሁለት ወራት ሊበልጥ አይችልም፡፡**

**<u>አንቀጽ ፻ ለፍርድ ቤት ሪፖርት ስለማቅረብ</u>**

፩.መርማሪ ፖሊስ በልዩ ማስረጃ የማሰባሰቢያ ዘዴ የተሰበሰበው ማስረጃ ሪፖርት በትእዛዙ ላይ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ትእዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የተፈቀደው ልዩ የወንጀል ምርመራ ጊዜ እንዳበቃ መርማሪ ፖሊስ የመጨረሻ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፪. መርማሪ ፖሊስ ለፍርድ ቤቱ በሚያቀርበው ሪፖርት የተሰበሰበውን ማስረጃ ዝርዝር፣ ለምርመራው አግባብነት ያለውንና የሌለውን በመለየት ይገልጻል፡፡

፫.ፍርድቤት የቀረበው የማስረጃ ሪፖርት ልዩ ምርመራው በተፈቀደው መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ከተሰጠው ትእዛዝ ውጭ የተከናወነ ተግባር ባጋጠመ ጊዜ በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰቡ እንዲቋረጥ ወይም ሌላ ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፬. ፖሊስ በልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴ የተሰበሰበው ማስረጃ ለምርመራው አግባብነት ከሌለው ከዐቃቤ ሕግ ጋር በመሆን እንዲወገድ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ ፻፩ ማስረጃ ተቀባይነት የማያገኝበት ሁኔታ**

ከዚህ በላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ከተፈቀደው ውጭ ልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴን በመጠቀም የሚሰበሰብ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡

## ክፍል ስድስት

## የተጠርጣሪ አያያዝ፣ቃል አቀባበል እና አቆያየት

**አንቀጽ ፻፪ ተጠርጣሪን ስለመያዝ**

፩.የተጠርጣሪው መቅረብ ለምርመራው ሂደት አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ተጠርጣሪው ሳይያዝ ምርመራው ይከናወናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ወንጀሉ ከባድ ሆኖ ስለወንጀሉ መፈጸም መርማሪው በቂ ማስረጃ ካለው ወይም ወንጀሉ ለመሠራቱ በአካባቢው ሁኔታ የተደገፈና የሚታመን መስሎ የተገኘ እንደሆነ ተጠርጣሪው በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት ተይዞ ምርመራው ሊካሄድ ይችላል፡፡ የአያያዝ ሂደቱም የተጠርጣሪውን ሰብዓዊ ሙብትና ክብር የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

፫. ተጠርጣሪው ያለመያዝ ወይም ያለመከሰስ ልዩ መብት ተጠቃሚ ከሆነ ከባድ ወንጀል ሲፈፅም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ ወይም ያለመከሰስ መብቱ ስልጣን ባለው አካል ካልተነሳ በስተቀር አይያዝም፡፡

፬. በዓለም አቀፍ ሕግ የማይደፈሩ መብቶች ያላቸው ሰዎችን በተመለከተ ሊያዙ የሚችሉት በዓለምአቀፍ ሕግ በተደነገገው አግባብ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፫ ተጠርጣሪን ስለመጥራት**

፩. መርማሪ ፖሊስ ወንጀል ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ተጠርጣሪው በምርመራ ቦታ እንዲቀርብ አመቺ በሆነ ማንኛውም መንገድ ሊጠራው ይችላል፡፡

፪. የመጥሪያው ይዘት እንደ አግባብነቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፪ የተዘረዘረው ይዘት ይኖረዋል፡፡

፫. መጥሪያ የደረሰው ተጠርጣሪ ለምርመራ ካልቀረበ መርማሪው የፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ በማውጣት ሊይዘው ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፬ የፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ**

፩. በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ሊያዝ ወይም በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት ሊቆይ የሚችለው በፍርድ ቤት ትእዛዝ ብቻ ነው ፡፡

፪. የመያዣ ትእዛዝ የሚሰጠው ተጠርጣሪው በሌላ መንገድ መቅረብ የማይችል እንደሆነ እና መቅረቡም ለምርመራው አስፈላጊ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

፫. መርማሪ ፖሊስ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ምርመራው በሚካሄድበት አቅራቢያ ያለ ፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ሆኖም አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ጥያቄው ለማንኛውም ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡ የመያዣ ትእዛዙም በማንኛውም ጊዜ የሚቀርብ ሆኖ ጥያቄው አንደቀረበ ወዲያውኑ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

፬.በፍርድ ቤት የሚሰጥ የመያዣ ትእዛዝ የተጠርጣሪውን ስም እና የታወቀ አድራሻ፣ የተጠረጠረበትን ወንጀል፣ መያዣውን የሰጠው ፍርድ ቤት፣ ማዘዣው የተሰጠበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምኅረት፣ መያዣው የሚጸናበት ጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

፭. በማንኛውም ፍርድ ቤት የተሰጠ የመያዣ ትእዛዝ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ያለምንም ተጨማሪ ሥነ-ሥርዐት ተፈፃሚነት አለው፤ ትእዛዙን ማንኛውም ተቋም የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

፮. ፍርድቤቱ የተሠጠው የመያዣ ትእዛዝ በስህተት መሆኑን ሲረዳ ወይም በማንኛውም ወገን አቤቱታ ሲቀርብለት ሊሰርዘው ይችላል፡፡**አንቀጽ ፻፭ አስቸኳይ ሁኔታ**

፩. መርማሪ ፖሊስ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመያዣ ትእዛዝ እስኪያወጣ ድረስ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በስልክ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ የመያዣ ትእዛዝ እንዲሰጠው በአቅራቢያው ለሚገኝ ፍርድ ቤት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪. መርማሪው ያቀረበውን የመያዣ ትእዛዝ ጥያቄ በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ በጽሑፍ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ጥያቄውን በጽሑፍ ካላቀረበ ወይም ፍርድ ቤቱ ካላጸደቀው የመያዣ ትእዛዝ ጥያቄው እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፤ የተያዘውም ሰው ከእስር ይፈታል፤ የተያዘ ዋስትና ካለ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፸፯ በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ተጠርጣሪን መያዝ</u>**

፩.ማንኛውም ሰው ወይም ፖሊስ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈፅም የተገኘን ተጠርጣሪ ያለ ፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ መያዝ ይችላል፡፡

፪. በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል እጅ ከፍንጅ ሲፈጽም የተገኘ ተጠርጣሪ ሊያዝ የሚችለው በግል ተበዳይ አቤቱታ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

፫.ተጠርጣሪን የያዘ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ አቅራቢያው ላለው ፖሊስ ተቋም ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፸፪ የመተባበር ግዴታ</u>**

፩. በፍርድ ቤት ወይም ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰው ሲያዝ ትብብር እንዲያደርግ በፖሊስ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው በራሱ ወይም በንብረቱ ላይ አደጋ የማያደርስ እንደሆነ መተባበር ይኖርበታል፡፡

፪.ተጠርጣሪን የያዘ ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ ምስክር ሆኖ የሚቀርብ ከሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷፫ በተደነገገው መሠረት ቃሉን መስጠት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፸፫ ተጠርጣሪ ሲያዝ ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት</u>**

፩. መርማሪ ፖሊስ የሚይዘውን ሰው ማንነት አስቀድሞ ማረጋገጥና በሚይዝበትም ጊዜ ማንነቱን ለሚያዘው ሰው መግለፅ ይኖርበታል፡፡

፪.ፖሊስ ለሚያዘው ሰው ያለመናገር መብት እንዳለው፣ በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል፣ጠበቃ ማቆም መብት እንዳለውና ጠበቃ ለማቆም አቅም የሌለው እንደሆነ መንግስት ጠበቃ እንደሚያቆምለት መንገር ይኖርበታል፡፡

፫. ተጠርጣሪው የሚያዘው በፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ከሆነ መርማሪ ፖሊስ ይህንኑ ለሚይዘው ሰው ማንበብና ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ትእዛዙ የተሰጠው በቃል እንደሆነ ይህንኑ ለተጠርጣሪው መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፬.ተጠርጣሪው በቃል ወይም እጁን በመስጠት እንዲያዝ ያልተስማማ እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ ሰውነቱን በመንካት ወይም በመጨበጥ መያዝ ይችላል፡፡

፫.ተጠርጣሪ ላለመያዝ በኃይል የተከላከለ ወይም ለማምለጥ የሞከረ እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ ሁኔታው የሚፈቅደውን ተጠርጣሪውን ለመያዝ የሚያስችል ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም ለመያዝ ይችላል፡፡

፮.ተጠርጣሪው የሚሰጠውን አድራሻ በመጠቀም መርማሪ ፖሊስ የተያዘው ሰው ቤተሰብ ወይም የቅርብ ዘመድ፣ የአገሩ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ተጠርጣሪው መታሰሩን እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፱ የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍና ናሙና መውሰድ</u>**

፩. መርማሪ ፖሊስ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍ፣ የእጅ ጽሑፍ፣ የፀጉር፣ የድምፅ፣ የሽንት፣ የደም፣ የምራቅ እና ሌላ በሰውነቱ የሚገኝ ፈሳሽ ናሙና እንዲሰጥ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፪. መርማሪው ፖሊስ ወይም ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል ተመልክቶ ተጠርጣሪው በሐኪም መመርመር የሚያስፈልገው መሆኑን ከተረዳ ፍቃድ ያለው ሐኪም ምርመራውን እንዲያደርግና የምርመራውንም ውጤት በጽሑፍ እንዲያስታውቅ ለማዘዝ ይችላል፡፡

፫. መርማሪ ፖሊስ በተጎጂው ወይም ተጎጂው በሕግ ችሎታ የሌለው እንደሆነ በሞግዚቱ ወይም በአሳዳሪው ፍቃድ በባለሙያ እንዲመረመር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ ሐኪሙም የምርመራውን ውጤት በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ፎቶግራፍ እና አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፲ የተጠርጣሪነት ቃል</u>**

፩. በወንጀል ተጠርጥሮ ለምርመራ እንዲቀርብ የተጠራ ወይም ተይዞ የቀረበ ሰው ስሙ፣ ፆታው፣ ዕድሜው፣ ዜግነቱ እና አድራሻው ተረጋግጦ ለቀረበበት የወንጀል ወይም የግል አቤቱታ ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል፡፡

፪. ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ምላሽ ለመስጠት እንደማይገደድ፣ ያለመናገር መብት እንዳለው፣ በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መንገር እና ይኸው መከናዎኑ በጽሑፍ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተጠርጣሪው ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ስሙን፣ ጾታውን፣ ዕድሜውን፣ ዜግነቱንና አድራሻውን እንዲገልጽ ለሚቀርብለት ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

፬. ተጠርጣሪው ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆነ ከመርማሪ ለሚቀርብለት ጥያቄ እንደአግባቡ በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምልክት ወይም በአስተርጓሚ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው በአስተርጓሚ ከሆነ አስተርጓሚውም የተጠየቀውንና የሰጠውን ምላሽ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

፭. ተጠርጣሪው ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ ሂደቱ በምስል ወይም በድምፅ ሊቀረፅ ይችላል፡፡

፮. መርማሪ ተጠርጣሪው የሰጠውን ቃል ብቻ ይመዘግባል፤ ይህንኑም በእርሱና በተጠርጣሪው እንዲፈረም ያደርጋል፤ ተጠርጣሪው ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይህንኑ በመዝገብ ላይ ያሰፍራል፡፡

፯. ተጠርጣሪው ቃሉን በማቆያ ቤት የምርመራ ክፍል ወይም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ጠበቃው በምርመራ ክፍሉ ሊገኝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፲፩ በመርማሪ ፖሊስ የሚሰጥ ዋስትና**

፩. በአንቀጽ ፻፲፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተያዘው ሰው የተጠረጠረበት ወንጀል ቀላል ከሆነ፣መርማሪ ፖሊስ እንደ ነገሩ ሁኔታ ተጠርጣሪውን በራስ ዋስትና፣ በዋስትና ወይም ያለዋስትና ሊለቀው ይችላል፡፡

፪. ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት ወንጀል መፈጸሙ ወይም የተያዘው ሰው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ አጠራጣሪ ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪውን በዋስትና ወይም በራስ ዋስትና ሊለቀው ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት የተያዘው ሰው በዋስትና በሚለቀቅበት ጊዜ፤

**(ሀ)** በተወሰነ ጊዜና ቦታ መርማሪ ጋር ወይም ሌላ አመቺ በሆነ ቦታ በአካል ቀርቦ ሪፖርት እንዲያደርግ፣

**(ለ)** የተወሰነ ቦታ እንዳይደርስ፣

**(ሐ)** ከምስክሮች ወይም ከግል ተበዳዮች ጋር እንዳይገናኝ፣

**(መ)** ከተወሰነ ክልል ወይም ቦታ ውጭ እንዳይሄድ፣ወይም

**(ሠ)** የመሳሰሉትን ቅድመ ሁኔታዎች፣

ግዴታ በማስገባትና በማስፈረም ሊለቀቅ ይችላል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ከዋስትና ጋር የሚቀመጥ ቅድመ ሁኔታ እንደ አግባብነቱ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ወይም ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች ሊያካትት ይችላል፡፡

፭.መርማሪ ፖሊስ የዋስትናውን መጠን ሲወስን የተያዘው ሰው የተጠረጠረበትን ወንጀልና የተጠርጣሪውን አቅም ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዋስትና የሚያዝ ገንዘብ በመንግሥት የገንዘብ አስተዳደር መሠረት በአደራ ይቀመጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፲፪ ተጠርጣሪን ፍርድ ቤት ማቅረብ</u>**

፩. የተያዘ ሰው በፖሊስ ዋስትና ያልተለቀቀ ከሆነ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡ ይህም ጊዜ ተጠርጣሪው ከተያዘበት ቦታ ፍርድ ቤት ለማድረስ አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡

፪. መርማሪው ፖሊስ በዚህ አንቀጽ መሠረት ፍርድ ቤት የቀረበ ተጠርጣሪ የተያዘው በበቂ ጥርጣሬ እንዲሁም መያዙ ለምርመራው አስፈላጊ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በማቆያ ቤት መቆየት ለምርመራው አይረዳም ብሎ ካመነ በዋስትና ይለቀዋል፡፡ ሆኖም የተባለው ድርጊት መፈጸሙ ወይም የተያዘው ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሲሆን ያለ ዋስትና ሊለቀው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፲፫ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ</u>**

፩. ፍርድ ቤት ምርመራው ያልተጠናቀቀ መሆኑንና ምርመራውን ለማድረግ የተጠርጣሪው በማቆያ ቤት መቆየት አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን በአንድ ጊዜ እስከ ፲፬ ቀናት የሚደርስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሚፈቀደው ጊዜ የወንጀሉን ክብደት፣ ውስብስብነት፣ የሚፈለገውን ማስረጃ ዓይነትና ብዛት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሚፈቀደው አጠቃላይ የምርመራ ጊዜ በማናቸውም ሁኔታ ከአራት ወር ሊበልጥ አይችልም፡፡

፬. ምርመራው ተጠናቆ ተጨማሪ ጊዜ የማያስፈልገው እንደሆነ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪው በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በዋስትና እንዲወጣ ወይም ዐቃቤ ሕግ በአንቀጽ ፻፺፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ክስ እስከሚመሠርት ድረስ ከሀያ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በማቆያ ቤት እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፲፬ ያልተጠናቀቀ ምርመራ ስለሚኖረው ውጤት</u>**

፩. በአንቀጽ ፻፲፫ በተቀመጠው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ውስጥ የወንጀል ምርመራው ካልተጠናቀቀ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪውን በዋስትና ይለቀዋል፤ ምርመራውም ይቀጥላል፡፡

፪. የወንጀል ምርመራው በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ካልተጠናቀቀ ፍርድ ቤት ከወንጀል ድርጊት መፈጸም ጋር በተያያዘ የታገደ ወይም የተያዘ ንብረት ሲኖር ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫. ፍርድቤቱ መርማሪ ፖሊስ የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤሕግ እንዲያስተላልፍና ዐቃቤ ሕግም በአንቀጽ ፻፴፯ መሠረት በጉዳዩ ላይ እንዲወስን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፬. ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ መሠረት ውሳኔ ያልሰጠ እንደሆነ ተጠርጣሪው በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ወይም ንብረት ካለ ይመለስለታል፤ የተጣለ እግድ ካለም ይነሳል፤ ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ አንድ ነፃ ሰው ያለው መብት ይኖረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፲፭ በማቆያ ቤት ያለ ሰው ስላለው መብት</u>**

፩.በማቆያ ቤት ያለ ሰው እንደአግባብነቱ በማረሚያ ቤት ያለ ሰው መብት አለው፡፡

፪.በዚህ ሕግ መሠረት ተይዞ በማቆያ ቤት የሚቆይ ሰው የትዳር ጓደኛውን፣ልጆቹን፣ የቅርብ ዘመዱን፣ የቅርብ ጓደኛውን፣ የኃይማኖት አባቱን ወይም መሪውን፣ ሐኪሙንና የሕግ አማካሪውን በግል የማነጋገር መብት አለው፡፡

፫.ማቆያ ቤቱ ተጠርጣሪው ዋስ እንዲያገኝ ወይም በተጠረጠረበት የወንጀል ጉዳይ ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እንዲችል ድጋፍና ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፲፮ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የተጠርጣሪነት ቃል</u>**

፩. የቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት ሥነ ሥርዐት ወይም የወንጀሉ ክስ መስማት ከመጀመሩ በፊት ማናቸውም ፍርድ ቤት ማንኛውንም የተሰጠውን ቃል ወይም የእምነት ቃል ለመመዝገብ ይችላል፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ቃል የሰጠውን ሰው በነፃ ፈቃዱ ቃሉን መስጠቱን መጠየቅ፣ማረጋገጥና በመዝገብ ያሰፍራል፡፡

፫.ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ በችሎት ውስጥ የፖሊስ ባልደረባ መገኘት የለበትም፡፡

፬.ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ማንኛውም ቃል ወይም የእምነት ቃል ሳያጓድል በጽሑፍ፣ በመቅረጸ ድምፅ ወይም በቪዲዮ ይመዘግባል፤ የተመዘገበው ቃል ወይም የእምነት ቃል ቃሉን ለሰጠው ሰው ከተነበበለት ወይም ከተገለጸለትና ትክክለኛነቱን ካረጋገጠ በኋላ በዳኛው ይፈረማል፡፡

፭. የተሰጠውን ቃል ግልባጭ ጉዳዩን ለሚከታተለው ዐቃቤ ሕግ ይላክለታል፡፡

**<u>ክፍል ሰባት</u>**

## የንብረት እግድ

### አንቀጽ ፻፲፯ መርህ

፩. ተፈጽሟል ከተባለው ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ንብረት ወይም ገንዘብ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት ሊታገድ፣ ሊያዝ እና አግባብነት ባለው አካል ሊተዳደር ይችላል፡፡

፪. በዚህ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት፡-

**(ሀ)** በወንጀል ሕግ ሊወረስ የሚችል ንብረት ሲሆን፣

**(ለ)** በግለሰብ እጅ እንዳይገባ የተደነገገ ወይም ልዩ ፍቃድ የሚያስፈልገው ንብረት ሲሆን፣

በዚህ ሕግ መሠረት ሊታገድ ይችላል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚታገደው ንብረት ተጠርጣሪው በተጠረጠረበት ወንጀል ሊቀጣ ከሚችለው የገንዘብ ቅጣት ወይም ካገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የግል ንብረት ነው፣

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ የተደነገገው ንብረት ወይም ገንዘብ፡-

**(ሀ)** ለተከሳሹና ለቤተሰቡ የእለት አገልግሎት የሚጠቅሙ የቤት ውስጥ መገልገያ፣ እና

**(ለ)** ተከሳሹና ቤተሰቡ የሚተዳደሩበት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆንና፣ የሚተዳደሩት ከታገደው ንብረት ከሚገኝ ገቢ ከሆነ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ለተከሳሹና ለቤተሰቡ ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ የሚገምተውን ያህል ገቢ፣

አይታገድም፡፡

### አንቀጽ ፻፲፰ የእግድ ማመልከቻ ማቅረብ

፩. ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ፖሊስ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፻፲፯** የተጠቀሰው ንብረት እንዲታገድ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪.ማመልከቻው የወንጀል ክስ ከመመሥረቱ በፊት ወይም ከተመሠረተ በኋላ ሊቀርብ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፻፲፱ የማመልከቻው ይዘት

በዚህ ሕግ መሠረት የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ፤

፩. የወንጀሉን ፍሬ ነገር እና በየደረጃው የተወሰዱትን ርምጃዎች፣ ክስ ያልተመሠረተ እንደሆነ ጉዳዩ የሚገኝበት ደረጃ የሚያሳይ መረጃ፣

፪. የሚታገደው ንብረት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፫ በተዘረዘሩት ሁኔታ የተገኘ መሆኑን የሚያሳይ ምክንያት፣

፫. የንብረቱ ዝርዝር ወይም የገንዘቡ መጠን፣ የንብረቱ መለያ እና ንብረቱ የሚገኝበትን አድራሻ፣ እና

፬. የንብረት እግድ የቀረበበት ምክንያትና እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን

መያዝ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፺ የእግድ ትእዛዝ መስጠት**

፩. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ የእግዱን አስፈላጊነት ካመነበት ንብረቱ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የእግድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ትእዛዙን የሚመለከተው አካልና የሚቻል እንደሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በሌለበት የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠ መርማሪ ፖሊስ ትእዛዙን ለተጠርጣሪው፣ ለተከሳሹ፣ ለወኪሉ ወይም በትእዛዙ ላይ ስሙ ለተጠቀሰ ሰው ያደርሳል፡፡

፫. የሚታገደው ንብረት የሚበላሽ ከሆነ ንብረቱ በጨረታ ተሸጦ ገንዘቡ በአደራ ይቀመጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፩ የእግድ ትእዛዝን ማንሳት ወይም ማሻሻል**

፩. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺ መሠረት የተሰጠ የእግድ ትእዛዝ የደረሰው ወይም እንዲያውቅ የተደረገ ሰው ወይም በትእዛዙ ምክንያት ቅር የተሰኘ ሦስተኛ ወገን ትእዛዙ እንዲነሳለት ወይም እንዲሻሻል ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

፪. የእግድ ትእዛዙ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማመልከቻ የታገደውን ንብረት ዐይነት፣ አድራሻና ዝርዝር መግለጫ፣ እግዱ የሚነሳበትን ምክንያት እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ዐቃቤ ሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፪ የእግድ ትእዛዝ ቀሪ መሆን**

ተጠርጣሪው የማይከሰስ ከሆነ፣ ክሱ ከተነሳ፣ ከተዘጋ፣ ከተሻሻለ ወይም ከተለወጠ ወይም ተከሳሹ በነፃ ከተለቀቀ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን የእግድ ትእዛዝ በማናቸውም ጊዜ ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ቀዳሚ ምርመራ

**አንቀጽ ፻፳፫ ዓላማ**

የቀዳሚ ምርመራ ዓላማ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ እንዲሁም ተጠርጣሪው እንዲመዘገብለት የሚፈልገውን ማስረጃ መያዝና መጠበቅ ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፳፬ ቀዳሚ ምርመራ የሚደረግባቸው ወንጀሎች**

፩. በዚህ ሕግ በሠንጠረዡከባድ ወንጀል መሆናቸው በተደነገጉ ጉዳዮች የተጠረጠረን ሰው ዐቃቤ ሕግ በቀጥታ ክስ ለመመሥረት ካልወሰነ በስተቀር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዐቃቤ ሕግ ጠያቂነት ቀዳሚ ምርመራ ሊካሄድ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ ምርመራ የሚያስፈልገው ከባድ ወንጀል መሆኑ በተደነገገ እና ሌላ ተደራራቢ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ የቀዳሚ ምርመራው በሁሉም የወንጀል ዓይነቶች ላይ ሊካሄድ ይችላል፡፡

፫.ቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ እና ተጠርጣሪው ያቀረቡትን ማስረጃዎች ይመዘግባል፤ ሲጠየቅም ክሱን ለሚያየው ፍርድ ቤት ይልካል፡፡

**አንቀጽ ፻፳፭ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት**

፩.ቀዳሚ ምርመራ ለማካሄድ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ለምስክሮች አቀራረብ ሲባል ዐቃቤ ሕግ የቀዳሚ ምርመራ እንዲካሄድ ለማንኛውም የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

፫. ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ሲወስን ለተጠርጣሪው ያለውን አመቺነትም ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፳፮ ቀዳሚ ምርመራ እንዲደረግ ስለማመልከት**

፩. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን መርምሮ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፻፳፬ መሠረት ጉዳዩ በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት እንዲጣራ ሲወስን ለቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ማመልከቻ ያቀርባል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት ማመልከቻው በቀረበለት ዕለት ቀዳሚ ምርመራ የሚጀመርበትን ቀን በመወሰን ዐቃቤ ሕግ፣ ተጠርጣሪ፣ ምስክሮች እና ሌሎች ማስረጃዎች በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፳፯ የማስረጃ አመዘጋገብ**

፩.ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው እንደቀረበ ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩን አስረድቶ ማስረጃውን እንዲያሰማ ያደርጋል፡፡

፪.የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተመዘገበ በኋላ ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ለተጠርጣሪው፣

**(ሀ)** ፈቃደኛ እንደሆነ ለክሱ መልስ ቃሉን ለመስጠት የሚችል እንዲሁም እንዲመዘገብለት የሚፈልገው ማስረጃ ካለ እንዲመዘገብለት፣

**(ለ)** ቃሉን ለመስጠት የማይገደድ መሆኑን እና የሚሰጠው ቃል በጽሑፍ ሆኖ ነገሩ ሲሰማ በማስረጃነት የሚቀርብ፣

መሆኑን ይነግረዋል፡፡

፫. በቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት የተመዘገበ ማስረጃ ግልባጭ ለዐቃቤ ሕግና ለተጠርጣሪው መሰጠት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፳፰ ተጨማሪ ማስረጃ**

የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት ለዚህ ምዕራፍ አፈጻጸም ምስክርነቱ ወይም የማስረጃ ምንጭነቱ አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ ሰው ወይም አግባብነት ያለው አካል እንዲቀርብና የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲመዘገብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፳፱ ምስክሮች እንዲቀርቡ ስለማሳወቅ**

በቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል ወይም ሌላ ማስረጃ የሰጠ ምስክር ወይም አግባብነት ያለው አካል ክሱ በሚሰማበት ፍርድ ቤት የመቅረብ ግዴታ እንዳለበት ፍርድ ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራስ ዋስትና እንዲፈርም ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፴ የመዝገብ ዝርዝር**

፩. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ ለዐቃቤ ሕግና ለተጠርጣሪ የሚሰጥ ግልባጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከተውን ዝርዝር መያዝ ይኖርበታል፡፡

**፪.** መዝገቡ፡-

**(ሀ)** የመዝገቡ ቁጥር፣

**(ለ)** የወንጀሉ ዓይነት፣ የተፈጸመበትን ቀን እና እንደአግባብነቱ ወንጀሉ የተፈጸመበት ንብረት ዋጋ ወይም ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ሁኔታ፣

**(ሐ)** የወንጀል ክስ የቀረበበትን ቀን እና የወንጀል ክስ አቅራቢው ስምና አድራሻ፣

**(መ)** የሚታወቅ እንደሆነ የተጠርጣሪው ስም፣ አድራሻ፣ ሥራ፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዜግነት፣ የቤተሰብ ሁኔታ እና ሌላ አስፈላጊ መረጃ፣

**(ሠ)** ተጠርጣሪው የተያዘበት ቀን ወይም እንዲያዝ የፍርድ ቤት ትእዛዝ የተሰጠበት ቀን፣

**(ረ)** ተጠርጣሪው ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት የቀረበበት ቀን፣

**(ሰ)** የዐቃቤ ሕግ ስምና አስፈላጊ ሲሆን የተጠርጣሪ ጠበቃ ስም፣

**(ሸ)** በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት የተሰጠ ቃል፣

**(ቀ)** የዐቃቤ ሕግና የተጠርጣሪ ሌላ የተመዘገበ ማስረጃ፤ እና

**(በ)**ቀዳሚው ምርመራ የተካሄደበት ቀን፣

ዝርዝር መያዝ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻ጠ፩ የተጠርጣሪ አቆያየት</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ በሌላ ምክንያት በተለየ ሁኔታ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት የሚቆይ ካልሆነ በስተቀር የቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ተጠርጣሪውን በዋስትና ይለቀዋል፡፡

**፪.**ቀዳሚ ምርመራ አድራጊው ፍርድ ቤት ድርጊቱ ስለመፈፀሙ ወይም ተጠርጣሪው ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሆኖ ሲያገኘው ተጠርጣሪውን ያለዋስትና ለጊዜው ይለቀዋል፡፡

**<u>ሦስተኛ መጽሐፍ</u>**

**<u>ዋስትና</u>**

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

**አንቀጽ ፻፴፪ መርህ**

፩.በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው፡፡

፪.ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄን ለመከልከል ወይም በቅድመ ሁኔታ መፍታትንጨምሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲያቀርብ እና ሌሎች የጥንቃቄ ርምጃዎች ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. ዋስትና እንደነገሩ ሁኔታ በመርማሪ ፖሊስ ወይም በፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገባ የዋስትና ግዴታ በማንኛውም የምርመራ፣ ክስና የፍርድ ሂደት ተፈጻሚነት አለው፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተደነገገው ቢኖርም ክሱን የሚያየው ፍርድ ቤት የተሰጠውን የዋስትና ግዴታ እንደነገሩ ሁኔታ ሊያሻሽል፣ ሊለውጥ ወይም ቀሪ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፴፫ ዋስትና በፍርድ ቤት ስለሚከለከልበት ሁኔታ**

ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሽ በዋስትና ቢለቀቅ ፡-

፩. በተፈለገ ጊዜ እና ቦታ ሊቀርብ አይችልም ብሎ ሲያምን፣ ወይም

፪. ምስክርን ያስፈራራል ወይም ማስረጃን ያጠፋል ብሎ በበቂ ምክንያት ሲያምን፣

ዋስትና ሊከለከል ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## በዋስትና ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

**አንቀጽ ፻፴፬ በዋስትና ለመለቀቅ የሚቀርብ ማመልከቻ**

፩. በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በሌላ ማናቸውም አመች መንገድ ማመልከት ይችላል፤ በራሱ ወይም በጠበቃው ማመልከት የማይችል እንደሆነ ቤተሰቡ ወይም ወኪሉ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪. የዋስትና ጥያቄው የቀረበበትን ምክንያት በአጭሩ መግለጽና የተያዘው ሰው ማቅረብ የሚችለውን የዋስትና አይነት ማመልከት ይኖርበታል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የዋስትና ጥያቄ፡-

**(ሀ)** ጉዳዩ በጊዜ ቀጠሮ በፍርድ ቤት እየታየ እንደሆነ የጊዜ ቀጠሮው ለቀረበለት ፍርድ ቤት፣

**(ለ)** ጉዳዩ በቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት እየታየ እንደሆነ ቀዳሚ ምርመራው ለቀረበለት ፍርድ ቤት፣

**(ሐ)** ክሱ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ እንደሆነ ክሱን ማየት ለጀመረው ፍርድ ቤት፣

ይቀርባል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፴፫ በማመልከቻ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ</u>**

፩.ፍርድ ቤቱ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ጥያቄ ማመልከቻ ሲቀርብለት ሳይዘገይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ፖሊስ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ አስተያየቱን እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ፍርድ ቤቱም አስተያየቱን በተቀበለ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ውሳኔውን ይሰጣል፡፡

፫.ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቱን መግለጽ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፴፬ ዋስትናን መፍቀድ</u>**

፩.ፍርድ ቤት በዋስትና ግዴታ የመለቀቅ ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የሚለቀቅበትን የዋስትና ግዴታ ዐይነትና መጠን ይወስናል፡፡

፪. እድሜው አስራስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ያላቸው ባልና ሚስት በተመሳሳይ ወይም አንድ ላይ የተያዙ እንደሆነ ለልጆቹ አስተዳደግ የበለጠ ይጠቅማል ለተባለው ወላጅ፣ ነፍሰጡር ለሆነች ሴት ወይም ዘጠኝ ዓመት ያልሞላው ልጅ ብቸኛ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የዋስትና መብት ይፈቀዳል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የዋስትና ግዴታ የራስ ዋስትና፣ የገንዘብ፣ የሰው ወይም የንብረት ዋስትና ግዴታ ሊሆን ይችላል፡፡

፬.ፍርድ ቤቱ ስለዋስትና ግዴታው ዐይነትና መጠን ሲወስን፡-

**(ሀ)** የወንጀሉን አፈጻጸም፣ የክሱን ብዛት፣ ክብደትና የክስ ባህሪያት፣

**(ለ)** ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ቀደም ሲል የዋስትና ግዴታውን የተወጣ ወይም ያልተወጣ መሆኑን፣

**(ሐ)** ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ያለውን ዕድል፣

**(መ)** የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ ወይም የዋሱ ሃብት፣ የገቢ መጠንና ማኅበራዊ ሁኔታ፣

በማመዛዘን ይሆናል፡፡

**፭.** ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በራስ ዋስትና ሲለቀቅ የዋስትና ግዴታ ይፈርማል፡፡

**፮.** ፍርድ ቤት ዋስትና ሲፈቅድ በዋስትና የተለቀቀው ሰው የዋስትና ግዴታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፫** በተመለከተው መሠረት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ተጨማሪ ግዴታዎችን እንዲፈፅም ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

**፯.**ፍርድ ቤቱ ዋስትና የፈቀደለት ሰው በፀብ ወይም አምባጓሮ፣ በሴት ወይም በሕጻን ላይ በተፈጸመ ወይም በተመሳሳይ ወንጀል የተጠረጠረ ከሆነ በመልካም ባህሪ ለመመራት የእጅ-ጠብቅ ዋስ ግዴታ መግባቱን ቅድመ-ሁኔታ ሊያደርገው ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፴፪ በመያዣ ትእዛዝ ላይ ዋስትናን ማመልከት**

**፩.** ፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ሲሰጥ የዋስትናውን ግዴታ በትእዛዙ ላይ ሊያመላክት ይችላል፤ ተጠርጣሪው የዋስትና ሁኔታውን ካሟላ ወዲያውኑ ይለቀዋል፡፡

**፪.** የመያዣ ትእዛዙ እንደአስፈላጊነቱ የዋስትናውን ዐይነትና መጠን፣ እንዲሁም ተጨማሪ የጥንቃቄ ርምጃዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

**፫.** የመያዣ ትእዛዙን እንዲያስፈጽም የታዘዘ መርማሪ ፖሊስ የተያዘው ሰው መለቀቁን ማሳወቅና ስለዋስትና የተሰጠውን ትእዛዝ ለፍርድ ቤቱ መመለስ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፴፫ ዋስትና ለማቅረብ ያልቻለ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ**

ተጠርጣሪው የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው በቀላል ወይም በመካከለኛ ወንጀል እንደሆነ እና የተወሰነው የዋስትና ግዴታ የገንዘብ፣ የሰው ወይም የንብረት ዋስትና ሆኖ ይህንን ግዴታ ለመፈጸም አቅም የሌለው መሆኑን ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን በማሻሻል ወይም በመለወጥ በራስ ዋስትና ከተጨማሪ የጥንቃቄ ርምጃ ጋር እንዲለቀቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፴፬ ስለመልቀቅ**

**፩.**ፍርድ ቤት ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስትና ግዴታ እንዲለቀቅ ከወሰነ ተገቢውን ሥርዐት እንዲፈጽምና ከእሥር እንዲለቀቅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፪.የመልቀቅ ትእዛዙ የደረሰው ማቆያ፣ ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት ትእዛዙ እንደደረሰው ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ወዲያውኑ መልቀቅ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፶ በስህተት ወይም በማታለል የተሰጠ ዋስትና**

፩. ዋስትና ሆን ብሎ በተፈጸመ የማሳሳት፣ የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት የተሠጠ መሆኑ ከታመነ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ አመልካችነት በዋስትና የተለቀቀው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፪. ፍርድ ቤት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ሲቀርብ አስተያየቱን ከጠየቀ በኋላ ዋስትናው የተሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከቱት ምክንያቶች መሆኑ ከተረጋገጠ የተፈቀደውን ዋስትና በማንሳት ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከተደነገገው ውጭ በሆነ ሌላ ምክንያት በስህተት የዋስትና ግዴታ የተሰጠ እንደሆነና ይኸው በፍርድ ቤቱ ከታመነ የተጠርጣሪውን ፣የተከሳሹን ወይም የዐቃቤ ሕግን አስተያየት በመጠየቅ ፍርድ ቤት ተጨማሪ የዋስትና ግዴታ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. የታዘዘውን የዋስትና ግዴታ ያልፈፀመ ወይም ለመፈጸም ያልቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በአንቀጽ **፻፴፫** መሠረት አግባብ ነው ያለውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፶፩ አዲስ ፍሬ ነገር**

፩. የዋስትና ጥያቄው በተፈቀደ ወይም በተከለከለ ጊዜ ያልታወቀ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተፈጠረ አዲስ ፍሬ ነገር ያለ እንደሆነ በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት የዋስትና ውሳኔውን መርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የዋስትና መብቱ ተከልክሎ በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ፣በዋስ እንዲለቀቅ ወይም አዲስ የዋስትና ግዴታ እንዲገባ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን ከመስጠቱ በፊት የዐቃቤ ሕግን፣ የተጠርጣሪውን ወይም የተከሳሽን አስተያየት ይቀበላል፡፡

**አንቀጽ ፻፶፪ የዋስትና ግዴታ ቀሪ መሆን**

፩. በዋስትና የተለቀቀ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በነፃ የተለቀቀ ወይም የተፈረደበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቀሪ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል፡፡

፪. የዋስትና ግዴታ የፈረመው ዋስ የሞተ እንደሆነ ዋስትናው ዋሱ ከሞተበት ቀን ጀምሮ ቀሪ ይሆናል፡፡ ሟች ከመሞቱ በፊት የዋስትና ግዴታውን በአግባቡ መወጣቱ ወይም ግዴታውን ያልተወጣው በበቂ ምክንያት

መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ የተያዘው ንብረት ከዋስትናው ግዴታ ነፃ ይሆናል፡፡ በዋስትና ግዴታ የተለቀቀው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ሌላ አዲስ ዋስ እንዲጠራ ፍርድ ቤቱ ያዛል፡፡

፫. ዋሱ በሕግ ችሎታ ካጣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ ተፈፃሚነት አለው፡፡

**አንቀጽ ፻፶፫ የዋስትና ግዴታ**

፩.ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በራስ ዋስትና ወይም በሌላ የዋስትና ግዴታ የተለቀቀ እንደሆነ ፍርድ ቤት በሚወስነው ማንኛውም ጊዜና ቦታ ወይም ጉዳዩን ለመስማት በሚሰጥ ቀጠሮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪. ዋሱ በዋስትና ግዴታ የተለቀቀውን ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ፍርድ ቤት በሚወስነው በማናቸውም ጊዜና ቦታ ወይም ጉዳዩን ለመስማት በሚሰጠው ቀጠሮ እንዲቀርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፫.የተጠርጣሪ ወይም የተከሳሽ ዋሶች ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ የጋራና የተናጠል የዋስትና ግዴታ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**አንቀጽ ፻፶፬ የዋስትና ግዴታን አለመፈጸም**

፩. በዋስትና ግዴታ የተለቀቀ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ፡-

**(ሀ)**የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብና ዋሱም ቀርቦ እንዲያስረዳ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**(ለ)**ዋስ ቀርቦ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ያልቀረበበትን ምክንያት ለፍርድቤቱ ያስረዳል

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩በተደነገገው መሠረት ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካላስረዳ በዋስትና ግዴታ የተያዘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ያልተወጣው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካላስረዳ እና በዋስትና ግዴታ የተያዘው ንብረት እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ በዋስትና ግዴታው ልክ ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ፍርድቤቱ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ንብረቱ ከመሸጡ በፊት የዋስትና ገንዘቡን ገቢ ከተደረገ የሽያጭ ሂደቱ ይቋረጣል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ መሠረት የተሰጠው ትእዛዝ ዐቃቤ ሕግ ተከታትሎ ያስፈፅማል፡፡

**አንቀጽ ፻፶፭ ዋስትናን ስለማውረድ**

፩.ዋሱ በማንኛውም ሁኔታ ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን በማቅረብ የዋስትና ግዴታው እንዲወርድለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

፪.ዋሱ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ይጠፋል ብሎ ከጠረጠረ ተይዞ እንዲቀርብና ዋስትናው እንዲወርድለት ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫.ዋሶቹ ከአንድ በላይ ሲሆኑ የዋስትና ግዴታ እንዲወርድላቸው በጋራ ወይም በተናጠል ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፡፡

፬.ዋስትና ተፈቅዶለት የነበረው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ እንደቀረበ ፍርድ ቤቱ የዋሱን የዋስትና ግዴታ ወዲያውኑ ያወርዳል፡፡

፭.ፍርድ ቤቱ የዋስትና ግዴታውን ካወረደ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ሌላ የዋስትና ግዴታ እንዲያቀርብ ወይም ይህንንም መፈጸም ያልቻለ እንደሆነ በማቆያ ቤት ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፵፰ ይግባኝ ማቅረብ**

፩.ዋስትና የተከለከለ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በሀያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

፪. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክሩን ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አራተኛ መጽሐፍ**

**በምርመራ መዝገብ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ**

**ምዕራፍ አንድ**

**በምርመራ መዝገብ ላይ የዐቃቤ ሕግ የመወሰን ሥልጣን**

**አንቀጽ ፻፵፱ ጠቅላላ**

፩. በምርመራ መዝገብ ላይ የመወሰን ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

**፪.** ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ ውሳኔዎችን ለመስጠት እንዲያስችለው መርማሪ ፖሊስ፡-

**(ሀ)** የተጠርጣሪ፣ የአቤቱታ አቅራቢ እና ሌሎች አግባብ ያላቸውን ሰዎች ስም፣

**(ለ)** ስለ ቀረበው አቤቱታ ዐይነትና የነገሩን ሁኔታ ያውቃሉ የተባሉትን ሰዎች ስም፣

**(ሐ)** የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች ዐይነት፣እንዲሁም የማስረጃ አጠባበቅ ወይም ሌሎች የምርመራ ክንውኖችን የሚያመለክት፡-

ሪፖርት ለዐቃቤ ሕግ መላክ ይኖርበታል፡፡

**፫.** ዐቃቤ ሕግ መሠረት የፖሊስ ምርመራ መዝገብ እንደደረሰው የዐቃቤ ሕግ መዝገብ በመክፈት፡-

**(ሀ)** ምርመራው የሚካሄድበትን አግባብ ለይቶ ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን፣

**(ለ)** የተጀመረ ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠ ምርመራ እንዲቀጥል፣

**(ሐ)** የምርመራ መዝገብ እንዲዘጋ፣

**(መ)** ክስ እንዲመሠረት ወይም ክስ አያስከስስም የሚል ውሳኔ ሊሰጥ፣

**(ሠ)** በዚህ ሕግ መሠረት ጉዳዩ በዕርቅ፣ በጥፋተኝነት ድርድር ወይም በሌላ አማራጭ ዘዴዎች እንዲታይ፣

ሊወስን ይችላል፡፡

**፬.** ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ሕግ፣ በቂ ማስረጃ እና የሕዝብ ጥቅም መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**፭.** ክስ ለመመሥረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም የሕዝብን ጥቅም የማያስከብር መሆኑ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከታመነ ክስ ላይመሠርት ይችላል፡፡

**፮.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል ላይ ክስ ለመመሥረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ሲኖር እና የግል ክስ እንዲቀርብ ዐቃቤ ሕግ ከፈቀደ የግል ተበዳዩ ወይም ወኪሉ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፯.**ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ በተመለከተው መሠረት ውሳኔ ለመስጠት አጠራጣሪ ሁኔታ በሚያጋጥመው ጊዜ መሪ ትእዛዝ እንዲሰጠው ለበላይ ዐቃቤ ሕግ ያስተላልፋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፵፫ የዐቃቤ ሕግ ሥራ ከተፅዕኖ ነፃ ስለመሆኑ</u>**

ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ከማንኛውም ዐይነት ተፅዕኖ ወይም ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፵፱ የምርመራ መዝገብን መዝጋት</u>**

ተጠርጣሪው፡-

**<u>፩</u>.**የሞተ እንደሆነ፣

**<u>፪</u>.** ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ዕድሜው የወንጀል ኃላፊነት የማያስከትል እንደሆነ፣

**<u>፫</u>.**የተጠረጠረበት ጉዳይ ወንጀል ካልሆነ፣

**<u>፬</u>.**የፈጸመው ወንጀል በይርጋ የታገደ፣ በይቅርታ ወይም በምኅረት ቀሪ የተደረገ እንደሆነ፣

**<u>፭</u>.**ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ እንደሆነ፣ ወይም

**<u>፮</u>.** ጉዳዩ በዚህ ሕግ በተመለከተው አግባብ በዕርቅ፣ በድርድር ወይም በሌላ አማራጭ የመፍትሔ ርምጃ ውሳኔ ያገኘ እንደሆነ፣

ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፶ ክስ የማይመሠረትባቸው ሁኔታዎች</u>**

ዐቃቤ ሕግ፡-

**<u>፩</u>.** ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ የለም ብሎ ካመነ፣

**<u>፪</u>.** ማስረጃ ቢኖርም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፻፵፩</u>** መሠረት ክስ እንዳይቀርብ ከወሰነ፣

**<u>፫</u>.** ተጠርጣሪው የፈፀመው ድርጊት ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት የማያሟላ ከሆነ፣

**<u>፬</u>.**ተጠርጣሪውን ለማግኘት የማይቻል እና ተጠርጣሪው በሌለበት ክሱ የማይታይ ከሆነ፣

**<u>፭</u>.** ተጠርጣሪው ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለው ሆኖ ይኸው መብቱ ያልተነሳ ከሆነ፣ ወይም

፯. ተጠርጣሪው በአእምሮ ወይም በሌላ የጤና ችግር ምክንያት የክርክር ሂደቱን መረዳት፣ መከታተል ወይም ራሱን መከላከል የማይችል ከሆነ፣

የአያስከስስም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፩ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ አለመመሥረት**

እንደጉዳዩ ልዩ ሁኔታ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

፩. ክሱ ቢመሠረት ዓለም አቀፍ ግንኙነትን ወይም ብሔራዊ ደኅንነትን የሚጎዳ እንደሆነ፤

፪. ወንጀሉ በማንኛውም ምክንያት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በመቆየቱ ወቅታዊነቱን ወይም አስፈላጊነቱን ያጣ እንደሆነ፤

፫.የክሱ መመሥረት ከፍ ያለ የኅንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል እንደሆነ፣

ዐቃቤ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲል ክስ ያለመመስረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፪ በክስ አለመመስረት ጊዜ የሚኖር ሥነ-ሥርዐት**

ዐቃቤ ሕግ፡-

፩. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ የማስረጃን ብቃት መሠረት በማድረግ ሆኖ ይህንኑ ውሳኔ የሚያስለውጥ አዲስ ማስረጃ ያገኘ እንደሆነ ውሳኔውን በማሻሻል ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፪. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተጠርጣሪው ያለመከሰስ መብቱ እንዲነሳ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፫ የምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም ክስ አለመመስረት ውጤት**

፩. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን ከዘጋ ወይም ክስ ላለማቅረብ ውሳኔ ከሰጠ እና ተጠርጣሪው በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ይሰጣል፤ የጊዜ ቀጠሮውን የሚከታተለው ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

፪. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም የክስ አላቀርብም ውሳኔ ሲሰጥ ከጉዳዩ ጋር የተያዘ ኤግዚቢት ወይም ሌላ ንብረት ላይ በሕግ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፫. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብ መዝጋት ወይም ክስ አላቀርብም ውሳኔ በጽሑፍ ለበላይ ኃላፊው፣ ለመርማሪው፣ ለግል ተበዳይ እና ለተጠርጣሪው ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ ፻፵ በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ**

፩. በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ቅር የተሰኘ መርማሪ ፖሊስ ወይም የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ ወይም ተጠርጣሪው ወይም ጠበቃው ቅሬታውን ደረጃውን ጠብቆ ላለው የበላይ ዐቃቤ ሕግ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የውሳኔ አቤቱታ የቀረበለት የበላይ ዐቃቤ ሕግ እንደ አስፈላጊነቱ ውሳኔውን ለማጽደቅ፣ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ሊወስን ይችላል፡፡

፫. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**የወንጀል ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጥባቸው አማራጭ መንገዶችና ተለዋጭ መፍትሔዎች**

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ**

**አንቀጽ ፻፵፩ ዓላማ**

የአማራጭ መንገዶች ዓላማ በወንጀል ፍትሕ ሥርዐት የማኅበረሰቡን ተሳትፎ በማረጋገጥ፣ እውነትን በማውጣት ፣የወንጀል ጉዳዮችን ሰላማዊ፣ ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ዘለቄታዊ ዕልባት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፵፪ አማራጭ መንገዶች**

ክስ የተመሠረተበት የወንጀል ጉዳይ ከመደበኛው የፍርድ ሂደት ውጭ በሚከተሉት አማራጭ መንገዶች ውሳኔ ሊያገኝ ይችላል፡፡

፩. ዕርቅ፣

፪. የጥፋተኝነት ድርድር፣

፫. የባሕላዊ ተቋማት ሥርዐት ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የአማራጭ መንገዶች አፈጻጸም</u>

## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

## <u>ዕርቅ</u>

**<u>አንቀጽ ፻፵፪ ዓላማ</u>**

የዕርቅ ዓላማ ተደጋጋሚ ወንጀሎችን እና ተደራራቢ ክሶችን በመቀነስ በግል ተበዳይና በተከሳሽ ወይም በቤተሰቦቻቸውና በሚገኙበት ማኅበረሰብ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በማስቀረት ሰላምን ማረጋገጥ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፵፫ መርህ</u>**

**<u>፩</u>.** ዕርቅ ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሊደረግ ይችላል፡፡

**<u>፪</u>.** ማንኛውም በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወይም ቀላል ወንጀል በዕርቅ እልባት ሊያገኝ ይችላል፡፡

**<u>፫</u>.** ዕርቅ የሚደረገው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ እና የግል ተበዳይ ጉዳዩን በዕርቅ ለመጨረስ ሲስማሙ ነው፡፡

**<u>፬</u>.** ዕርቅ በተከሳሽ፣ በግል ተበዳይ፣ በማኅበረሰብ መሪዎች አመልካችነት ወይም በፍርድ ቤት፣ በዐቃቤ ሕግና በመርማሪ ፖሊስ አነሳሽነት ሊፈጸም ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፵፬ ዕርቅ የሚደረግበት ሁኔታ</u>**

በዚህ ክፍል የተደነገገው ቢኖርም፡-

**<u>፩</u>.** ተጠርጣሪው ወይምተከሳሹ በግል ተበዳይ ላይ የፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንዱ በዕርቅ የሚያልቅ ሆኖ ሌላኛው በዕርቅ የማያልቅ ከሆነ፣ በዕርቅ የሚያልቀው የወንጀል ጉዳይ ብቻ በዕርቅ እንዲያልቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

**<u>፪</u>.** ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከአንድ በላይ በዕርቅ የሚያልቁ ወንጀሎችን በተመሳሳይ ጊዜ ፈፅሞ ቢገኝም ጉዳዩ በዕርቅ ሊያልቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ ጉዳዩ በዕርቅ አያልቅም፡፡

፫.ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች በዕርቅ በሚያልቅ የወንጀል ድርጊት ላይ በተሳተፉ ጊዜ፣የግል ተበዳይ በዕርቅ ለመጨረስ ከተስማማው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ጋር ብቻ መዝገቡ በዕርቅ ተዘግቶ በሌሎች ተጠርጣሪዎች ላይ ይቀጥላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፷ የዕርቅ ይዘት</u>**

የዕርቅ ስምምነት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

፩.የተስማሚዎቹን ስምና አድራሻ፣ ካሉም የአደራዳሪዎች ስምና አድርሻ፣

፪.ስምምነት የተደረገበትን ጉዳይ ባጭሩ፣

፫.በስምምነቱ ሃላፊነት የወሰደ ወገን ማንነትና የሃላፊነቱ ወሰን፣

፬. ካሳ ተወስኖ ከሆነ መጠንና ዓይነቱ፣

፭. የተለየ የይቅርታ አጠያየቅ ሁኔታ ተወስኖ ከሆነ ይኸው ሁኔታ፣

፮. የምስክሮች ስምና አድራሻ፣ እና

፯. ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፷፩ የዕርቅ ውጤት</u>**

፩.ጉዳዩ ክስ ያልተመሰረተበት ከሆነ ዐቃቤ ሕግ የስምምነት ሠነዱን በመመዝገብ መዝገቡን ይዘጋል፤ ክስ ተመሥርቶ እንደሆነም ክሱን ያነሳል፡፡

፪. ክስ በቀረበበት ፍርድቤት የቀረበለትን የዕርቅ ስምምነት ሕግና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ያፀድቃል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት በዕርቅ ስምምነት ያለቀ ጉዳይ ላይ በማንኛውም ጊዜ ክስ ወይም ይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የጥፋተኝነት ድርድር</u>**

**አንቀጽ ፻፷፪ ዓላማ**

የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማ ተከሳሹ ለተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በራሱ ነፃ ፍቃድ እንዲፀፀት እና እንዲታረም እድል ለመስጠት ፣የወንጀል ጉዳዮችን በተቀላጠፈ ሂደት በመጨረስ ወንጀል ፈፃሚዎች ቅጣታቸውን እንዲያገኙ በማድረግ ሕብረተሰቡን ማስተማር ነው ፡፡

**አንቀጽ ፻፷፫ የጥፋተኝነት ድርድር ሥርዐት**

የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሄደው ተከሳሽ ጥፋቱን አምኖ እና የድርጊቱን አፈፃፀም አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በዝርዝር አስረድቶ የክስ ብዛት ወይም ቅጣት እንዲቀነስለት፣ የቅጣቱ ዓይነት እንዲለወጥለት በፈቃደኝነት ሲስማማ ብቻ ነው ፡፡

**አንቀጽ ፻፷፬ በጥፋተኝነት ድርድር የሚታዩ ጉዳዮች**

ማንኛውም የወንጀል ጉዳይ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በጥፋተኝነት ድርድር ሥርዐት ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፷፭ የተከለከሉ ተግባራት**

የጥፋተኝነት ድርድር

፩. ዓላማውን፣ሕግን ፣ የሙያ ሥነ- ምግባርን በሚፃረር አኳኋን ማካሄድ፤

፪. በግል ከሳሽ አማካኝነት ማድረግ ፤

የተከለከለ ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፷፮ ቅድመ ሁኔታ**

፩. የጥፋተኝነት ድርድር በማናቸውም ተከራካሪ ወገን አነሳሽነት ሊከናወን ይችላል፡፡

፪.የጥፋተኝነት ድርድር በዐቃቤ ሕግ እና በጠበቃው ይካሄዳል፤ተከሳሹ በቻለ ጊዜ ሁሉ በድርድሩ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

፫. በወንጀል ፍትህ ሂደት ጠበቃ ለማቆም የገንዘብ አቅም የሌለው ተከሳሽ የሕግ ምክር የሚያገኝበትን ወይም በጠበቃ የሚወከልበትን ሁኔታ በተመለከተ በዚህ ሕግ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ዐቃቤ ሕግ ከተከሳሹ ጋር ድርድር ከማድረጉ በፊት ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፭.ተከሳሹ በሕግ የተደነገጉ የተከሳሽ መብቶችን ለመተው የተስማማ መሆኑን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፮. በአንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ በተከሰሱ ሰዎች መካከል የከፊሎቹ ወይም የሁሉም ጉዳይ በጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓት ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይችላል፡፡

፯. ጉዳዩ በጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓት ያልታየው ተከሳሽ መደበኛውን ክርክር አድርጎ በፍርድ ቤት ውሳኔ መከላከል ሳያስፈልግ ነፃ ተብሎ ወይም ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክስ በመጨረሻ ውሳኔ በዚህ ሕግ መሠረት ተከላክሏል ተብሎ ወይም ዐቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም ተብሎ ከቀረበበት ክስ ነፃ የሆነ እንደሆነ፣ በጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓት የተወሰነበት ተከሳሽ የወንጀል ተሳትፎው ተመሳሳይ መሆኑ ተረጋግጦ ከክሱ ነፃ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፷፪ ሂደቱን ለተከሳሽ ማስረዳት</u>**

የተከሳሽ ጠበቃ ለተከሳሹ ከድርድሩ በፊት፡-

፩. ድርድሩን በነፃ ፈቃዱ እንደሚያደርግ ፣

፪.የሚቀርብበትን ወይም የቀረበበትን የክስ ዓይነት፣ ይዘት፣ ብዛት እና ሊያስቀጣው የሚችለውን ቅጣት ፤

፫.ድርድር ቢያካሂድ ሊያገኝ ወይም ሊያጣ የሚችለውን መብትና ጥቅም፤

፬.በድርድሩ ሂደት መሳተፍ የሚችል መሆኑንና ሥርዐቱን የተረዳው መሆኑን፣

፭.በድርድሩ የሚገኝ ስምምነት በፍርድ ቤት ከፀደቀ ተፈፃሚ እንደሚሆን፣ እና

፮.የድርድሩን ሂደት፣ ውጤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮችን፣

ያስረዳዋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፷፫ በድርድር ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ሥነ ሥርዐት</u>**

፩. ዐቃቤሕግ ክሱን ከፍርድቤት መጥሪያ ጋር ለተከሳሽ ሲልክ ጉዳዩን በጥፋተኝነት ድርድር ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆኑን እና በበኩሉ ሊቀነስ የሚችል የክስ ብዛት፣የክስ ዐይነት እና የቅጣት መጠን ጋር አብሮ ሊልክ ይችላል፡፡

፪. ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ ለፍርድቤቱ ጉዳዩን በድርድር ለመጨረስ ፈቃደኝነቱን ይገልፃል፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ መሠረት ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ በጥፋተኝነት ድርድር ለመጨረስ ሲስማሙ ፍርድቤት ለድርድር የሚበቃቸውን ጊዜ በመወሰን ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

፬.ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጣመ በስተቀር የጥፋተኝነት ድርድር ለማካሄድ ከተስማሙበት ቀን ጀምሮ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ ድርድሩ ይጠናቀቃል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፳፱ የጥፋተኝነት ድርድር ይዘት</u>**

**፩.**የጥፋተኝነት ድርድር በክስ ብዛት፣በክስ ዐይነት ፣በፍሬ ነገር ፣ በቅጣት ዐይነት እና በቅጣት መጠን ሊደረግ ይችላል፡፡**፪.** የጥፋተኝነት ድርድር የወንጀሉን ክብደት፣ የተከሳሹን ባሕርይ፣ የቅጣትን ወጥነት፣ ተገማችነትና አግባብነት ከግምትውስጥ ያስገባል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፴ የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>**

**፩.** የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነት በጽሑፍ ወይም በቃል ለፍርድቤት ይቀርባል፡፡

**፪.** ፍርድ ቤቱ ድርድሩ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት የተከናወነ መሆኑንና ተከሳሹ በዚህ ሕግ አንቀፅ <u>**፻፳፯** መሠረት መረዳቱን </u>ለማረጋገጥ የዐቃቤሕግን ወይም የተከሳሽን ወይም የጠበቃውን ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፫.** የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነት _ሕግን እና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን ሲያረጋግጥ ስምምነቱን ያፀድቃል፤ ስምምነቱም ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**፬.** ፍርድቤቱ ስምምነቱ በዚህ ሕግ መሠረት ጉድለት ያለበት ሆኖ ካገኘው ተስተካክሎ እንዲቀርብ ወይም ውድቅ እንዲሆን ሊወስን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፴፩ የስምምነት አለመጽደቅ ውጤት</u>**

ፍርድ ቤት ስምምነቱን ሳያጸድቀው የቀረ እንደሆነ ስምምነቱ እንዲሻሻል ወይም  የክስ ሂደቱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፸፪ የተጎጂ ተሳትፎ**

**፩.** ዐቃቤ ሕግ ድርድር ሲካሄድ የተጎጂውን አስተያየት መጠየቅ ይኖርበታል፤ ድርድሩን ለማድረግ አስቸጋሪ በማይሆንበት ጊዜ ሁሉ በድርድሩ ሂደት እንዲገኝ ማድረግ ይችላል፡፡

**፪.**ድርድር የሚካሄድበት የወንጀል ጉዳይ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስከትል እንደሆነ እና ዐቃቤ ሕግ ከተጎጂ ፈቃድ ካገኘ የፍትሐብሔሩን ጉዳይ ሊጨርስ በ ይችላል፡፡

**፫.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ለተጎጂው ሊከፈል የሚገባውን የጉዳት ካሣ ወይም ሊተካ የሚገባውን ገንዘብ ወይም ሌላ ወጪ እና ኪሳራ ያካትታል ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ባሕላዊ ስርዐቶች

**አንቀጽ ፻፸፫ ዓላማ**

የባህላዊ ሥርዐት ዓላማ የወንጀል ድርጊት በባሕላዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኝ በማስቻል በማኅበረሰቡ ውስጥ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፸፬ መርህ**

**፩.** ማንኛውም  በክስ እና የፍርድ ሂደት ላይ ያለ የግል ተበዳይ ያለበት የወንጀል ጉዳይ ማስረጃ ከመሠማቱ በፊት በባሕላዊ ሥርዐት መሠረት ታይቶ ውሳኔ ወይም መፍትሔ ሊሰጥበት ይችላል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም  ሴትን መጥለፉ ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች  እና መሠል በሴቶች እና ሕፃናት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ  እንደሆነ ባሕላዊ ሥርዐት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ  ፻፸፭ የተከለከሉ ተግባራት**

፩. ተከሳሹ በፈጸመው አንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ባሕላዊ ሥርዐቶችን ተፈፃሚ ማድረግ ወይም ተከሳሹ ያልተቀበለውን ባሕላዊ ሥርዓት ተፈጻሚ ማድረግ ወይም ባሕላዊ ሥርዐቱን ከሌላ መፍትሔ ጋር መቀላቀል የተከለከለ ነው፡፡

፪.ተከሳሹ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ ጉዳዩ በባሕላዊ ሥርዐት አይታይም፡፡

**አንቀጽ ፻፸፪ ቅድመ ሁኔታ**

፩. ለጉዳዩ ዕልባት የሚሰጥ የታወቀ ባህላዊ ሥርዐት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

፪. ጉዳዩ በባህላዊ ሥርዐት እንዲታይ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፸፪ መሠረት ጥያቄ ሊቀርብ ይገባል፡፡

፫.ተከሳሹ ጉዳዩ በባህላዊ ሥርዐት ታይቶ እልባት እንዲያገኝ ፈቃደኛ ሊሆን ይገባል፡፡

፬.ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በባሕላዊ ሥርዐት እንዲታይ ሲወስን ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፭.ዐቃቤ ሕግ ጉዳዩ በባሕላዊ ሥርዐት እንዲታይ ውሳኔ ሲሰጥ እንደነገሩ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ እውቀት ካለው ባለሙያ፣ ባሕላዊ ሥርዐቱን ከሚያስፈፅሙ ሰዎች፣ ከተጎጂው ወይም ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፸፪ በባሕላዊ ሥርዐት እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ አቀራረብ**

፩. ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ፣በግል ተበዳይ ወይም በባሕላዊ ሥርዐት ሥልጣን ባለው ሰው፣አግባብ በሆነ የመንግስት አካል ወይም በዐቃቤ ሕግ አነሳሽነት ተከሳሹ ፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት በባሕላዊ መንገድ እንዲታይ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪. ፍርድቤቱ የዐቃቤሕግ እና የተከሳሽን ፈቃደኝነት አረጋግጦ ጉዳዩን ወደ ባህላዊ ሥርዐቱ ይመራዋል፡፡

**አንቀጽ ፻፸፫ በባሕላዊ ሥርዐት እና በመደበኛው ሥርዐት የሚታዩ ተያያዥ ወንጀሎች**

ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሽ ፈጽሟቸዋል የተባሉ ተያያዥ ወይም ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ በባሕላዊ መንገድ ቀሪዎቹ በመደበኛው ሥርዐት ሊታዩ የሚችሉ በሆነ ጊዜ ሁሉም ወንጀሎች በመደበኛው ሥርዐት እንዲታዩ ይደረጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፸፱  የውሳኔ አሰጣጥ</u>**

፩. የባህላዊ ሥርዐቱ ጉዳዩን  በሠላሳ ቀናት አጠናቆ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪.በባሕላዊ ሥርዐት መሠረት የተሰጠ ውሳኔ ክሱ በተመሠረተበት ፍርድቤት የሥራ ቋንቋ ሆኖ በዐቃቤ ሕግ ወይም በአማራጭ ቅጣት አፈጻጸም ቦርድ  በጽሑፍ ይቀርባል፡፡

፫. ፍርድቤት የቀረበው የባህላዊ ሥርዐት ውሳኔ ሕግን እና ሞራልን የማይቃረን ፣ሰብዓዊ ክብርን የማይነካ መሆኑን፣ የሂደቱን ዓላማ ያሳካ በማረጋገጥ ያጸድቃል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ፍርድቤቱ ያላፀደቀው ከሆነ የክስ ሂደቱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ተለዋጭ መፍትሔዎች</u>

**<u>አንቀጽ  ፻፹ ዓላማ</u>**

የወንጀል ጉዳይ  በተለዋጭ መፍትሄዎች እልባት እንዲያገኝ የሚደረግበት ዓላማ የወንጀል ድርጊቱን ፈፅመዋል የተባሉ ሰዎች ከባሕሪያቸውና ከዕድሜያቸው ጋር በሚስማማ ሁኔታ እንዲያዙ፣እንዲታከሙ ወይም ወንጀል ከመፈጸም ተገልለው እንዲቀመጡ በማድረግ የወንጀል ፍትህ ሂደቱን ፍትሐዊነትና ውጤታማነት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ  ፻፹፩  ተለዋጭ መፍትሔዎች ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው ሰዎች</u>**

ተለዋጭ መፍትሔዎች  በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሹ ፡-

፩. ክስ በሚሰማበት ጊዜ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ሕመምተኛ በመሆኑ የፍርድ ሂደቱን ለመከታተል የማይችል ከሆነ፣

፪. በዕድሜ የጃጀ ከሆነ፣

፫. የአልኮል፣ የመድሐኒት፣ወይም የእፅ ሱሰኛ ከሆነ፣ወይም

**፬.** ከአእምሮው ጤና መጓደል የተነሳ ወይም ሙያዊ ክህሎት በማነሱ ምክንያት ተደጋጋሚ ስህተት የሚሰራ ከሆን ፣

ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፹፪ ተለዋጭ መፍትሔዎች እና የመወሰን ስልጣን**

**፩.** በዚህ ክፍል በተደነገገው መሠረት በአንቀጽ ፻፹፩ በተመለከተው አኳኋን የሚገኝ ሰው ለፈጸመው የወንጀል ድርጊት የሚወሰድ ተለዋጭ የመፍትሔ ርምጃዎች እንደነገሩ ሁኔታ ፡-

**(ሀ)**ለተከሳሹ በራሱ ወይም በመንግሥት ወጪ የሚሰጥ ሕክምና ፣ የሙያ ስልጠና ፤የቀለም፣ የተሃድሶ ወይም የግብረ ገብ ትምህርት፤

**(ለ)** ማሕበራዊ አገልግሎት መስጠት፣

**(ሐ)** ለተወሰነ ጊዜ በተወሰነ ቦታ መቆየት፣

**(መ)** ምክርና ተግሳጽ ፣ ወይም

**(ሠ)** በሕግ የሚወሰነውን ሌላ አማራጭ መፍትሔን ፣

ሊያካትት ይችላል፡፡

**፪.** ክስ የተመሠረተበት ጉዳይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከቱ ተለዋጭ መፍትሄዎች መሠረት እልባት እንዲያገኝ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ጥያቄ ከቀረበ ወይም ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ከወሰነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በዚህ ክፍል በተመለከቱ ተለዋጭ መፍትሄዎች እልባት እንዲያገኝ ለሚመለከተው ተቋም ይመራል፡፡

**አንቀጽ ፻፹፫ የውሳኔው ይዘት**

**፩.** በዚህ ሕግ መሠረት ፍርድ ቤት ጉዳዩ በተለዋጭ የመፍትሔ ርምጃ እልባት እንዲያገኝ ውሳኔ ሲሰጥ መፍትሔው፡-

**(ሀ)** ተፈጻሚነቱ ስለሚጀምርበትና ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ፣ እና

**(ለ)** የአስፈጻሚውን ተቋም እና አፈጻጸሙ ክትትል ስለሚደረግበት ሁኔታ

ይወስናል፡፡

፪. ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሌሎች የመፍትሔ ርምጃ እልባት እንዲያገኝ ሲወስን አግባብነት ካላቸው አካላት አስተያየት መጠየቅ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፹፬ የተለዋጭ መፍትሔዎችፈጻሚ አካላት</u>**

፩. በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዕውቅና የተሰጣቸው አካላት ተለዋጭ መፍትሔዎችን ይፈጽማሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ዕውቅና የተሰጣቸው አካላት፡-

**(ሀ)** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚዘረጋውን ተለዋጭ መፍትሔዎች ተግባራዊ የማድረግ፤

**(ለ)**በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማንኛውንም ትእዛዝ የመፈጸም ወይም የማስፈጸም፤

**(ሐ)**የተከሳሹን አስፈላጊ መረጃ የመያዝና በዐቃቤ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ሲጠየቁ የማቅረብ፤

**(መ)**ለፍርድ ቤት ስለተጠርጣሪው ወይም ስለተከሳሹ ሁኔታ አስፈላጊውን ሪፖርት የማቅረብ፤

**(ሠ)** ሌሎች ተያያዥነትና አግባብነት ያላቸውን ተግባራት የማከናወን፤

ግዴታ አለባቸው፡፡

፫. በዚህ ሕግ የተመለከተው ተለዋጭ መፍትሔመፈጸሙ የሚረጋገጠው በበፍርድ ቤቱ ነው ፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፹፭ የተፈጸመ ተለዋጭ መፍትሔ የሚኖረው ውጤት</u>**

፩. በዚህ ሕግ መሠረት በተለዋጭ መፍትሄ እልባት እንዲያገኝ የተወሰነ ጉዳይ በውሳኔው መሠረት የተፈጸመ እንደሆነ ፍርድ ቤት መዝገቡን ይዘጋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በተዘጋ መዝገብ ላይ በማናቸውም ሁኔታ ክስ አይመሠረትም፤ ተከሳሹ በሌላ ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ቢባል ሪከርድ ሆኖ አይቀርብበትም፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፹፮ ያልተፈጸመ ወይም ውጤታማ ያልሆነ ተለዋጭ መፍትሔ ውጤት</u>**

፩. በፍርድ ቤት የተወሰነ ተለዋጭ መፍትሔ ሳይፈጸም ወይም ውጤታማ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ መፍትሄውን እንዲያስፈፅም የታዘዘው ተቋም ወይም አግባብነት ያለው አካልበሚያቀርበው አስተያየት መሠረት ፍርድ ቤት ተገቢውን ይወስናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍርድ ቤት፡-

**(ሀ)** ቀድሞ የተወሰነው የተለዋጭ መፍትሔ በድጋሚ ተፈጻሚ እንዲሆን፤ እንደአስፈላጊነቱም መፍትሄውን የሚያስፈጽመው ተቋም እንዲቀየር፣

**(ለ)** በሌላ የተለዋጭ መፍትሔ እንዲተካ፣ ወይም

**(ሐ)** ጉዳዩ በመደበኛ የክስ መሰማት ሂደት እንዲታይ

ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የወንጀል ጉዳይ በማንኛውም ሁኔታ ከሁለት ጊዜ በላይ በተለዋጭ መፍትሔ እንዲታይ አይደረግም፤ እንዲህ በሆነ ጊዜ ጉዳዩም በመደበኛ የክስ መስማት ሂደት ይታያል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፹፯ ይግባኝ</u>**

በተለዋጭ መፍትሔ እልባት ያገኘ ጉዳይ ይግባኝ አይባልበትም፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**

**<u>ክስ መመስረት</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>በዐቃቤሕግ የሚቀርብ ክስ</u>**

**<u>አንቀጽ ፻፹፰ መርህ</u>**

ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን መርምሮ ተጠርጣሪን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ክስ ይመሰርታል፤ክሱም በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ስልጣን ላለው ፍርድቤት ይቀርባል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፹፱ የክስ ማመልከቻ ይዘት</u>**

፩.ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል አውቆ መልስ ለመስጠትና ራሱን መከላከል እንዲችል እያንዳንዱ ክስ ወንጀሉንና የወንጀሉን ድርጊት ሁኔታ በዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡ በክሱ ውስጥ ስለ ወንጀሉና አፈፃፀሙ የሚጠቀሰው ዝርዝር ተከሳሹ ተላለፈ የተባለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ አነጋገር መከተል ይኖርበታል፡፡

፪.ማንኛውም የክስ ማመልከቻ፡-

**(ሀ)** ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ፣

**(ለ)** ክሱ የሚቀርብበት ፍርድ ቤት ስምና አድራሻ፣

**(ሐ)** የዐቃቤ ሕግ ስም፣ ማዕረግ፣ ፊርማ፣

**(መ)** የተከሳሽ ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜና አድራሻ፣

**(ሠ)** ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ በተቻለ ግልጽነት፣ እንደአግባብነቱ የተበዳይ ስም ወይም ወንጀሉ የተፈጸመበት ንብረት፣

**(ረ)** ወንጀሉ የተፈጸመበት ቀንና ቦታ በትክክል ያልታወቀ እንደሆነ ወንጀሉ ተፈጽሟል ተብሎ የሚገመትበት ጊዜና ቦታ፣

**(ሰ)** ተከሳሹ ወንጀሉን በመፈጸም ተላልፏል የተባለው ሕግ፣ አንቀጽ እና ወንጀሉን የሚያቋቁመው ፍሬ ነገር ፣

**(ሸ)** የማስረጃ ዝርዝር ከነማስረጃው፣

ይይዛል፡፡

**አንቀጽ ፻፺ ክስን ማጣመር**

**፩.** በወንጀል ሕግ አንቀጽ ፷ ፣ ከአንቀጽ ፷፪ እስከ ፷፯ በተመለከተው መሠረት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ በአንድ ማመልከቻ ክሶቹን አጣምሮ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፪.** የተፈፀሙት ወንጀሎች ተደራራቢ ሆነው የተለያዩ ክልሎች ወይም የክልልና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተቋማት ክስ የማቅረብ ስልጣን ባላቸው ጊዜ በከባዱ የወንጀል ጉዳይ ላይ ክስ የማቅረብ ሥልጣን ያለው የዐቃቤ ሕግ ተቋም ክሱን በማጣመር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

**፫.**ተያያዥነት ያላቸው የወንጀል ጉዳዮች ከተፈፀሙና በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ ሥልጣን የተለያዩ ክልሎች ወይም የክልሎችና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተቋማት በመሆኑ ሥልጣኑን ለመወሰን ባልተቻለ ጊዜ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ክስ የሚመሰርተውን የዐቃቤ ሕግ ተቋም ይወስናል፡፡

**፬.** ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ክሶችን አጣምሮ ሲያቀርብ እያንዳንዱን ክስ በተናጠል መግለጽ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፩ ክሶችን መነጣጠል**

ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከሳሽ ጠያቂነት የክሶቹ በአንድነት መሰማት የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል መሆኑን ከተረዳ ክሶቹ ተነጣጥለው እንዲሰሙ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፪ ተከሳሾችን አጣምሮ መክሰስ**

**፩.**ከአንድ በላይ የሆኑ ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ ፴፪ እስከ ፵ እና አንቀጽ ፷ እስከ ፷፯ በተደነገገው መሠረት ወንጀል ፈጽመው በተገኙ ጊዜ በአንድ ማመልከቻ ክስ ሊመሠረትባቸው ይችላል፡፡

፪. ከአንድ በላይ የሆኑ ተከሳሾች በአንድ የወንጀል ድርጊት የፈጸሙት ወንጀል የተለያየ ቢሆንም እንደነገሩ ሁኔታ በአንድ ክስ በጋራ ሊከሰሱ ይችላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፺፫ አማራጭ ክስ</u>**

፩.የተፈጸመው የወንጀል ዐይነት የሚያጠራጥር እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ አማራጭ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪.ለተፈጸመ ድርጊት የሚቀርበው ማስረጃ ከብዙ ወንጀሎች ውስጥ የትኛውን እንደሚያረጋግጥ ለማወቅ አጠራጣሪ እንደሆነ ተከሳሹ ለመፈጸሙ ይበልጥ የተረጋገጠ በሚመስለው ወንጀል እና በአማራጭ በማስረጃው ሊረጋገጥ ይችላሉ በሚባል ወንጀል ሁሉ ሊከሰስ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፺፬ ቅጣትን የሚያከብዱ ወንጀሎች ክስ አቀራረብ</u>**

፩.ተከሳሹ ከዚህ በፊት በፈፀማቸዉ ወንጀሎች ምክንያት ቅጣትን በሚያከብድ ወንጀል የሚከሰሰዉ ቅጣቱ በማይከብድበት ወንጀል ሆኖ ክሱ የሚታየዉ ቅጣትን የሚያከብድ ወንጀሎችን ለማየት ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡

፪. ተከሳሹ ቅጣቱ በማይከብድበት ወንጀል ጥፍተኛ ሆኖ ከተገኘ ዐቃቤሕግ የተከሳሹን የቀድሞ ጥፋተኝነት ያስረዳል፡፡ ፍርድቤቱም በወንጀል ሕግ መሰረት የጥፋተኝነቱን ዉሳኔ ለውጦ ቅጣት ይወስናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፺፭ በሙከራ፣ በአነሳሽነት ፣በአባሪነት ወይም በመዘጋጀት ጥፋተኛ መሆን</u>**

፩. ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በሙከራ ወይም በመዘጋጀት ክስ ባይቀርብበትም በሙከራ ወይም የሚያስቀጣ እንደሆነ በመዘጋጀት ጥፋተኛ ሊባል ይችላል፡፡

፪. ማንኛውም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከሶ፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ክስ ባይቀርብበትም በወንጀሉ አነሳሽነት ወይም በአባሪነት ጥፋተኛ ሊባል ይቻላል፡፡

፫.የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን በአማራጭ ሊያስከስሰው ይችል በነበረ ወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት በቂ እንደሆነና ይህም ወንጀል ክስ ከቀረበበት ወንጀል ያነሰ ቅጣት የሚያስቀጣ እንደሆነ በዚህ ወንጀል ክስ ያልቀረበበት ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በዚሁ ወንጀል ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገው ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፩ ክስ ስለሚመሠረትበት የጊዜ ገደብ**

፩. ዐቃቤ ሕግ እንደወንጀሉ ክብደትና ውስብስብነት የምርመራ መዝገቡ በደረሰው በሀያ ቀናት ውስጥ ክስ ይመሠርታል፡፡

፪. ተጠርጣሪው ዋስትና ተከልክሎ በጊዜ ቀጠሮ ላይ ያለ ከሆነ ዐቃቤ ሕግ ክስ እስኪመሠርት ድረስ በማረፊያ ቤት ይቆያል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፪ በጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አለመመሥረት**

፩. ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፻፺፩** በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ የማይመሰርት እንደሆነ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ የጊዜ ቀጠሮውን ባየው ፍርድ ቤት በመቅረብ ምክንያቱን ያስረዳል፡፡

፪.ፍርድቤቱ ዐቃቤሕግ በቀጠሮው ቀን ቀርቦ ክስ ያልመሰረተበትን ምክንያት በቂ ሆኖ ካገኘው ክስ ለመመስረት እስከ አስር የስራ ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫.ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በበቂ ካለስረዳ ወይም በንዑስ አንቀፅ ፪ መሠረት በአስር ቀን ውስጥ ክስ ካልመሠረተ ፍርድ ቤቱ እና ተጠርጣሪው ዋስትና ተከልክሎ የቆየ ከሆነ ተጠርጣሪው በዋስትና ወይም ያለዋስትና ይለቀዋል፡፡

፬.ተጠርጣሪው ዋስትና ይውረድልኝ፣ እግድ ይነሳልኝ፣ እሸግ ይነሳልኝ፣ኤግዚቢት ይለቀቅልኝ እና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክስ ያልተመሠረተበትን ምክንያትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፺፫ ክስ ማቋረጥ እና ማንሳት**

፩. ዐቃቤ ሕግ ክርክሩ ከሚቀጥል ክሱ ቢነሳ የሚያሳካው የሕዝብ ጥቅም አለ ብሎ ሲያምን ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ያቀረበውን ክስ ለፍርድ ቤት በማሳወቅ ማንሳት ይችላል፡፡

፪.ዐቃቤ ሕግ መከላከያ ምስክር ከመሠማቱ በፊት ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለፍርድ ቤት ምክንያቱን በማሳወቅ ማቋረጥ ይችላል፡፡

፫.ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ክስ ካነሳ ወይም ካቋረጠ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በመዝጋት ክሱ ለጊዜው እንዲቋረጥ እና ተከሳሹ ማረፊያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ በክሱ ምክንያት የተያዘ ኤግዚቢት ወይም የታገደ ንብረት ካለ እንዲለቀቅ ወይም ዕግዱ እንዲነሳ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተነሳ ክስ ድጋሚ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡

## ክፍል ሁለት
## የግል ክስ የሚቀርብበት ሥነ ሥርዐት

### አንቀጽ ፻፺፱ የግል ክስ አቀራረብ

፩. የግል ክስ ማቅረብ የሚቻለው፡-

**(ሀ)** በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ከሆኑ፣

**(ለ)** ተጠርጣውን ጥፋተኛ ሊያስብል የሚያስችል በቂ ማስረጃ ሲኖር፣ እና

**(ሐ)** ዐቃቤ ሕግ የግል ክስ እንዲቀርብ ሲፈቅድ፣

ነው፡፡

፪. ዐቃቤ ሕግ የግል ተበዳይ የግል ክስ እንዲያቀርብ ከፈቀደ ውሳኔውን የግል ክስ ለማቅረብ መብት ላለው ሰው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ክስ እንዲያቀርብ ፍቃድ ያገኘው የግል ተበዳይ ከዐቃቤ ሕግ ፍቃድ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አሥራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይኖርበታል፤ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡

፬.በዚህ ሕግ የዐቃቤ ሕግ ክርክርና ክስ በሚመለከት የተደነገገው እንደአግባብነቱ የግል ከሳሽንም ይመለከታል፡፡

### አንቀጽ ፪፻ የግል ክስ ለማቅረብ መብት ያለው ሰው

፩. የግል ክስ ማቅረብ የሚችለው የግል ተበዳዩ ወይም ጠበቃው ይሆናል፡፡የግል ተበዳዩ ክስ ፈቃድ ለማግኘት ሳያመለክት ወይም ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃድ አግኝቶ ክስ ሳያቀርብ የሞተ እንደሆነ ክሱ በትዳር ጓደኛው፣ በተወላጆቹ ወይምበወላጆቹና፣  እንደ ቅደም ተከተላቸው ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ዐቃቤ ሕግ የግል ክስ እንዲመሠረት ሲፈቅድ በወንጀል ሕጉና በዚህ ሕግ ዓላማ መሠረት እየተከናወኑ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ዐቃቤ ሕግ ክትትል ሲያደርግ የወንጀል ሕጉንና የዚህ ሕግ ዓላማ በሚፃረር አኳኋን እየተፈጸመ መሆኑን ከተረዳ  ክሱ እንዲቋረጥ ለፍርድ ቤት ያመለክታል ወይም ክሱን በራሱ ይከታተላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፩  የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል ስለማዘዝ</u>**

የክስ ማመልከቻው የቀረበው የግል ከሳሹ በዐቃቤ ሕግ በተፈቀደለት መሠረት ካልሆነ ክሱን በተፈቀደለት መሠረት እንዲያሻሽል ፍርድ ቤቱ  ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፪  ተከራካሪዎችን ስለመጥራት</u>**

የክስ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ  በተደነገገው መሠረት ለግል ከሳሹ መጥሪያ ይሰጣል፤ የግል ከሳሹም መጥሪያውን ለተከሳሹ ያደርሳል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፫   ተከራካሪዎችን ስለማስታረቅ</u>**

፩. ፍርድ ቤቱ የክስ ማመልከቻውን ለተከሳሽ ከማንበቡ በፊት ጉዳዩ በዕርቅ እንዲቋጭ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡

፪.በዕርቅ  የሚቋጭ የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ በዚህ ሕግ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፬  ኪሣራ ላይ ስለሚደረግ መተማመኛ</u>**

በተከራካሪዎቹ መካከል ዕርቅ ለማድረግ ባልተቻለ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የግል ከሳሹ የኪሳራ ዋስትና እንዲሰጥ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን የዋስትናውን የገንዘብ ልክ ይወስናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፭   ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል መፈፀሙ በታወቀ ጊዜ የሚፈጸም ሥነ ሥርዐት</u>**

፩. ዐቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከቀረበው የግል ክስ የተለየ በግል ተበዳይ አቤቱታ ወይም በወንጀል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል መፈጸሙን በተረዳ ጊዜ የግል ከሳሹን ተክቶ በጉዳዩ እስከሚገባ ድረስ የግል ክሱ ለጊዜው እንዲቋረጥ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከቀረበው የግል ክስ የተለየ እና በወንጀል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል መፈጸሙን በተረዳ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ የግል ከሳሹን ተክቶ በጉዳዩ እንዲገባ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት ዐቃቤ ሕግ የግል ከሳሽን ተክቶ በገባ ጊዜ የተቋረጠው ክስ እንዲቀጥል፣ እንደ ሁኔታው ክሱ እንዲሻሻል ወይም አዲስ ክስ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለተቋረጠ ክስ የኪሳራ ወጪ አይከፈልም፡፡

## ክፍል ሦስት
## የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ የሚቀርብበት ሥርዐት

### አንቀጽ ፪፻፺ በዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ

፩. ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ ለወንጀል ክሱ ምክንያት የሆነው ድርጊት በሕዝብና መንግሥት ወይም በፍርድ ቤት ለመከራከር አቅም የሌላቸው ሰዎች መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ የፍትሐብሔር ክሱን ከወንጀሉ ክስ ጋር አጣምሮ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ጉዳቱ የደረሰው በሕፃናት ወይም በሴቶች ላይ በተፈጸመ ጾታዊ ጥቃት እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ በተጎጂው ወይም በወኪሉ ፍቃድ የፍትሐብሔር ክሱን ከወንጀል ክሱ ጋር አጣምሮ ያቀርባል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ መሠረት በሚመሠረት የፍትሐብሔር ክስ የመንግሥት አካል ተጣምሮ የሚቀርብ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ የፍትሐብሔር ክስ አያቀርብም፡፡

፬.በዚህ ሕግ መሠረት ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ላይ አግባብነት ያለው ሕግና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ ተፈጻሚነት አለው፡፡

### አንቀጽ ፪፻፺፩ ተጎጂ ስለሚያቀርበው የፍትሐብሔር ክስ

፩. የዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ማመልከቻ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ እና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ክሱ ጋር ተጣምሮ እንዲታይለት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የቀረበው ክስ ከወንጀል ክሱ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ የፈቀደ እንደሆነ፣ የፍትሐብሔር ክስ የሚያቀርበው ሰው የዐቃቤ ሕግንና የተከሳሹን የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር ቅጅ ማግኘት እና ተጨማሪ ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ በተከራካሪዎች ጥያቄ ወይም በራሱ አነሳሽነት የፍትሐብሔሩ ክስ ተጣምሮ እንዲታይ ማድረጉ ለትክክለኛና ለተፋጠነ ፍትሕ አሰጣጥ አመቺ ሆኖ ካላገኘው ተነጥሎ እንዲታይ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

፬.የወንጀል ክሱ የቀረበው በግል ከሳሽነት እንደሆነ እና የግል ከሳሽ የፍትሐብሔር ክስ ተጣምሮ እንዲታይ ያቀረበ እንደሆነ የቀረበውን የወንጀል እና የፍትሐብሔር ክስ ለማስረዳት የሚያቀርባቸውን የማስረጃ ዝርዝር ለያይቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፫ የዳኝነትና ሌሎች ወጪዎች ክፍያ**

ከወንጀል ክስና ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምረው የሚቀርቡ የፍትሐብሔር ክስ የዳኝነት ወጪዎችን በተመለከተ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፬፻፳፫** ጀምሮ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ ፪፻፬ ክስ አቅራቢው ስለሚኖረው መብት**

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፪ መሠረት የፍትሐብሔር ክስ ያቀረበ ተጎጂ በወንጀል ክሱ የክስ መሰማት ሂደት እና በሚቀርበው ማስረጃ ሁሉ ለፍትሐብሔር ክሱ ዓላማ እንደ መደበኛ ተከራካሪ ወገን የመሳተፍ መብት አለው፡፡

**አንቀጽ ፪፻፭ የተከሳሽ ጥፋተኛ አለመሆን ወይም የመለቀቅ ውጤት**

ተከሳሹ የወንጀል ክሱ የተቋረጠለት ወይም በነጻ የተሰናበተ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የፍትሐብሔሩን ክስ ሰምቶ ለመወሠን ወይም ሥልጣን ባለው ሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

# አምስተኛ መጽሐፍ

## መደበኛ የክርክር ሥነ-ሥርዐት፣ ማስረጃ እና ፍርድ

## ምዕራፍ አንድ

## መደበኛ የክርክር ሥነ-ሥርዐት

### ክፍል አንድ

### መጥራት

**አንቀጽ ፪፻፲፩ ጠቅላላ**

**፩.** በዚህ ሕግ መሠረት በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በምስክርነት፣ በአስተርጓሚነት፣ በእጁ የሚገኘውን ማንኛውንም ማስረጃ ለፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ወይም ለሌላ ማንኛውም ተግባር ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚፈለግ ማንኛውም ሰው የፍርድ ቤት መጥሪያ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም፣

**(ሀ)** የመያዣ ትእዛዝ የወጣበት፣

**(ለ)** በችሎት የተገኘ፣ ወይም

**(ሐ)** ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በችሎት የተነገረው ሰው፣

መጥሪያ ማድረስ ሳያስፈልግ ይቀርባል።

**አንቀጽ ፪፻፲፪ የመጥሪያ ይዘት**

**፩.** መጥሪያ የተጠሪውን ሙሉ ስም፣ የተጠራበትን ምክንያት፣ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት፣ ችሎት እና የሚገኝበትን አድራሻ፣ የሚቀርብበትን ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመተ ምኅረት እና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን የሚይዝ ይሆናል፡፡

**፪.**ለተከሳሹ የሚደርሰው መጥሪያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለጸውን ክስና ማስረጃውን ይጨምራል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፲፫ መጥሪያ የማዘጋጀትና የማድረስ ኃላፊነት**

**፩.** ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ለሚጠራ ሰው የሚላክ መጥሪያ የሚዘጋጀው በፍርድ ቤት ነው፡፡

**፪.** የክስ ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽ መጥሪያ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

፫. መጥሪያ የሚዘጋጀው በጽሑፍ ሆኖ ቀጠሮ ከተያዘበት ቀን አሥር ቀናት አስቀድሞ ለተጠሪው በአካል መድረስ ይኖርበታል፡፡ ተከሳሹ እድሜው ከአሥራ አምስት ዓመት በታች ወይም በፍርድ የተከለከለ እንደሆነ ለሞግዚቱ ወይም ለአሳዳሪው፣ የሕግ ሰውነት ያለው እንደሆነ ለዋናው ወይም ለቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ወይም ወኪል እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል፡፡

፬. ለተከሳሽ እና ለዐቃቤ ሕግ ምስክሮች መጥሪያ የማድረስ ኃላፊነት የፖሊስ ነው። ለተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች መጥሪያ በተከሳሽ ወይም በፖሊስ ሊደርስ ይችላል ፡፡

**አንቀጽ ፪፻፲መጥሪያ የመቀበል ግዴታ**

መጥሪያ የተላከለት ማንኛውም ሰው መጥሪያውን የመቀበልና የደረሰው ለመሆኑ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ መጥሪያውን ለመቀበል ወይም ማረጋገጫ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ መጥሪያውን እንዲያደርስ የታዘዘው ሰው ይህንኑ ለፍርድ ቤት ያረጋግጣል።

**አንቀጽ ፪፻፲፩ የመጥሪያ አለመድረስ**

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ቀጠሮ በሰጠበት ቀን መጥሪያው ያልደረሰ ወይም በአግባቡ ያልደረሰ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ የተጠራው ሰው የሚቀርብበትን ቀን በመወሰን መጥሪያ በድጋሚ እንዲደርሰው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፲፪ የተከሳሽ ወይም በፍርድቤት የተጠራ ሰው አለመቅረብ**

፩. ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ተለዋጭ ቀጠሮ ሊሰጥ፣ በፖሊስ ተይዞ እንዲቀርብ ሊያዝ ወይም ተከሳሹ ወጣት ጥፋት አጥፊ ሲሆን መዝገቡን ሊዘጋ ይችላል፡፡

፪. ምስክር ወይም ሰነድ አቅራቢ ወይም ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የታዘዘ ማንኛውም ሰው መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣል፤ እንደአስፈላጊነቱም ተጠሪው ታስሮ እንዲቀርብ ሊያደርግ ወይም የቀረበውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. መጥሪያ የደረሰው ሰው በቀጠሮው ቀን ያልቀረበ ወይም መቅረብ የነበረበት ሰው ባለመቅረቡ ጉዳዩን ማየት የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፪ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ የሚታይበትን ቀጣይ የቀጠሮ ቀን ይወስናል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፲፯ ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ክስ**

**፩.**ሠባት ዓመትና ከዛ በላይ የሚያስቀጣ የወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ ይችላል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ክርክሩ ተከሳሹ በሌለበት የሚታየው ተከሳሹ መጥሪያ ደርሶት በቀጠሮው ቀን ሳይቀርብ በመቅረቱ ፍርድ ቤቱ ታስሮ እንዲቀርብ የሰጠው ትእዛዝ መፈጸም አለመቻሉ ሲረጋገጥና በሀገሪቱ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ፣ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን በሚነገር ማስታወቂያ ተሰራጭቶ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ነው፡፡ የተሰራጨው ማስታወቂያም የቀጠሮውን ቀን የያዘ ሆኖ በቀጠሮው ቀን ባይቀርብ ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ የሚታይ መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

**፫.**ተከሳሹ ክርክሩ በሌለበት በመታየት ላይ እያለ ተይዞ ወይም በራሱ ፈቃድ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ በደረሰበት ደረጃ ገብቶ ክርክሩን ይቀጥላል፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ሳይቀርብ የቀረው በበቂ ምክንያት ከሆነ፣ አስቀድሞ የተደረገው ክርክር የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ፍትሕን የሚያጓድል ሲሆን ፍርድ ቤቱ ቀድሞ የተደረገው ክርክር ቀሪ ሆኖ የክርክሩ ሂደት እንደገና እንዲከናዎን ያዛል፡፡

**፬.**ጉዳዩ ከአንድ በላይ ተከሳሾች ያሉበት ሆኖ የጉዳዩ እንደገና መታየት የሌሎች ተከሳሾችን የመከላከል መብት የሚነካ ወይም የተፋጠነ ፍትሕ ለመስጠት የሚያዳግት እንደሆነ ተነጥሎ ሊታይ ይችላል።

**አንቀጽ ፪፻፲፰ ተከሳሹ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ**

ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ ፍርድ፡-

**፩**. ተከሳሹ እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰው መሆኑን፣ ወይም

**፪.** መጥሪያው ደርሶት ከዐቅም በላይ በሆነ ምክንያት መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደሆነ የተሰጠው ፍርድ ቀሪ ተደርጎ ክርክሩ እንደገና ይታያል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፲፱ የክሱ እንደገና መታየት**

**፩**.ፍርድ እንደገና እንዲታይ የቀረበው አቤቱታ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ የተሰጠው ፍርድ መፈጸም አይጀምርም፡፡

**፪.**በክርክሩ ወቅት አቤቱታውን የሚያየው ፍርድ ቤት አመልካቹ በዋስትና እንዲቆይ ለመፍቀድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፳ ማመልከቻ የሚቀርብበት ጊዜ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፲፯** መሠረት ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚቀርብ ማመልከቻ ምክንያት የሆነው ነገር በቀረ ወይም በተወገደ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ ፩፻፳፩ ተከሳሽ በሌለበት የማይታይ ክስ**

በፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን የሚመለከት እንደሆን ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት አይታይም።

**ክፍል ሁለት**

**የችሎት አመራር**

**አንቀጽ ፩፻፳፪ ግልጽ ችሎት**

፩. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጉዳዩ በዝግ ችሎት እንዲታይ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ይኸው ጥያቄ በዝግ ችሎት ታይቶ ይወሰናል፡፡

፪. ጉዳዩ በዝግ ችሎት የሚታይ እንደሆነም በችሎቱ የግድ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት በችሎት ከተደረገ ክርክር ያገኙትን መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ማስጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡

፫. በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ ወይም በችሎቱ በተለየ ካልታዘዘ በስተቀር ለሕዝብ ግልጽ የሆነ ችሎት ለመገናኛ ብዙኃንም ግልጽ ይሆናል፡፡

፬. በግልጽ በሕግ ካልተከለከለ በስተቀር ማንኛውም በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ለሕዝብ ግልጽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፳፫ የችሎት ሥርዐት ማስጠበቅ**

የችሎቱ ዳኛ፡-

፩. የፍርድ ሒደቱ ሁሉም ወገን በእኩልነት የሚስተናገድበት፣ የሕግ የበላይነት የሚረጋገጥበት፣ ክርክርን በምቾትና በነፃነት ለማቅረብ በሚያስችል አግባብ እንዲከናወን ተገቢውን ሥርዐት ማስከበር ይኖርበታል፡፡

፪. ሥርዐቱን በሚተላለፍ ላይ በሕግ መሠረት ተገቢውን ይወስናል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፳፬ የውሳኔ አሰጣጥ**

**፩.** ማንኛውም ፍርድ፣ ውሳኔ፤ ብይን ወይም ትእዛዝ በዳኞች ሙሉ ድምጽ ይሰጣል፡፡

**፪.** ሙሉ ድምጽ ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ አብላጫው ድምጽ ፍርድ፤ ውሳኔ፤ ብይን ወይም ትእዛዝ የፍርድ ቤቱ ፍርድ፤ ውሳኔ፤ ብይን ወይም ትእዛዝ ይሆናል።

**፫.** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ **፪** መሠረት በውሳው ያልተስማማ ዳኛ የልዩነት ሀሳቡን ያሰፍራል፡፡

**፬.** በተሠጠው ፍርድ፤ ውሳኔ፤ ብይን ወይም ትእዛዝ የተስማማ ዳኛ በምክንያቱ ላይ የተለየ ከሆነ ይህንኑ በፅሑፍ ማስፈር ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ቅድመ ክስ መስማት ተግባራት

### አንቀጽ ፪፻፷፫ የክስ ማመልከቻ ማቅረብ

የክስ መሰማት ሂደት የሚጀመረው ዐቃቤ ሕግ ያዘጋጀውን የክስ ማመልከቻ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ነው።

### አንቀጽ ፪፻፷፬ የክስ መዝገብ መክፈት

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፷፫** መሠረት ክስ ሲቀርብ የፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘሩ ምስክሮች ስምና አድራሻ በአግባቡ መገለፁን እና ክሱና ማስረጃው በበቂ ቅጂ መዘጋጀቱን አረጋግጦ፡-

**(ሀ)** መዝገብ ይከፍታል፣

**(ለ)** ለመዝገቡ እንደ ቅደም ተከተሉ ቁጥር ይሰጣል፣

**(ሐ)** በመዝገቡ ላይ የተሟላ መረጃ በመመዝገብ መረጃዎቹ በመረጃ ቋት እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

**፪.**ተሟልቶ የተከፈተውን መዝገብም ጉዳዩን ለሚመለከተው ችሎት ያቀርባል።

### አንቀጽ ፪፻፷፭ የክስ ሕጋዊ ብቃት ማረጋገጥ

**፩.** የክስ መዝገብ የቀረበለት ችሎት፡-

**(ሀ)** ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑን፣

**(ለ)** በክሱ የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊትና የተጠቀሰው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የሚጣጣም መሆኑን፣

**(ሐ)** በክሱ የተዘረዘረው ፍሬ ነገር የወንጀል ተግባር መሆኑን፣

**(መ)** ክሱ በይርጋ ያልታገደ መሆኑን፣

**(ሠ)** ክሱ በማስረጃ መግለጫና በማስረጃ ተሟልቶ የቀረበ መሆኑን፣ እና

**(ረ)** ሌሎች ከክስ አመሠራረት ጋር የተያያዙ የሕግ ጉዳዮችን ፤

በማረጋገጥ ክሱ የሚሰማበትን ቀን ይወስናል፡፡

**፪.** ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ወይም ክስ የቀረበበት ተግባር ወንጀል አለመሆኑን ወይም ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን ካረጋገጠ ይህንኑ ገልጾ መዝገቡን ይዘጋል።

**፫.** ፍርድ ቤቱ የተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ እና የወንጀሉ ዝርዝር የማይጣጣም ወይም ክሱ ግልጽነት የጎደለው መሆኑን ሲያረጋግጥ እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ወይም አጭር ቀጠሮ በመስጠት ክሱ ተስተካክሎ ወይም ተሻሽሎ እንዲቀርብ ያዛል፡፡

**፬.** በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ክሱ ተስተካክሎ ወይም ተሻሽሎ ካልቀረበ ክሱ በተሻሻለ ጊዜ መንቀሳቀሱ እንደተጠበቀ ሆኖ መዝገቡ ይቋረጣል።

**፭.** ፍርድቤቱ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የዐቃቤ ሕግ አስተያየት ሊቀበል ይችላል።

**<u>አንቀጽ ፪፻፹፫ ክሱ የሚሰማበትን ቀን ስለመወሰን</u>**

**፩.** ፍርድ ቤቱ የክሱን ሕጋዊነት እንዳረጋገጠ ክሱ የሚሰማበትን ቀን ወስኖ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሽ እና እንደአስፈላጊነቱ የከሳሽ ምስክሮች እንዲቀርቡ ሬጅስትራር መጥሪያ እንዲደርሳቸው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪.** ተከሳሹ በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት የሚገኝ ከሆነ ምርመራውን ያጣራው ፖሊስ ወይም ማረሚያ ቤቱ ተከሳሹን እንዲያቀርበው ትእዛዝ ይሰጣል።

**<u>አንቀጽ ፪፻፹፱ የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት</u>**

**፩.** የክስ ማመልከቻው ቀርቦለት ሕጋዊነቱን ያረጋገጠ ዳኛ፡-

**(ሀ)** የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት ማከናወን አስፈላጊ መሆኑን፣

**(ለ)** የቅድመ ክስ ተግባራት የሚከናወኑባቸውን ጉዳዮች እንዲሁም፣

**(ሐ)** ተግባራቱ በዳኛው ወይም በሬጅስትራር አማካኝነት የሚከናወን መሆኑን

ይወስናል።

፪. የቅደመ ክስ መስማት ተግባራት በቃል ሊካሄድ ይችላል፡፡

፫. የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት እንዲከናወን ከተወሰነ የቅድመ ክሱ የሚሰማበትን ቀንና ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ መጥሪያ ለዐቃቤ ሕግ እና ለተከሳሽ ይላካል።

፬. ክሱና የማስረጃ ዝርዝር ከቀጠሮው ቀን ቢያንስ አሥር ቀን አስቀድሞ ለተከሳሹ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ተከሳሹም በቅድመ ክስ መስማት ተግባራት በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ያለውን አስተያየት ይዞ መቅረብ እንዲችል ዝርዝሩ በትእዛዙ ላይ ይገለጽለታል።

**<u>አንቀጽ ፪፻፴ በቅድመ ክስ መስማት የሚከናወኑ ተግባራት</u>**

፩. በቅድመ ክስ መስማት ተግባር ውስጥ፡-

**(ሀ)**የፍርድ ሂደት መርሃግብርን በዝርዝር የማስቀመጥ፣

**(ለ)**ጉዳዩ በልዩ ሁኔታ በዝግ ችሎት መታየት ያለበት ስለመሆኑ የመለየት፣

**(ሐ)**የተከላካይ ጠበቃ፣ አስተርጓሚ፣ ለፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ባለሙያዎችን አስቀድሞ እንዲሟሉና እንዲታወቁ የማድረግ፣

ተግባር ይከናወናል፡፡

፪. የቅድመ ክስ መሰማት ተግባራት በሬጅስትራር የተከናወነ እንደሆነ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ ሬጅስትራሩ ስለተከናወኑ ተግባራት ዝርዝርና የተሟላ መግለጫ ለዳኛው በጽሑፍ ያቀርባል፡፡

፫. የቅድመ ክስ መሰማት ተግባር በዳኛው የሚከናወን እንደሆነ በተለዩት ጉዳዮች ላይ እንደነገሩ ሁኔታ ወድያውኑ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

ክስ መስማት**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

**<u>አንቀጽ ፪፻፴፩ የክስ መስማት አጀማመር</u>**

**፩.** ችሎቱ ክሱን በንባብ ከማሰማቱ በፊት ፡-

**(ሀ)** የተከሳሹን ማንነት ለማረጋገጥ ሙሉ ስሙን፣ ዕድሜውን፣ ፆታውን፣ የመኖሪያ አድራሻውን፣ ሥራውን፣ የትምህርት ደረጃውን፣ የቤተሰቡን ሁኔታ እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን መረጃዎች ጠይቆ ወይም የተረዳውን ይመዘግባል፡፡

**(ለ)**የጠበቃ እና አስተርጓሚ መሟላቱን ያረጋግጣል።

**(ሐ)**የፍርድ ቤቱን የስራ ቋንቋ ለማይረዳ ተከሳሽ አስተርጓሚ ይመድባል፡፡

**(መ)** በአቅም ማጣት ምክንያት በጠበቃ ያልተወከለ መሆኑንና ያለጠበቃ ቢከራከር ፍትሕ ይዛባል ብሎ ያመነ እንደሆነ በመንግሥት ወጪ ተከላካይ ጠበቃ እንዲመደብለት ያዛል፡፡

**፪.**ችሎቱ የዝግጅት ተግባራትን እንዳከናወነ እያንዳንዱን ክስ በንባብ ለተከሳሹ በማሰማት የተረዳው መሆኑን ያረጋግጣል።

**፫**. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተደነገገው በጊዜ ቀጠሮ፣ በቀዳሚ ምርመራ፣ ወይም ፍርድ ቤት በሚቀርብበት ማናቸውም ጊዜ ሁሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**፬.** ተከሳሹ የኃይል ድርጊት የሚፈጽም፤ አደገኛ ወይም ለማምለጥ የሚሞክር ለመሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ምክንያት ቀርቦ በችሎቱ ካልተፈቀደ በስተቀር በሠንሰለት ታስሮ ችሎት አይቀርብም፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፴፪ የመደበኛ ክርክር ሥነ-ሥርዐት ተፈፃሚነት</u>**

በዚህ ሕግ በልዩ ሥነ-ሥርዐት ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሌሎች የክርክር ሥነ-ሥርዐቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ቀጠሮና የቀጠሮ ውጤት

### አንቀጽ ፪፻፴፫ የፍርድ ሂደት ተከታታይነት

፩. በዚህ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የወንጀል ክርክር ከዚህ በታች በተመለከተው አግባብ በመደበኛ የክርክር ሥርዐት በተቀላጠፈ ሁኔታ ታይቶ ይወሰናል።

፪.ማንኛውም ጉዳይ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተከታታይ የሚታይ ሆኖ በተቀጠረበት ዕለት እልባት ያገኛል፡፡

### አንቀጽ ፪፻፴፬ የመደበኛ ክርክር ሥርዐት የጊዜ ገደብ

፩. በመደበኛ የክስ መስማት ሥርዐት የሚመራ ቀላል የወንጀል ጉዳይ በሦስት ወር፣ መካከለኛ የወንጀል ጉዳይ በስድስት ወርና ከባድ የወንጀል ጉዳይ በአስራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ በቂና አሳማኝ ምክንያት ሲያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገውን ጊዜ ግማሽ ያህል ሊያራዝመው ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፪፻፴፭ የቀጠሮ ምክንያት

፩. በማንኛውም የወንጀል ክርክር ሥርዐት ላይ ቀጠሮ የተያዘለት የወንጀል ጉዳይ በቀጠሮው ቀን የተቀጠረበት ምክንያት መከናወን ይኖርበታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት፣በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ መሆኑን ሲገነዘብ በሚከተሉት ምክንያቶች ለሚከናወነው ተግባር በቂ ነው ብሎ ያመነበትን ቀጠሮ ለመስጠት ይችላል፡፡

**(ሀ)** በቀጠሮ ዕለት ዐቃቤ ሕጉ ፣ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በበቂ ምክንያት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ፣

**(ለ)** ተከሳሹ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በቀጠሮው ቀን ችሎት መከታተል አይችልም ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ፣

**(ሐ)** በጉዳዩ ላይ የክስ መቃወሚያ የተነሳ እንደሆነና ወዲያውኑ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ፣

**(መ)** ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ክሱ የደረሰው ወይም ጠበቃ ያገኘው ከነገሩ መሰማት ጥቂት ቀናት በፊት በመሆኑ ለመዘጋጀት በቂ ጊዜ ያላገኘ እንደሆነ፣

**(ሠ)** የዐቃቤ ሕግ ወይም የተከሳሽ ምስክሮች ተሟልተው ባለመቅረባቸው የቀሩትን ምስክሮች ለመስማት ቀጠሮ የሚያስፈልግ እንደሆነ፣

**(ረ)** በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፺፫** መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ወይም ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ቀድሞ ይቀርባል ብሎ ያልገመተው ወይም ሊገምት የማይችለው አዲስ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ፣

**(ሰ)** የክስ ማመልከቻ በተለወጠ፣ በተጨመረ ወይም አዲስ ክስ በቀረበ ጊዜ ተከሳሽ ማስተካከያውን ወይም አዲሱን ክስ በተመለከተ አስተያየት ለመስጠት ወይም ጉዳዩን መስማት ለመቀጠል ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው ሲሆን፣

**(ሸ)** በሌላ ፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይ መጀመሪያ ውሳኔ ካላገኘ በቀር በቀረበው ክስ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል ሲሆን፣

**(ቀ)** የተከሳሹን አእምሮ ትክክለኛነት አስመልክቶ የልዩ አዋቂ አስተያየት መቀበል የሚያስፈልግ ሲሆን፣

**(በ)** ሌሎች ማስረጃዎችን ከሚመለከተው አካል ለመቀበል ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ወይም

**(ተ)** የክሱን መስማት ለመቀጠል የማያስችል ሌላ አስገዳጅ ምክንያት ሲኖር፣

፫. ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን ወይም የተከሳሽን ማስረጃ በሚሰማበት ጊዜ በተከታታይ መስማት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ለዳኞች፣ ለተከራካሪ ወገኖች እና ለምስክሮች ዕረፍት ወይም ጉዳዩን በአዳሪ በቀጣዩ የሥራ ቀን ለመስማት ወይም ሌላ አስገዳጅ ነገር ሲከሰት ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ለመስጠት ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፴፺ የክስ መስማት ሂደትን በሕመም ምክንያት መከታተል አለመቻል**

፩. ማንኛውም የተከሰሰ ሰው የክስ መስማት ሂደቱና ክርክሩን ለመከታተል ብቁ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በተከሳሹ የአካል ወይም የአዕምሮ ሕመም ምክንያት፡-

**(ሀ)** የእምነት ክህደት ቃል መስጠት ካልቻለ፣

**(ለ)** የቀረበበትን ክስና ውጤት መረዳት ካልቻለ ወይም በዚህ ረገድ ጠበቃውን ማገዝ ካልቻለ፣

**(ሐ)** የቀረበበትን ክስ መከላከል ካልቻለ ፣ወይም

**(መ)** በሌላ መሰል ምክንያት የመስማት ሂደቱን መከታተል ካልቻለ፣

በራሱ ወይም በጠበቃው አመልካችነት የክስ መስማት ሂደቱ ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፫. የተከሳሽ ጥያቄ ተገቢ በመሰለው ጊዜ ፍርድ ቤቱ የተከሳሹ ጤንነት በባለሙያ እንዲመረመርና የምርመራ ውጤቱ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፬. ፍርድ ቤቱ የተከሳሽ የጤና ችግር ጊዜያዊ ነው ብሎ ካመነ አጭር ቀጠሮ በመስጠት የክስ መስማቱን ሂደት ይቀጥላል፡፡ ፍርድ ቤቱ በተሰጠው ቀጠሮ የተከሳሹ ጤንነት ካልተሻሻለ በባለሙያ እንዲመረመርና የምርመራ ውጤቱ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭. የቀረበው የባለሙያ አስተያየት ተከሳሽ ጉዳዩን ለመከታተል ብቁ አለመሆኑን ካመላከተ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ አስተያየት ይቀበላል፡፡ የዐቃቤ ሕግንና የባለሙያውን አስተያየት መርምሮና አስፈላጊም ሆኖ ካገኘው ተገቢውን ክርክር አድርጎ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፮. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን ያስተላለፈ እንደሆነ ተከሳሹ በራሱ ወይም በሕብረተሰቡ ላይ አደጋ የሚፈጥር እንደሆነ አግባብነት ባለው ተቋም ሥር እንዲቆይ፣ወይም በዋስ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፯. ተከሳሹ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ወይም ከአንድ ዓመት በኋላ መሻሻል ካላሳየ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ መሠረት ተለዋጭ መፍትሄ እንዲያገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የክስ መቃወሚያ እና የተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የክስ መቃወሚያ**

**አንቀጽ ፪፻፴፪ ክስን መቃወም**

፩.ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ክሱ ተነቦለት መቃወሚያ ያለው እንደሆነ ይጠይቀዋል፡፡

፪.ተከሳሽ የሚከተሉትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ መቃወሚያ በቃል ወይም በፅሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

(ሀ) ፍርድ ቤቱ ክሱን ለመስማት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው እንደሆነ፣

(ለ) በቀረበበት ክስ ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ፣

(ሐ) ጉዳዩ በዚህ ሕግ መሠረት በአማራጭ መንገዶች ታይቶ ውሳኔ ወይም መፍትሄ ያገኘ እንደሆነ፣

**(መ)** ክስ የቀረበበት ወንጀል በይርጋ የታገደ ፣ በይቅርታ ወይም በምህረት የታለፈ እንደሆነ ፣

**(ሠ)** ተከሳሹ ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለው ከሆነ ወይም ክስ ለመመስረት ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልግ እንደሆነ፣

**(ረ)** ተከሳሹ የቀረበበት ክስ በሌላ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት እየታየ እንደሆነ፣

**(ሰ)** በሌላ ፍርድ ቤት ወይም በሌላ ችሎት የቀረበ ክስ ሳይጠናቀቅ በዚህ የወንጀል ክስ ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል እንደሆነ፣

**(ሸ)** የቀረበበት ክስ ሁለትና ከዚያ በላይ ሆኖ የተወሰኑት ክሶች በአንድ ክስ የሚጠቃለሉ እንደሆነ፣ ወይም

**(ቀ)** የቀረበበት ክስ ወንጀል ካልሆነ ወይም የተሻረ ሕግን መሠረት በማድረግ የቀረበ ከሆነ፣

**(በ)** ክስ አለአግባብ ተጣምሮ ወይም ተነጥሎ የቀረበ እንደሆነ፣

**(ተ)** የወንጀሉ ዝርዝር ተግባሩን ወንጀል ከሚያደርገው ድንጋጌ ጋር የማይጣጣም እንደሆነ፣

**(ቸ)** የክሱ ይዘት አስፈላጊ ዝርዝሮችን አሟልቶ ያልያዘ እንደሆነ፣

**(ኀ)** በግል ከሳሽ የቀረበው ክስ ዐቃቤ ሕግ ለግል ከሳሽ በፈቀደው መሠረት የቀረበ ካልሆነ፣ ወይም

**(ነ)**እድሜ እና ሌሎች መሰል ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ ለማየት የማያስችሉ ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ ከሆነ፡፡

**፫.** ፍርድ ቤቱ በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ወደ ሥረ- ነገሩ እንዳይገባ የሚከለክለው የሕግ ጉዳይ ወይም ፍሬ ነገር መኖሩን ከተረዳ በራሱ አስተያየት አግባብነት ያለው ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

**፬.** ተከሳሹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት መቃወሚያውን ወዲያውኑ ያላቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱን የሚጸና ፍርድ ለመስጠት የሚያግደው ካልሆነ በቀር በሌላ ጊዜ መቃወሚያ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፴፫ በመቃወሚያ ላይ መወሰን</u>**

**፩.** ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ያቀረበው የክስ መቃወሚያ ላይ የዐቃቤ ሕግን አስተያየት ተቀብሎወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ በቀረበው ክስ መቃወሚያ ወዲያውኑ ውሳኔ መስጠት ያልተቻለ መሆኑን ወይም ጉዳዩን ማጣራት ወይም በተጨማሪ ማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ካመነበት አጭር ቀጠሮ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፴፱ ክስ ተነጣጥሎ የሚታይበት ሁኔታ</u>**

ፍርድ ቤቱ መቃወሚያ ባይቀርብበትም በአንድ ክስ በርካታ ሰዎች በተከሰሱበት ክስ ተከሳሾቹን በአንድነት አጣምሮ ጉዳያቸውን መስማት የመከላከል መብታቸውን የሚያጣብብ ፣ የተቀላጠፈ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል መሆኑን ከተረዳ ጉዳያቸው ተነጣጥሎ እንዲታይ ማዘዝ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፵ ክስን መለወጥ፣መጨመር ወይም ማሻሻል</u>**

፩.ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ በራሱ አስተያየት ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት የቀረበው ክስ፡-

(ሀ) መሠረታዊ ስህተት የታየበት፣ ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ ፤ ማካተት የሚገባውን ፍሬ ነገር ሳያካትት ወይም በዝርዝር ሳያስቀምጥ የቀረ ፣ የተከሳሽን የመከላከል መብት የሚያጣብብ ወይም ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል መሆኑን የተረዳው እንደሆነ፣ ወይም

(ለ) የክስ ማመልከቻው በዚህ ሕግ መሠረት አለመዘጋጀቱን፣በክስ ማመልከቻው የተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር የማይጣጣም መሆኑን ወይም ተከሳሹ የቀረበበት ክስ ተነጥሎ ካልታየ የመከላከል መብቱን እንደሚያጣብበው የተረዳ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ ወይም እንዲሻሻል ወይም ተጨማሪ ወይም አዲስ ክስ እንዲቀርብ ቀጠሮ በመያዝ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በተሰጠ ጊዜ ውስጥ ዐቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ ወይም ለውጦ ወይም አዲስ ክስ ካላቀረበ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋል፡፡ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት ያለ እንደሆነ ይለቀቃል፤ በዚህ ክስ ምክንያት የተያዘ ወይም የታገደ ንብረት ካለ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ ወይም ለውጦ ወይም አዲስ ክስ ለማቅረብ ያልቻለበትን በቂ ምክንያት አቅርቦ ተቀባይነት ካገኘ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከሰጠው ጊዜ ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. ክሱ በተለወጠ፣ በተጨመረ ወይም በተሻሻለ ጊዜ ለተከሳሹ በፅሑፍ እንዲደርሰው፣ እንዲነበብለትና እንዲረዳው አስፈላጊ ሲሆን መቃወሚያ እንዲያቀርብበት ወይም ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
## <u>የተከሳሽ እምነት ክህደት ቃል</u>

**<u>አንቀጽ ፪፻፵፩ ተከሳሹን የእምነት ወይም ክህደት ቃል መቀበል</u>**

<u>፩</u>.ፍርድ ቤቱ፣ ተከሳሹ መቃወሚያ ያላቀረበ ወይም መቃወሚያው ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የእምነት ክህደት ቃሉን ተቀብሎ ይመዘግባል፡፡

<u>፪</u>.ክሱ ከአንድ በላይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ ክስ እምነት ክህደት ቃሉን ተቀብሎ ይመዘግባል፡፡

<u>፫</u>.የተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃል ተከሳሹ በሚሰጠው ቃል አነጋገር ዓይነት ይመዘግባል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፵፪ የተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃል</u>**

<u>፩</u>.ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸሙና ጥፋተኛ ለመሆኑ በሙሉ ያመነና ስለ ወንጀሉ አፈጻጸም ፍርድ ቤቱ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ዝርዝርና አሳማኝ ምላሽ የሰጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ሲል ከመዘገበ በኋላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

<u>፪</u>.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ <u>፩</u> በተደነገገው መሠረት ተከሳሽ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል መፈፀሙን ያመነ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ካመነበት ዐቃቤ ሕግ ማስረጃውን እንዲያሰማ ለማዘዝና እንደሁኔታው ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ለማዘዝ ይችላል፡፡

<u>፫</u>.ተከሳሹ ወንጀል መፈፀሙን በግልፅ የካደ፣ ለእምነት ክህደት ጥያቄው መልስ ያልሰጠ ወይም ወንጀሉን መፈጸሙን አምኖ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል በማለት ይመዘግባል፤በክሱ ላይ ወይም በተካደው ጉዳይ ላይ ማስረጃ ይሠማል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፵፫ የተከሳሹን የእምነት ክህደት ቃል ስለማሻሻል</u>**

<u>፩</u>.ተከሳሹ ከፍርድ በፊት ባለ ማናቸውም የክስ ሂደት ላይ የሰጠውን የእምነት ቃል በመለወጥ ጥፋተኛ አይደለሁም ሊል ይችላል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የእምነት ቃሉን ከለወጠ የተለወጠውን ቃል ይመዘግባል፤ በተከሳሹ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ውድቅ ያደርጋል፤ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሚሰሙበትን ቀን ይወስናል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**

**<u>ማስረጃና ብይን</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>የክስ መግለጫና የክርክር መክፈቻ ንግግር</u>**

**<u>አንቀጽ ፪፻፵፬ የክርክር መክፈቻ ንግግር</u>**

፩.ተከሳሽ ወንጀሉን ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃውን ከማሰማቱ በፊት የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡

፪.የክርክር መክፈቻ ንግግር ዓላማም ዐቃቤ ሕግ ክርክሩን ስለሚያቀርብበት አግባብ፣ የማስረጃ ዓይነት፣ ቅደም ተከተልና ስለሚያስረዱት ጉዳይ መግለጽ ነው፡፡ ይህንንም ዐቃቤሕግ በትክክልና ያለ አድልዎ ይገልፃል፡፡

፫.የክርክር መክፈቻውም ምስክሮች የሚመሰክሩበትን ጉዳይ እና ይህንኑ ለማስረዳት የሚጠሩ ምስክሮች ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ዜግነት፣ ሥራና አድራሻ፣ ክሱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማስረዳት የቀረበ የኤግዚቢት ዝርዝር፣ ማስረጃና ስለሚያስረዳው ጉዳይ አጭር መግለጫ ይይዛል፡፡

፬.ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ የክርክር መክፈቻውን ካበቃ በኋላ በዚህ ሕግ መሠረት መንግስትን ወይም የወንጀል ተጎጂዎችን በመወከል ያቀረበውን የፍትሐብሔር ክስ የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡

፭. ዐቃቤ ሕግ የክስ መክፈቻ ንግግሩን ካበቃ በኋላ በፍትሐብሔር የግል ከሳሽ አጣምሮ ያቀረበውን የፍትሐብሔር ክስ የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በማስረጃ መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸውና የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

### <u>በማስረጃ የሚረጋገጡ ፍሬ ነገሮች</u>

**<u>አንቀጽ ፪፻፷፫ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ፍሬ ነገር</u>**

**፩.** ዐቃቤ ሕግ በፍርድ ቤቱ በጭብጥ የተያዘን ፍሬ ነገር እና በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር አግባብነትና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ያስረዳል፡፡

**፪.** ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው በአንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ላይ አንድና ከዚያ በላይ ጭብጦች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

**፫.** በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር ወይም አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር ዐቃቤ ሕግ አረጋግጧል የሚባለው የነገሩን ሁነት፣ መከሰት ወይም አለመከሰት በዚህ ሕግ በተደነገገው የማስረዳት መጠን ማረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፷፬ አግባብነት ያለው ማስረጃ</u>**

**፩.** በጭብጥ የተያዘውን ወይም አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር የሚያስረዳ ወይም የሚያስተባብል የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር፡-

**(ሀ)** የተፈጥሮ ወይም የሁነት፣ የጊዜና ቦታ ጥብቅ ትስስር ያለው  በመሆኑ በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር አካል መሆኑን፣

**(ለ)** ለመፈጸም ምክንያት ወይም የታቀደ ዓላማ የሆነ መኖሩን፣

**(ሐ)** ለመፈጸም ወይም ለመከሰት ኢጋጣሚን የፈጠረ መሆኑን፣

**(መ)** ለመፈጸም የተደረገ ዝግጅት ወይም በተከታይ የተከናወነ ተግባር ፍሬ ነገር መኖሩን፣

**(ሠ)** ከመከሰቱ በፊትና ከተከሰተ በኋላ የተከሳሹ፣ የግል ተበዳይ ወይም በአካባቢው የነበሩ የሌሎች ሰዎች ተግባር፣ ክስተት መኖሩን፣

**(ረ)** የሁነት ውጤት ቁርኝት መኖሩን፣

**(ሰ)** ከመከሰቱ በፊትና ከተከሰተ በኋላ የነበረ የአካባቢው ሁኔታ ፣

**(ሸ)** የፍሬ ነገሩ ሁነት በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ተመሳሳይነት ሁነት ያለው መሆኑን፣

**(ቀ)** የተከሳሽ ወይም የተበዳይ መልካም ወይም መልካም ያልሆነ ጠባይ፣

**(በ)** በሌላ በማናቸውም መልኩ በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መከሰት ወይም አለመከሰት ፣

የሚያሳይ ማስረጃ አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## በማስረጃ መረጋገጥ የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

### አንቀጽ ፪፻፷፪ ጠቅላላ

በተከሳሹ በግልጽ የታመነ ፍሬ ነገር ፣ ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ወይም የሕግ ግምት የሚወስድበት ፍሬ ነገር ለማስረዳት ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም ፡፡

### አንቀጽ ፪፻፷፫ የታመነ ፍሬ ነገር

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፵፪** ተከሳሹ የተከሰሰበት የወንጀል ጉዳይ በሚታይበት የፍርድ ሂደት በግልጽ ያመነው ፍሬ ነገር ወይም ወንጀሉን መፈጸሙን አምኖ የሰጠው የእምነት ቃል በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ መረጋገጥ አያስፈልገውም።

**፪.** ተከሳሹ ክሱን ሲከላከል ማስረጃ አቅርቦ ካላስተባበለው በስተቀር ተከሳሹ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፷** በሌላ ፍርድ ቤት ያመነው ፍሬ ነገር ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንደተረጋገጠ ይቆጠራል፡፡

**፫.** ተከሳሹ በምርመራ ወቅት ለፖሊስ የሰጠው ቃል እንደታመነ ፍሬ ነገር አይቆጠርም፡፡

### አንቀጽ ፪፻፷፬ ፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወስድበት ፍሬ ነገር

**፩.** በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል የሕግ ጋዜጣ ታትመው የወጡ ሕጎች፣አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው የታተሙ ውሳኔዎች እንደተረጋገጡ ይቆጠራሉ፡፡

፪. ፍርድ ቤቶች በዚህ ሕግ መሠረት ግንዛቤ የሚወስዱበት በጠቅላላ እውቀት እውነትነቱ የታወቀ ፍሬ ነገር ወይም በቀላሉ በሚገኝ አስተማማኝ ሰነድ ሊረጋገጥ የሚችል ፍሬነገር የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንደተረጋገጠ ይቆጠራል ፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ወይም ፪ ላይ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮችን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ያቀርባል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ወይም ፪ የተመለከተው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ በጭብጥ የተያዘው ወይም አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር በፍርድ ቤቱ ግንዛቤ እንዲወሰድበት ጥያቄ ሊያቀርብ ወይም ተከሳሹ በቀረበው ጥያቄ ላይ መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፶ የሕግ ግምት</u>**

፩.በጭብጥ ከተያዙ ወይም አግባብነት ካላቸው ፍሬ ነገሮች ላይ የተወሰኑ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተረጋገጠ ተያያዥ የሆነ የሌላን ፍሬ ነገር ሁነት ወይም መከሰት በተመለከተ የሕግ ግምት ለመውሰድ እንደሚቻል በፍሬ ሕጉ የተደነገገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ መቅረብ ሳያስፈልግ ሌላኛው ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ ለመቁጠር ወይም ማስረጃ እንዲቀርብበት ለማዘዝ ይችላል፡፡

፪.በጭብጥ ከተያዙ ወይም አግባብነት ካላቸው ፍሬ ነገሮች ላይ የተወሰኑ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተረጋገጡ ተያያዥ የሆነን የሌላን ፍሬ ነገር ሁነት ወይም መከሰት አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ የሕግ ግምት መውሰድ እንዳለበት በፍሬ ሕጉ የተደነገገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮቹ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ሲረጋገጡ ሌላው ተያያዥ ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ ይቆጠራል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሕግ ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ባረጋገጠው መሰረታዊው ፍሬ ነገርና የሕግ ግምት በሚወሰድበት ፍሬ ነገር መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የማስረጃ ተቀባይነት</u>**

**<u>አንቀጽ ፪፻፶፩ ተቀባይነት ስላለው ማስረጃ</u>**

በሕገ መንግስቱ ፣በዚህ ሕግ ወይም በሌሎች ሕጎች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር አግባብነት ያለው ማስረጃ ሁሉ ተቀባይነት አለው፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፶፪ ተቀባይነት የሌለው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ</u>**

**፩.** የሚከተሉት የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተቀባይነት የላቸውም፡-

**(ሀ)**በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል እና ሌላ ማስረጃ፣

**(ለ)**ልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴን የሚመለከት የዚህን ሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የተገኘ ማስረጃ፤

**(ሐ)** በአማራጭ መንገዶች አፈፃፀም ወቅት የተገኘ ማስረጃ ወይም የተሰጠ የእምነት ቃል፣

**(መ)** ተከሳሽ ተጎጂን ለመርዳት ወይም አንድን ጉድለት ለማሻሻል ያደረገውተግባር ወይም የወሰደው የእርምት ርምጃ፣

**(ሠ)** በዐቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክሱን ክዶ የሚከራከረውን ተከሳሽና ክዶ የሚከራከርበትን በጭብጥ የተያዘ ወይም ለጭብጡ አግባብነት ያለው ፍሬ ነገርን በተመለከተ በአንድ ዓይነት ወንጀል በተከሰሰ ሌላ ተከሳሽ የተሰጠ የእምነት ቃል፣

**(ረ)** ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ በፍርድ ቤቱ ታዞ ያልተረጋገጠ ማስረጃ፤

**፪.** በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ማስረጃው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ምስክርነቱ በሚሰጥበት ጊዜ የምስክርነት ቃሉን ለማስተባበል ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፶፫ የተከሳሽን ወይም የተጎጂን ጠባይ የሚያስረዳ ማስረጃ</u>**

**፩.** የተከሳሹን መልካም ያልሆነ ጠባይ በማስረዳት የተከሰሰበትን የወንጀል ተግባር ማስረዳት አይቻልም፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ የተከሳሹ ጠባይ መልካም መሆኑን ለማሳየትየቀረበ ማስረጃ ወይም ክርክር ለማስተባበል የተከሳሹን መልካም ያልሆነ ጠባይ ማስረዳት ይችላል።

**፫.** ተከሳሽ የተጎጅውን መልካም ያልሆነ ጠባይ ለማሳየት ማስረጃ ወይም ጥያቄ ካቀረበ ዐቃቤሕግ የተጎጅውን መልካም ጠባይ ወይም የተከሳሹን መልካም ያልሆነ ጠባይ ማስረዳት ይችላል፡፡

**፬.** ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ምስክር እውነተኛነቱን ማናቸውንም ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፵፬ የቀድሞ ጥፋቶችና መሰል ተግባራት**

የተከሳሹ የቀድሞ ጥፋቶችና ሌሎች መጥፎ ተግባራት አሁን የተከሰሰበትን የወንጀል ተግባር ለማስረዳት ተቀባይነት የላቸውም። ሆኖም የተከሳሹን ማንነት፣የቀድሞ እቅድ፣ አጋጣሚ፣ ዝግጅት፣ ሀሳብ ወይም የነገሩ ሁነት ድንገተኛ አለመሆኑን ለማስረዳት ተቀባይነት አለው፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የማስረጃ ዓይነቶች**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የሰው ማስረጃ**

**አንቀጽ ፩፻፵፫ የመመስከር ብቃትና ግዴታ**

፩. በሕግ ገደብ ያልተጣለበት ማንኛውም ምስክር ለመመስከር ብቃት እንዳለው ይገመታል።

፪. በምስክርነት የተጠራ ማንኛውም ምስክር ፍርድ ቤት ቀርቦ የመመስከር ወይም የማይመሰክርበትን ምክንያት ማስረዳት ይኖርበታል።

፫.ምስክሩ ልዩ አዋቂ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የምስክሩን የትምህርት ደረጃና ሥራ፣ የሥራ ልምድ እንዲሁም ሌሎች የብቃት ማረጋገጫዎችን ከመረመረ በኋላ በጭብጥ በተያዘው ወይም አግባብ ባለው ፍሬ ነገር ላይ ለመመስከር ብቃት ያለው መሆን አለመሆኑን ይወስናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ በዕድሜ ለጋነት ወይም መጃጀት፣ በአካል ወይም በአዕምሮ ሕመም ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት የሚመሰከረውን ፍሬ ነገር ወይም የሚቀርብለትን ጥያቄ ሊረዳው የማይችል መሆኑን ሲረዳ የምስክርነት ቃሉን እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫.ፍርድ ቤት ምስክር እንዳይሆን ክልከላ ያደረገበት ልዩ አዋቂ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ በምስክርነት ሊቀርብ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ ፄየሃጌ ለመመስከር ያለመገደድ ልዩ መብት</u>**

**፩.**የተከሳሹ የኃይማኖት አባት፣ ጠበቃ ወይም ሐኪም በሚሰጠው የኃይማኖት ወይም የሙያ አገልግሎት አጋጣሚ ባገኘው መረጃ ላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ በተከሳሹ ላይ እንዲመሰክር አይገደድም።

**፪.**አንድ ሰው በትዳር ዘመኑ ከትዳር አጋሩ ባገኘው መረጃ ላይ እና ከወላጅ ወይም ከልጁ ባገኘው መረጃ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ ለመመስከር አይችልም። ሆኖም አንደኛው የትዳር አጋር ወይም ወላጅ ወይም ልጅ በሌላኛው ላይ ወንጀሉን በፈፀመ ጊዜ ይህ ልዩ መብት ተፈፃሚ አይሆንም።

**<u>አንቀጽ ፄየሃጊ በምስክርነት አለመቅረብ</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ **ፕጊ** መሠረት በልዩ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የተሳተፈ ሰው በተሳተፈበት ጉዳይ ላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**፪.**ዳኛ ወይም ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ በሰጠበት የወንጀል ጉዳይ ላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ በምስክርነት ሊቀርብ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ ፄየሃጟ የመንግሥት ምስጢርን ስለመጠበቅ</u>**

**፩.**የመረጃው ምስጢርነት በሕግ በተደነገገ ጉዳይ ላይ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ምስክር ሆኖ አይመሰክርም ወይም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማናቸውንም ሰነድ እንዲሰጥ አይገደድም።

**፪.** ፍርድ ቤቱ የመረጃው ሚስጢርነት በሕግ ባልተደነገገ ጊዜና የመረጃው መገለጥ አለመገለጥ አከራካሪ በሆነ ጊዜ የአገርን ደኅንነት ፣ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ መሆን አለመሆኑን በዝግ ችሎት ያያል፡፡

**<u>አንቀጽ ፄየሃፀ በሌላ ፍርድ ቤት የተሰጠ የምስክርነት ቃል ስለሚቀርብበት ሁኔታ</u>**

**፩.** በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል የሠጠ ሰው የሞተ እንደሆነ፣ የአእምሮ ጉድለት ካገኘው፣ ምስክሩን ማግኘት ያልተቻል እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት ፍርድ ቤት መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ የሰጠው የምስክርነት ቃል ተነቦ በማስረጃነት ይያዛል፡፡

**፪.** ምስክርነት የተሰጠው ተከሳሹ ተከራካሪ ወገን በነበረበት በሌላ ፍርድ ቤት ሆኖ ተከሳሹ መስቀልኛ ጥያቄ የማቅረብ እድል የነበረው እንደሆነ የምስክርነቱ ቃል ተነቦ ጉዳዩን በሚሰማው ፍርድ ቤት በማስረጃነት መቅረብ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳ በምርመራ ላይ የተሰጠ ቃል በማስረጃነት መቅረብ</u>**

**፩.** በምርመራ ጊዜ ለፖሊስ የተሰጠ የምስክርነት ቃል በፍርድ ቤት በማስረጃነት አይቀርብም፡፡

**፪.**የዐቃቤ ሕግ ምስክር በፍርድ ቤት ቀርቦ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በፖሊስ ምርመራ ጊዜ ከተሰጠ የምስክርነት ቃል ጋር የሚጣረስ እንደሆነ፣ የምስክሩን ቃል ለማስተባበል ዐቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ የፖሊስን የምርመራ መዝገብ ሊመለከተው ይችላል፡፡

**፫.** ፍርድ ቤቱም የዚህ ቃል ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፩ የምስክሮች ብዛትና አቀራረብ ቅደም ተከተል መወሰን</u>**

**፩.**ዐቃቤ ሕግ አንድን ፍሬ ነገር በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ምስክሮች ማስረዳት ይችላል።

**፪.** ዐቃቤ ሕግ በጭብጥ የተያዘውን ወይም አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት ይጠቅመኛል ብሎ ባመነበት ቅደም ተከተል ምስክሮቹን ያቀርባል።

**፫.** አንድ ፍሬ ነገር በጭብጥ ለተያዘው ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖረው በመጀመሪያ ሌላ ፍሬ ነገር ሲረጋገጥ በሚሆንበት ጊዜ በቀዳሚው ፍሬ ነገር ላይ ምስክሮች ከመመስከራቸው በፊት በኋለኛው ፍሬ ነገር ላይ እንዲመሰክሩ ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፪ ቃለ- መኀላ መፈጸም ወይም ማረጋገጫ መስጠት</u>**

**፩.** የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ ፍርድ ቤት የቀረበ ማንኛውም ሰው የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት እንደኃይማኖቱ፣ እምነቱ ወይም ልማዱ መሠረት ቃለ-መኃላ ይፈፅማል ወይም እውነቱን ለመናገር ማረጋገጫ ይሰጣል።

**፪.**በዕድሜ ማነስ ወይም በሌላ ምክንያት የቃለ-መኃላውን ወይም የማረጋገጫውን ውጤት ለመገንዘብ የማይችሉ በምስክርነት የተጠሩ ሰዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ቃለ-መኃላ ለመፈጸም ወይም እውነቱን ለመመስከር ማረጋገጫ ለመስጠት አይገደዱም፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፫ የምስክርነት ቃል መቀበል</u>**

የዐቃቤ ሕግ ምስክር በችሎት ላይ የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ፍርድ ቤቱ፡-

**፩.** የምስክሩን ሙሉ ስም፣ የመኖሪያ አድራሻ፣ ዕድሜና ሥራ፣ አስፈላጊ ሲሆን ዜግነት በመጠየቅ ማንነቱን ያረጋግጣል፡፡

**፪.**ከተከሳሽ፣ ከተበዳይ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው ሌላ ሰው ጋር ያለውን ፀብ፣ ዝምድና፣ ጓደኝነት፣ የተለየ ቅርበት ወይም በምስክርነት ቃሉ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ነገሮችን ጠይቆ ይረዳል፡፡

**፫.**የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ሀሰተኛ እንደሆነ በወንጀል እንደሚያስጠይቀውይነግረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፳፱ ማስታወሻ፣ ሰነድ ወይም መሣሪያን ስለመጠቀም</u>**

**፩.**የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሚመሰክረው በቀጥታ ስለሚያውቀው ፍሬ ነገር ነው፡፡ የምስክርነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ በማስታወሻነት የሚያገለግል ሰነድ ወይም መሣሪያ መጠቀም አይችልም፡፡

**፪.**የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ምስክሩ ፡-

**(ሀ)** ልዩ አዋቂ ምስክር ሲሆን፣

**(ለ)** የሚያውቀውን ነገር ለማስታወስ ከተቸገረ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያገኘን አንድን ሰነድ ወይም ኤግዚቢት እየተመለከተ፣ ወይም

**(ሐ)** ሰነድ ሳይዝ ወይም በመሣሪያ ሳይታገዝ የተሟላ ምስክርነት ለመስጠት የማይችል ወይም የሚቸገር ወይም የሚመሰክርበት ጉዳይ ባሕርይ የሚያስገድድ መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ አስፈላጊውን ማስታወሻ ፣ሰነድ ፣መሣሪያ በመጠቀም፣

እንዲመሰክር ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

**፫.**ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) ምስክሩ ማስታወሻ ሰነድ ወይም መሣሪያ እንዲጠቀም የፈቀደ እንደሆነ አስፈላጊ የሆነውን የሰነዱን ክፍል ወይም መሣሪያ ግልባጭ ለተቃራኒ ወገን መስጠት ወይም ማሳየት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፳፲ ለምስክር የሚቀርብ ጥያቄ አግባብነት</u>**

**፩.** በመሰማት ላይ ላለ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሚቀርብ ጥያቄ አግባብነት፣ተቀባይነት ወይም ሌላ በሕግ የተመለከተ ምክንያትን በመጥቀስ ተከሳሽ ተቃውሞ ሊያነሳበት ይችላል፡፡ ምስክሩ የቀረበለትን ጥያቄ ከመመለሱ በፊት የጠያቂውን ወገን አስተያየት ሰምቶ ፍርድ ቤቱ ብይን ይሰጣል፡፡ ሆኖም ምስክሩ ጥያቄውን መልሶ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ ተቃውሞውን ከተቀበለው ጥያቄውንና መልሱን ከመዝገብ እንዲሰረዝ ያዛል፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ በክርክር ሂደት ለምስክሩ የቀረበው ጥያቄ አግባብነት፣ ተቀባይነት ወይም ሌላ በሕግ በተመለከተ ምክንያት አግባብነት የለውም ብሎ ካመነ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ተቃውሞ ባይቀርብም ምስክሩ መልስ ከመስጠቱ በፊት ምክንያቱን በመግለጽ ጥያቄው እንዲስተካከል ወይም እንዳይቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፰፫ ለምስክር የሚቀርብ ዋና ጥያቄ</u>**

፩. ዐቃቤ ሕጉ ለጠራው ምስክር ዋና ጥያቄ ያቀርባል፡፡ ምስክሩም በጭብጥ ስለተያዘው ወይም አግባብነት ስላለው ፍሬ ነገር በቀጥታ የሚያውቀውን እንዲመሰክር ይጠየቃል፡፡

፪. በዋና ጥያቄ ጊዜ ምስክሩ ስለሚመሰክርበት ፍሬ ነገር መሪ ጥያቄ መጠየቅ የተከለከለ ነው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም ምስክሩ፡-

**(ሀ)** አስጠቂ ምስክር እንደሆነ፤

**(ለ)** ስለሚመሰክረው ነገር የዘነጋ እንደሆነና የፍሬ ነገሩን ጫፍ ለማስያዝ፤ ወይም

**(ሐ)** ምስክሩ ሕፃን ፣ የጃጀ፣ በአእምሮው ልል የሆነ፣ በፍርሃት የተናወጠ መንፈስ የሚታይበት ወይም መሰል ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ እርዳታ የሚያስፈልገው እንደሆነ፤

ዐቃቤ ሕጉ ፍርድ ቤቱን አስፈቅዶ መሪ ጥያቄ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

፬. መሪ ጥያቄ ማለት ጠያቂው እንዲመለስለት የሚፈልገውን መልስ የሚያመላክት ጥያቄ ማለት ነው፡፡

፭. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም '**አስጠቂ ምስክር**' ማለት ምስክሩ ከዐቃቤ ሕጉ የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ በበቂ ፍላጎት የማይመሰክር እንደሆነ ወይም የፀብና የጠላትነት መንፈስ ያሳየ እንደሆነ በተለይም በቅንነት ማነስ ምስክሩ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል አስቀድሞ በመርማሪ ወይም በሌላ ውሳኔ ሰጪ አካል ፊት ከሰጠው የምስክርነት ቃል ጋር የማይጣጣም ምስክርነት የሚሰጥ ምስክር ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፰፬ መስቀልኛ ጥያቄ</u>**

፩.የዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ እንዳበቃ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ምስክሩን መስቀልኛ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡ የመስቀልኛ ጥያቄ ዓላማም በዋና ጥያቄ በተሰጠው ምስክርነት ውስጥ ያለውን ስህተት የሆነውን፣ የሚቃረነውን፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነውን ወይም ተዓማኒነት የሌለውን ምስክርነት ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽና ለማሳየት ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳካት እስከቻለ ድረስ ምስክሩ በዋና ጥያቄ ባልተነሳ ፍሬ ነገርም ላይ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ምስክሩ ልዩ አዋቂ እንደሆነ በጭብጥ ለተያዘው ወይም አግባብነት ስላለው ፍሬ ነገር ለመመስከር ያለውን ብቃት በተመለከተ ጥያቄ ሊቀርብለት ይችላል፡፡

፫.ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በመስቀልኛ ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፬.የተከሳሽ ወይም የጠበቃው መስቀልኛ ጥያቄ አለመጠየቅ በዋና ጥያቄ በዐቃቤ ሕግ ምስክር የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር እውነተኛነት እንዳመነ አይቆጠርም፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፰፫ የማስተባበያ ጥያቄ የተከለከለ መሆን</u>**

፩. የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተዓማኒነት ወይም ባሕሪ አስመልክቶ በራሱ በምስክሩ የተሰጠን መልስ ለማስተባበል ሌላ ጥያቄ ማቅረብ አይፈቀድም፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ በምስክሩ የተሰጠው መልስ ግልጽ የሆነ ፍሬ ነገርን በመካድ የተፈጸመ ሐሰተኛ መሆኑን ከተረዳ የተሰጠው መልስ ስህተት መሆኑን ለማስረዳት ተጨማሪ ጥያቄ እንዲቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፰፱ ድጋሚ ጥያቄ</u>**

፩. የተከሳሹ ወይም የጠበቃው መስቀልኛ ጥያቄ እንዳበቃ ዐቃቤ ሕጉ ምስክሩን ድጋሚ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡

፪. የድጋሚ ጥያቄ ዓላማ በመስቀልኛ ጥያቄ ስህተት የመሰለውን፣ የሚቃረን፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነ የሚመስልን ምስክርነት በርግጥም ስህተት፣ የሚቃረን፣ የሚያጠራጥር ወይም ተዓማኒ አለመሆኑን ወይም የምስክሩ ቃል እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡

፫. ተከሳሹ ወይም ጠበቃው መስቀልኛ ጥያቄ ካልጠየቀ ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ መጠየቅ አይችልም፡፡ በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ ጥያቄ የሚቀርብባቸው ፍሬ ነገሮች በመስቀልኛ ጥያቄ የተነሱ ፍሬ ነገሮች ብቻ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፺ የፍርድ ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ</u>**

ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ያመነውን የማጣሪያ ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፺፩ በፍርድ ቤቱ ስለሚጠራ ምስክር</u>**

፩.ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ሲያምን ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በዐቃቤ ሕግ ያልተቆጠረ ምስክር ቀርቦ እንዲሰማ ለማዘዝ ይችላል፡፡

**፪**.ለተጠራው ምስክር ፍርድ ቤቱ አግባብ የመሰለውን ጥያቄ በጭብጥ በተያዘው ወይም አግባብነት ባለው ፍሬ ነገር ላይ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፫**.የፍርድ ቤቱ ጥያቄ እንዳበቃ ለዐቃቤ ሕግ ወይም ለተከሳሽ ወይም ለተከሳሽ ጠበቃ ጥያቄ እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜም ሌላኛውም ወገን ድጋሚ ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል፡፡

**፬**.ፍርድ ቤቱ ግልጽ ያልሆነ ነገር ለማጥራት ወይም ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ሲረዳ አስቀድሞ የምስክርነት ቃሉን የሰጠ የዐቃቤ ሕግ ምስክር እንደገና እንዲመሰክር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፸፪ በዳኛ ስለሚወሰድ ጥንቃቄ</u>**

የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን የምስክርነት ቃል የሚቀበል ዳኛ፣

**፩**.ምስክርነት የሰጠ ካልሰጠው ጋር እንዳይገናኝ፣

**፪**.የተከሳሽ ምስክሮች የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሲመሰክር በችሎት አዳራሽ እንዳይገኙ፣

**፫**.ምስክርነት እንደ ቪዲዮ ኮንፈረንስና በመሳሰሉት መገናኛ ዘዴዎች የሚሰጥ እንደሆነ እውነተኛ ምስክርነት እንዲሰጥ፣

**፬**.እውነተኛ ምስክርነት ለመስጠት የሚያስችል የችሎት ድባብ እንዲኖር ፣

እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊው ዝግጅቶች መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፸፫ ክንዋኔዎችን መመዝገብ</u>**

**፩**. ፍርድ ቤቱ በክርክር ሂደቱ ሁሉ፡-

**(ሀ)** የዳኛው ስም፣ የችሎቱን ስያሜ፣ ቀንና መዝገብ ቁጥሩን፣

**(ለ)** የከሳሽና የተከሳሽ ስምና አድራሻ፣እንዲሁም

**(ሐ)** ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ሁኔታዎች፣

በመዝገብ ውስጥ ያሰፍራል፡፡

**፪**. ዳኛው የእያንዳንዱ የምስክር ቃል አመቺ በሆነ መንገድ መመዝገቡን ያረጋግጣል፡፡

**፫**. ማስረጃው ሲመዘገብ ዋና፣ መስቀልኛ እና ድጋሚ ጥያቄ ተብሎ መለየት አለበት፡፡ ዋና ጥያቄ፣ መስቀልኛ ጥያቄ ወይም ድጋሚ ጥያቄ የሚጀምርበትና የሚያበቃበት በግልጽ መለየት ይኖርበታል፡፡

**፬**. ሌላ ማስረጃም ምልክት እየተደረገበት ይመዘገባል፡፡

፯. ዳኛው አንድን ጥያቄ ወይም መልስ በተለየ ለመፃፍ፣ ለመቅረጽ ወይም ለመቅዳት ካልፈቀደ በስተቀር የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ምንጊዜም ቢሆን በተነገረበት አግባብ በሐተታ ዓይነት ይመዘግባል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የሰነድ ማስረጃ

### አንቀጽ ፪፻፫፬ ፍሬ ነገሮችን በሰነድ ማስረዳት

፩. ዐቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ማንኛውም የሰነድ ማስረጃ ይዘት የሚረጋገጠው በዋናው ቅጅ ወይም ሰነዱን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ቅጂ በማቅረብ ነው፡፡

፪. ዐቃቤ ሕግ ከክሱ ጋር ያያዘውን የሰነድ ማስረጃ ትክክለኛነት አስመልክቶ ተቃውሞ ከቀረበበት የሰነዱን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ዋናው ሰነድ ወይም የተረጋገጠው ቅጂ  የጠፋ፣ የተቃጠለ፣ ወይም ከአቅሙ በላይ በሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ የሰነዱን ይዘት ከዋናው ሰነድ ጋር በተመሳከረ ቅጂ ወይም በምስክር ማስረዳት ይችላል፡፡

፬. ከሰነዱ ይዘት ፣ ብዛት፣  ግዙፍነት ወይም ሌላ ቴክኒካዊ ምክንያት የሰነዱን ይዘት መመርመር ለፍርድ ቤቱ አስቸጋሪ እንደሆነ  ዐቃቤ ሕግ የሰነዱን ይዘት በምስክር ፣ በፎቶግራፍ ፣ወይም በተንቀሳቃሳሽ ምስል ማስረዳት ይችላል፡፡

፭. ሰነዱ ግልጽነት የጎደለው ወይም በይዘቱ እርስ በርሱ የሚጋጭ በሆነ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ የሰነዱን ይዘት በምስክር ማስረዳት ይችላል፡፡

፮. ተከሳሽ አንድን የሰነድ ማስረጃ ዋጋ ለማሳጣት ወይም በሕግ ፊት የጸና አለመሆኑን ለማሳየት ማንኛውንም ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፪ እስከ ፮ ከተዘረዘረው በቀር ዐቃቤ ሕግ በማስረጃነት የቀረበውን ሰነድ ይዘት በምስክር ማስረዳት አይችልም ፡፡

### አንቀጽ ፪፻፫፭  የአንድን ፍሬ ነገር መከሰት ስለማስረዳት

፩.ዐቃቤ ሕግ  በሕዝብ  ወይም በንግድ መዛግብት መመዝገብ የነበረበት ፍሬ ነገር በዚሁ መዝገብ ውስጥ መኖሩን በማሳየት የፍሬ ነገሩን መከሰት ማስረዳት ይችላል፡፡

፪.ሆኖም ፍርድ ቤቱ በንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍሬ ነገሩ ተረጋግጧል ወይም ተስተባብሏል ከማለቱ በፊት የተጠቀሰው ምዝገባ በትክክል እንደሚከናወን ወይም መዝገቡ የተሟላ መሆኑ ያረጋግጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፸፯ የሕዝብ መዛግብትን ይዘት ትክክለኛነት ማረጋገጥ</u>**

ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ዋና ዋና ሁነቶችንና መሰል ፍሬ ነገርን ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው የመንግሥት ተቋም የተመዘገበ የሕዝብ መዝገብ ይዘት ትክክለኛ ነው ተብሎ የሚገመተው ፡-

፩. በሕግ በተቀመጠው ወይም ሁነቱ በተከሰተ ጊዜ ወይም ወዲያውኑ እንደተከሰተ የተመዘገበ እንደሆነ፣

፪. ሁነቱን ለመመዝገብ ሥልጣን በተሰጠው ሰው የተመዘገበ ከሆነ እና፣

፫. መዝገቡ የተሰረዘ፣ የተደለዘ ወይም ሌላ የሚያጠራጥር ነገር የሌለበት መሆኑ በፍርድ ቤቱ ሲረጋገጥ፣

ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፸፯ የመንግስት ሰነድ ይዘት ትክክለኛነት ማረጋገጥ</u>**

፩.ዐቃቤ ሕግ በማስረጃነት ያቀረበው የመንግስት ሰነድ ይዘት እምነት የሚጣልበት ትክክለኛ ማስረጃ እንደሆነ ይገመታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ተቃራኒው ወገን ባቀረበው መቃወሚያ ወይም በራሱ አነሳሽነት የቀረበው የመንግሥት ሰነድ ይዘት ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ ትእዛዛ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፸፰ የንግድ መዝገብ ይዘትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ</u>**

ዐቃቤ ሕግ በማስረጃነት ያቀረበው የንግድ ድርጅት ስለሚያከናውነው የንግድ ተግባር ሕግ በሚያዘው ዓይነት ወይም በድርጅቱ ልማድ መሠረት ተዘውትሮ የሚመዘገብበት የንግድ መዝገብ ይዘት ወይም በዚሁ መዝገብ የሚመዘገብ ፍሬ ነገር ትክክለኛ መሆኑ የሚረጋገጠው፡-

፩. ፍሬ ነገሩ በተከሰተ ጊዜ ወይም ከተከሰተ በኋላ ወዲያውኑ የተመዘገበ እንደሆነ፣

፪. ፍሬ ነገሩ በመዝገብ የሰፈረው ይህንኑ ፍሬ ነገር መመዝገብ መደበኛ ሥራው በሆነ ሰራተኛ እንደሆነ ፣እና

፫. ሰነዱ የተሰረዘ፣ የተደለዘ ወይም ሌላ የሚያጠራጥር ነገር የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፸፱ የፊርማን ወይም የጽሑፍ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ</u>**

፩. ዐቃቤ ሕግ በማስረጃነት ያቀረበው የተከሳሽ ወይም የምስክር የእጅ ጽሑፍ ወይም ፊርማ ትክክለኛነት እንደነገሩ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ከዚሁ ሰው ናሙና የእጅ ጽሑፍ ወይም ፊርማ ጋር በማነጻጸር፣ በራሱ ወይም ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ምስክር ወይም በልዩ አዋቂ ምርመራ እንዲረጋገጥ ማድረግ ይችላል፡፡

፪.ይህንንም ለማድረግ የተባለው ሰው ቀድሞ የጻፈው ወይም የፈረመው ሰነድ ካለ ዐቃቤ ሕግ እንዲያቀርብ ወይም ተከሳሹ ወይም ምስክሩ የተወሰኑ ቃላትን ወይም አኃዞችን እንዲጽፍ ወይም ፊርማ እንዲፈርም ፍርድ ቤቱ ሊያዘው ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹ በማኅተም ወይም ፊርማ ላይ የሚወሰድ የሕግ ግምት**

፩. ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ሕግ በቀረበለት ሰነድ ላይ ያረፈ ፊርማ ወይም ማኅተም ትክክል ስለመሆኑና ማኅተሙን ያተመው ወይም ፊርማውን የፈረመው ሰው ማኅተሙን ባተመበት ወይም ፊርማውን በፈረመበት ጊዜ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ልክ እንዳከናወነው ይገመታል ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ተቃራኒው ወገን ባቀረበው መቃወሚያ ወይም በራሱ አነሳሽነት የቀረበ ማኅተም ወይም ፊርማ ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹፩ የሕግ ግምት የሚወሰድበት ሰነድ**

፩. ፍርድ ቤት በዐቃቤ ሕግ በማስረጃነት የቀረበ ፡-

**(ሀ)** በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል የተሠራና ለሕዝብ ይፋ የሆነ የቦታ ካርታ ወይም ፕላን ትክክለኛ መሆኑ፤

**(ለ)** በማንኛውም የውጭ መንግሥት የታተመ የፍርድ ውሳኔ ትክክለኛ መሆኑ፤

**(ሐ)** የሕዝብ ጉዳዮችን የሚመለከት ማንኛውም መጽሐፍ፣ ታትሞ የወጣ የቦታ ካርታ ወይም ቻርት ጽፎ ወይም አትሞ አወጣ የተባለው ሰው ተጻፈ ወይም ታተመ በተባለበት ጊዜና ቦታ የጻፈውና አትሞ ያወጣው ሰው መሆኑን፣

የሕግ ግምት ይወስዳል፡፡

፪.በሕግ ሥልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ በዐቃቤ ሕግ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ በውስጡ ስለሚገኘው ይዘት ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት በቂ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ማንኛውም ዓይነት ተቃራኒ ማስረጃ ማቅረብ ይዘቱን መቃወም ይቻላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹፪ በሦስተኛ ወገን ይዞታ ስለሚገኝ ሰነድ**

ፍርድ ቤት በዐቃቤ ሕግ ጠያቂነት ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት ያለው ማስረጃ በሦስተኛ ወገን ይዞታ ሥር ያለ ሰነድ እንዲቀርብ ለባለይዞታው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሦስት**

**የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ**

**አንቀጽ ፩፻፹፫ በኤሌክትሮኒክ ማስረጃ የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር**

**፩.** ዐቃቤ ሕግ በጭብጥ የተያዘውን ወይም አግባብነት ያለውን ፍሬ ነገር በኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ማስረዳት ይችላል፡፡

**፪.** በዚህ ሕግ "**የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ**" ማለት ዳታን፣ የኤሌክትሮኒክ መዝገብን፣ ሥርዐትና መተግበሪያን ጨምሮ በማንኛውም መሣሪያ የተመዘገበ፣ የተከማቸ በሰው ወይም በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሣሪያ ሊነበብ ወይም ሊታወቅ የሚችል ፍሬ ነገር ነው፡፡

**አንቀጽ ፩፻፹፬ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ትክክለኛነት**

**፩.**አስተማማኝነቱ በተረጋገጠ የኤሌክትሮኒክ ዳታ የተመዘገበበት ወይም የተከማቸበት ሥርዐትን ተከትሎ የተገኘ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ትክክለኛ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ እንደሆነ ይገመታል፡፡

**፪.** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በተከታታይ ሲሠራበት በቆየ አስተማማኝነት ባለው ዳታን ሲያከማች ወይም ሲመዘግብ በቆየ ሥርዐት ወይም በመተግበሪያ የተከማቸ፣ ወደ ሠነድ ተቀይሮ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**፫.** የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ሥርዐትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ፣

**(ሀ)** ኮምፒውተሩ ወይም መሣሪያው በተግባር ሲሠራ መቆየቱን፣ ብልሽት ያጋጠመው ቢሆንም የኮምፒውተሩን ሥርዐት አስተማማኝነት የማያጓድለው መሆኑን፤

**(ለ)** የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ እንዲመዘገብ የተደረገው ማስረጃውን ለማቅረብ ከሚፈልገው ወገን በተቃራኒ ባለው ሌላኛው ተከራካሪ ወገን መሆኑን ወይም፣

**(ሐ)** የኤሌክትሮኒክ መዝገቡ እንዲመዘገብ ወይም እንዲከማች ያደረገው ሰው ማስረጃውን ለማቅረብ በሚፈልገው ሰው ቁጥጥር ሥር ያለመሆኑና ምዝገባው ወይም ክምችቱ የተለመደውን ሥራ ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን፣

የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ የማስረጃውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

**፬.** የማስረጃውን ትክክለኛነት ለማስተባበል መረጃው የተመዘገው የመረጃ ክምችት፣ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ፣ ወይም መረጃው የተመዘገበበት ኮምፒዩተር፣ መሣሪያ፣ የመረጃ ሥርዓት ወይም መተግበሪያ ተቃራኒው ወገን እንዲያየው ወይም በልዩ አዋቂ እንዲያሳየው ይደረጋል፡፡

**፭.**በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት አንድን የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ትክክለኛነት ዋጋ ለማሳጣት ወይም እምነት የሚጣልበት አለመሆኑን በማንኛውም ማስረጃ ማስረዳት ይቻላል፡፡

**ንዑስ ክፍል አራት**

**ኤግዚቢት**

**አንቀጽ ፪፻፹፩ ኤግዚቢት**

ዐቃቤ ሕግ ግዙፋዊነት ያለው ወይም የሌለው ማንኛውንም ነገር ለፍርድ ቤት እይታ በኤግዚቢትነት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹፪ የኤግዚቢትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ**

፩. ዐቃቤ ሕግ የሚያቀርበውን ኤግዚቢት ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

፪.ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ኤግዚቢት ትክክለኛነት ለማስረዳት ኤግዚቢቱን የሚለዩና በኤግዚቢቱ ላይ የሚገኙ ልዩ ምልክትና የምርት መለያ ቁጥር የመሳሰሉ ነገሮች ማሳየት ወይም የኤግዚቢቱን አሰባሰብ፣አጠባበቅ እና አቀራረብ በተመለከተ በምስክር ማስረዳት ይችላል፡፡

**ክፍል አራት**

**ብይን ስለመስጠት**

**አንቀጽ ፪፻፹፫ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ የሚሰጥ አስተያየት**

የዐቃቤሕግ ማስረጃ ተሠምቶ እንዳበቃ ተከሳሽ በዐቃቤሕግ ማስረጃ ላይ አስተያየት ሊሠጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹፬ የዐቃቤ ሕግ የማስረዳት ኃላፊነትና የማስረዳት ደረጃ**

፩. ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ መሠረት ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ሞራላዊና ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮችን፣ ሌሎች በጭብጥ የተያዙ ወይም አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር ወይም በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር በዐቃቤ ሕግ ተረጋግጧል የሚባለው ዐቃቤ ሕግ የነገሩን ሁነት፣ መከሰት ወይም አለመከሰት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው የማስረዳት መጠን ማረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፪የ፹፱ ብይን**

፩. የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ አልተረጋገጠም ብሎ ሲያምን ተከሳሹ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ያሰናብታል፡፡

፪. የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወይም በአማራጭ ሊያስከስሰው ወይም ሊያስቀጣው የሚችል ወንጀል ስለመፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ተረጋግጧል ብሎ ሲያምን ተከሳሹ መከላከል ይገባዋል ያለውን ነጥብ ለይቶ መከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ያዛል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ተከሳሹን በነጻ ሲያሰናብት ከእስር እንዲለቀቅ፣ እግድ እንዲነሳ፣ እሽግ እንዲነሳ፣ ዋስትና እንዲወርድ፣ በኤግዚቢት የተያዘ ዕቃ እንዲመለስ እና ሌላ ተገቢ የሆነ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ**

**አንቀጽ ፪የ፺ የተከሳሹ የክርክር መክፈቻ ንግግር**

፩. ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የክርክር መክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ ተረጋግጧል ወይም አልተረጋገጠም ብሎ የሚያምንበትን መከላከያና የሚያቀርበውን የማስረጃ ዓይነት ባጭሩ ይገልፃል፡፡

፪.በተከሳሹ የቀረበው የመከላከያ ጭብጥ እና የማስረጃ መግለጫ በጽሑፍ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት መከላከያ ማስረጃ ከሚሰማበት ቀጠሮ ከአስር ቀናት በፊት ለዐቃቤ ሕግ እንዲደርስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫. ተከሳሹ የተከሳሽነት ቃሉን ብቻ ለመስጠት ወይም በራሱ ጉዳይ በምስክርነት ለመቅረብ ይችላል፡፡ ውሳኔውንም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በክርክር መክፈቻ ንግግሩ ለፍርድ ቤቱ ያስመዘግባል፡፡

**አንቀጽ ፪የ፺፩ የተከሳሽን የመከላከያ ማስረጃ መስማት**

፩.ተከሳሹ የምስክርነት ቃሉን ወይም የተከሳሽነት ቃሉን ሌሎች ምስክሮች ከማሰማቱ በፊት ይሰጣል፡፡ ሆኖም በራሴ ጉዳይ የምስክርነት ቃሌን እሰጣለሁ ብሎ ያስመዘገበ ተከሳሽ መመስከሩን ለሙተው ይችላል፡፡ በዚህ አግባብ ቃሉን የለወጠ ተከሳሽ በተለዋጭ የተከሳሽነት ቃሉን ለመስጠት አይችልም፡፡

፪.ተከሳሹ በራሱ ጉዳይ ላይ ምስክር ሆኖ ለመቅረብ የመረጠ እንደሆነ ቃለ-መኃላ ፈጽሞ ወይም እውነቱን ለመመስከር ማረጋገጫ ሰጥቶ ይመሰክራል፡፡ ዐቃቤ ሕጉም መስቀልኛ ጥያቄ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ የሚሰጠውም ምስክርነት እንደማንኛውም የምስክር ቃል ይመዘናል፡፡

፫.ተከሳሹ የተከሳሽነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ቃለ-መኃላ እንዲፈጽም ወይም እውነቱን ለመመስከር ማረጋገጫ እንዲሰጥ አይደረግም፤ በዐቃቤ ሕግም መስቀልኛ ጥያቄ አይጠየቅም፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ አንዳንድ ግልጽ ባልሆኑ ነገሮች ላይ የማብራሪያ ጥያቄ ብቻ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

፬.ተከሳሹ የሚሰጠውን የተከሳሽነት ቃል ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት አግባብ ነው ያለውን ዋጋ ይሰጠዋል፡፡

<u>**አንቀጽ ፪፻፺፪ በዐቃቤ ሕግ ወይም በፖሊስ እጅ የሚገኝ ማስረጃ**</u>

፩. ዐቃቤሕግ ተከሳሹን የሚጠቅም በፖሊስ ወይም በዐቃቤ ሕግ የሚገኝ ማስረጃ ለተከሳሹ በመከላከያ ማስረጃነት እንዲጠቀምበት በራሱ ተነሳሽነት ለተከሳሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፩ ቢኖርም ተከሳሽ በዐቃቤሕግ ወይም በፖሊስ እጅ የሚገኝ ማስረጃን በመለየት ወይም በጥቅሉ እንዲሰጠው በማንኛውም ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ፍርድቤቱም ማስረጃው እንዲደርሰው ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

<u>**አንቀጽ ፪፻፺፫ የተከሳሹ የማስረዳት ኃላፊነት**</u>

፩.ተከሳሹ ባቀረበው መከላከያ የቀረበበትን ክስ ተከላክሎ ከወንጀሉ ነፃ ለመሆን በተከሰሰበትና ዐቃቤ ሕጉ ባረጋገጣቸው ወንጀሉን በሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ወይም ማስረጃዎች ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ መፍጠር ይኖርበታል፡፡

፪.ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መፈጸሙን አምኖ ስለአፈጻጸሙ ሙብቱን ጠብቆ ወይም በሕግ የተደነገገና በወንጀል የማያስጠይቅ መሆኑን ጠቅሶ በመከራከር ያቀረበውን መከላከያ ለማስረዳት ላቀረባቸው ክርክሮች መሠረት የሆኑ ፍሬ ነገሮችን በፍትሐብሔር የማስረዳት መጠን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፫.በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር ወይም በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር በተከሳሽ ተስተባብሏል የሚባለው ተከሳሽ የፍሬነገሩን መከሰት ወይም አለመከሰት በዚህ አንቀጽ በተደነገገው የማስረዳት መጠን መረጋገጡን ፍርድቤቱ ሲያምን ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፺፩ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት**

ከዚህ በላይ በምዕራፍ ሦስት ስለ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በአጠቃላይ የተነገረው አግባብ ያለው ማሻሻያ ተደርጎበት የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**ክፍል ስድስትየወል ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ ፪፻፺፪ ተጨማሪ ማስረጃ**

**፩.** ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ማስረጃውን አጠቃሎ ያቀርባል፡፡ ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ያልታወቀ ወይም በወቅቱ ያልተገኘ ተጨማሪ ወይም ድንገተኛ ማስረጃ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የቀረበው ጥያቄ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሳይሆን የነገሩን መሰማት ለማዘግየት የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን አይቀበለውም፡፡

**፫.**ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ሲያምን በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ያልቀረበ ማስረጃ እንዲቀርብለት ለማዘዝ ይችላል፡፡

**፬.** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ መሠረት በፍርድቤት ትእዛዝ ተጨማሪ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ ምስክር ሲሆን ጥያቄ እንዲጠይቁ ፤ ሌሎች ማስረጃዎች ሲሆኑ አስተያየት እንዲሰጡበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፺፫ አግባብነት ወይም ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ውጤት**

ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሹ አመልካችነት የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት እንደሌለው ከተረዳ ማስረጃውን ውድቅ ያደርገዋል፡፡

**አንቀጽ ፪፻፺፬ በማስረጃ ላይ ስለሚቀርብ መቃወሚያ**

**፩.**ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ በሚያቀርበው ማስረጃ ላይ ሌላኛው ወገን ማስረጃው አግባብነት ወይም ተቀባይነት የለውም ወይም ሌላ በሕግ የተመለከተ ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በሚል መቃወሚያ በቃል ወይም በፅሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፪.**ፍርድ ቤቱ በቀረበው መቃወሚያ ላይ ማስረጃውን ያቀረበው ወገን አስተያየት ተቀብሎ የመቃወሚያው አግባብነትና ተቀባይነት ላይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፺፰ የክርክር ማቆሚያ ንግግር</u>**

**፩**.የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ተሰምቶ እንዳበቃ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ ግልፅና ዝርዝር የሆነ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ያደርጋሉ፡፡

**፪**.ዐቃቤ ሕጉ በክርክር ማቆሚያ ንግግሩ ያቀረበውን ክስ፣ የጠቀሰውን ሕግ፣ ፍሬ ነገሩንና ያቀረበውን ማስረጃ እንዲሁም ተከሳሹ ያላስተባበለበትን ሁኔታ በመጥቀስ ጥፋተኛ ሊያስብሉ የሚችሉ ምክንያቶችን ይናገራል፡፡

**፫**. ተከሳሹ የዐቃቤ ሕጉን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በመከላከያነት ያቀረበውን ማስረጃ በመጥቀስ ጥፋተኛ የማይባልበትን ምክንያት ያስረዳል፡፡ ተከሳሹም ሁልጊዜ የመጨረሻ ንግግር ያደርጋል፡፡

**፬**. ተከሳሾቹ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተለየ ካላዘዘ በቀር በክሱ ላይ ስማቸው በተጠቀሰበት ቅደም ተከተል ይናገራሉ፡፡

**፭**. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የክርክር ማቆሚያ ንግግር በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፪፻፺፱ የሥርዐት ጉድለትን ማረም</u>**

በማንኛውም የክርክር ደረጃ በሚሰጥ ትእዛዝ የሚፈጸም የሥነ-ሥርዐት ስህተት፣ በአጻጻፍ ምክንያት የሚፈጸም የስም፣ የቁጥር፣ መለያና ድምር ወይም ሌላ ማናቸውም ስህተት ሲያጋጥም በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አመልካችነት ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም ሌላ ያገባኛል በሚል ወገን አመልካችነት ያስተካክላል፡፡

**<u>ምዕራፍ አራት</u>**

**<u>ፍርድ እና ቅጣት</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>የፍርድ አሠጣጥ</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻ ፍርድ</u>**

**፩**. ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግንና የተከሳሹ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ከሰማ በኋላ ፡-

**(ሀ)** ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፪፻፺፫</u>** በተደነገገው አግባብ አልተከላከለም ብሎ ሲያምን የጥፋተኝነት ፍርድ ይሰጣል፡፡

**(ለ)** ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፺፫** በተደነገገው አግባብ ተከላክሏል ብሎ ሲያምን ተከሳሹን በነፃ ያሰናብተዋል፡፡

**፪.** ፍርዱም በጽሑፍ ሆኖ ፍርዱን በፈረደው ዳኛ ወይም ዳኞች ተፈርሞ በግልጽ ችሎት ይነበባል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፭ የፍርድ አፃፃፍ**

**፩.**በዚህ ሕግ መሠረት የሚሰጥ ፍርድ በቅደም ተከተሉ፡-

**(ሀ)** የመዝገብ ቁጥር፣ ፍርዱ የተሰጠበትን ቀን፣ ወር፣ እና ዓመተምህረት፤ የፍርድ ቤቱን እና ፍርድ የፈረደውን ዳኛ ስም፤

**(ለ)** ክሱ በአጭሩ፣ እንደአስፈላጊነቱ ክሱ በቀረበበት ዐይነት፣ ቀድመው ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች በአጭሩ፤ የክርክሩ ጭብጥ፣ ጭብጡን ያስረዱ ማስረጃዎች አጭር መግለጫ፤

**(ሐ)** ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው ማስረጃዎች ከነምክንያቱ፣ ጭብጡን ያላስረዱ ማስረጃዎች፣ ፍርድ ቤቱ ያልተቀበላቸው ማስረጃዎች ምክንያት፣ለድምዳሜ መሠረት የሆነው ዝርዝር የፍሬ ነገር፣የማስረጃና የሕግ ምክንያቶች፤

**(መ)** ፍርዱን፣ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ የቅጣቱ አፈጻጸም፣ ነፃ የተባለ እንደሆነ በዋስትና ጉዳይ፣ ስለሚለቀቅበት ሁኔታ፣ ስለ እግድ፣ ስለተያዙ ንብረቶች እና መሰል ጉዳዮችን የተመለከቱ ልዩ ልዩ ትእዛዞች፤እና

**(ሠ)** ፍርዱን የሠጠው የዳኛ ፊርማ፤

መያዝ ይኖርበታል፡፡

**፪.** በማስረጃነት የቀረበ ምስል ወይም ሌላ በጽሑፍ ሊገለጽ የማይችል ማስረጃ በማጣቀሻ ሊገለጽ ይችላል፡፡

**፫.** በውሳኔ ውስጥ የሚካተተው ከፍርድ ድምዳሜ በመነሳት ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባው የፍርድ አካል ብቻ ነው፡፡

**፬.** ለተለያዩ አካላት የሚገለጹ ጉዳዮች፣ የመዝገብን አስተዳደር የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ የይግባኝ መብት የሚመለከቱ ጉዳዮች በትእዛዝ ሥር ይገለጻሉ፡፡

**አንቀጽ ፫፻፮ የቅጣት አስተያየት**

**፩.**ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ፍርድ የሰጠ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሹ የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪.** የግል ተበዳይ ስለደረሰበት ጉዳት ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በግል ተበዳይ አመልካችነት ማጠቃለያ ሀሳብ እንዲሰጥ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

፫. ዐቃቤ ሕግ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በማስረጃ አስደግፎ በቃል ወይም በጽሑፍ ያቀርባል፡፡

፬. ተከሳሽ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶቹን እንደአግባብነቱ በማስረጃ አስደግፎ በቃል ወይም በጽሑፍ ያቀርባል፡፡

፭.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች ባቀረቧቸው የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች እንዲሁም በቅጣቱ ላይ ክርክር ማቅረብ ይችላሉ፡፡

፮. ፍርድቤቱም የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ማስረጃዎችን በፍትሐብሔር የማስረዳት መጠን ይመዝናል፡፡

፯. ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግና ተከሳሽ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በማስረጃ አስደግፎ ለማቅረብ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፫ የቅጣት ውሳኔ</u>**

ፍርድ ቤቱ፡-

፩. የቅጣት አስተያየቱን መሠረት በማድረግ ማስረጃ ለመስማት ወይም ለመመርመር የሚያስፈልገውን ያህል አጭር ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ ማስረጃ ሰምቶ ቅጣት ለመወሰን የሚሰጥ ቀጠሮ እጅግ ቢበዛ ከአሥራ አምስት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ቅጣቱን ለመወሰን ቀጠሮ ሲሰጥ ተከሳሽ በዋስ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊያዝ ይችላል፡፡

፫. ጥፋተኛው የተፈረደበት የወንጀል ድንጋጌ አማራጭ ቅጣቶችን የሚደነገግ ከሆነ በክርክሩ ወቅት ከባዱን የቅጣት አማራጭ ለመከተል የሚያስችል ምክንያት ካልተገኘ በቀር ቀላሉን የቅጣት አማራጭ ይከተላል፡፡

፬. ቅጣትን ሲወስን በሕግ አውጭው ለወንጀሉ ከተደነገገው መነሻ ቅጣት በመነሳት፣ የተቀበለውን የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መሠረት በማድረግ ቅጣቱን አክብዶ ከደረሰበት ቅጣት በመነሳት የተቀበለውን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መሠረት በማድረግ ቅጣቱን አቅልሎ የሚፈጸመውን ቅጣት ይወስናል፡፡

፭.ልዩና ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ተደራርበው ሲገኙ በመጀመሪያ በልዩ የቅጣት ማክበጃው ምክንያት ቅጣቱን አክብዶ ከደረሰበት ቅጣት በመነሳት በጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ቅጣቱን ያከብዳል፡፡

፯.ልዩና ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱን በማክበድ ከደረሰበት ቅጣት በመነሳት በመጀመሪያ በልዩ ማቅለያው ቅጣቱን ካቀለለ በኋላ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቱን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

፰.የቅጣቱ ውሳኔ የሚፈጸምበትን ሁኔታ በተለይም ቅጣቱን ለሚያስፈጽመው አካል ትእዛዝ እንዲተላለፍ እንዲሁም ተከሳሹ የይግባኝ መብት እንዳለው በመግለጽ በመዝገቡ ያሰፍራል፡፡

ክፍል ሁለት**የቅጣት አፈፃፀም**

ንዑስ ክፍል አንድ **ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ ፫፻፴ መርህ**

፩. ቅጣትና የጥንቃቄ ርምጃ የሚፈጸመው የወንጀል ሕጉን ዓላማ ለማሳካት ሆኖ ቅጣቱና የጥንቃቄ ርምጃው ምንጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መልኩ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

፪.በዚህ ሕግ እና በወንጀል ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ቅጣት እንደተወሰነ ይፈፀማል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፩ የቅጣት አፈጻጸም ትእዛዝ**

ፍርድ ቤቱ የወሰነው ቅጣት፡-

፩.የሞት ቅጣት እንደሆነ ቅጣቱ ፀድቆ እስኪፈፀም ፍርደኛው በማረሚያ ቤት እንዲቆይ፣

፪. የእስራት ቅጣት እንደሆነ እስራቱን የሚያስፈፅመውን ማረሚያ ቤት በመለየት፣

፫.የገንዘብ መቀጮ እንደሆነ ወይም የእሥራት ቅጣትና የገንዘብ ቅጣት በአንድነት የተወሰነ እንደሆነ የገንዘቡን አከፋፈል ሁኔታ እና የሚያስፈፅመውን አካል በግልፅ በመለየት ፣ ወይም

፬.ሌሎች የቅጣት እና የአማራጭ መፍትሄ ርምጃዎች ከሆኑ አፈጻጸማቸውን በሚመለከት፣

ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

**የሞት ቅጣት አፈጻጸም**

**አንቀጽ ፫፻፴፪ የሞት ቅጣት ውሳኔ የሚፈጸምበት ሁኔታ**

፩.የሞት ቅጣት ፍርድ የሰጠ ፍርድ ቤት ውሳኔውንና የመዝገቡን ግልባጭ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያስተላልፋል፡፡ በፍርዱ ላይ ይግባኝ ካልተባለበት በጠቅላይ ፍርድ ቤት አምስት ዳኞች በተሰየሙበት

የውሳኔውን ትክክለኛነት አረጋግጦ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፤ ፍርድቤቱ የይግባኝ ሠሚው ፍርድቤት ያለው ስልጣን ይኖረዋል፡፡

**፪.** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሞት ፍርዱ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ፣ በይቅርታ ወይም ምህረት ያልተሻረ ወይም ያልተለወጠ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲጸና ለርዕሰ ብሔሩ ያቀርባል፡፡

**፫.**የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት የሞት ፍርድ በማንኛውም ምክንያት ሳይፈጸም ከሁለት ዓመት በላይ የቆየ እንደሆነ ወደ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ይለወጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፯ የሞት ቅጣት አፈጻጸምን ስለማገድ</u>**

በወንጀል ሕግ አንቀጽ ፻፲፱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት የሞት ቅጣት አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ ፍርዱን ለፈረደው ፍርድ ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ሰምቶ ሊያግደው ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል ሦስት

**<u>የእስራት ቅጣት አፈጻጸም</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻፰ ቅጣት እንዲፈፀም የሚሰጥ ትእዛዝ</u>**

**፩.**ፍርድ ቤቱ ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት የሚወስን እንደሆነ አፈጻጸሙ የሚጀምርበትን ቀን እና አስፈጻሚውን ለይቶ እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪.**ፍርደኛው የሌለ ወይም ጉዳዩ በሌለበት የታየ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተይዞ ቅጣቱ እንዲፈጸም ለፖሊስ ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፱ የእስራት ቅጣት እንዲተላለፍ የሚቀርብ አቤቱታ</u>**

**፩.** ጥፋተኛ የተባለ ፍርደኛ የሚወሰንበት የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍለት ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፪.** ፍርደኛው የቅጣት አፈጻጸም ጊዜው እንዲተላለፍለት የሚያቀርበው አቤቱታ፡-

**(ሀ)** አቤቱታው የቀረበበትን ምክንያትና ማስረጃ፣ እና

**(ለ)** የቅጣቱ አፈጻጸም ለምን ያህል ጊዜ ሊተላለፍለት እንደሚገባ፣

ከቅጣት አስተያየት ጋር አብሮ ያቀርባል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ በቀረበው አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ አስተያየቱን እንዲሰጥበትና አስፈላጊ ሲሆን ማስረጃውን ወይም የባለሙያ አስተያየት ከሰማ በኋላ ከቅጣት ውሳኔው ጋር አብሮ ውሳኔውን ይሰጣል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፫፻ የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ**

፩. የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ጊዜ፣

**(ሀ)** ፍርደኛው በጠና ከመታመሙ የተነሳ በማረሚያ ቤት ቅጣቱን ለመፈጸም የማይችል መሆኑ በሐኪም ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ከሕመሙ እስኪድን አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚወስነው ጊዜ፣

**(ለ)** አስራ ስምንት ወር ያልሞላው ሕጻን ያላት እናት ስትሆን ሕጻኑ ሠላሳ ወር እስኪሞላው ድረስ፣

**(ሐ)** ነፍሰ ጡር እንደሆነች የእርግዝና ጊዜው እስከሚያበቃና ከወለደች በኋላ ሕፃኑ ሠላሳ ወር እስኪሆነው፣

**(መ)** ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን በፊት ባለው ሁለት ሳምንታት ውስጥ ወላጁ፣ ልጁ ወይም የትዳር ጓደኛው የሞተ ወይም በጠና የታመመ እንደሆነ ከአስራአምስት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ፣

**(ሠ)** ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የትዳር ጓደኛው የወለደች ወይም ፍርድ ከተሰጠ በሚቀጥለው አንድ ወር ውስጥ የምትወልድ እንደሆነ እና ከተፈረደበት ሰው ሌላ ረዳት የሌላት እንደሆነ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

**(ረ)** ቤተሰቡን የሚንከባከብ ሌላ ሰው ከሌለና ባልና ሚስት በተመሳሳይ ጊዜ የተፈረደባቸው እንደሆነ ሚስት ወይም ከሁለቱም አንዱ ቀደም ብሎ የታሰረ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

**(ሰ)** የቅጣቱ አፈጻጸም እንዲተላለፍለት የተጠየቀለት ምክንያት አጣዳፊ ወይም ወቅታዊ ለሆነ የግብርና ሥራ ወይም ባልታሰበ ምክንያት የተፈጠረ በአስቸኳይ ሊከናወን የሚገባው ሥራ እንደሆነ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

**(ሸ)** የተፈረደበት ሰው ቀደም ብሎ የጀመረው ሆኖ በሌላ ሰው ሊጠናቀቅ የማይችል ሥራ ወይም ጉዳይ ሲሆንና ሥራው ባለመጠናቀቁ ምክንያት ጉዳት የሚደርስ እንደሆነ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

**(ቀ)** የተፈረደበት ሰው የጀመረውን ትምህርት ወይም የተማረበትን ፈተና ለማጠናቀቅ እንደሆነና በሌላ ሁኔታ ማጠናቀቅ የማይቻል እንደሆነ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ወይም ለፈተናው የሚያስፈልገው ጊዜ፣

ሊተላለፍ ይችላል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው የቅጣት አፈፃፀም ሊተላለፍ የሚችለው ፍርድ ቤቱ እስከ አምስት ዓመት እስራት የተፈረደበት ፍርደኛ ለሕብረተሰቡ ደኅንነት አደጋ እንደማይሆን መረጋገጡን እና የእስራት ቅጣቱን መፈጸም በሚገባው ጊዜ እንዲጀምር ለማረጋገጥ የሚያስችለው በቂ ዋስትና የሚያቀርብና እንዲፈጽማቸው የታዘዙትን የጥንቃቄ ርምጃዎች የሚያከብር መሆኑን ሲያረጋግጥ ይሆናል፡፡

**፫.**ፍርደኛው የተላለፈውን የቅጣት ጊዜ በአግባቡ ጨርሶ የተመለሰ እንደሆነ የተላለፈው የቅጣት ጊዜ እንደ ተፈጸመ ቅጣት ይቆጠርለታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፲፩ የተላለፈን ቅጣት ማቋረጥ</u>**

**፩.**በሚከተሉት ምክንያቶች የቅጣት መተላለፉ ቀሪ ሆኖ ቅጣቱ ይፈጸማል፡-

**(ሀ)** ፍርደኛው የተላለፈውን የእስራት ጊዜን ለሌላ ዓላማ ካዋለው፣

**(ለ)** ፍርደኛው በማንኛውም መንገድ ለሕዝብ ደኅንነት አደጋ መሆኑ ከተረጋገጠ ፣

**(ሐ)** ያመልጣል ተብሎ በበቂ ምክንያት የሚጠረጠር ከሆነ፣

**(መ)** ቅጣቱ እንዲተላለፍለት ያቀረበው ምክንያት የሌለ ወይም የተቋረጠ ወይም ሀሰተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍርድቤቱ ቀሪ ከማድረጉ በፊት የፍርደኛውን አስተያየት ይቀበላል፡፡**፫.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተላላፈለት ቅጣት ተቋርጦ እንዲፈጽም ትእዛዝ የተሰጠበት ፍርደኛ የተላለፈበት የእስራት ጊዜ ከዋናው ቅጣት አይታሰብለትም፡፡ **፬.**በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፫፻፲</u>** የተላለፈው የእስራት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ የተላለፈውን የእስራት ቅጣቱ እንዲፈጸም በተወሰነበት ጊዜ መፈጸም ያልጀመረ እንደሆነ ቅጣቱ እንዲፈፀም ይደረጋል፣ በዋስትና የተያዘ ገንዘብ ወይም ንብረት ገቢ ይሆናል፡፡

ንዑስ ክፍል አራት

## <u>የገንዘብ ቅጣት</u>

**<u>አንቀጽ ፻፺፪ የገንዘብ ቅጣት አፈጻጸም</u>**

**፩.** ፍርድ ቤቱ የገንዘብ መቀጮ የወሰነ እንደሆነ ተቀጪው መቀጮውን ወዲያውኑ ገቢ እንዲያደርግ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፪.**ፍርደኛው የገንዘብ መቀጮውን ወድያውኑ ለመክፍል የማይችል ሲሆን ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፺፫ እና ፺፬ በተደነገገው መሠረት መቀጮውን እንዲከፍል ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፫.**ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ መፈፀሙን ተከታትሎ ያረጋግጣል፡፡

**፬.** የፍርደኛው ንብረቱ ተሸጦ ገቢ የሚደረገው ለቅጣቱ ተመጣጣኝ በሆነ ልክ ሆኖ ንብረቱ ከመሸጡ በፊት የቅጣት ገንዘቡን ገቢ ካደረገ የሽያጭ ሂደቱ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

**፭.** የገንዘብ ቅጣት የተወሰነበት ፍርደኛ፣ ቅጣቱን መክፈል ባለመቻሉ ብቻ መታሰር አይገባውም፡፡

**፮.** ፍርደኛው ቅጣቱን መክፈል ካልቻለ ቅጣቱ ወደ ሥራ ወይም የግዴታ ሥራ እንዲለወጥ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፺፫ የክፍያ ቅደም ተከተል</u>**

በሌላ ሕግ የተደነገገ ቢኖርም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፪ **(፬)** መሠረት የፍርደኛው ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጭ የተገኘ ገንዘብ እንደ ቅደም ተከተሉ ንብረቱን ለማስተዳደርና ለሀራጅ ሽያጭ የወጣ ወጪ፣ ለተጎጂ እንዲከፈል የተወሰነ ካሳ እና ለገንዘብ መቀጮ ክፍያ ይውላል፡፡

ንዑስ ክፍል አምስት**<u>የተጨማሪ ቅጣት አፈጻጸም</u>**

**<u>አንቀጽ ፻፺፬ ተጨማሪ ቅጣት</u>**

**፩.**ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ቅጣት የወሰነ እንደሆነ ስለቅጣቱ አፈጻጸም ግልጽ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**፪.**ተጨማሪ ቅጣቱ በፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ የሚፈጸም ቅጣት ዐይነት ሲሆን እንደተወሰነ በፍርድ ቤት ይፈፀማል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፺፭ ተጨማሪ ወይም የጥንቃቄ ርምጃዎችን ስለማሳወቅ</u>**

ፍርድ ቤቱ በፍርደኛው ላይ ተጨማሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ ርምጃዎችን ሲወስን ይኸው እንዲፈጸም አግባብ ላለው አካል ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፲፪ ንብረትን መውረስ</u>**

**፩.**ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ በዚህ ሕግ መሠረት የታገደ እና በሕግ እንዲወረስ የተደነገገ ንብረት እንዲወረስ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪.** ፍርድ ቤት ንብረት እንዲወረስ የወሰነ እንደሆነ ስለአወራረሱና ስለ አስተዳደሩ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**፫.** እንዲወረስ ትእዛዝ የተሰጠበት ንብረት እንዲለቀቅለት መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ማንኛውም ሰው ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡ የሚቀርበው ማመልከቻ በጹሑፍ ሆኖ አመልካቹ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ከሚያሳይ ማስረጃ ጋር አያይዞ ያቀርባል፡፡

**፬.** ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፫** መሠረት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የመውረስ ትእዛዙን ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

**፭.** ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፫** እና ፬ አመልካቹ ላቀረበው ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ አግባብነት ያለውን ሕግና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፮.**ንብረት እንዲወረስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ፡-

**(ሀ)** ንብረቱ በተገኘበት እንዲወረስ ትእዛዝ ያልተሰጠበት ከሆነ፣

**(ለ)**ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ ንብረቱን ለማግኘት ጥረት ማድረጉን ዐቃቤ ሕግ ካስረዳ፣

**(ሐ)** በተከሳሽ ማታለል ወይም ማጭበርበር የተሰወረ ከሆነ፣

ንብረቱ እንዲወረስ በአቤቱታ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**፯.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፮** የሚቀርበው የንብረት ይወረስ ጥያቄ ውሳኔ እንደተሰጠ ወይም ንብረቱ እንደተገኘ ወዲያውኑ መቅረብ ይገባዋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፲፫ ይቅርታ</u>**

**፩.**ፍርድ ቤቱ ፍርደኛው ጥፋቱን አምኖ ተበዳዩን ወይም ስለ እሱ ባለመብቶች የሆኑትን በግልጽ ይቅርታ እንዲጠይቅ የወሰነ እንደሆነ የአካባቢውን ልማድ ግምት ውስጥ በማስገባት፡-

**(ሀ)** ጥፋተኛው በእነማን ፊት ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት፣

**(ለ)** ይቅርታ የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜ፣

**(ሐ)** አስፈላጊ እንደሆነ ይቅርታ በሚፈጸምበት ቦታ መገኘት ያለበት የመንግሥት አካል፣

በመለየት ይቅርታ እንዲጠይቅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪**.ፍርድ ቤት ፍርደኛው በእሥር ላይ ያለ ከሆነ ማረሚያ ቤት የይቅርታ ሥርዐቱን እንዲያስፈጽም እና ይህንኑ ሥርዐት ሳይፈጽም በአመክሮ ሊለቀቅ እንደማይገባ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፫**.ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይቅርታው እንደአግባብነቱ በመገናኛ ብዙኃን ወይም ሌሎች አመች መንገድ እንዲገለጽ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ቅጣትን ስለመለወጥ፣አማራጭ ቅጣትና ስለመሰየም**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**ቅጣትን ስለመለወጥ**

**አንቀጽ ፻፲፯ የቅጣት ትእዛዝን መለወጥ**

**፩**.ቅጣትን ወይም የጥንቃቄ ርምጃን የወሰነው ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ ፺፬ መሠረት ቅጣትን ወይም የጥንቃቄ ርምጃውን ሊለውጠው ይችላል፡፡

**፪**.በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን በተመለከተ የሚሰጥ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ ርምጃ በዚህ ሕግ መሠረት ሊለወጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፲፰ የማመልከቻ አቀራረብና ውሳኔ**

**፩**. ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርደኛ ወይም ቅጣቱን ወይም የጥንቃቄ ርምጃው እንዲያስፈጽም፣ ወይም አፈጻጸሙን እንዲቆጣጠር የተፈቀደለት ሰው ወይም ተቋም የበላይ ኃላፊ ለፍርድ ቤት በጽሑፍ ወይም በሌላ ዘዴ ቅጣቱ እንዲለወጥ ማመልከት ይችላል፡፡

**፪**. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ለቀረበው ማመልከቻ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፫**. ፍርደኛው ቅጣቱን ከወሰነበት ፍርድ ቤት የአስተዳደር ወሰን ሥልጣን ውጭ በሆነ ማረሚያ የሚገኝ እንደሆነ የተቀጣበትን ወንጀል ለማየት የሥረ- ነገር የዳኝነት ሥልጣን ያለው ፍርደኛው በሚገኝበት ቦታ የሚገኝ ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፪ እስከ ፪፻፯ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ቅጣቱ እንዲቀየር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**አማራጭ ቅጣት**

**አንቀጽ ፻፸፺ መርህ**

**፩.**ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ወይም በፍርደኛው ጥያቄ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በዋና ቅጣት ምትክ አማራጭ ቅጣትን መወሰን ይችላል፡፡ በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የሚወሰነው አማራጭ ቅጣት በስራ ወይም በግዴታ ሥራ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**፪.**ፍርድ ቤት አማራጭ ቅጣት የሚወስነው የቅጣት ዓላማን ይበልጥ ያሳካል ብሎ ሲያምን እና ፍርደኛው፡-

**(ሀ)** ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በገንዘብ ብቻ የሚያስቀጣ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ በቀላል እስራትና በገንዘብ የሚያስቀጣ ወንጀል ከሆነ፣

**(ለ)** ጤንነቱ ተመርምሮ የጉልበት ሥራ መሥራት መቻሉ ሲረጋገጥ፣ እና

**(ሐ)** ከእስራት ይልቅ በጉልበት ሥራ ቢቀጣ ለሕብረተሰቡ አደገኛ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፫.**አማራጭ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፻፸፺፩ በውሳኔ የሚገለጹ ጉዳዮች**

**፩.**ፍርድ ቤት የአማራጭ ቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

**(ሀ)** የቅጣቱ ዐይነት፣ የሚፈፀምበት ቦታ እና የሚቆይበት ጊዜ ፣

**(ለ)** ከተወሰነ ቦታ ውጭ መሥራት ስለመቻሉ፣

**(ሐ)** የግል ነፃነቱ የሚገደብ እንደሆነ የገደቡ አግባብና ጊዜ፣

**(መ)** ፍርደኛው ቁጥጥር ሊደረግበት የሚገባ ስለመሆኑ እና የሚቆጣጠረውን አካል፣

**(ሠ)** ከሥራው ፍሬ ፍርደኛው ስለሚያገኘው ገቢ እና ለመንግሥት ገቢ ስለሚሆነው የገንዘብ መጠን፣ እና

**(ረ)** ተቋማት ወይም ግለሰቦች የጉልበት ሰራተኛ ሲቀጥሩ ቅድሚያ ለታራሚ ሊሰጡ እንደሚገባ፣ በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር ይኖርበታል፡፡

**፪.**ፍርድ ቤቱ ፍርደኛው ቅጣቱን በሚፈጽምበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ በማሕበራዊ ሳይንስ፣ በሥነ-ልቦና ወይም በሌላ ባለሙያ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫.ፍርድ ቤቱ ፍርደኛው አማራጭ ቅጣት አፈፃፀሙን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ ቅጣቱ በቀረው ጊዜ ልክ ወደ ቀላል እስራት እንዲለወጥ ያዛል፡፡

፬. ከፍርደኛው ግዴታ ሥራ መንግስት የሚያገኘው ገቢ ከአንድ ሦስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፳፪ አማራጭ ቅጣትን ማቋረጥ</u>**

፩. ፍርድ ቤት፡-

(ሀ) ፍርደኛው ግዴታውን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ፣

(ለ) ፍርደኛው ያለበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ወይም የቤተሰብ ኃላፊነቱ የቅጣቱን መፈጸም እንዲያቋርጥ ያስገደደው እንደሆነ፣ ወይም

(ሐ) አሳማኝ ነው ባለው ሌላ ምክንያት፣

በራሱ ተነሳሽነት ወይም በማንኛውም ሰው አመልካችነት የአማራጭ ቅጣቱ እንዲቋረጥ ሊወስን ይችላል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የቅጣቱ መፈጸም ሲቋረጥ ፍርድ ቤት እንደ ነገሩ ሁኔታ ቅጣቱ እንዲፈጸም፣ እንዲሻሻል ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲ መሠረት ለሌላ ጊዜ ተላልፎ እንዲፈጸም ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፳፫ የአማራጭ ቅጣት አስፈፃሚ አካል</u>**

የአማራጭ ቅጣት አስፈጻሚ አካላት በሕግ ይቋቋማሉ፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ስለመሰየም</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻፳፬ ዓላማ</u>**

የመሰየም ዓላማ የፍርደኛው መልካም ስም እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፳፭ የመሰየም ሥነ-ሥርዐት</u>**

፩. የተቀጣ ወይም ይቅርታ የተደረገለት ሰው የመሰየም ጥያቄ በወንጀል ሕጉ መሠረት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤትም፡-

(ሀ) የመሰየም ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

(ለ) ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ ፪፻ወ፫ እና ፪፻ወ፬ በተደነገገው መሠረት እንዲፈጸምና የተሰረዘው ቅጣት፣ የተሰያሚው ስም በጥፋት ተመዝግቦበት ከነበረው የወንጀለኞች መዝገብ ላይ እንዲፋቅ አግባብ ላላቸው አካላት ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ በግልጽ ችሎት ሊነበብ፣ በአደባባይ ወይም በብዙሃን መገናኛ ሊገለፅ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቱ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

## ስድስተኛ መጽሐፍ

## ፍርድን እንደገና ማየት፣ ይግባኝና ሰበር

## ምዕራፍ አንድ

## ተከሳሽ በሌለበት የተካሄደን የፍርድ ሂደትና ፍርድን እንደገና ስለማየት

### አንቀጽ ፫፻፳፯ ማመልከቻ ማቅረብ

፩. በወንጀል ተከሶ በሌለበት የተፈረደበት ሰው ፍርዱ ውድቅ እንዲሆንለት ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ምክንያቱን በመዘርዘር ማመልከት ይችላል፡፡

፪. ማመልከቻው ሊቀርብ የሚችለው አመልካቹ ፍርዱን ባወቀ ወይም በዚህ ሕግ በ አንቀጽ ፪፻፲፯ በተመለከተው አግባብ ከአቅሙ በላይ የሆነው ምክንያት በተወገደ በሠላሳ ቀን ውስጥ ነው፡፡

### አንቀጽ ፫፻፳፰ በማመልከቻው ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ

፩.ፍርድ ቤቱ ማመልከቻው በዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፯ መሠረት መቅረቡን ካረጋገጠ በኋላ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን በመወሰን ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥ የማመልከቻውን ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

፪. አመልካች በሌለበት የሞት ወይም የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት እንደሆነ የቀረበው ማመልከቻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ያዛል፡፡

፫. አመልካች በሌለበት የገንዘብ ቅጣት የተወሰነበት እንደሆነ የቀረበው ማመልከቻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ገንዘቡን በአደራ እንዲያስቀምጥ ወይም ዋስ እንዲጠራ ፍርድ ቤቱ ያዛል፡፡

፬.ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በሰጠበት ቀን አመልካቹ ያለበቂ ምክንያት የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፭.ዐቃቤ ሕጉ እና አመልካቹ የቀረቡ እንደሆነ አመልካቹ ማመልከቻውን መሠረት በማድረግ በቃል ያስረዳል፤ ዐቃቤ ሕግም መልስ ይሰጣል፡፡ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን አመልካቹ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፮.ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግንና የአመልካቹን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካቹ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ይወስናል፡፡ የአመልካቹ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከተረዳ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶ የተሰጠ ፍርድ እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፯. አመልካቹ ቀርቦ ሊከራከር ያልቻለው በዚህ ሕግ አንቀጽ **፪፻፲፰** በተደነገገው መሠረት መጥሪያ ያልደረሰው ወይም መጥሪያ ደርሶት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ፍርድ ቤት እንደአግባብነቱ የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ተነስቶ ጉዳዩ በሌላ ዳኛ ወይም ፍርድ ቤት እንደገና እንዲታይ ይመራዋል፡፡ ጉዳዩ የተመራለት ዳኛ ወይም ፍርድ ቤት ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ይግባኝ

**አንቀጽ ፫፻፳፫ ዓላማ**

የይግባኝ ዓላማ፡-

፩. በሥር ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ የተከሳሽን ይግባኝ የማቅረብ ሕገ መንግሥታዊ መብት ለማረጋገጥ፤

፪. በሥር ፍርድ ቤት የተፈጸመ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስሕተትን ለማረም፤

፫. ወጥ ወይም ተቀራራቢ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማድረግ፤

የሚፈጸም ነው፡፡

**አንቀጽ ፫፻፳፬ ይግባኝ ማቅረብ**

ማንኛውም ይግባኝ ጠያቂ ይግባኝ ከመጠየቁ በፊት በሥር ፍርድ ቤት መፍትሄ ማግኘት የሚገባው እንደሆነ ይህንን ሥርዐት ሳይፈጽም ይግባኝ ማቅረብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ ፻፵፴ ይግባኝ ስለሚያቀርቡ ሰዎች**

**፩.** በወንጀል ጉዳይ ላይ በተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችለው ዐቃቤ ሕግ፣ ፍርደኛ ወይም ጠበቃው ብቻ ናቸው፡፡

**፪.** ከወንጀል ክስ ጋር ተያይዞ በቀረበ የፍትሐብሔር ክስ ላይ በተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት ይቻላል፡፡ ይግባኝ ማለት የሚችለው እንደነገሩ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ፣ ተጎጂ፣ ፍርደኛ፣ ጠበቃው ወይም ሌላ በፍትሐብሔር ሕግ ይግባኝ እንዲያቀርብ መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

**፫.** ይግባኝ የሚቀርበው በይግባኝ የወንጀል ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው፡፡

**አንቀጽ ፻፵፴፩ ይግባኝ የሚባልባቸው ጉዳዮች**

**፩.**በዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን፡-

**(ሀ)** ከፍርድ በፊት በማንኛውም ሁኔታ ለዘለቄታ መዝገብ በሚያዘጋ ትእዛዝ ፣

**(ለ)** የተከሳሽ የዋስትና መብትን በመከልከል በሚሰጥ ውሳኔ፣

**(ሐ)** በተከሳሹ የጥፋተኝነት ወይም ነፃ የማለት ፍርድ፣ እና

**(መ)** በቅጣት ዐይነትና መጠን፣

ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

**፪.**ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔን አጽንቶ ቅጣቱን የለወጠ ወይም ቅጣቱን አጽንቶ ጥፋተኛ ነው የተባለበትን ውሳኔ የለወጠ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው በተባለበት ወይም ቅጣቱ እንዲለወጥ በተወሰነበት ላይ ብቻ ሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

**፫.**ተከሳሽ በሌለበት በተፈረደው ጉዳይ ወደ ክርክር ለመግባት በቀረበ አቤቱታ ላይ በቂ ምክንያት ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ባለመኖሩ አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ ስለጥፋተኝነት ፍርድ ወይም ስለቅጣት መጠን ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፵፴፪ ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች**

**፩.** ይግባኝ፡-

**(ሀ)** በዚህ ሕግ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር በዕርቅ ወይም በድርድር ወይም በሌላ አማራጭ የመፍትሔ ሥርዐት ባለቀ ጉዳይ፣

**(ለ)** ማስረጃ በመቀበል ወይም ባለመቀበል በሚሰጥ ትእዛዝ፣

**(ሐ)** ተከሳሹ ጥፋቱን ያመነ እንደሆነ በእምነት ቃሉ መሠረት የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ፣

**(መ)**ተከሳሽ በሌለበት በተወሰነ ጉዳይ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በተሰጠ ውሳኔ፤

ላይ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**፪**.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶ መዝገብ የተዘጋ እንደሆነ ይግባኝ በሚባልባቸው ጉዳዮች ላይ ለይግባኝ ምክንያቶች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፫ የቅጣት ውሳኔ ማገድ**

**፩**.ፍርደኛው ይግባኙ ከመቅረቡ በፊት የቅጣት ውሳኔ እንዲታገድ ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ፍርዱ፣ ውሳኔው፣ ብይኑ ወይም ትእዛዙ ከተሰጠ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡

**፪**. የቅጣት ውሳኔውን የሰጠው ችሎት ውሳኔው እንዳይፈጸም ከሰባት ተከታታይ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል፡፡

**፫**.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የእግድ ትእዛዝ የሚሰጠው የእግድ ጥያቄው ሳይዘገይ መቅረቡ እና ፍርዱ፣ ውሳኔው ወይም ትእዛዙ ቢፈጸም የማይተካ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የታመነ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

**፬**. ስለ ካሣ ወይም ኪሣራ ወጪ የተሰጠ ፍርድ ከመፈጸም አይታገድም፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፬ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስልጣን**

**፩**.ፍርደኛው ይግባኝ ከመሰማቱ በፊት ወይም ይግባኙ በሚሰማበት በማናቸውም ጊዜ ፍርዱ፣ ውሳኔው፣ ብይኑ ወይም ትእዛዙ እንዲታገድ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማመልከት ይቻላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበውን አቤቱታ ተመልክቶ ተገቢ የመሰለውን ትእዛዝ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

**፪**.ፍርደኛው ይግባኙ እስኪወሰን ድረስ በዋስትና ወረቀት የተለቀቀ እንደሆነ የእስራቱ ቅጣት የይግባኙ ፍርድ ቤት ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ አይጀመርም፡

**፫**. ዐቃቤ ሕግ የተያዘ ንብረት፣ ገንዘብ ወይም ኤግዚቢት እንዳይመለስ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በይግባኝ ጥያቄው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተከሳሹ፣ በተያዘው ንብረት ወይም በገንዘብ ወይም ኤግዚቢት ላይ በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሳይፈጸም እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬.ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ቤት እንዲፈጸሙ ለጥንቃቄ የሰጣቸው ትእዛዞች ይግባኝ የተባለባቸው ቢሆኑም መፈጸም አለባቸው፡፡

፭.ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ወደ ነገሩ ለመግባት በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን እና የሥር ፍርድ ቤት ፍርድ ፣ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ቢፈጽም የማይተካ ጉዳት ይደርሳል ብሎ ሲያምን፣ የእግድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፫ ሰነድ ፣ ግልባጭ ወይም መረጃ ማግኘት**

፩.በሌላ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ  መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ሰው መዝገቡ ውስጥ የሚገኝን  ሰነድ ወይም  የሰነድ ግልባጭ ወጪውን ችሎ በማንኛውም ጊዜ ማግኘት ይችላል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ፣  ፍርደኛው፣ ጠበቃው፣ የወንጀል ተጎጂ ወይም ሌላ ባለመብት የሚጠይቀውን ግልባጭ ወድያውኑ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፬ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ**

፩.ማንኛውም በፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ማለት ሲፈልግ የይግባኝ መጠየቂያ  ማመልከቻ ፍርዱን፣ ውሳኔውን፣ ብይኑን ወይም ትእዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት በጽሑፍ ወይም በቃል ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ሬጅስትራር የፍርዱን፣ ውሳኔውን ወይም ትእዛዙን ግልባጭ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

፪.ይግባኝ ባይ የይግባኝ ማመልከቻውን ወይም የይግባኝ መጠየቂያውን  በአካል፣ማረሚያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ በጠበቃው ወይም በማረሚያ ቤቱ በኩል ማቅረብ ይችላል፡፡

፫. ይግባኝ ባዩ ማረሚያ ቤት ከሆነ ማረሚያ ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ፣ የይግባኝ መጠየቂያና የይግባኝ ማመልከቻ ቅጽ እንዲያገኝ እንዲሁም ማመልከቻውን ለመጻፍ ወይም የውሳኔ ግልባጭ ለማስተርጎም እንዲችል ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፣ የገንዘብ አቅም የሌለው በሆነ ጊዜም በዚህ ሕግ አንቀጽ **፲፬(፫)** በተደነገገው መሠረት በመንግስት ወጪ የትርጉም አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

፬.የይግባኝ ማመልከቻ ፍርዱ፣ ውሳኔው ወይም ትእዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስልሳ ተከታታይ ቀናት ለይግባኝ  ሰሚ ፍርድ ቤት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፭.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው ጊዜ የፍርድ፣ የውሳኔ ወይም የትእዛዝ ግልባጭ ለመስጠት የወሰደውን ጊዜ አይጨምርም፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፭ የይግባኝ ማመልከቻ ይዘት**

፩. የይግባኝ ማመልከቻ፣

(ሀ) ቀን፣ወር፣ ዓመተ ምኅረት፣ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስምና አድራሻ፣

(ለ) የይግባኝ ባይ ስምና አድራሻ፣

(ሐ) የመልስ ሰጪ ስምና አድራሻ፣

(መ) ይግባኝ የተባለበት ጊዜ አለማለፉን ማረጋገጫ፣

(ሠ) ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ስምና አድራሻ እንዲሁም የመዝገቡ ቁጥር፣

(ረ) ይግባኝ የተባለበት የወንጀል ጉዳይ፣

(ሰ) ይግባኝ ባይ ቅር የተሰኘበትና ስሕተት ነው ብሎ ያመነበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ጉዳይ፣

(ሸ) የሚጠይቀውን ዳኝነት፣

(ቀ) የይግባኝ ባይ ወይም የጠበቃው ፊርማ፣

አካቶ አጭርና ግልጽ በሆነ መልኩ ይቀርባል፡፡

፪. ይግባኝ ባይ አዲስ ማስረጃ እንዲቀርብለት የሚፈልግ ከሆነ ይህንኑ የሚገልፅ አቤቱታ ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ አቤቱታውም አዲስ ማስረጃ እንዲቀርብ ያስፈለገበትን ምክንያት በዝርዝር ይገልፃል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፴፫ ሬጅስትራር የሚያከናውነው ተግባር</u>**

፩. የፍርድቤቱ ሬጅስትራር፡-

(ሀ) የይግባኝ ማመልከቻው ወይም ማስፈቀጃው በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፫፻፴፪</u>**የተዘረዘሩ ነጥቦችን ማሟላቱን፣

(ለ) የሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ መያያዙን ወይም ከመረጃ ቋት መቅረቡን፣

በማረጋገጥ መዝገብ በመክፈት እና ይግባኙ ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም የሚለውን ለመስማት ቀጠሮ ሰቶ ለችሎት ያቀርባል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ይግባኙ የቀረበው በፍርደኛው ከሆነ ዐቃቤ ሕግ እንዲቀርብ መጥሪያ እንዲደርሰው ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ ይግባኙን የማየት ሥልጣን የሌለው እንደሆነ የይግባኝ ማመልከቻውን የማይቀበል መሆኑን ሬጅስትራሩ ለይግባኝ ባዩ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

፬. ይግባኝ ባይ ሬጅስትራሩ በሰጠው ውሳኔ የማይስማማ እንደሆነ ቅሬታውን ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት እንደአስፈላጊነቱ በጽሑፍ ወይም በቃል ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፕሬዚዳንቱም ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፮.** ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ያለው እንደሆነ ሬጅስትራር፣ መዝገቡን ለችሎት ያቀርባል፣ መዝገቡ የቀረበበት ችሎት፣ ቀጠሮ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ለይግባኝ ባይ ይነግራል፡፡

***<u>አንቀጽ ፻የ፹፱ የይግባኝ ማስፈቀጃ</u>***

**<u>፩</u>.**ይግባኝ ባይ በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፻የ፹፯</u>** የተደነገገው ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ ጊዜው ያለፈበትን ምክንያት የያዘ የይግባኝ ማስፈቀጃ ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር አያይዞ በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**<u>፪</u>.**ይግባኝ ባይ፣ የይግባኝ ባይ ተወካይ ወይም ጠበቃው መቅረቡን ካረጋገጠ በኋላ ማመልከቻውን በመመርመር ይግባኙን በጊዜው ያላቀረበበት በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ የሚያረጋግጥ እንደሆነ ተቃዋሚውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙ እንዲሰማ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**<u>፫</u>.**ችሎቱ መዝገቡን መርምሮ ወድያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

***<u>አንቀጽ ፻የ፺ የይግባኝ ቅሬታ መመርመር</u>***

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት፡-

**<u>፩</u>.**የቀረበው ይግባኝ በዚህ ሕግ መሠረት የተሟላ መሆኑን፣ ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ ሥልጣን ከሌለው መዝገቡን ዘግቶ ይህንኑ ለይግባኝ ባይ ያሳውቃል፡፡

**<u>፪</u>.**ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ካለው ይግባኝ ባዩ መቅረቡን ያረጋግጣል፣ ይግባኝ ባዩ ያልቀረበ እንደሆነ ውሳኔውና የይግባኝ ማመልከቻውን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ ይግባኝ ባዩ ሳይቀርብና ሳይሰማ ውሳኔ መስጠት የማይቻል እንደሆነ ይግባኙን ሰርዞ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

***<u>አንቀጽ ፻የ፺፩ መጥሪያ</u>***

**<u>፩</u>.**በዚህ ሕግ ስለ መጥሪያ በአንቀጽ **<u>፪የ፲፫</u>** የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኝ ባይ ወይም መልስ ሰጪ በማረሚያ ቤት የሚገኝ እንደሆነ መጥሪያው በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ፣ በፍርድ ቤቱ ፖስተኛ ፣ በዐቃቤ ሕግ ወይም በመርማሪ ፖሊስ አማካኝነት በማረሚያ ቤቱ በኩል ሊደርሰው ይችላል፡፡

**<u>፪</u>.** ይግባኝ ባዩ ፍርደኛ ከሆነ መጥሪያው በፍርድቤት በኩል ለዐቃቤሕግ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

***<u>አንቀጽ ፻የ፺፪ ይግባኙን መስማት</u>***

**<u>፩</u>.**ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ በቀጠሮ ቀን መቅረባቸውን በማረጋገጥ፡-

**https://ethiolex.com**

**(ሀ)** ሁለቱም ከቀረቡ ይግባኙን ይሰማል፣ እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**(ለ)** ይግባኝ ባይ ቀርቦ መልስ ሰጪ ካልቀረበ ያልቀረበው መጥሪያ ሳይደርሰው ቀርቶ እንደሆነ በድጋሚ መጥሪያ እንዲደርሰው ያደርጋል፣ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ይሰማል፡፡

**(ሐ)** መልስ ሰጪ ቀርቦ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ መዝገቡን መርምሮ የመልስ ሰጪን መልስ ይሰማል፣ መልስ ሰጪ ይግባኙን ያልተቃወመው እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**(መ)** መልስ ሰጪ ቀርቦ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ፣ መልስ ሰጪ ይግባኙን ከተቃወመው እና የይግባኝ የቃል ክርክር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የይግባኝ ባይ የቃል ክርክር ሳይሰማ ውሳኔ መስጠት የማይቻል እንደሆነ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

**(ሠ)** ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ ካልቀረቡ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

**፪.** ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ በቀጠሮ ቀን መቅረባቸውን ካረጋገጠ ይግባኝ ባይ በቅድሚያ ይግባኙን እንዲያስረዳ እና መልስ ሰጭም ለቀረበው ይግባኝ መልስ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ይግባኝ ባይ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**፫.** ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን መርምሮ ስልጣን የለኝም ብሎ ይግባኙን ላይቀበለው ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ውሳኔ ይግባኝ ባይ ስልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙን ከማቅረብ አያስቀረውም፡፡ ይግባኙን ለማቅረብ የይግባኝ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜም ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲታይ ለቆየበት ጊዜ ያህል ይቋረጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፫ የተዘጋ መዝገብ መክፈት</u>**

**፩.** በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፫፻፶፪</u>** ንዑስ አንቀጽ ፩(ሠ) በተደነገገው መሠረት መዝገቡ የተዘጋበት ይግባኝ ባይ መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ውስጥ የይግባኝ ክርክሩ እንዲሰማለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፪.**ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይ በቀጠሮው ቀን ያልቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካረጋገጠ መዝገቡ ተከፍቶ ይግባኙ እንዲሰማ እና ይግባኝ የሚሰማበትን ቀን በመወሰን መልስ ሰጪ እንዲጠራ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፬ ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል</u>**

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ ማስረጃው የሚቀርብበትን ምክንያት በመግለጽ ማስረጃው እንዲሰማ ወይም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፵፫ ውሳኔ መስጠት</u>**

፩.ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ በመሻር፣ በማጽናት ወይም በማሻሻል ፍርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ፣

**(ሀ)** በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በመመስረት እንደሆነ፣

**(ለ)** ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት ፣ወይም

**(ሐ)** ወደ ሥር ፍርድ ቤት ሊያስመልስ የሚችል ሌላ ምክንያት ላይ ተመሥርቶ የተሰጠ እንደሆነ፣

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ቀድሞ ጉዳዩን ወዳየው ፍርድ ቤት ወይም ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ሥር ፍርድ ቤቱ ሌላ ችሎት ተመልሶ እንዲታይ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመቺ ነው ብሎ ካመነ ጉዳዩን መመለስ ሳያስፈልገው እራሱ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. ይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ ፍርደኛው የሞተ እንደሆነ መዝገቡ ይቋረጣል፤ ሆኖም ከመዝገቡ ጋር በተያያዙ ንብረት የመወረስ ወይም የካሣ ወይም ፍርደኛው በመሞቱ ሊቋረጡ የማይችሉ ተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤት መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ውሳኔ ይግባኝ ባልጠየቁ በሥር ፍርድ ቤት በአንድነት በተፈረደባቸው ሰዎች ላይ በውሳኔው የሚጠቀሙ ከሆነ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፮. በዚህ ሕግ ስለመደበኛ የክርክር ሥነ-ሥርዐት የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለይግባኝ ክርክርም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**

**<u>ሰበር</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻፵፬ ዓላማ</u>**

የሰበር ዓላማ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን በማረም በፍርድ ቤቶች ወጥ ወይም ተቀራራቢ የሕግ አተረጓጎምን እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፵፭ መርህ</u>**

፩. ሰበር መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት የመጨረሻ ውሳኔ የሚታረምበት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን ነው ፡፡

፪.በዚህ ክፍል በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ለይግባኝ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ ለሰበር ጉዳዩችም ተፈጻሚ ይሆናሉ ፡፡

፫. ለዚህ ክፍል ዓላማ **"የመጨረሻ ውሳኔ"** ማለት በሕግ መሠረት የመጨረሻ የተባለ ወይም በማናቸውም ምክንያት ይግባኝ የማይባልበት ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፶፰ የሰበር ማመልከቻ ማቅረብ</u>**

፩.የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ጉዳይ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ተከራካሪ ወገን አቤቱታውን ለሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ ይችላል፡፡

፪.ማንኛውም የሰበር ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት የይግባኝ፣ ፍርድን እንደገና የማየት ሥርዐት ወይም ሌላ ሕጋዊ ሥርዐት መጠናቀቅ ይገባዋል፡፡

፫.የሰበር ማመልከቻ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ ዘጠና ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻፶፱ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት</u>**

መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባለው ውሳኔው፣ ፍርዱ ብይኑ ወይም ትእዛዙ በሕግ ሥርዐቱ ላይ መናጋት የሚፈጥር ሆኖ፤-

፩.የሕገ መንግሥት ወይም የሕግ ድንጋጌን ወይም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ውሳኔን በመጣስ ፣

፪.የተሻረ ወይም አግባብነት የሌለውን ሕግ መሠረት በማድረግ፣

፫.የወንጀል ሕግ በጠቅላላው ክፍል የተደነገጉ መርሆችን በመጣስ

፬.የተዛባ የሕግ ትርጉምን መሠረት በማድረግ ፣

፭.በሕግ ከተሰጠ ሥልጣን ክፍፍል ውጭ ፣ወይም

፮. በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ፣ የተሰጠ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶ ለሰበር የማይቀርብ ጉዳይ</u>**

የሰበር ማመልከቻ፣

**፩.** መሠረታዊ ያልሆነ የሕግ ስህተት ባለው ጉዳይ፣

**፪.** የፍሬነገር ስህተት ባለበት ውሳኔ፣ወይም

**፫.**አግባብነት ባለው ሕግ የሚወሰድ ርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በነፃ በተለቀቀበት ጉዳይ መብቴ ተጥሷል በማለት ብቻ በሚቀርብ አቤቱታ፣

ላይ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፩ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝን ማገድ</u>**

**፩.** እግድን በተመለከተ ለይግባኝ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፫፻፴፫**የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር ጥያቄው መነሻ የሆነውን ውሳኔ የሰጠው ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሆነ ፣

**(ሀ)** በፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት፣

**(ለ)** ጉዳዩ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ እንደሆነ የሰበር ችሎቱ፣

የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በፕሬዚዳንቱ የሚሰጥ የእግድ ትእዛዝ ከሰባት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

**፫.** በዚህ አንቀጽ መሠረት በተሰጠ እግድ ላይ የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ የእግድ ትእዛዙን ለሰጠው አካል ሊቀርብ ይችላል፤ ጥያቄውም እንደቀረበ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፪ የሰበር ማመልከቻ ይዘት</u>**

የሰበር ማመልከቻ የክሱን ይዘትና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችን ግልባጭ፣ ተፈጸመ የተባለው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት እና የሚጠይቀውን ዳኝነት አጭርና ግልጽ ይሆናል፡፡ ከማመልከቻው ጋር በየደረጃው የተሰጡ ፍርዶች በአመልካቹ ወይም ከመረጃ ቋት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፫የሰበር ማመልከቻን መመርመር</u>**

የሰበር ሰሚ ችሎት ማመልከቻውን መሠረት በማድረግ፡-

**፩.**አመልካቹን አቅርቦ ማነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ጉዳዩን መርምሮ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የለም ብሎ ካመነ ምክንያቱን በማብራራት አቤቱታውን ውድቅ ያደርጋል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፪.መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ይህንኑ በግልጽ ለይቶ በማመልከት ተጠሪው መልስ እንዲሰጥበት ቀጠሮ በመስጠት የሰበር ማመልከቻውን ከመጥሪያው ጋር እንዲደርሰው ያደርጋል፤

፫.የሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ በሚሰማበት ቀን ተከራካሪዎች ባይቀርቡም መዝገቡ ተመርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፬ የሰበር ውሳኔ መስጠት</u>**

የሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ከሰማ በኋላ የለየውን አከራካሪ ነጥብ እና ማመልከቻ የቀረበበትን ውሳኔ በመሻር፣ በማጽናት ወይም በማሻሻል ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ችሎቱ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለሥር ፍርድ ቤቱ ሌላ ችሎት ወይም በሌላ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ሊመልሰው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፭ የሰበር ውሳኔ ውጤት</u>**

፩. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በሰበር ችሎቱ ፍርድ ወይም በሌላ ሕግ ካልተለወጠ በስተቀር በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት አለው፡፡

፪. ሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ነው በማለት የሰጠውን የሕግ ትርጉም ለይቶ በውሳኔው ላይ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ አስገዳጅ የሚሆነውም ፍርዱ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**<u>ምዕራፍ አራት</u>**

**<u>የመጨረሻ ፍርድን እንደገና ማየት</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፮ ዓላማ</u>**

የመጨረሻ ፍርድን እንደገና የማየት ሂደት ዓላማ በተዛባ ፍርድ ንፁኃን እንዳይቀጡ ፍርዱን ለማረም ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፯ የወንጀል ፍርድ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩.ማንኛውም የጥፋተኝነት ፍርድ የተሰጠበት ፍርደኛ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ወንጀል አለመፈጸሙን የሚያሳይማስረጃ በተገኘ ጊዜ ፍርደኛው፣ ወኪሉ፣ ቤተሰቡ ወይም ዐቃቤ ሕግ ፍርዱ እንደገና እንዲታይ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪.ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም የሚቀርበው ማስረጃ ቀደም ብሎ ቢገኝ ኖሮ ፍርዱ በማያጠራጥር ሁኔታ አይሰጥም ነበር የሚያስብል ሆኖ፣

**(ሀ)** ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ጥፋተኛውን ነፃ ሊያደርግ የሚችል ጠቃሚ ማስረጃ ከተገኘ፣

**(ለ)** ከፍርድ በኋላ በሳይንሳዊ ዘዴ የተገኘ እውነት እንደሆነ፣

**(ሐ)** ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ዳኛው ኃላፊነቱን አጓድሏል ተብሎ በወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፣

**(መ)** በጉዳዩ ላይ ሌላ በነፃ የተለቀቀ ሰው ከፍርድ ቤት ውጭ በሚታመን ሁኔታ ወንጀሉን መፈጸሙ ጥፋተኛነቱን በማመን ቃል የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

**(ሠ)** እውነተኛ መስሎ የቀረበ ማስረጃ በሐሰት ወይም በማጭበርበር መዘጋጀቱ ሲረጋገጥ፣

ነው፡፡

፫.ማመልከቻው የሚቀርበው በጉዳዩ ላይ የጥፋተኝነት ፍርድ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሰጠው ፍርድ ቤት ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፫ የማመልከቻው ይዘትና የሚቀርብበት ጊዜ</u>**

፩.ፍርዱ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ በማንኛውም ጊዜ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪.በዚህ ሕግ የመጨረሻ ፍርድ እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ የይግባኝ ማመልከቻ በሚቀርብበት ዓይነት መሆን ይኖርበታል፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፶፬ ማመልከቻውን መስማት እና መወሰን</u>**

፩.ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታና ማስረጃ መርምሮ ፍርዱን እንደገና ለማየት በቂ ምክንያት ካላገኘ አቤቱታውን ውድቅ ያደርጋል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ ፍርዱን እንደገና ለማየት በቂ ምክንያት ካገኘ ዐቃቤሕግ መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጥበት ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

፫.የዐቃቤሕግንመልስና የፍርደኛውን ማስረጃ መርምሮ ፍርድ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፷ ካሣ</u>**

፩. ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ የተሰጠውን ፍርድ የሻረ ወይም ያሻሻለ እንደሆነ ቅጣቱን ባስከተለው ውሳኔ ምክንያት አመልካቹ ለደረሰበት የሞራልና የንብረት ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ ከመንግሥት እንዲከፈል ያዛል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ የሞት ቅጣት በመሆኑ ተጎጂው በሕይወት የሌለ እንደሆነ ለተጎጂ ሊከፈል ከሚገባው ካሣ በተጨማሪ ቅጣቱን ባስከተለው ውሳኔ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት የትዳር ጓደኛ ወይም ወራሽ የሞራል እና የንብረት ጉዳት ካሣ ከመንግሥት እንዲከፈል ያዛል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ተጎጂውን፣ የትዳር ጓደኛውን ወይም ወራሾቹን ለደረሰባቸው ጉዳት ይቅርታ ይጠይቃል፡፡

፬. <u>የካሳ ዓይነትና መጠን በፍትሐብሔር ሕግ እና ሥነሥርዐት መሠረት ይወሰናል፡፡</u>

*[*

**<u>ሰባተኛ መጽሐፍ</u>**

**<u>ልዩ ሥነ-ሥርዐት</u>**

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ተፈፃሚነት</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻፹፩ ተፈፃሚነት</u>**

**፩.** በልዩ ሥነ -ሥርዐት የሚታዩ ጉዳዮች፡-

**(ሀ)** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች ፤እና

**(ለ)** ደንብ መተላለፍ ፤

ናቸው፡፡

**፪.** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፩** እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መጽሐፍ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ መደበኛው የክርክር ሥነሥርዓት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶችና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች የክስ ሥነ ሥርዐት</u>**

**<u>አንቀጽ ፫፻፹፪ መርህ</u>**

፩.በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ምርመራ፣ ክስ መስማት፣ የፍርድ ሂደትና ውሳኔ በተፋጠነና መደበኛ ባልሆነ ሥነ ሥርዐት ይመራል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚከናወን ሥነ ሥርዐት፡-

**(ሀ)** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጥቅምና ደኅንነት ማስከበርና ቅድሚያ ይሠጣል፡፡

**(ለ)** ወጣቱን የማያገል፣ የሚያሳትፍ፣ ምቹና የማያስፈራ መሆን አለበት፡፡

**(ሐ)** የወጣቱን ማሕበራዊና ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና በማሕበራዊ፣ በሥነ-ልቦናና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ባለሙያዎች ይታገዛል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፳፫ ተፈፃሚነት</u>**

**፩.** የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ዕድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት የሆነ ወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርምእድሜውከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ስምንት ዓመት የሆነው ወጣት እንደነገሩ ሁኔታ አካለ መጠን እንደላደረሰ ተቆጥሮ የምርመራ፣የክስና የክርክር ሂደቱ በዚህ ልዩ ሥነሥርዐት ድንጋጌዎች ሊመራ ይችላል፡፡

**፫.** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት የሞላው እንደሆነ የምርመራ፣ የክስና የክርክር ሂደቱ በዚህ ሕግ በተመለከቱ መደበኛ ድንጋጌዎች እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

**፬.** በዚህ ክፍል የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እስካልተቃረኑና በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ጥቅምና ደኅንነት እስከጠበቁ ድረስ የዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው በተገኙ ወጣቶች በሚቀርብ የወንጀል ክስ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፳፬ የምርመራ አጀማመርና የክስ አመሠራረት</u>**

**፩.** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቷል የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር መርማሪ ፖሊሱ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወላጁ፣ ሞግዚቱ፣ ወይም አሳዳሪው በቅርብ ወደሚገኘው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይዞት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፪.** ፍርድ ቤት በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ያመጣ ሰው የወንጀሉንና የማስረጃውን ዝርዝር እንዲገልጽ ያደርጋል፤ የቀረበውን አቤቱታ እና የሚሰጠውን ቃል በመዝገብ ይጽፋል፡፡

**፫.**ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታና ቃል መርምሮ ምርመራ እንዲጀመር ከወሰነ ምርመራው የሚፈጸምበት ዝርዝር ሁኔታ ላይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ መርማሪው ፖሊስ የወጣቱን ቃል አይቀበልም፡፡

**፬.** ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ፍርድ ቤት የሚያቀርበው እንደሆነ ወላጁ፣ ሞግዚቱ፣ ወይም አሳዳሪው እና ተበዳዩ አብረው እንዲቀርቡ ተገቢውን ይፈጽማል፡፡

**፭.**ጉዳዩ መቀጠር ወይም ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ሌላ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚያስፈልገው እንደሆነ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ነገሩ በሚሰማበት ቀን ለማቅረብ ለሚችሉ ለወላጆቹ፣

ለአሳዳጊው፣ ለዘመዶቹ፣ ለመንግሥታዊ ተቋም ወይም ሌላ ድርጅት ወይም ራሱን ለቻለ እምነት ለሚጣልበት ሰው እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ምስክሮች ነገሩ በሚሰማበት ቀን ሊቀርቡ ግዴታ መግባት አለባቸው፡፡

**፫.**ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **፪** መሠረት ትእዛዝ ሲሰጥ፣

**(ሀ)**ከሌሎች ወንጀል ፈፃሚዎች ጋር እንዳይቀላቀል፣

**(ለ)** ለሞራላዊ፣ አካላዊ ወይም ሥነ-ልቦናዊ አደጋ የማይጋለጥ መሆኑ እና

**(ሐ)**የተጠረጠረበት ወንጀል ክብደት እና ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የማያደናቅፍ መሆኑን ፣

ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፫ ምርመራው የሚያካትታቸው ሁኔታዎች</u>**

**፩.** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን በተመለከተ የሚካሄድ ምርመራ፤-

**(ሀ)** ባሕሪውን፣

**(ለ)** የግል ኑሮውን፣ ያደገበትንና የኖረበትን አካባቢ ሁኔታ፣

**(ሐ)** የተከሰሰበትን ወንጀል ፈፀመ ከተባለበት ጊዜ በፊትና በኋላ የነበረውን ጠባይ፣እና

**(መ)** ሌሎች ለእርምትና ለትምህርታዊ እርምጃዎች አወሳሰድ መሠረት፣

የሚሆኑ ሁኔታዎች ለማጣራት የሚረዳ መሆን ይኖርበታል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱትን ሁኔታዎች በትክክል ለማረጋገጥ እንደነገሩ ሁኔታ መርማሪው፣ ዐቃቤ ሕጉ ወይም ፍርድ ቤቱ የወጣቱን ወላጆች፣ አሳዳሪ፣ ቤተዘመድና እንዲሁም በቂ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን ወይም ተቋማትን ጠርቶ መጠየቅ፣ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች መመልከትና እንደአስፈላጊነቱ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፬ ቤተሰብ ወይም አሳዳጊ መጥራት</u>**

በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወደ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ወላጆቹ፣ አሳዳጊው፣ ወይም ከቤተ ዘመዶቹ አንዱን ሰው እንዲሁም ዕጓለ ማውታው ወይም የተቋም ተወካይ ባልቀረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እነዚህ ሰዎች እንዳሉ ጠይቆ እንዲቀርቡ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፹፯ በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ማቆየት</u>**

**፩.**ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ አይሰጥም፡፡

**፪.**በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፫፻፹፬</u>** ንዑስ አንቀጽ **፫** ማቆየት ካልተቻለ እና፡-

**(ሀ)** በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ስለመሆኑ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው እና በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት መቆየቱ ሊደርስበት ከሚችል አደጋ የሚጠብቀው እንደሆነ፣

**(ለ)** ከወላጅ፣ ከሞግዚቱ ወይም ከሌሎች ቤተ ዘመዶቹ እንደሚያመልጥ ለማመን በቂ ምክንያት ያለ እንደሆነ፣ ወይም

**(ሐ)** ክሱ በመሰማት ላይ እያለ ከሀገር የሚወጣ ስለመሆኑና ተመልሶ እንደማይቀርብ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር፣

በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ሊቆይ ይችላል፡፡

**፫.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ ለተገኘ ወጣት በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት ሊቆይ የሚችለው በወንጀል ነገር ገብተው ለተገኙ ወጣቶች በተዘጋጀ በተለየ ቦታ ብቻ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፹፰ የተቋም ክትትል</u>**

ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የአቤቱታውን ወይም የክስ ማመልከቻውን እና ሌሎች ተገቢ ሰነዶችን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ደኅንነት መጠበቅ ለሚችል ተቋም በመላክ ጉዳዩን እንዲከታተል ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፹፱ ጊዜያዊ ትእዛዝ</u>**

**፩.**በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የፍርድ ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ወላጁ፣ ሞግዚቱ፣ አሳዳሪው ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ከወጣቱ ጋር ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ፍርድ ቤቱ ጊዜያዊ ትእዛዝ እንዲሰጥ አግባብ ያለው አካል ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፪.**በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት በተመለከተ ፍርድ ቤት፡-

**(ሀ)** በተወሰነ ሰው ወይም ተቋም ጊዜያዊ ጥበቃ ሥር እንዲሆን፣

**(ለ)** ለመጎብኘት መብት ባላቸው ሰዎች ላይ ገደብ እንዲጣል፣

**(ሐ)** ለጤናው፣ ለምግቡና ለመልካም አያያዙ አስፈላጊ የሆነ ወጪ እንዲመደብ፣

**(መ)** በሚኖርበት ቤት ወይም ቦታ ያለ ሰው ለቀ እንዲሄድ፣

**(ሠ)** ወላጁ፣ አሳዳሪው፣ ጠባቂ ወይም ሌላ ግንኙነት ያለው ሰው አስፈላጊውን ምክር እንዲያገኝ፣ ወይም

**(ረ)** ማንኛውም ከጥቅሙ ጋር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት እንዲቆም፣

ፍርድ ቤት ጊዜያዊ ትእዛዝ እንዲሰጥለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፫.** ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ ለተገኘ ወጣት ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የወጣቱን አስተያየት በመቀበል የከሳሽና የተጎጂ መገኘት ሳይጠብቅ ጊዜያዊ ትእዛዙን ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

**፬.** ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ጊዜያዊ ትእዛዝ በራሱ አስተያየት ወይም በሌላ ሰው አመልካችነት እንደገና መርምሮ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፫ ክስ መመሥረት</u>**

**፩.**በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ወጣት ላይ የቀረበ ክስ አሥር ዓመት እና በላይ ወይም በዕድሜ ልክ ወይም በሞት የሚያስቀጣ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለወጣት ጥፋት አድራጊ በሚስማማ መልክ በጽሑፍ ያቀርባል፡፡

**፪.**በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ወጣት ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ አካለ መጠን ከደረሰ ሰው ክስ ጋር አብሮ መታየት የለበትም፡፡ ክሱ በአንድ ላይ የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱ ተለይቶ እንዲቀርብ እና ተነጥሎ እንዲሰማ ያዛል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፬ መጥራት</u>**

**፩.**በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚጠራው በወላጆቹ፣ በአሳዳሪው፣ በሞግዚቱ ወይም አደራ በተቀበለው ሌላ ሰው ወይም ተቋም አማካኝነት መሆን አለበት፡፡

**፪.**በጥበቃ ሥር ያለ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የሚጠራው በጥበቃው አስተዳደር በኩል ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፭ ክሱ የሚሰማበት ሁኔታ</u>**

**፩.** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጉዳይ  የሚሰማው በዝግ ችሎት ነው፤ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ከጠበቃው፣ከምስክር፣ ከልዩ አዋቂ፣ ከወላጅ፣ ከሞግዚት ወይም ከሚመለከተው ተቋም ባልደረባ በስተቀር ማንም ሰው መገኘት የለበትም፤ ዐቃቤ ሕግ ክስ የተመሠረተ እንደሆነ መገኘት ይኖርበታል፡፡

፪. በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የተከሰሰበትን ነገር የሚሰማው ችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚመራመበት አኳኋንና ሁኔታ የተለየ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ ሕግ አንቀጽ **፩፻፴** መሠረት የቀረበ ክስ ወይም አቤቱታ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ ለተገኘው ወጣት ከተነገረው በኋላ ለክሱ ወይም ለአቤቱታው የሚሰጠው መልስ እንዳለው ይጠየቃል፡፡

፬. ወጣቱ  በሚሰጠው መልስ የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ በሙሉ ዐውቆ ያመነ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ለፍርድ ቤቱ በታየው ጊዜ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት የሰጠውን መልስ በመዝገብ ጽፎ ወዲያውኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡

፭. ወጣቱ የተከሰሰበትን ወንጀል በሙሉ ከተረዳው በኋላ ክሱን ወይም አቤቱታውን ያላመነ እንደሆነ ለቀረበው ክስ ወይም አቤቱታ ለመመስከር የሚጠሩትን ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ይጠይቃል፡፡ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወይም እንደራሴው ወይም ጠበቃው ማንኛውም ምስክር እንዲጠራለት ማድረግ ይችላል፡፡

፮. ምስክሮቹን ሁሉ ፍርድ ቤቱ በጥያቄ ከመረመረ በኋላ የወጣቱ ወገን መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፯. ማስረጃ ተሰምቶ ካለቀና የወጣቱ ወገን ስለነገሩ ጠቅላላ ንግግር ካደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ፍርድ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፴፩ ፍርድ**

፩. ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፩፻፴፪** መሠረት በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘው ወጣት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ወንጀል መፈፀሙን በማስረጃ ማረጋገጥ ካልተቻለ በነፃ የመልቀቅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪. በዚህ ሕግ አንቀጽ **፩፻፴፪** መሠረት ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣትን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በወንጀል ሕግ ከአንቀጽ ፻፶፯ ጀምሮ የተመለከቱ የጥንቃቄ ርምጃዎችን እና በዚህ ሕግ አማራጭ መፍትሄዎች ወይም ቅጣትን ይወስናል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ በወጣቱ ላይ የጥንቃቄ ርምጃ ወይም ቅጣት ከመወሰኑ በፊት  በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት የሚጠቅም ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው ስለወጣቱ ጠባይና ስለቀድሞ ጥፋቱ ለመጠየቅ ከማንኛውም ድርጅት ማንኛውንም ሰው ወይም እንደራሴ ሊጠራ ይችላል፡፡

፬.ፍርድ የሚሰጠው እንደ ማንኛውም መደበኛ ክስ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘው ወጣት ካስረዳው በኋላ ለወደፊቱ ጠባዩን እንዲያርም ያስጠነቅቀዋል፡፡

፫. ፍርዱ በየትኛው ሕግ መሠረት እንደተሰጠ በፍርዱ ውስጥ ይጠቀሳል፡፡ ፍርዱ በዚህ ሕግ የተመለከቱ ዝርዝሮችን የሚይዝ ሆኖ ፣ ስብዕናው፣ የወደፊቱን እና አጠቃላይ ሁኔታውን በማይጎዳ መልኩ መዘርዘር ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴ ሌሎች ሰዎች ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ**

፩. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ወላጅ፣ ሞግዚት፣ አሳዳሪ ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ ሰው ተግባሩን በሚገባ ያልፈፀመ መሆኑን ካመነ በሌሎች ሕጎች የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማስጠንቀቂያ እና እርምት መስጠት ወይም መውቀስ ይችላል፡፡

፪. ፍርድ ቤት በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ የተገኘውን ወጣት በሚገባ ባለመጠበቁና ባለመያዙ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ወጣቱን በሌላ ሰው እጅ እንዲያድግ ወይም ወደሚታረምበት ወይም ወደሚሻሻልበት ተቋም የሚልከው እንደሆነ ለእድገቱና ለኑሮው የሚያስፈልገውን ወጪ በሙሉ ወይም በከፊል ወላጅ፣ ሞግዚት፣ አሳዳሪ ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ ሰው እንዲከፍል ማዘዝ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚጣለውን ግዴታ ልክና የሚቆይበትን ጊዜ በውሳኔው ውስጥ መመልከት ይኖርበታል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፫ በተመለከተው መሠረት በተሰጠ ትእዛዝ እና ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፴፩ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ መለወጥ ወይም ማሻሻል**

፩.ስለ ይግባኝ፣ ሰበርና ፍርድን እንደገና ስለማየት በዚህ ሕግ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወንጀል ነገር ውስጥ ገብቶ በተገኘ ወጣት ላይ ትእዛዝ የሰጠ ማንኛውም ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ወይም ወጣቱ በጠበቃው፣ በዐቃቤ ሕጉ፣ በወላጅ፣ በሞግዚቱ፣ በአሳዳሪው፣ ኃላፊ በሆነለት ሌላ ወይም አደራ በተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት አመልካችነት ቀደም ሲል የሰጠውን ትእዛዝ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ይችላል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን ሲሰጥ ለወጣቱ ጥቅም አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ እና ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው፣ ባለሙያ እና ድርጅት የሚያቀርበውን አስተያየት መቀበል ይኖርበታል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ደንብ መተላለፍ ስለሚመራበት ሥነ ሥርዐት**

**አንቀጽ ፫፻፸፮ ተፈጻሚነት**

፩. ደንብ መተላለፍን የሚመለከት ጉዳይ በዚህ ምዕራፍ በተደነገገው መሠረት ይመራል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ያልተሸፈነ የደንብ መተላለፍን የሚመለከት ጉዳይ በልዩ ሕግ በተደነገገበት አግባብ ይመራል፡፡

፫.በዚህ ምዕራፍ ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ የዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**አንቀጽ ፫፻፸፯ ደንብ ተላላፊ እንዲጠራ የሚቀርብ ማመልከቻ**

፩.የደንብ መተላለፍ በተፈጸመ ጊዜ ደንብ ተላላፊው እንዲጠራ ፍርድ ቤቱ መጥሪያ እንዲሰጥ ከሳሹ ያመለክታል፡፡

፪.ማመልከቻውም የደንብ ተላላፊውን ስም፣ የደንብ መተላለፍ የተፈጸመበትን ሁኔታ፣ ክስ የቀረበበት ሕግና የሕጉን አንቀጽ እንዲሁም ሌሎች ለክሱ አስፈላጊ ጉዳዩችን እና እንደአስፈላጊነቱ ማስረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፸፰ መጥሪያ መላክ**

፩.ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት መመራት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ካረጋገጠ ለተከሳሹ መጥሪያ ይልካል፡፡

፪.መጥሪያው ማመልከቻውን አባሪ ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

**(ሀ)** ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ቦታ፣ ቀን፣ሰዓት፣ ተጠሪው ወይም ወኪሉን መላክ እንደሚችል፣

**(ለ)** ተጠሪ የቀረበበትን ክስ ካመነ ፍርድ ቤት መቅረብ ሳያስፈልገው ማመኑን በጽሑፍ ለፍርድ ቤቱ ከቀጠሮ በፊት መግለጽ ወይም፣ በተወካዩ መላክ የሚችል መሆኑንና የደንብ መተላለፍ ሊያስከትልበት የሚችለውን ከፍተኛ ቅጣት መጠን፣

**(ሐ)**መጥሪያው የደረሰው መሆኑን ለማረጋገጥ በተላከለት መጥሪያ ላይ መፈረም ያለበት መሆኑን፤መቅረብ ያለበት ከሆነም እንዲቀርብ የሚያመላክት ዝርዝር ፣

መያዝ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፸፱ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ክስን ማመን**

፩.ደንብ ተላላፊው የቀረበበትን ክስ ካመነ ፍርድ ቤት መቅረብ ሳያስፈልገው ማመኑን በጽሑፍ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

፪.ጥፋተኝነቱን የሚገልፀው ጽሑፍ የደንብ ተላላፊውን ስም እና ፊርማ መያዝ ይኖርበታል፤ በመጥሪያው የተመለከተውን መቀጮ በፖስታ፣ በመልዕክተኛ ወይም በሌላ ተገቢ መንገድ መላክ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፹ ክሱ በታመነ ጊዜ የሚኖር ሥነ ሥርዐት**

፩.ተከሳሹ ጥፋቱን ያመነ እንደሆነ እና ፍርድ ቤቱ የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ብቻ የሚፈርድ እንደሆነ ውሳኔው ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡ የውሳኔውንም ግልባጭ ለደንብ ተላላፊው ይልካል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ደንብ ተላላፊው የገንዘብ መቀጮ የተወሰነበት ሆኖ የመቀጮውን ገንዘብ አስቀድሞ የላከ እንደሆነ እና ፍርድ ቤቱ የወሰነው መቀጮ በመጥሪያ ላይ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን የበዛ ወይም ያነሰ እንደሆነ ልዩነቱን ለደንብ ተላላፊው ተመላሽ እንዲሆን ወይም ተጨማሪ ልዩነቱ እንዲከፍል ያዛል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በማቆያ ቤት እንዲታሰር፣የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ወይም እንዲወቀስ ሲፈልግ ተከሳሹ እንዲቀርብ በማድረግ ስለቅጣቱ አስተያየቱን ይጠይቀዋል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፹፩ ክሱ በተካደ ጊዜ የሚኖር ሥነ ሥርዐት**

፩.ተከሳሹ መጥሪያው ላይ ጥፋተኝነቱን በማመን ያልፃፈ እንደሆነ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረው ቀንና ሰዓት ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

፪. ከሳሽ እና ደንብ ተላላፊው ምስክር ወይም ሌላ ማስረጃ እንዳላቸው በቀጠሮው ቀን እንዲቀርቡ አስፈላጊውን ይፈጽማሉ፡፡

፫.ክርክሩና የማስረጃ መስማት ሒደቱ በቃል ይፈፀማል፡፡ ፍርድ ቤቱም ምስክሩ ከሚሰጠው ቃል ውስጥ ዋናውን ነገር ብቻ በመዝገብ ይጽፋል፡፡

፬.የክሱ መሰማት ሂደት ማመልከቻ ከቀረበበት ቢበዛ በሁለት ሳምንት ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

፭.ፍርድ ቤቱ ውሳኔው የተመሠረተበትን ሕግና ምክንያት በአጭሩ በመግለጽ ውሳኔውን ያነባል፤ ይመዘግባል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፹፪ ደንብ ተላላፊ ባልቀረበ ጊዜ የሚኖር ሥነ ሥርዐት**

፩. ደንብ ተላላፊው በቀጠሮ ቀን ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሚያስፈጽመውን አካል ለይቶ በማመልከት ውሳኔው እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፻፶፫ ልዩ ሁኔታ**

፩.በዚህ ክፍል ለደንብ መተላለፍ የተደነገገው ቢኖርም በደንብ ተላላፊው ላይ የሚጣለው ቅጣት፡-

**(ሀ)** የገንዘብ ቅጣት ብቻ ፣

**(ለ)** የመንገድና የማሽከርከር ገደብ ማለፍ ላይ የሚሰጥ ቅጣት ፣

**(ሐ)** ለሕዝብ ጥቅም ንብረትን መልቀቅን በተመለከተ በሚቀርብ ክስ ላይ የሚወሰድ ቅጣት ፣

**(መ)** ቅጣቱ ማስጠንቀቂያ ብቻ ፣

**(ሠ)** በአንድ የተለየ ነገር እንዳይገለገል ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል የተጣለ ቅጣት፣

**(ረ)** የስራ ፍቃድ የተመለከተ ቅጣት፣

**(ሰ)** በወንጀል ሕጉ በማረፊያ ቤት እስራት የሚያስቀጡ ፣

ሲሆንና ከሳሽ የምርመራ ውጤቱን ተመልክቶ የሚጣልበትን ቅጣት ለይቶ ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ወስኖ ውሳኔውን ከመጥሪያው ጋር ለደንብ ተላላፊው ሊልክለት ይችላል፡፡

፪. ደንብ ተላላፊው አምኖ ውሳኔውን በጽሑፍ የተቀበለና ውሳኔውን ከፈፀመ ወይም ሊፈጽም ከተስማማ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ እንዲፈጽም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫.ደንብ ተላላፊው  መጥሪያ ደርሶት በሁለት ሳምንት ውስጥ መልስ ያልሰጠበት እንደሆነ እንዳመነና ውሳኔውን እንደተቀበለ ተቆጥሮ ውሳኔውን እንዲፈጽም ፍርድቤት ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፬.ደንብ ተላላፊው  ያልተስማማ እንደሆነ ክሱ በመደበኛ የደንብ መተላለፍ ሥነ ሥርዐት ይታያል፡፡

## ስምንተኛ መጽሐፍ

## በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር

## ምዕራፍ አንድ

## በወንጀል የምርመራ፣ ክስ እና የፍርድ ሂደት ጉዳዮች ትብብር

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፫፻፹፩ ዓላማ**

፩.በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ የዓለም አቀፍ ትብብር ዓላማ ኢትዮጵያ በወንጀል ጉዳይ ከሚደረግ ትብብር ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖሩ መብትና ጥቅሞችን ለማስከበር እና ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል ሥርዐት መዘርጋት ነው፡፡

፪.በዚህ ክፍል ውስጥ **‹‹ዓለም አቀፍ ትብብር ››** ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ወይም በፈረመቻቸው ስምምነቶች ፤ በእንካ ለእንካ መርህ እና በዚህ ሕግ መሠረት በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር ነው፡፡

፫.ለዚህ ምዕራፍ አፈጻጸም ‹‹ፍርድ ቤት›› ማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

**አንቀጽ ፫፻፹፪ መርህ**

፩.መንግሥት በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚያደርገው ዓለም አቀፍ ትብብር ኢትዮጵያ በፈረመችው ወይም በተቀበለችው ስምምነት መሠረት ይፈጸማል፡፡

፪.ግልጽ የሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነት የሌለ ወይም ያልተሟላ እንደሆነ ትብብሩ በዚህ ክፍል በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

፫. የትብብር ጥያቄው ሕገ መንግሥቱንና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ እና በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

፬.ማንኛውም የትብብር ጥያቄ የወንጀል ተጎጂን ወይም የወራሹን የካሣ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ በማያጓድል መልኩ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፫፻፹፫ ትብብር ማድረግ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች**

፩. ከመንግስት ጋር በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚደረግ የትብብር ጥያቄ፡-

**(ሀ)** የማንኛውንም ሰው መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሊጥስ ይችላል ተብሎ የሚታመን እንደሆነ በተለይም ለግርፋት፣ ጭካኔ፣ ኢ-ሰብዓዊ ለሆነ አያያዝ ወይም ቅጣት ይጋለጣል ተብሎ ሲታመን፣

**(ለ)** አንድን ሰው በዘር፣ በብሔር ማንነት፣ በኃይማኖት፣ በፆታ፣ በቀለም፣ በዜግነት ወይም ባለው የፖለቲካ አቋም ሊያስከስሰው ወይም ሊያስቀጣው ይችላል ተብሎ ሲታመን፣

**(ሐ)** ለተጠየቀው ትብብር መነሻ የሆነውን በጦር ሕግ ብቻ የሚያስቀጣ ተግባር ጋር የተያያዘ የትብብር ጥያቄ ሆኖ ለወንጀሉ የተቀመጠውን ቅጣት የመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለልዩ ፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ፣

**(መ)** የትብብር ጥያቄው አንድ ሰው ተከሶ ነፃ ከተባለበት፣ ይቅርታ በተደረገበት ፣ በይርጋ ቀሪ ከሆነ ወይም ቅጣቱን ከፈጸመበት የወንጀል ድርጊት ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ወይም

**(ሠ)** የቀረበው የትብብር ጥያቄ የሀገርን ሉዓላዊነት፣ የሀገርና የሕዝብ ደህንነትን፣ የሕግ የበላይነት ወይም የሀገር ጥቅምን የሚነካ ከሆነ፤

ትብብር አይደረግም፡፡

**፪.** የትብብር ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ የክስ ማቅረቢያ ወይም የቅጣት ውሳኔ ማስፈጸሚያ የይርጋ ጊዜ በወንጀል ሕግ መሠረት ይቆጠራል፡፡

## <u>አንቀጽ ፩፻፹፯ የትብብር ዐይነቶች</u>

በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር በወንጀል ምርመራ፣ ክስ እና የፍርድ ሂደት ባሉ ጉዳዮች ሲሆን፡-

**፩.** የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን፤

**፪.** መረጃና ማስረጃ ልውውጥን፤

**፫.** የወንጀል ተጎጅዎች፣ ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃን፤

**፬.** አሳልፎ መስጠትን፤

**፭.** የማስተላለፍ ጥያቄ መፈጸምን፤

**፮.** ወንጀል ለመፈፀም ያስቻለ ንብረትና የወንጀል ፍሬ የሆነ ንብረትን ወይም ገንዘብን ማገድና መውረስ፤

**፯.** የተያዘ ሰው ልውውጥ ወይም ፍርደኛንና የፍርድ ሂደትን ማስተላለፍን፤

**፰.** የፍርድ ቤት ውሳኔ ዕውቅና መስጠትና መፈፀምን፤

**፱.** ሌሎች በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚፈቀዱ መሰል የትብብር ዐይነቶችን፤

ያጠቃልላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፻፹፫ የትብብር መስመርና የማስፈጸም ሥልጣን</u>**

**፩.** በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ የዓለም አቀፍ ትብብር ጥያቄ በዲፕሎማሲያዊ የግንኙነት መስመር መቅረብና መፈጸም ይኖርበታል፡፡

**፪.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ የሆነ ጉዳይ የገጠመ እንደሆነ ጠቅላይ ዐቃቤ ከዲፕሎማሲያዊ የግንኙነት መስመር ውጭ የትብብር ጥያቄ ሊያቀርብ ወይም ሊፈጽም ይችላል፡፡

**፫.** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማስፈጸም፣ መምራት እና መከታተል ይኖርበታል፡፡ ይህንንም ሲፈፅም እንደአግባብነቱ ከሀገር ደህንነትና ፀጥታ አካላትና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመመካከር ይሆናል፡፡

**፬.** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ መሠረት የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ትብብር የትብብሩ ዓላማ እና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እየተፈጸመ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

**፭.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ዐይነትና ለግንኙነቱ መሠረት በሆነ ስምምነት ወይም ሕግ መሠረት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፻፹፬ የትብብር ወጪ</u>**

**፩.** በስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር የትብብር ወጪ በትብብር ጠያቂ ሀገር የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**፪.** በኢትዮጵያ የሚጠየቅ ትብብር ወጪው በፌዴራል መንግሥት ይሸፈናል፡፡

**፫.** በኢትዮጵያ የሚሸፈን የትብብር ወጪ ክፍያ በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ሥርዐት እና የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፲፻፺ የትብብር ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ አካላት</u>**

**፩.** በወንጀል ጉዳይ ሥልጣን ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል በዚህ ሕግ መሠረት የትብብር ጥያቄውን በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፪.**በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፲፻፹፫</u>** ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል መንግሥት አካል በቀጥታ የትብብር ጥያቄ እንዲያቀርብ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የትብብር ጥያቄ

**አንቀጽ ፻፶፩ የጥያቄው አቀራረብ**

፩.ማንኛውም የትብብር ጥያቄ በጽሑፍ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም የትብብር ጥያቄው በቃል፣ በኢሜል፣ በፋክስ ወይም መሠል መገናኛ ዘዴዎች ዲፕሎማቲክ መስመሩን ሳይጠብቅ ሊቀርብ ይችላል፤ ጥያቄውም በሠላሳ ቀን ውስጥ ዲፕሎማቲክ መስመሩን ጠብቆ በጽሑፍ ካልቀረበ ጥያቄው እንዳልቀረበ ይቆጠራል፡፡

፫.ጥርጣሬ በመኖሩ ምክንያት ማረጋገጥ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከጥያቄው ጋር የተያያዙ አባሪ ሰነዶች ወይም በጽሑፍ የተሰጡ ምላሾችን ሰነድ ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው አካል ማረጋገጥ አያስፈልግም፡፡

**አንቀጽ ፻፶፪ የትብብር ጥያቄ ይዘት**

ማንኛውም የትብብር ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

፩.የትብብሩን ዓላማ እና ዓይነት፣

፪.የቀረበውን ጥያቄ የሚከታተል ተቋም ስምና አድራሻ፣ ጥያቄውን ለማቅረብ ያለው ሕጋዊ መሠረት፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ያለው ኃላፊነት እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች፣

፫.ጥያቄው ከግለሰብ ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ግለሰቡ የሚጠራበትና የሚታወቅበት ስም፣ ወቅታዊ አድራሻ፣ ዜግነት እና እንደነገሩ ሁኔታ የግለሰቡ አሻራ፣ ፎቶግራፍና ሌላ መለያና ዝርዝር ሁኔታ፣

፬.ጥያቄው ከንብረት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የተወረሰ ወይም የታገደ የንብረት ዐይነትን እና ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ የሚያብራራ አጭር መግለጫ፣ ጥፋተኝነቱን የሚያሳይ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣

፭. ወንጀሉን የሚደነግገውን ሕግ፣ መግለጫ፣ ተፈጸመ የተባለውን ድርጊት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ፣ የሚያስከትለውን ወይም የተወሰነበትን ቅጣት፣ የወንጀሉ የይርጋ ጊዜ፣ ውሳኔ የሰጠው አካል እንደጉዳዩ ሁኔታ፣ የወንጀሉን ፍሬ ነገርና ጉዳዩ በምርመራ ላይ እንደሆነ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ የሚያስረዳ የምርመራ ውጤት መግለጫ፣ እና

፮. የተፈለገው ማስረጃ ዐይነት እና ዝርዝር፣

፯. ትብብሩ መፈፀም ያለበት ጊዜ፣

፰. ትብብሩን አስመልክቶ መወሰድ ያለበት የሚስጥራዊነት ጥንቃቄዎች፣

፱. ጠያቂው ሀገር ትብብሩ ሲከናወን እንዲወሰድ የሚፈልጋቸው የተለዩ ሥነ ሥርዐቶች ወይም ሁኔታዎች፣ እና

፲. በሚመለከተው አካል የሚጠየቁ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፣

መያዝ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፻፶፫ የጥያቄውን ተቀባይነት፣ አግባብነት ማረጋገጥ እና ውሳኔ መስጠት**

፩.ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የትብብር ጥያቄው በዚህ ሕግ የተመለከቱትን የሚያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ይወስናል፡፡

፪.ተቀባይነት የሌለው ወይም ያልተሟላ ጥያቄ እንደሆነ ለጠያቂው አካል ውሳኔውን ወዲያውኑ ያሳውቃል፣ በጥያቄው ላይ የታዩ ጉድለቶችን ለይቶ በማመልከት ማስተካከያ ተደርጎበት ወይም ጥያቄውን አሟልቶ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

፫.ጥያቄው ተቀባይነት ያለው እንደሆነ እና የቀረበው በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት አካል እንደሆነ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ትብብር ለሚጠይቀው አካል ይልካል፡፡ ሆኖም ጥያቄው የቀረበው ለኢትዮጵያ መንግስት እንደሆነ እንደአግባብነቱ በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

፬. የቀረበው የትብብር ጥያቄ በተጀመረ የወንጀል ምርመራና ክስ ሂደት ላይ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትብብሩን ለሌላ ጊዜ ለማድረግ ሊወስን ይችላል፡፡

፭. ሰነድ እንዲተላለፍ የቀረበ የትብብር ጥያቄ ከሆነና ሰነዱ በተጀመረ የፍትሐብሔር ክስ ላይ የሚያስፈልግ ከሆነ ትብብሩ ለሌላ ጊዜ ለማድረግ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፻፶፬ ማረጋገጫ መስጠት**

**፩**.በዚህ ሕግ የተደነገጉ መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለትብብር የሚላከው ሰው ትብብር ጠያቂ ሀገር፡-

**(ሀ)** በጊዜያዊነት የሚሰጠው ሰው በግዛቱ ውስጥ ከመግባቱ በፊት በፈጸመው ተግባር እንደማይያዝ፣ እንደማይከሰስ፣ እንደማይቀጣ ወይም የትኛውም የግል ነፃነቱ እንደማይገደብ፣ ወይም በማንኛውም የፍትሐብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን፣

**(ለ)** በራሱ እና በጊዜያዊነት በሚሰጠው ሀገር ፍቃድ ካልሆነ በስተቀር ትብብር ከተጠየቀበት ጉዳይ ውጭ ድጋፍ እንዲሰጥ እንደማይገደድ፣

**(ሐ)** በስምምነት በተገለጸው የጊዜ ገደብ ቀደም ሲል ወደነበረበት ሀገር እንደሚመለስ፣

**(መ)**የተጠረጠረ፣ በማቆያ ወይም በማረፊያ ቤት የነበረ ሰው ከሆነ መሠረታዊ መብቶች ሊያስጠብቅ በሚችል ማቆያ ወይም ማረፊያ እንደሚያቆየው፣

ማረጋገጫ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**፪**. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የትብብር ጥያቄው የቀረበለት ሀገር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፫**.ለተጨማሪ ጊዜያት ግለሰቡ ለትብብር እንዲቆይ ጥያቄ ከቀረበ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህንኑ ጥያቄ በመመርመር ይወስናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የትብብር አፈፃፀም

### አንቀጽ ፫፻፺፫ ጠቅላላ

**፩**.የቀረበው የትብብር ጥያቄ በዚህ ሕግ መሠረት ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ በዚህ ሕግና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፪**.የቀረበው የትብብር ጥያቄ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ የማይታወቅ እንደሆነ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ በሆነ ሕግ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፫፻፺፬ የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ትብብር

**፩**.ትብብር ጠያቂው ሀገር አንድ የወንጀል ድርጊት እንዲመረመር በጠየቀ ጊዜ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ምርመራው በዚህ ሕግ ከአንቀጽ **፶፮** እስከ አንቀጽ **፻፲፮**በተደነገገው ሥነ ሥርዐት በሕግ የመመርመር

ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ የምርመራውንም ውጤት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ለጠያቂው ሀገር ይልካል፡፡

፪.በጋራ የምርመራ ቡድን ወንጀልን ለመመርመር ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ምርመራው በዚህ ሕግ ምርመራ እንዲያከናውን ሥልጣን የተሰጠው አካል እና የጥያቄ አቅራቢው ሀገር የምርመራ አካል ወንጀሉን በጋራ የሚመረምሩበትን አግባብ ይወስናል፡፡

፫.የትብብር ጠያቂው ሀገር ምርመራ አካል በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ ወንጀልን እንዲመረምር ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዐት ጋር የሚመሳሰል ምርመራ እንዲካሄድ ጥያቄ ከቀረበ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አግባብነቱን አይቶ ይወስናል፤

**<u>አንቀጽ ፮፻፲፪ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ሰው በጊዜያዊነት የማስተላለፍ ትብብር</u>**

፩.ተፈላጊው ሰው በማረፊያ ወይም በማቆያ ቤት የማይገኝ እንደሆነ እና ለተፈለገው ዓላማ በጊዚያዊነት ሊተላለፍ ፈቃደኛ እንደሆነ ፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይህን ያስፈጽማል፡፡

፪.በማረፊያ ወይም በማቆያ ቤት ያለ ሰው ምስክርነት ለመስጠት ወይም ለሌላ ምርመራን የማገዝ ሥራ በተጠየቀ ጊዜ ትብብር ጠያቂው ሀገር በዚህ ሕግ አንቀጽ **፮፻፲፩** የተመለከተውን ማረጋገጫ ሲያሟላ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትብብሩ እንዲፈጸም ለፍርድቤት ያመለክታል፣ ፍርድቤቱም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚተላለፈው ሰው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እንደሆነ በጊዜያዊነት ሊተላለፍ የሚችለው ፈቃደኛ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

፬.የፌዴራል ፖሊስ ከፍርድ ቤት ትእዛዝ በማውጣት ለትብብር የተጠየቀውን ሰው ከሚገኝበት ማረፊያ ወይም ማቆያ ቤት በመረከብ ለጠያቂው ሀገር እንዲያስረክብ፣ ትብብሩን አጠናቆ ሲመለስም ወደ ነበረበት ማረፊያ ወይም በማቆያ ቤት እንዲያስረክብ ይደረጋል፡፡

፭. በትብብር ጠያቂው ሀገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት የትብብሩን አፈጻጸም እንዲከታተል መደረግ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፮፻፲፫ በውጭ ሀገር ያለን ሰው ለትብብር መጠየቅ</u>**

፩.በውጭ ሀገር በቁጥጥር ሥር ያለ ሰው ለትብብር በተፈለገ ጊዜ እና ተጠያቂው ሀገር ወይም ተቋም ሲፈቅድ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተጠየቀውን ሰው ተረክቦ ትብብሩን ለጠየቀው አካል እንዲያስረክብ እና ትብብሩም ከተጠናቀቀ በኋላ ከትብብር ጠያቂው ተረክቦ ትብብሩን ላደረገው ሀገር እንዲያስተላልፍ ለፌዴራል ፖሊስ ያሳውቃል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለኢትዮጵያ የተላለፈ ሰው ወደ ኢትዮጵያ መግቢያ ፍቃድ ይሰጠዋል፡፡

፫.የተላለፈ ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ይደረጋል፤ ማረፊያ ቤት በሚቆይበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ማረፊያ ቤት በሚገኙ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግ ይሆናል፡፡ በተቻለ መጠን የመጣበትን ጉዳይ ጨርሶ እንዲሄድ አስፈላጊው ይደረጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፫፻፺፱ በጠያቂ ሀገር ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት መቆየት ያለው ውጤት</u>**

በዚህ ሕግ መሠረት የተላለፈ ሰው በክርክር ሂደት ወይም የፍርድ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ የነበረ እንደሆነ ተላልፎ በተሰጠበት ጊዜ በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት የቆየው ጊዜ መፈጸም ካለበት ግዴታ ገብቶ ይታሰብለታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻ መረጃና ማስረጃ ልውውጥ</u>**

**፩.** ለጠያቂ አካል የተሰጠ ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ፣ መረጃ፣ ሰነድ ወይም መዛግብትን እና ሌላ የማስረጃ ዋጋነት ያለው ነገር በአግባቡ የሚያዝ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት እና ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ መመለስ ይኖርበታል፡፡

**፪.**በትብብር ጥያቄ የተገኘው ማንኛውም መረጃ ወይም ማስረጃ ትብብር ከተጠየቀበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፩ መጥሪያና ሌሎች ሰነዶች የማድረስ ትብብር</u>**

**፩.**ለኢትዮጵያ የቀረበው የትብብር ጥያቄ የመጥሪያ ወይም ሌላ ሰነድ የማድረስ እንደሆነ ይኸው ወዲያውኑ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

**፪.**ጥያቄው መጥሪያ የማድረስ የሆነ እንደሆነ ይኸው ተፈላጊው እንዲቀርብ ከተፈለገበት ቀን ቀደም ብሎ ከሃያ ስምንት ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ መጥሪያና የመጥሪያ ማድረስ ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፤ የፌዴራል ፖሊስ መጥሪያው እንደደረሰው ከአሥራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለተፈላጊው ማድረስ ይኖርበታል፡፡

**፫.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም እና ይኸው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ከታመነ ጥያቄው ከተደነገገው ጊዜ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ቢቀርብም ተቀባይነት አለው፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፪ የፍርድ ሂደትን ማስተላለፍ</u>**

**፩.**የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በምትክነት ተፈፃሚ በሚሆንባቸው ወንጀሎች ላይ የፍርድ ሂደት እንዲተላለፍ የትብብር ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ሂደቱ በዚህ ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ሊታይ ይችላል፡፡

**፪.**ለተላለፈው የፍርድ ሂደት ውጤታማነት ለማገዝ የሚያስችል አስፈላጊ ምርመራ ማካሄድ ተገቢ ካልሆነ በስተቀር የፍርድ ሂደት ማስተላለፍ በተጠየቀው ሀገር ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ በዚህ ሕግ መሠረት የተመለከቱ የዕርቅ፣ የጥፋተኝነት ድርድር፣ የሌሎች የመፍትሔ ርምጃዎች ወይም የክስ ሂደት መቋረጥ ይኖርበታል፡፡

**፫.**በዚህ አንቀጽ መሠረት የተላለፈ የፍርድ ሂደት ውሳኔ ካገኘ ይኸው ለጠያቂው ሀገር መገለጽ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፫ ፍርደኛን ማስተላለፍ</u>**

**፩.**በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት በመጨረሻ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ሰው  ቅጣቱን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈጸም የትብብር ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፤ አፈጻጸሙም በዚህ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይሆናል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቀርብ ፍርደኛን የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄ፡-

- **(ሀ)** ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ቅጣት የተጣለበት ፍርደኛ ሙሉ ወይም ቀሪ ቅጣቱን እንዲፈጽም፣
- **(ለ)** ቅጣት የተገደበለት ፍርደኛ የገደቡን ቅድመ ሁኔታዎች መፈጸሙን ለመከታተል፣ ወይም
- **(ሐ)** በአመክሮ የተለቀቀ ወይም ቅጣት የተላለፈለት ፍርደኛ ለአመክሮው ወይም ለቅጣቱ መተላለፉ ምክንያት የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን  መፈጸሙን ለመከታተል፣

ሊሆን ይችላል፡፡

**፫.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው ቢኖርም፡ ፍርደኛው ቋሚ ኗሪ ካልሆነ፣ ወይም  በዚህ ወይም ሌላ ሕግ ቅጣቱ የሚፈጸምበት የይርጋ ጊዜ ካለፈ፣ፍርደኛን የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**፬.** የተላለፈ ፍርደኛን ቅጣት በማስፈጸም ሂደት ፍርዱ እንዲከለስ ወይም የመጨረሻ ፍርድን እንደገና የማየት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ፍርዱን የሰጠው ሀገር ይሆናል፡፡

**፭.** በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ፍርደኛን በማስተላለፍ የትብብር ሂደት የፍርደኛውን ባሕርይ፣ የቅጣት አፈጻጸም፣ የክትትል አግባብና አተገባበር ሪፖርት የሚቀርብበትን ሁኔታ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይወስናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፬ የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ፍርድ፣ ብይን ወይም ውሳኔ ዕውቅና መስጠትና  ማስፈጸም</u>**

፩. በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠ ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ዕውቅና የመስጠትና የማስፈጸም የትብብር ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በዚህ ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

፪. ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲወረስ በጠያቂው ሀገር የተሰጠ ትእዛዝ፣ ፍርድ፣ ብይን ወይም ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

፫. በተቃራኒው ካልተወሰነ በስተቀር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የተወረሰ ማንኛውም ንብረት ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

<u>**አንቀጽ ዐ፻፫በኢትዮጵያ ግዛት እስረኛን ማስተላለፍ**</u>

፩. ትብብር ጠያቂ ሀገር እስረኛን በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ወደ ሦስተኛ ሀገር ለማስተላለፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተላላፊውን ማንነት፣ የሚተላለፍበትን ምክንያት በቀረበው ማስረጃ መሠረት መርምሮ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ የእስረኛውን መተላለፍ ያልፈቀደ እንደሆነ ትብብር ጠያቂው ሀገር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ምክንያቱን እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡

፪. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍቃድ በሰጠ ጊዜ የተላላፊውንና የአስተላላፊውን ማንነት እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ማስረጃዎችን በመላክ አግባብ ያለው ባለሥልጣን እንዲያስፈጽም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑም ትብብሩን እንዳስፈጸመ ወዲያውኑ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፫. ያልተጠበቀ የእስረኛ ማስተላለፍ ባጋጠመ ጊዜ፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መረጃ እንደደረሰው ወይም በአስተላላፊው ሀገር ባለሥልጣን አመልካችነት ተላላፊው ሰው በኢትዮጵያ ግዛት ክልል እንዲተላለፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ማስተላለፉ ባልተፈቀደ ጊዜ ተላላፊው ሰው በመጣበት አግባብ ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት በኢትዮጵያ ግዛት ክልል እንዲተላለፍ ፈቃድ ያልተሰጠበት ሰው ኢትዮጵያዊ ከሆነ እና ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

፭.ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ አፈጻጸም ተላላፊው ሰው ከአርባ ስምንት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በፌዴራል ፖሊስ ቁጥጥር ሥር እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>**ምዕራፍ ሁለት**</u>

**<u>በወንጀል ተፈላጊን ሰው አሳልፎ ስለመስጠት</u>**

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>አሳልፎ ለመስጠት በቀረበ ጥያቄ ላይ የሚፈጸም ሥነ-ሥርዓት</u>**

**<u>አንቀጽ ፩፻፮ ትርጉም</u>**

**‹‹አሳልፎ መስጠት››** ማለት አንድን የሚፈለግ ተጠርጣሪ፣ ተከሳሽ ወይም ፍርደኛ ለወንጀል የክስ ሂደት፣ ቅጣት ለመወሰን ወይም ለማስፈጸም የሚቀርብ የትብብር ጥያቄ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፯ አሳልፎ የሚያሰጥ ወንጀል ወይም ቅጣት</u>**

**፩.**በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣

**(ሀ)** ሁለት ዓመትና በላይ በእሥራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል ተግባር ለወንጀል የክስ ሂደት ወይም ቅጣትን ለመወሰን፣ ወይም

**(ለ)** ስድስት ወር እና በላይ ያልተፈጸመ ወይም ሳይፈጸም የቀረ የእሥራት ቅጣትን ለማስፈጸም፣

አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበት ሰው የተከሰሰበት ወይም ጥፋተኛ የተባለበት ሌላ ተደራቢ ወንጀል ከሁለት ዓመት በታች በእሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ወይም ፍርደኛው ሳይፈጽመው የቀረ ከስድስት ወር በታች የእሥራት ቅጣት እንደሆን ተላልፎ ሊያሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፰ ጣምራ የወንጀል ድርጊት</u>**

**፩.**ድርጊቱ ወይም በድርጊቱ ምክንያት ተወስኖ ሳይፈጸም የቀረ ቅጣት በውጭ ሀገር እና በኢትዮጵያ ሕግ ወንጀል ወይም ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ የተደነገገ ካልሆነ በቀር አሳልፎ አያሰጥም፡፡

**፪.**የትብብር ጥያቄ የሚመለከተው ወንጀል ወይም ቅጣት በውጭ ሀገርና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በአንድ ዓይነት ስያሜ አለመጠራቱ ወይም በተመሳሳይ የወንጀል ድንጋጌ ሥር አለመጠቀሱ ወይም በአንድ ዓይነት አገላለጽ አለመቀመጡ አሳልፎ የሚያሰጥ ወንጀል ወይም ቅጣት መሆኑን አያስቀረውም፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፱ አሳልፎ መስጠት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች</u>**

ተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄ የቀረበበት ሰው፡-

**፩.**የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ከሆነ፣

**፪.**በተከሰሰበት ወይም ጥፋተኛ በተባለበት አሳልፎ በሚያሰጥ የወንጀል ተግባር አስቀድሞ በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር ፍርድ ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ቅጣት ተወስኖበት የፈጸመ፣ ወይም

**፫.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ወይም በጠያቂው ሀገር ሕግ መሠረት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በይቅርታ፣ በምኅረት፣ በይርጋ የታገደ ወይም ከመከሰስ ወይም ከቅጣት ነፃ የሚያደርግ ማንኛውም ምክንያት ያለ እንደሆነ፣

**፬.** ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈፀመ ወንጀል ወይም በኢትዮጵያ የዳኝነት ስልጣን ስር በሚወድቅ ጉዳይ የሚፈለግ ከሆነ ይህ ሥርዐት እስከሚያልቅ፣

ተላልፎ አይሰጥም፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የአሳልፎ መስጠት ሥነሥርዓት**

**አንቀጽ ፬፻፲ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ይዘትና ስለሚቀርብ ሰነድ**

**፩.**አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ሥልጣን ባለው የጠያቂ መንግሥት አካል በጽሑፍ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፪.**አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

**(ሀ)** በዚህ ሕግ አንቀጽ **፬፻፯** የተመለከቱ ሁኔታዎችን፣

**(ለ)** በተፈላጊው ሰው ላይ ሊቀርብበት የሚችለውን ክስ፣ ወንጀሉን የሚደነግገው ሕግ ፣ወንጀሉ የሚያስከትለው ቅጣት፣

**(ሐ)** ተፈላጊው ሰው ክስ የተመሰረተበት እንደሆነ ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜ፣ ቦታና የወንጀሉ አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታ፣ ተፈላጊው ሰው ያለው ተሳትፎ፣ ወንጀሉ የሚያስከትለው ቅጣት፣ ማስረጃና የሚያስረዱት ጭብጥ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ የመያዣ ትእዛዝ፣

**(መ)** ተፈላጊው ሰው ቅጣት የተጣለበት እንደሆነ የፈጸመው ወንጀል አጭር መግለጫ፣ ጥፋተኝነቱን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣ የተጣለበትና ያልፈጸመው የቅጣት ዐይነት ወይም መጠን፣

**(ሠ)** ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነበት እንደሆነ ተፈላጊው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) ከተመለከቱ መረጃዎች በተጨማሪ በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የተሰጠ

መጥሪያ፣ መከላከያውን ለማቅረብ የሚያስችለው የሕግ መነሻ ስለመኖሩ ወይም ጉዳዩን እንደገና ለማየት ስለሚፈቅድ ሕግ ድጋፍ አጭር መግለጫ፣

**(ረ)** ተፈላጊው ሰው ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ እንደሆነ የፈጸመው ወንጀል አጭር መግለጫ፣ ጥፋተኝነቱን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ውሳኔና ቅጣቱን ለመወሰን የሚያስችል ማረጋገጫ፣

**(ሰ)** ሌሎች በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚጠየቁ መረጃዎችን ወይም አባሪ ሰነዶችን፣

መያዝ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፲፩ ተደራራቢ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ</u>**

**፩.** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተፈላጊ ሰው ለአንድ ዓይነት ወይም ለተለያየ አሳልፎ ለሚያሰጥ ወንጀል ወይም ቅጣት ከተለያዩ መንግሥታት የተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ፡-

**(ሀ)** በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፻፱፫</u>** የተቀመጡትን መርሆዎች በተሻለ ሁኔታ የሚያስከብር መሆኑን፣

**(ለ)** ከጠያቂው መንግሥት ጋር የተፈጸመ አሳልፎ የመስጠት ስምምነት እና በስምምነቱ የተደነገገ ግዴታን፣

**(ሐ)** ጥያቄው የቀረበበትን ቅደም ተከተልና ይዘት፣ የወንጀሉና የቅጣቱን ዐይነት፣

**(መ)** ተፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት ዐይነት ወይም ሳይፈጸም የቀረ ቅጣት መጠን፣

**(ሠ)** የተፈላጊውን መብት በተሻለ ሁኔታ የሚያስጠብቅ መሆኑን፣

**(ረ)** የተጎጂውንና የተፈላጊውን ሰው ዜግነት እና የተጎጅውን መኖሪያ ሀገር እና

**(ሰ)** መሰል ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

ተፈላጊውን ሰው ለመዳኘት ወይም የተጣለበትን ቅጣት ለማስፈጸም ቅድሚያ የሚኖረውን ጠያቂ መንግሥት ይወስናል፡፡

**፪.** ተፈላጊው ሰው ቅድሚያ ለተሰጠው መንግሥት አሳልፎ ያልተሰጠ እንደሆነ የሌሎች ጠያቂ መንግሥታት ጥያቄ በዚህ ሕግ መሠረት ታይቶ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፲፪ጊዜያዊ እሥር</u>**

**፩.**በጉዳዩ አስቸኳይነት ምክንያት ተላልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ የሚቀርብበትን ሰው በእሥር ማቆየት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በዚህ ሕግ መሠረት የአሳልፎ መስጠት ጥያቄው እስኪቀርብ ድረስ ወይም የማስተካከያ ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተፈላጊው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የጊዜያዊ እሥር ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪.ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የአሳልፎ መስጠት የትብብር ጥያቄን ወስኖ በፍርድ ቤት እስኪያቀርብ ድረስ ተፈላጊውን በጊዚያዊ እስር ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ እንደአግባብነቱ በዚህ ሕግ የተመለከቱ የመያዝና የዋስትና ግዴታ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫.የጊዚያዊ እሥር ጥያቄ፡-

**(ሀ)** ተፈላጊው ሰው መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ የሆነ ወይም በተደጋጋሚ ወደ ኢትዮጵያ የሚመላለስ እንደሆነ፣

**(ለ)** ጥያቄው ተፈጸመ ከተባለው ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው እንደሆነ፣

**(ሐ)** ለእስር ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም በውጭ ሀገር ክስ የተመሠረተ እንደሆነ እና

**(መ)** እንዳያመልጥ ወይም ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም ሲባል፣

ሊቀርብ እና ሊፈጸም ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከቱ የትብብር ጥያቄዎች ለሚመለከተው አካል በሀያ ስምንት ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ተፈላጊው ሰው ከእስር ይለቀቃል፡፡ የተፈላጊው ሰው ከእስር መለቀቅ የድጋሜ እስር ወይም የተላልፎ ይሰጥ ጥያቄ ሂደትን ደግሞ ከማቅረብ የሚከለክል አይሆንም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የጊዚያዊ እስር ጥያቄ ወይም ማመልከቻ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፬፻፲** የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፲፫ የአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄን ለፍርድ ቤት ማቅረብ</u>**

፩. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፬፻፲** በተደነገገው መሠረት የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ከተቀበለ የተላልፎ ይሰጥ ማመልከቻ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ያቀረበውን መንግሥት፣ በተፈላጊው ሰው ላይ የቀረበበት ክስ፣ ወይም የተሰጠ ውሳኔ አጭር መግለጫ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

፫. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ እንዲታይ ከተወሰነበት ቀን በፊት የተላልፎ ይሰጥ ማመልከቻውን ቅጅ ለተፈላጊው ሰው እንዲደርስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፬. ተፈላጊው ሰው በቀረበው ተላልፎ ይሰጥ ጥያቄ ላይ ያለውን መልስና አስተያየት ከቀጠሮ ቀን በፊት በጽሑፍ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፲፬ ተፈላጊውን ሰው መያዝ</u>**

**፩.** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄውን ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ተፈላጊው ያልተያዘ እንደሆነ የመያዣ ትእዛዝ እንዲሰጠው ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፪.** ፍርድ ቤቱ የተፈላጊው ሰው መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ካመነ በዚህ ሕግ መሠረት የመያዣ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፫.** ፍርድ ቤቱ ተፈላጊው ተይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ከሰጠ የፌዴራል ፖሊስ ተፈላጊውን ፍርድ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፬.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ስለመያዝ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፲፭ ተፈላጊውን ሰው ፍርድ ቤት ማቅረብ</u>**

**፩.** ፌዴራል ፖሊስ ወይም ውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ በዚህ ሕግ አንቀጽ **፻፲፫** መሠረት የተያዘውን ተፈላጊ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፪.** ፍርድ ቤቱ፡-

**(ሀ)** ተፈላጊው ተላልፎ እንዲሰጥ ፈቃደኝነቱን ካልገለጸ ወይም ተቃውሞ ካቀረበ ጉዳዩን ሰምቶ ከአሥራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**(ለ)** በዋስትና መልቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ካላመነ በስተቀር ጉዳዩን ሰምቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተፈላጊው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**<u>አንቀጽ ፬፻፲፮ መስማትና ውሳኔ መስጠት</u>**

**፩.**ፍርድ ቤቱ፡-

**(ሀ)** ጉዳዩ በሚሰማበት ዕለት አግባብ ሆኖ ባገኘው ማንኛውም መንገድ የተፈላጊውን ሰው ማንነት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**(ለ)** ተፈላጊው ሰው በቀረበው አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ላይ ያለውን መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

**፪.**ፍርድ ቤቱ በአመልካች የቀረበውን ጥያቄ እና በተፈላጊው ሰው የተሰጠውን መልስ ወይም አስተያየት ከመረመረ በኋላ እንደነገሩ ሁኔታ፡-

**(ሀ)** ተፈላጊው ተላልፎ እንዲሰጥ ፈቃደኝነቱን ከሰጠ፤ ማንነቱን በማረጋገጥ ተላልፎ እንዲሰጥ፣

**(ለ)** ፈቃደኝነቱን ካልገለጸ ወይም ተቃውሞ ካቀረበ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ የቀረበበት ሰው መሆኑን እና አሳልፎ ለመስጠት የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ተፈላጊው ሰው ተላልፎ እንዲሰጥ፣ ወይም

**(ሐ)** የቀረበው ሰው ተፈላጊው አለመሆኑን ወይም ተፈላጊው አሳልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀበትን የወንጀል ተግባር ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ የሚያሳድር ማስረጃ አለመቅረቡን ሲረዳ ዋስ መጥራት ሳያስፈልገው እንዲለቀቅ፣ እንደነገሩ ሁኔታ የተያዘ ንብረት እንዲመለስለት፣

ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ዐየ|ፘ በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት</u>**

**፩.**ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በሚሰማበት ዕለት ተፈላጊው ሰው ያልቀረበ እንደሆነ ታስሮ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪.**በተለዋጭ የቀጠሮ ቀን ተፈላጊው ሰው ፍርድ ቤት ያልቀረበ እንደሆነ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ዐየ|ፗ ይግባኝ ወይም እንደገና እንዲታይ መጠየቅ</u>**

**፩.**በዚህ ሕግ መሠረት በፍርድ ቤት በተሰጠ የአሳልፎ መስጠት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ወይም እንደገና እንዲታይ ሊያመለክት ይችላል፡፡

**፪**በዚህ ሕግ መሠረት ጉዳዩ በመታየት ላይ ያለ ወይም ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ፣ በሌላ ወንጀል ወይም በሌላ ጠያቂ ሀገር ጥያቄ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት የአሳልፎ መስጠት ጉዳይ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

**፫.**በዚህ ሕግ ስለ ይግባኝ አቀራረብ የተደነገገው እንደአግባብነቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት በቀረበ ይግባኝ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ ዐየ|ፀ ውሳኔን ስለማሳወቅ</u>**

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ፡-

**፩.**በዚህ ሕግ መሠረት የተሰጠ የአሳልፎ መስጠት የመጨረሻ ውሳኔን ለጠያቂው ሀገር ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፪.ፍርድ ቤት በመጨረሻ ውሳኔ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄውን ውድቅ ካደረገ የውሳኔውን ምክንያት ለጠያቂው ሀገር ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷ ተፈላጊውን ማስረከብ**

፩. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፡-

(ሀ) በመጨረሻ ውሳኔ ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበትን ተፈላጊ ለጠያቂው መንግሥት ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በፌዴራል ፖሊስ አማካኝነት ማስረከብ ይኖርበታል፤ ርክክቡ እንደአስፈላጊነቱ ተያያዥ ሰነዶችንም ሊያካትት ይችላል፡፡

(ለ) ተፈላጊው ተላልፎ እስኪሰጥ ድረስ ተይዞ በእስር የቆየ እንደሆነ ይኸው የጊዜ መጠን ማስረጃን ለጠያቂው መንግሥት መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ጠያቂው መንግሥት የተረከበውን ተፈላጊ ሰው ወይም ሰነድ መመለስ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄው የቀረበበት ዓላማ እንደተፈጸመ የሚመለስ ስለመሆኑ መተማመኛ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፩ የውሳኔ ተፈጻሚነትን ማራዘም ወይም ማገድ**

፩.ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፡-

(ሀ) ተፈላጊው ሰው ተላልፎ ቢሰጥ ከባድ የጤና መታወክ ያጋጥመዋል ወይም ሕይወቱ ለአደጋ ይጋለጣል ብሎ ሲያምን፣ በተፈላጊው ሰው ላይ የወንጀል ምርመራ እየተጣራ ከሆነ፣ በወንጀል ክስ የቀረበበትና ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ ካለ ወይም ሌላ ቅጣት እየፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተፈላጊው ተላልፎ የሚሰጥበትን ጊዜ ለፍርድ ቤት በማሳወቅ ሊያራዝም ይችላል ፡፡

(ለ) ተፈላጊው ተላልፎ እንዲሰጥ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን የሚያስቀይር ወይም እንዲራዘም የሚያስገድድ ምክንያት ባጋጠመ ጊዜ ምክንያቱ ቀሪ እስኪሆን ድረስ ውሳኔው ታግዶ እንዲቆይ ወይም እንዲሻር ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪.ፍርድ ቤቱ የተለየ ውሳኔ ካልሰጠ በስተቀር የአሳልፎ መስጠት ውሳኔው እንዲራዘም ትእዛዝ ከተሰጠ እና ተፈላጊው በእሥር ላይ ያለ እንደሆነ በዋስትና እንዲለቀቅ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፪ ውድቅ በተደረገ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄ ላይ ስለሚፈፀም ሥነሥርዐት**

በወንጀል ሕግ ከአንቀጽ ፲፯ እስከ ፳ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአሳልፎ መስጠት ጥያቄው፡-

፩.በዚህ ሕግ አንቀጽ **፩፻፲፱** መሠረት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አግባብነቱን መርምሮ ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ወይም

**፪**.በዚህ ሕግ አንቀጽ **፩፻፲፱** ንዑስ አንቀጽ **፪** መሠረት የመጨረሻ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት የተላልፎ ይሰጥ ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገው ወይም ውሳኔውን የሻረው እንደሆነ፣

በዚህ ሕግ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ክስ እንዲመሠረት፣ ቅጣት እንዲወሰንበት ወይም የተጣለበትን ቅጣት እንዲፈፅም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፫ በጊዚያዊነት ተላልፎ የተሰጠ ሰው**

**፩**.በውጭ ሀገር በእስር ላይ ያለ ተፈላጊ በጊዚያዊነት ለኢትዮጵያ ተላልፎ የተሰጠ እንደሆነ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ግለሰቡ በእስር ላይ እንዲቆይ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

**፪**.ተላልፎ የተሰጠው ሰው በእስር እንዲቆይ የሚሰጠው ትእዛዝ ተላልፎ የተሰጠበት ምክንያት እስኪጠናቀቅ ድረስ ይሆናል፡፡

**፫**.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መሠረት ተላልፎ የተሰጠው ሰው የተላለፈበት ምክንያት ከተጠናቀቀ አሳልፎ ለሰጠው ሀገር መመለስ ይኖርበታል፡፡

**፬**.በጊዚያዊነት ተላልፎ በተሰጠ እና ክስ በተመሰረተበት የወንጀል ድርጊት ፈፃሚ ላይ የመጨረሻው የአሳልፎ መስጠት ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የተላለፈበት ፍርድ አይታሰብለትም፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፬የተፈላጊው ሰው እና ማስረጃ ርክክብ**

**፩**.ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበትን ተፈላጊ ሰው የፌዴራል ፖሊስ ይረከባል፡፡

**፪**.**የፌዴራል** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፡-

**(ሀ)** ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፎ የተሰጠው ሰው የፍርድ ሂደቱን ወይም ቅጣቱን ሲያጠናቅቅ እንደአግባብነቱ ተመልሶ ከሀገር መውጣቱን ፣ እና

**(ለ)** በማስረጃነት የቀረበ ሰነድ፣ ወይም ማናቸውም ማስረጃ በተገቢው መንገድ መያዙን ወይም የቀረበለት ዓላማ ሲጠናቀቅ በሕግ መሠረት መመለሱን፣ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**ምዕራፍ ሦስት**

**በኢትዮጵያ ማስተላለፍ የሚፈጸምበት ሥነ ሥርዐት**

**አንቀጽ ፩፻፷፭ ማስተላለፍን ስለመፍቀድ**

**፩.**ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር ተላልፎ የተሰጠን ተፈላጊ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲተላለፍ የትብብር ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**፪.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የቀረበ የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በማለፉ የሀገሪቱን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን በማረጋገጥ ተላላፊውን እንዲያልፍ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፯ በመተላለፍ ያለ ተፈላጊን ስለማሰር</u>**

**፩.**በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፩፻፳፭</u>**ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማስተላለፍ የተፈቀደ እንደሆነ ማስተላለፉ እስኪፈፀም ድረስ ወይም በማስተላለፉ ሂደት ተፈላጊው ከአርባ ስምንት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በማቆያ ወይም ማረፊያ ቤት ሊቆይ ይችላል፤ የፌዴራል ፖሊስ ተፈላጊውን በመረከብ ትእዛዙን ያስፈጽማል፡፡

**፪.**ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተፈላጊውን ማስተላለፍ እስኪፈጸም ድረስ ወይም የማስተላለፉ ሂደት ባለመጠናቀቁ ምክንያት ተፈላጊውን ሰው ከአርባ ስምንት ሰዓት በላይ በእስር ማቆየት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ጉዳዩን ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

**<u>አንቀጽ ፩፻፳፰ ልዩ ሁኔታ</u>**

**፩.**ተላላፊው ሰው በአየር ትራንስፖርት የሚጓጓዝ ወይም በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ እንዲያርፍ የታሰበ ካልነበረ በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፩፻፳፭</u>** ፍቃድን የተመለከተ ቅድመ ሁኔታ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፪.**ባልታሰበ ሁኔታ ተላላፊው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያረፈ እንደሆነ እና አጃቢው ተላላፊው በእስር እንዲቆይ ጥያቄ ካቀረበ ከአርባ ስምንት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በእስር እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

**፫.**ተቀባዩ ሀገር በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ መደበኛ የማስተላለፍ የትብብር ጥያቄ ካላቀረበ ተፈላጊው ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

**፬.**በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ከተቀባዩ ሀገር መደበኛ የማስተላለፍ ጥያቄ ከቀረበና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በማስተላለፍ ጥያቄው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ከአርባ ስምንት ሰዓት በላይ ተላላፊውን በእስር ማቆየት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ጉዳዩን ፍርድ ቤት እንዲያውቀው በማድረግ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

**፭**.በዚህ ሕግ አንቀጽ **<u>፩፻፳፮</u>**ንዑስ ቁጥር ፪ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ጉዳዩን ያወቀ ፍርድ ቤት ተገቢውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## **ዘጠነኛ መጽሐፍ**

## **ልዩ ልዩ ጉዳዮች**

## **ምዕራፍ አንድ**

## **ኪሳራና ወጪ**

### **አንቀጽ ፬፻፳፫ የዐቃቤ ሕግ የክስ ወጪ**

፩.በዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርበው የክስ፣ ይግባኝና የሰበር ክርክር ወጪ በሙሉ በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

፪.በተፈረደበት ሰው ክርክር ምክንያት ዐቃቤሕግ የተለየ ወጪ ያወጣና የተፈረደበት ሰው የመክፈል አቅም ያለው እንደሆነ ከተወሰነበት ቅጣት በተጨማሪ ዐቃቤሕግ የሚያቀርበውን የወጪ ዝርዝር ተመልክቶ የተፈረደበት ሰው በሙሉ ወይም በከፊል ልዩ ወጪውን እንዲከፍል ፍርድቤቱ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ኃላፊ የሆኑ የተፈረደባቸው ሰዎች ከአንድ በላይ የሆኑ እንደሆነ ወጪው በተለየ ኃላፊ የሚሆን ሰው የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ሁሉም በአንድነት ወይም በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

፬.ፍርድቤቱ ወጪው እንዲከፈል ከማዘዙ በፊት የተፈረደበት ሰው በቀረበው የወጪ ዝርዝር ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡

### **አንቀጽ ፬፻፳፬ በግል አቤቱታ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወጪ**

፩. በግል ከሳሽ ስለሚቀርበው የክስ፣ የይግባኝና የሰበር ክርክር ወጪ በሙሉ በራሱ ይሸፈናል፡፡ ከአንድ በላይ የሆኑ ከሳሾች ሲኖሩ በአንድነት ወይም በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

፪. በግል ክስ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ እንደሆነ ከሳሽ ያወጣው ወጪ በሙሉ ወይም በከፊል በተከሳሽ እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

፫.በግል ክስ ቀርቦ ተከሳሽ ነፃ የተለቀቀ እንደሆነና ክሱ የቀረበው በቅን ልቦና አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ ተከሳሹ ያወጣው ወጪ በሙሉ ወይም በከፊል የግል ከሳሹ እንዲከፍል ያዛል፡፡

### **አንቀጽ ፬፻፳፭ የፍትሐብሔር ክርክር ወጪና ኪሳራ**

፩.በዚህ ሕግ መሠረት የፍትሐብሔር ክስ ሲቀርብ የዳኝነት ክፍያን ጨምሮ ወጪና ኪሳራ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ መሠረት ይመራል፡፡

፪.የፍትሐብሔር ክሱን ያቀረበው ዐቃቤ ሕግ እንደሆነ የዳኘነት ክፍያ አይከፍልም፡፡ ይሁንና ተከሳሽ የክሱን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል ሲወስን የዳኘነት ክፍያውንም ጨምሮ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፴፩ የምስክር ወጪ**

፩.ለምስክር እና ሰነድ አቅራቢ የሚከፈለው አበልና የወጪ ማካካሻ በደንብ ይወሰናል፡፡

፪.የግል ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ለሚጠራው ምስክር ወይም ሰነድ አቅራቢ አበልና የወጪ ማካካሻ በግል ከሳሽ ወይም በተከሳሽ ይሸፈናል፡፡

፫.ምስክር ወይም ሰነድ አቅራቢ ለመጥራት የገንዘብ አቅም የሌለውና መክፈል የማይችል ተከሳሽ አበልና የወጪ ማካካሻ በመንግሥት የሚሸፈንበት ሥርዐት በደንብ ይወሰናል፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

**አንቀጽ ፩፻፴፪ ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

በዚህ ሕግ የተደነገገው ደንብ የማውጣት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የክልል መስተዳድር ምክር ቤት፡-

፩.የተለዋጭ መፍትሔ አፈፃፀምና አስፈፃሚ አካላት እውቅና አሰጣጥ፤

፪.የተለዋጭ ቅጣት አስፈፃሚ ቦርድ ማቋቋሚያ ፤፫.የምስክሮች አቀራረብ፣ የአበልና የወጪ ማካካሻ፣ እና

፬.የተከላካይ ጠበቃ ተቋም ማቋቋሚያ

የተመለከቱ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፴፫መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

በዚህ ሕግ የተደነገገው መመሪያ የማውጣት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

**(ሀ)** የችሎት ሥነ ሥርዐት ክትትልና  የጉዳይ ፍሰት አስተዳደር

**(ለ)** የቅሬታ ማስተናገጃና አወሳሰን ፤

**(ሐ)**

**(መ)** የዝግ ችሎት አፈጻጸም ፤

**(ሠ)** አብላጫ ድምጽ በማይኖርበት ጊዜ የፍርድ ቤቱን ብይን፣ ትእዛዝ ፣ፍርድ ወይም ውሳኔ መለየት፤

**(ረ)** በወንጀል ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች ምርመራ የወንጀል ክስ እና ፍርድ አመራር፤

**፪.** ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፡-

**(ሀ)**

**(ለ)** በምርመራና ክስ የሚቀርቡ ቅሬታ ማስተናገጃና ውሳኔ አሰጣጥ፤

**(ሐ)** የግል ክስ አመራር፤

**(መ)** የቅጣት አፈፃፀም ክትትል ፤

**(ሠ)**

**(ረ)**

**(ሰ)** የአማራጭ መንገዶች አፈጻጸም ፤

**(ሸ)** የሞት ፍርድ አፈጻጸም ፤

**(ቀ)** ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ የሚመሠረትባቸው እና ክስ የማይመሠረትባቸው ጉዳዮችን ፤

**(በ)** ስለ ኤግዚቢት አያያዝ፣ አስተዳደርና አወሳሰን ፤

**(ተ)** የምስክሮችና የወንጀል ተጎጂዎች አጠባበቅ፣ አያያዝ፣ ድጋፍና ጥበቃ፤

**(ቸ)** በልዩ መንገድ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ፤

**(ነ)** በቀላል፣በመካከለኛና በከባድ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ክስ ለመመስረት የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ አፈፃፀም ፤

አስመልክቶ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፫.የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፡-**

**(ሀ)** የኃይል አጠቃቀምን ፤

**(ለ)** ስለወንጀል ሥፍራ ማስረጃ አሰባሰብና የምርመራ ሂደት፤

**(ሐ)** የወንጀል ምርመራ ስለሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ፤

በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፬.በዚህ ሕግ መሠረት የሚወጣ መመሪያ መታተምና ለሚመለከተው አካል መሰራጨት ይኖርበታል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የሥነ ሥርዐት ሕጉን ማሻሻል

### አንቀጽ ፬፻፴፬ ሕጉን ስለማሻሻል

ይህንን ሕግ ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም የማሻሻያ ሀሳብ በፍትሕ አካላት ውይይት ተደርጎበት በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በኩል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፀድቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ ይቀርባል፡፡